# ሰዋስው ወልሳነ ግእዝ መጽሐፍ

## በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

# ማውጫ

**አርዕስት** **ገጽ**


ምዕራፍ -፩ ........ 1

ፊደለ ግእዝ ........ 1

፩ ትርጉም፡- ........ 1

፪-ጥንተ ግእዝ /መሠረተ ግእዝ ........ 1

ግእዝ ቋንቋ የመጀሚሪያ ቋንቋ ስለመሆኑ መረጃዎች ........ 1

፫-የግእዝ ቋንቋ ፊደላት ........ 2

የ ፳፮ቱ የግእዝ ቋንቋ ፊደላት ዝርዝር ........ 3

አእማድ ፊደል እና መስተጻምር ፊደል ........ 3

ባሕርየ-ድምጸ ፊደላት ........ 4

ሕጹጻን ፊደላት ........ 4

አናባቢ /voules/ ........ 4

ጉባኤ ፊደላት ........ 4

የተመሳሳይ ፊደላት አጠቃቀም በቃላት ውስጥ ........ 5

የገእዝ ቋንቋ ፊደላት እና ትርጉም ........ 7

የግእዝ ቋንቋ የመማር ጥቅም ........ 7

ምዕራፍ---፪ ........ 8

ሥርዓተ-ንባብ/ፍኖተ-ንባብ ዘልሳነ ግዕዝ ........ 8

፪.፩ የንባብ ዐበይት ክፍሎች ........ 8

፩.ተነሽ ንባብ- ........ 8

፪.ወዳቂ ንባብ ........ 8

፫.ተጣይ ንባብ--- ........ 9

፬.ሰያፍ ንባብ--- ........ 9

፪.፪ የንባብ ነዑሳን ክፍሎች ........ 9

፩.ቀዋሚ/ዐራፊ/ንባብ ........ 9

፪.ተነባቢ ንባብ---- ........ 9

፫.ጠባቂ እና ልሕሉሕ /ልል/ንባብ ........ 10

፬.ቆጣሪና ጠቅላይ ንባብ ........ 11

፭.ጐራጅ ንባብ ........ 11

፮.መጠይቅ ንባብ........ 12

፯.የትራስ ፊደላት ሥርዓተ ንባብ ........ 12

፪.፫ የእርባታ ንባቦች........ 13

፪.፬ የተጸውዖ ስሞች ንባብ ........ 13

ምዕራፍ--፫........ 16

ስም ........ 16

ሀ.አስማት እምነ ግስ/ውልድ ስሞች ........ 16

ለ.አስማት እምነ ተፈጥሮ/ነባር ........ 16

ክፍላተ አስማት........ 17

፩.ስመ ተጸውዖ /proper noun/ ........ 17

፪.ስመ ጉባሬ/common noun/የወል ስም /ስመ መድበል ........ 17

፫.ስመ ምዕላድ /መድበል/collective noun /ጥቅል ስም........ 18

፬.ስመ ቍስ /material noun/የነገር ስም ........ 18

፭.ስመ ረቂቅ/abstract noun/ የረቂቅ ነገሮች ስም ........ 18

ምዕራፍ--፬........ 20

መራኅያን ........ 20

የመራሕያን አገልግሎት........ 20

፩.ሰብአዊ ተውላጠ ስም/personal pronoun/ ........ 20

፪.እንደ ነባር አንቀጽ /ከዊነ ግስ/ኰነታዊ አንቀጽ /verb to be/ ........ 21

፫.አመልካች /እማሬአዊ/ቅጽል/demonstrative adjective/ይሆናሉ........ 21

፬.ተሳቢ ተውላጠ ስም ይሆናሉ/Objective pronoun/ ........ 22

፭.የተሳቢ ቅጽል ይሆናሉ........ 23

፮.ፈጽሞተ ርእስ/intensive/ ........ 23

፯.ንዋያዊ ቅጽል/possessive/ምስለ መራሕያን -- በቂ ቅጽል ይባላል፡፡ ........ 24

፰.መስተዋድዳዊ ተሳቢ ምስለ መራሕያን........ 26

፱.ምክንያታዊ ተውላጠ ስም ........ 26

ምዕራፍ---፭ ........ 27

ቅጽል/adjective/ ........ 27

፩.ከሣቲ ቅጽል/descriptive adjective/........ 27

ሀ.ግስን በማገሰስ የሚገኙ ቅጽሎች........ 28

ሳድስ ውስጠ ዘ ቅጽል ........ 28

ሣልስ ቅጽል ........ 29

መስም ውስጠ ዘ ቅጽል /መስሕብ ቅጽል/........ 29

ወገናዊ ውስጠዘ ቅጽል ...... 30
ዘር ውስጠ ዘ ቅጽል ...... 30
መድበል ውስጠ ዘ  ቅጽል...... 31
መተርጉም ቅጽል ...... 31
ለ.የግሶችን ማሠሪያነት እያፈረሱ የሚገኙ ቅጽሎች ...... 31
፪.ኍልቋዊ ቅጽል/adjective quantity/ ...... 32
ሀ.ኍልቋዊ ቅጽል ዘ ተባዕታይ ...... 32
፩.ደሞላዊ ኍልቋዊ ቅጽል/nominal number/ ...... 32
፪.ኆላቊ ኍልቋዊ ቅጽል/cardinal number/ ...... 33
፫.መዓርጋዊ ቅጽል/ordinal number/ ...... 34
ለ.ኍልቋዊ ቅጽል ዘ አንስታይ ጾታ ...... 35
፩.ደምላዊ ቅጽል ዘአንስት...... 35
፪.ኆለቊ ቅጽል ዘ አንሰታይ ጾታ ...... 35
፫.መዓርጋዊ ቅጽል ዘአንስታይ ጾታ...... 36
ሐ.ኍልቋዊ ቅጽል ዘዕለት ...... 36
፩.ደምላዊ ቅጽል ዘዕለት...... 36
፪.ኆለቊ ቅጽል ዘዕለታት...... 36
፫.መዓርጋዊ ቅጽል ዘዕለታት ...... 37
፫.ንዋያዊ ቅጽል/possessive adjective/ ...... 37
፬.አማሪ/አመልካች ቅጸል/demonstrative adjective/--ደቂቅ ቅጽል ነው፡፡ ...... 37
፭.ክፍላዊ ቅጽል ...... 37
፮.ጥያቄአዊ ቅጽል /ንኡስ ቅጽል/introgative adjective ...... 38
፯.አጽንዖታዊ ቅጽል/Inphasise adjective/ ...... 38
ምዕራፍ--፯ ...... 41
ዝርዝር ...... 41
የባለቤት ዘመድ ዝርዝር ...... 41
የባለቤት ባዕድ ዘር ...... 41
ግሳዊ ተሳቢ ዝርዝር...... 42
የተሳቢ ድርብ ዝርዝር ...... 43
ነባራዊ ዝርዝር ...... 44
ምዕራፍ--፯...... 45
ባዕድ ፣ምዕላድ እና ባዕድ ከምዕላድ...... 45
ባዕድ ሰዋስው/prefixes/ ...... 45

ክፍላተ ባዕድ ዘር ሰዋስው ........ 45
ሀ.ብትን ባዕድ ዘር ሰዋስው ........ 45
፩.የብትን ሰዋስው ተገብሮ /ተደራጊ /ስልቱ ........ 45
፪.ገቢር /ተገቢነት/ ስልቱ ........ 46
ለ.ግሳዊ ባዕድ ዘር ሰዋስው ........ 46
፩.ባዕድ ዘር ዐቢይ አንቀጽ ........ 46
፪.ባዕድ ዘር ንዑስ አንቀጽ ........ 46
ምዕላድ ሰዋስው ........ 47
የምዕላድ ዓይነቶች ........ 47
ክፍላተ ምዕላድ ሰዋስው ........ 48
ሀ.ስማዊ ምዕላድ ........ 48
ለ.ግሳዊ ምላድ ሰዋስው ........ 49
ሀ.ሳቢዘር እና አርእስት ምዕላድ ሰዋስው /ንዑሳን ምዕላድ ሰዋስው/ ........ 49
ለ.ዐቢይ አንቀጽ ምዕላድ ሰዋስው ........ 50
ምዕራፍ--፫ ........ 51
ረብሓ ግስ ........ 51
የረብሓ ግስ ዓይነቶች ........ 51
ሀ.የዋሕ ረብሓ ግስ ........ 51
ለ.መሠሪ ረብሓ ግስ ........ 52
የግስ አረእስት እና ሠራዊቶች ከነርባታ ዘርዝራቸው ........ 54
ሀ.የግስ አርእስቶች-- ........ 54
ገሲሰተ ግስ ዘልሳነ ግእዝ ........ 56
ክፍላተ ገሲሰተ ግስ ........ 56
፩.ቀዳማይ(፩ᵉ)ገሲሰተ ግስ ........ 56
፪.ካልአ ገሲሰተ ግስ ........ 58
፫.ሣልሳይ ገሲሰተ ግስ ........ 59
የግዕዝ አርስቶች በአምስቱ አእማድ ቀለማት ሲገሰሱ ........ 66
፩.አድራጊ አምድ ........ 66
፪.ተደራጊ አምድ ........ 66
፫.አስደራጊ አምድ ........ 67
፬.ተደራጊ አምድ ........ 67
፭.አድራጊ አምድ ........ 67
የቀደሰ እርባታ ........ 68
የተንበለ እርባታ ........ 69

የባረከ እርባታ ........ 70
የማህረከ እርባታ ........ 71
የዴገነ እርባታ/ሴሰየ ማለት ነው/ ........ 72
የክህለ እርባታ ........ 72
የጦመረ እርባታ ........ 73
ሥረይ ግሶች ........ 74
፩.በቀተለ ሥር የሚመደቡና የእርባታ አመል ያላቸው ሥረይ ግሶች ........ 75
፪.በቀደሰ ሥር የሚመደቡና የእርባታ አመል ያላቸው ሥረይ ግሶች። ........ 79
፫.በተንበለ ሥር የሚመደቡ ሥረይ  ግሶች ........ 81
፬.በባረከ ሥር የሚመደቡ ሥርይ ግሶች ........ 82
፭.በማህረከ ሥር የሚመደቡ ሥረይ ግሶች ........ 83
፮.በዴገነ/ሴሰየ ሥር የሚመደቡ ሥረይ ግሶች ........ 84
፯.በክህለ ሥር የሚመደቡ ሥርይ ግሶች ........ 86
፰.በጦመረ ሥር የተመደቡ ሥረይ ግሶች ........ 87
አንቀጽን የሚስብ አንቀጽ(ይቤ) ........ 89
አመላተ ሰዋስው ........ 97
፩..የ«ሀ» እና የ«አ» አመል ........ 97
፪..የ«ወ» አመል ........ 98
፫.የ«የ» አመል ........ 99
የዐሥራው ቀለማት ሕጐች ........ 101
ቱሱሐን እርባታ ........ 104
ተመኩሳይያን/ሞግሸዎች ........ 107
ምዕራፍ ---፱ ........ 110
ገቢር ተገብሮ /active & passive ........ 110
ተገብሮ/ኢሰጋሪ/ኢሰሐቢ ግስ ........ 110
ተሻጋሪ ግሶች በተሳቢነት ያላቸው ደንበ ........ 111
ሀ.ፊደልን በመለወጥ ........ 111
ለ.ፊደልን ባለመለወጥ ........ 114
ሐ.የተጸውዖ ስም ላይ የገቢር ግሶች «ሀ» ን ይጨምራሉ ........ 115
መ.ባለቤት ተውላጠ ስም ወደ ተሳቢ ተውላጠ ስም ይለወጣል ........ 115
ሠ.በአመልካች ጊዜ ........ 116
ረ.አንዳንድ ልዩዎች ........ 116
ምዕራፍ ---፲ ........ 118
አንቀጽ ........ 118

ሀ.ዘማች አንቀጽ-- 118
፩.ዐበይት አናቅጽ /main verb/ 118
፪.ንዑሳን አንቀጽ 120
ለ.ነባር አንቀጽ 122
ሀ.ከዊን አንቀጽ /verb to be 123
ለ.ህልው አንቀጽ /verb to have 125
ምዕራፍ--፲፩ 128
ዘርፍ ሰዋሰው 128
ክፍላተ ዘርፍ ሰዋስው 129
ሀ.የባለቤት ዘርፍ --የማሠሪያ አንቀጽ ባለቤት ሰወስው 129
ለ.የተሳቢ ዘርፍ ሰዋስው 132
ምዕራፍ ---፲፪ 133
አገባብ 133
ክፍላተ አገባብ 133
ሀ.አንቀጽ አጐላማሽ/ተውሳከ ግስ 133
ክፍላተ ተውሳከ ግስ 133
ሀ. ተውሳከ ግስ ዘ ጊዜ 134
ለ.ተውሳከ ግስ ዘ ኵነት 134
ሐ.ምክንያትን የሚፈልጉ 135
መ.ሁኔታን የሚገልጽ 136
ሠ.ውጤትን አመልካች 136
ረ.ቦታ ገላጭ 136
ለ.ዐቢይ አገባብ /መስተጻምር/ 138
ሀ.ምክንያት አስረጅ ዐቢይ አገባብ 138
ለ.ማንጸሪያ/ማነጻጸሪያ/ ዓቢይ አገባብ 146
ሐ.አሉታ/አፍራሽ/ዓቢይ አገባብ 147
ሐ.ንዑስ አገባብ 149
ሀ.መጠይቅ ንዑስ አገባብ-- 149
ለ.ትእምርተ አንክሮ/ፍሥሐ እና ሐዘን ንዑስ አገባብ 151
ሐ.ትእምርተ ጽዋዔ /ጥሪ ንዑስ አገባብ 152
መ.ትእምርተ እማሔ፡አቤቱታ ፣እሽታናመልእክት ንዑስ አገባብ 152
ሠ.ትእምርተ አዎንታ እና አሉታ ንኡስ አገባብ 152
ረ.ትእምርተ ጊዜ ንዑስ አገባብ 153
ሰ.ትእምርተ ጥርጣሬ /አማራጭ እና አብላጫ ንዑስ አገባብ 154

ቀ.ትእምርተ ጸጸት/ተምኔት፡መጠን እና ቀስታ /ሥውር ንዑስ አገባብ ........ 154
በ.እስኩ፣አዲ፣ዓ፣እስመ፣ቅድመ፣ሂ፣ኒ ንዑስ አገባብ........ 155
መ.ደቂቅ አገባብ ........ 156
ሀ.ትምህርተ ላዕል መታሕት/ላይ እና ታች ደቂቅ አገባብ ........ 156
ለ.ትዕምርተ ማዕከል ወውስጥ ደቂቅ አገባብ ........ 157
ሐ.ትምሕርት መነሻ ፣መገስገሻ እና መድረሻ ደቂቅ አገባብ........ 158
መ.ማድረጊያ አቀባይ/ተጠቃሽ አጫፋሪና አነጻጻሪ ደቂቅ አገባብ ........ 159
ሠ.ትእምርተ ቤዛነት ፣ምትክነት፣መማጸን ደቂቅ አገባብ ........ 160
ረ.ትእምርተ ጊዜና ቦታ ደቂቅ አገባብ ........ 161
ሰ.አንጻሪ ደቂቅ አገባብ /አወዳዳሪ ደቂቅ አገባብ ........ 163
ምዕራፍ ---፲፫ ........ 164
ቅኔ ........ 164
የቅዱስ ያሬድ እና የመምህራን ቅኔ ልዩነት ........ 164
ነገረ-ሰወስው........ 165
፩.የዋሕ ነገረ ሰዋስው-........ 165
፪.ጥበብ ነገረ ሰዋስው- ........ 166
፩.ወርቅ ለበስ/ስም ረገፍ/ነገረ ሰዋስው -........ 166
፪.ምሳሌ አዊ ነገረ ሰዋስው /ቅኔ/........ 167
የቅኔ ክፍሎች /ደረጃዎች ትርጉማቸው የቤት ብዛታቸው ........ 170
፩.ጉባኤ ቃና -- ........ 170
፪.ዘአምኪየ-- ........ 170
፫.ሚበዙኁ-- ........ 170
፬.ዋዜማ--........ 170
፭.ሥላሴ--- ........ 171
፮.ዘይዜ---........ 171
፯.መወድስ---........ 171
፰.እጣነ ሞገር--- ........ 171
፱.ክብር ይእቲ---........ 171

# ምዕራፍ -፩

## ፊደለ ግእዝ

### ፩ ትርጉም፡-

ግእዝ የሚለው ቃል"አግኣዘ" ነጻ አወጣ ወይም "ግእዝ" ኢጋዘ፣ተማረ ፣ቆጠረ ከሚለው የግእዝ ቃል/ግስ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙ ፡-

፩-እግዚእ እግዚአብሔር አግአዚ ለኃጢአት ለጣዖት ከመገዛት ነጻ አውጥቶ ግዕዛንን የሚሰጥ ወይም የሥጋ የነፍስ ነጻነትን ከሚሰጥ ጌታ ከልዑል እግዚአብሔር ተገኝቶ ለኢጋዕዝያን ለአዳም እና ለልጆቹ የተሰጠ ማለት ነው።

- ግዕዝ-ግ-ጋሜል -ግሩም እግዚአብሔር
  - እ -አሌፍ-አብ ፈጣሬ ኩሉ ዓለም
  - ዕ-ዔ -ዐቢይ እግዚአብሔር
  - ዝ -ዛይ-ዝኩር እግዚአብሔር

ስለዚህም "ግዕዝ" ማለት ግሩም እና ታላቅ የሆነ እግዚአብሔር የሚታሰብበት ቋንቋ እንደ ማለት ነው።ወይም ድንቅ የሆነ ዓለምን የፈጠረ አባት እግዚብሔር የሚታሰብበት እንደማለት ነው።

፪-ግዕዝ ስንል የመጀመሪያ መነሻ መሰረት ማለት ነው፡ምክንያቱም የፊደል መጀመሪያውን ግዕዝ እንለዋለን እንዲሁም የዜማ መጀመሪያ ግዕዝ ፡የንባብ መጀመሪያውንም ግዕዝ እንለዋለን ፣በዚህና በመሳሰሉት ነገሮች የመጀመሪያ የሚለውን ቃል ይዞ ይገኛል፡፡

- ግዕዝ ጥንታዊ ልሳነ ኢትዮጵያ (ትንሣኤ አማርኛ -ግዕዝ መዝገበ ቃላት በላይ መኰንን ሥዩም (ሊቀ፡ኅ)

### ፪-ጥንተ ግእዝ /መሠረተ ግእዝ

የግእዝ መጀመሪያው /መነሻው መቸ ነው የሚለው ጥያቄ በብዙ ቦታዎች የሚያወዛግብ ቢሆንም የሚከተሉትን እንመለከታለን፡-

#### *ግእዝ ቋንቋ የመጀሚሪያ ቋንቋ ስለመሆኑ መረጃዎች*

፩-ፊደሉ ጥፈቱ እራሱን የተለየ ሆኖ ድምጡንም በሚሠጠብበት ጊዜ ራሱን በራሱ ያናግራል እንጂ ረዳት የማይሻ ስለሆነ እና ሌሎችም የዓለም ቋንቋ ፊደሎች ግእዝኛውን ድምጥ በመስጠት የማይመሳሰሉት ስለሆነ ። «ኢትዮጵያ በሦስቱ ሕግጋት ሊቀ ጠበብት አለቃ አያሌው ታምሩ ፲፱፻፶፫»

፪-"፳፪ ተመድቦ በሰባት ስልት ሲነገር ልዑል እግዚአብሔር ፳፪ቱን ፍጥረታት ፈጥሮ በ፯ቱ ዕለታት ሐሳቡን እንደጨረሰ ስለሚያመለክት እንዲሁም ፳፪ኛውን ሰው ከሰባት ነገር ፈጥሮ ጉድለት የሌለበት የፀጋ ገዥ ፡የእግዚአብሔር ማደሪያ አድርጎ የሰባቱ ሀብታት ባለቤት ማድረጉን ስለሚያስረዳ

፫-"በባቢሎን የተመሰረቱ ቋንቋዎች በየወገኑ የፍጡራንን ስም ተደግፈው ይሔዳሉ።ለምሳሌ የሚከተሉትን ማየት ይቻላል ።

ኤቦር(የሰው ስም)-----እብራይስጥ

ጽረዕ(የቦታ ስም)----ጽርዕ

ሮም(የቦታ ስም)-------ሮማይስጥ

ዐረብ(የቦታ ስም)-------ዐረበኛ

ግእዝ ግን እግዚእ እግዚአብሔር አግአዚ ለኃጢያት ለጣዎት ከመገዛት ነጻ አውጥቶ ግእዘን የሥጋ የነፍስ ነጻነትን ከሚሰጥ ጌታ ከልዑል እግዚአብሔር ተገኝቶ ለኢጋዝያን ለአዳምና ለልጆቹ የተሰጠ ስለሆነ

፬-"ግእዝ አዳም እና እግዚአብሔር ይነጋገሩበት የነበረ ቋንቋ ነው " ይላሉ ጀርመኖች የአለቃ ወልደ  ክፍሌ መጽሐፍ

-በሳናዖር ግንብን ለመሥራት የተስማሙበት የውል ጽሑፍ ግእዝ ነው ብለው ይተርካሉ፡፡(ኢትዮጵያ በሦስቱ ሕግጋት )

❖ ከዚህ ላይ ልናስተውል ይገባል ማለትም እንዲህ ከተባለ ልሳን የተከፈለው ከሰናዖር ህንጻ መጀመር በኋላ ስለሆነ።ዘፍ፡፲፪፡፮

፭-"ነቢዩ ሄኖክ የነበረበት ዘመን የሰው ልጅ ራሱ ወደ ሰማይ የደረሰውን የባቢሎንን ህንጻ/ግንብ ለመሥራት ከማቀዱ ብዙ ዘመን /ትውልድ ቀደም ብሎ ነበር ።ነቢዩ ሄኖክ የነበረው የጥፋት ውኃ ከመድረሱ ሦስት ትውልድ ቀደም ብሎ ነበር ከባቢሎን ግንብ መፍረስ በፊት ደግሞ ምድር በአንድ ከንፈር ብቻ ይነጋገር ነበር ማለትም ሄኖክ በነበረበት ዘመን የዓለም ቋንቋ አንድ ብቻ ነበር።ነቢዩ ሄኖክ ደግሞ በኢትዮጵያ የተገኘውን መጽሐፍ የጻፈው በጥንቱ የኢተዮጵያ ቋንቋ በግእዝ እንደነበረ ተረጋግጧል ፡ስለዚህ እስከ ባቢሎን ግንብ መፍረስ ድረስ ዓለም ሲጠቀምበት የነበረው ቋንቋ ግእዝ ነበር ማለት ነው።(መጽሐፍ ቅዱስ እና ኢትዮጵያ በምኒልክ መርእድ ዓለሙ 1999 እ አ )

፮-"የአውሮፓ ጸሐፊዎች ሴሜቲ ከእስያ ወደ ኢትዮጵያ የገባው ነው ያሉበት ምክንያት በአረቡ ዓለም ግድብ ላይ ተጽፎ በመገኘቱ ነው፡ኢትዮጵያውያን በንግድና በጦርነት በተለያዬ መንገድ ቀይ ባህርን ተሻግረው በመሔዳቸው ፊደል በእስያ መገኘቱ ትክክል ነው ።ያ ማለት ግን የግእዝ ፊደል ወደ ኢትዮጵያ መጣ ማለት አይደለም።የግእዝ ፊደል ወይም የሳባ ፊደልም ይበሉት በተለያዩ ምክንቶች ከኢትዮጵያ ወደ ተለያዩ አገራት ተሰራጨ እንጂ ከእስያ ወደ ኢትዮጵያ የመጣ አይደለም ።

ኢትዮጵያ የሰው ዘር የተገኘባት የእምነት እና የሥልጣኔ ምንጭ ናት (አቶ አማረ ከፍ አለ በላቸው)

፯-"ግእዝ የደቡብ ሴማዊ ልሳን ሳይሆን በዐረብ ምድር ተመጀመሪያዎቹ የአፍሪካውያን /ኩሻውያን ቋንቋ  ነው ፡

| | | |
|---|---|---|
| የሶቬት ምሁራን | አቢ ዶጎ ፓልስኪ | አቤንጃ |
| | ኢሳር  ዲያከኖፍት | ኃይሉ ሀብቱ |
| | ቸከ አንተ ዲዮፕ | አስረስ የነሰው |

(ትንሣኤ ግእዝ መ/ር ደሴ ቀለብ)

፰-"ግእዝ አፍሪካዊ የኢትዮጵያ ልሳን ልደቱን እና እድገቱን **ኢትዮጵያ** አድርጎ  በዘመነ ባቢሎን ሊነገር የሚችል ዓለም አቀፋዊ እና ጥንታዊ ልሳን ነው

ይህም  ሀ/ የጽሕፈት ዘደየ አቡጌዳ

ለ/ የጽሕፈት አቅጣጫ ከግራ ወደ ቀኝ አግድም (ከሳባ የሚለይበት)

ሐ/ እያንዳንዱ ፊደል በአናባቢ የተገለጸ እና አናባቢ የሌለው ሆኖ ሊጻፍ የሚችል ዓለም አቀፋዊና ጥንታዊ ልሳን ነው። (ትንሣኤ ግእዝ መ/ር ደሴ ቀለብ ማ/ቅ ፳፻፪)

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት እና በአይናችን የማናያቸው ማለትም  "አዳም፡ሄዋን፡እግዚአብሔር " የመሳሰሉት በሌሎች ቋንቋ  ስም ነው ከማለት ውጭ ትርጉም ሳይኖራቸው በግእዝ ግን አራሳቸውን የቻለ ትርጉም አለቸው።እንዲሁም የአባታችን የቅዱስ ያሬድ ዜማ በልሳነ ግእዝ መሰጠቱ ማኅበረ መላእክት የሚጠቀሙበት የግእዝ ቋንቋ መሆኑን ያስረዳል አነዚህ ሁሉ ግእዝ የመጀመሪያ አዳም እና እግዚአብሔር ፡አዳም እና መላእክት ፡አዳም እና እንስስት ሲግባቡበት የነበረ ጥንታዊ ቋንቋ ነው።

## ፫-የግእዝ ቋንቋ ፊደላት

ፊደል የሚለው ቃል "ፈደለ" ጻፈ ከሚለው የግእዝ ግስ የተገኘ ሲሆን ፊደል ማለት ጽሕፈት ፡አጻጻፍ ማለት ነው ማለትም ፊደል የቋንቋ ፡የቃል የአነጋገር ሁሉ ምልክት  አምሳል ወይም መግለጫ ማስታወቂያ ማለት ነው ።

እግዚአብሔር ፊደልን ለመጀመሪያ ጊዜ በልሳን ተመጦ /ተሰውሮ የነበረውን አካሉን በሰማይ ገበታላይ /በጸፍጸፈ ሰማይ ላይ /ተጽፎ ተቀርጾ እንዲገለጥለት ያደረገው የአዳም ሦስተኛ ትውልድ ለሆነው ለሄኖስ በ፺፪ ዓመተ ዓለም ነው፡፡መ፡ኩፋ ፰፡፲ ከዚህ ላይ ትኩርት ሊሰጠው የሚገባው ነገር ቢኖር በጸፍጸፈ ሰማይ ላይ ያየው ሄኖስ ይሁን እንጂ ለሥነ-ጽሑፍ እንዲውል ያደረገው ነቢዩ ሄኖክ መሆኑን ልብ ይሏል።

- ለሄኖስ የተገለጠው ፊደላት ብዛት ፳፪ ናቸው። ፳፪ቱ አሌፋት ማለት ነው።
- በአጠቃላይ የግዝ ቋንቋ ፊደላት ብዛት ፳፪ ነው። አራቱ ፊደላት የት ተገኙ ቢሉ ፣ድርብ ፊደላት ናቸው ከ"ሀ፡ሠ፡አ፡ጸ፡ጋር የሚደረቡ ፊደላት አሉ እነዚህን ስንጨምር ፳፮ ይሆናሉ ማለት ነው።

## ***የ ፳፮ቱ የግእዝ ቋንቋ ፊደላት ዝርዝር***

ሁለት አይነት አዘራዘር ወይም አቀማመጥ አላቸው ።

### ***ሀ-ኑባሬ ቀዳማይ***

ይህ የአቀማመጥ ሥርዐዓት አባታችን አቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ከመምጣታቸው በፊት የነበረው ሥርዓተ ኑባሬ ነው።ይህ ሥርዓት "አበገደ " የሚባለው ሥርዓት ነው።

### **ለ-ካልአይ ኑባሬ**

ይህ የአቀማመጥ ሥርዓት በአባታችን በአቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን የተዘጋጀው የአቀማመጥ ሥርዓት ነው ። ይህም ዛሬ በኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤ.ክ እየተጠቀመችበት ያለው "ሀ፡ለ፡ሐ፡መ፡ ወዘተ የሚባለው አቀማመጥ ነው።

- ከዚህ በላይ በተመለከትነው በሁለቱም አቀማመጥ ፊደላቱን በሁለት እንመድባቸዋለን  እነዚህም

**ሀ. አሥራው ፊደላት** -ግእዝ ወይም የመጀመሪያዎቹ ናቸው ።ማለትም እዝል ቅጥል የሌላቸው ፊደላት ናቸው ።

**ለ.ሠራዊተ ፊደላት-** እነዚህ ፊደላት ከግእዙ በኋላ የሚነሱ ካልአይ ፡ሣልሳይ፡ራብአይ፡ኃምሳይ፡ሳድስ እና ሳብእ ፊደላት ናቸው።

ሠራዊት ፊደላት ላይ የሚቀጠሉ ቅርንጫፎች ወይም አእጹቀ ፊደል ተብለው ይጠራሉ ።

በሌላ መልኩ ፊደላትን

## ***አእማድ ፊደል እና መስተጻምር ፊደል***

- በግእዝ የፊደላት ሥነ-ጽሕፈት የቀለም አሣሣል ሥርዓት ከላይ ወደታች የሚወርድ ፊደላዊ ቅርጻቸው ዓምደ ፊደል ይባላል።
- ወደጐንና ጐን ወይም ዙሪያውን የሚወድቀው የሚጻፈው  ፊደላቸው ቅርጻቸውም  መስተጻምር ፊደል ይባላል።

የፊደል ማያያዣ ማጣበቂያ አንድ ማድረጊያ ማለት ነው።

ምሳሌ፡-አእማደ ፊደል ከነ መስተጻምራቸው

- ባለ አንድ አምድ ረ፡ነ፡ቀ፡ተ-መስተአምር አምድ
- ባለ ሁለት አምድ ሀ፡ለ፡በ፡ዘ፡ፀ
- ባለ ሦስት አምድ ሐ፡ሠ፡ወ፡ጠ
- ባለ አራት አምድ  መ

## ***ባሕርየ-ድምጸ ፊደላት***

ባሕርየ ድምጽ ማለት የድምጽ ጠባይ ማለት ነው።የግእዝ ፊደል በሰው ሕዋሳተ ድምጽ /የድምጽተንቀሳቃሽ አካላት ልክ በስድስት መደቦች የተመደበ የእያንዳንዱ ፊደል ባህርየ ድምጽ አለው።

ሀ. ልሕሉሕ /ልል ድምጽ ጉርኤ ሀ፡አ

ለ. ጠባቂ ድምጸ ጉርኤ ተ፡ዐ

ሐ. ድምጸ ታሕናግ  ቀ፡ኀ፡አ፡ገ

መ. ድምጸ ልሳን /ምላስ / ለ፡ረ፡ተ፡ነ፡ደ፡ጠ፡ዘ

ሠ. ድምጸ ከናፍር  መ፡በ፡ወ፡ጰ፡ፈ፡ፐ

ረ.  ድምጸ ስን /ጥርስ/  ሥ፡ሰ፡ጸ፧ፀ

## ***ሕጹጻን ፊደላት***

እነዚህ ፊደላት ከ፳፮ቱ የግእዝ ቋንቋ ፊደላት ውጭ ሲሆን በግእዝ ቋንቋ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ያላቸው ናቸው።ፊደላቱም በተለያዩ አጠራር ይጠራሉ።

***ሀ. ሕጹጻን ፊደላት*** -ይህም ማለት “ ሐጸ-ጐደለ ከሚለው አንቀጽ የተገኘ ሲሆን ሕጹጽ ማለትም ጐደሎ ማለተ ነው ይህ ስያሜ የተሰጠበት ዋና ምክንያት ፊደላቱ እንደ ሌሎች (፳፮ቱ ) እስከ ሳብእ ሰለማየዘልቁ ነው።

***ለ. ዲቃላ ፊደላት-*** ይህም ማለት በድምጻቸው በቅርጻቸው ከሌሎች (፳፮ቱ) ስለሚለዩ ነገርግን የነዚህን ቅርጽ እና ድምጽ መነሻ አድርገው /ይዘው መገኘታቸው ከነዚህ ፊደላት የተገኙ /የተደቀሉ ለማለት ተሰጧቸዋል

ሐ. ዝርዋን ፊደላት-ይም ማለት ብትን ድምጾች ፡ብትን ቅርጾች ማለተ ነው።

በአጠቃላይ በተለያየ ስያሜ ቢሰየሙም ዋናው ነገራቸው በግእዙ ውስጥ ያላቸው ቦታ ነው የሚታየው አነዚህን ፊደላትም ቀጥለን እንመለከታለን።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ኰ | ኲ | ኵ | ኳ | ኴ |
| ጐ | ጒ | ጕ | ጓ | ጔ |
| ቈ | ቊ | ቍ | ቋ | ቌ |
| ኈ | ኊ | ኍ | ኋ | ኌ |

## ***አናባቢ /voules/***

በጥንት የልሳነ ግእዝ ሥነ-ድምጽ ሀ፡አ፡ወ፡የ የግእዝ ፊደላት አናባቢ ወይም ድምጽ ሰጪዎች ሆነው መዘጋጀታቸው በታሪክ ይታወሳል ።እነዚህ አናባቢዎቹ ፊደላት ከሌላው የግእዝ ፊደል ጋር በጠናጥል እተደመሩ እያንዳንዱ ድምጽ የየራሱን ድምጽ እንዲአሰማ ያደርጉት ነበር።

በሌላ መልኩ አናባቢ የሚባሉት ዉ፡ዪ፡ኣ፡ዬ፡ህ፡ዎ ናቸው ይላሉ።(አለቃ አያሌው ታምሩ ፡ኢትዮጵያ በሦስቱ ሕግጋት)

-ሌሎችም ነገሮች ቢኖሩም ዋናው ነገር ዛሬ እየተጠቀምንበት ያለው ፊደል አናባቢ አያስፈልገውም የሚሉ ጽሑፎች አሉ።

## ***ጉባኤ ፊደላት***

የፊደሎች ስብስብ /ስብሰባ  ማለት ነው።

ከዚህ በላይ ብንቀርጻቸው ዓይነታቸው ባህርየ ድምጻቸው እና ሌሎች ጠባያቶቻቸውን የተመለከትናቸው ፊደላት ሁሉት ሁለት፡ሦስት ሦስት ፡ዐራት ዐራት ከዚህም በላይ እስከ ዐሥር እና ዐሥራ ሁለት በላይ አንድ ላይ እየተሰበሰቡ የግእዝን ዘር እና ነባር/ግስንና ስምን/ያስገኛሉ።

ምስሌ፡-ግስ -ሀለወ <u>ነባር አንቀጽ -አልቦ</u> <u>ዘርእ -ምልክና</u>

-ሐለመ -ውእቱ -ልዕልና

-ሰከበ -አኮ -ብርሃን

-ቦ -ክብር

<u>ነባር(ስም)</u> -መልከ ጼዴቅ <u>ጥንታዊው ግእዝ ግሥ</u>

-አብርሃም ሀረበደ--ሀረበደ

-ኢዮብ ሀየመነ--ሀየመነ

-ኤልያስ መወተ--ሞተ

ከዚህ ላይ ጀምሮ ግስ/አንቀጽ/እና ነባር ማጥናት ተማሪዎች እንዲያጠኑ ይደረጋል።

## *የተመሳሳይ ፊደላት አጠቃቀም በቃላት ውስጥ*

- ተመሳሳይ ድምጽ ያሏቸው ፊደላት አገባብ እና አጻጻፍ አንዱ በሌላው የማይሰካ ነው ።ተመሳሳይ ድምጽ ያሏቸውን ፊደላት በተገቢው መንገድ አለመጠቀም በግሥ ላይ የሚመጣውን የትርጉም ለውጥ ቀጥሎ በተዘረዘሩት ግሶች ላይ ማየት ይቻላል።

| | | |
|---|---|---|
| ሐለየ-----አሰበ | ሰብሐ-----አመሰገነ | ሐለወ--------ጠበቀ |
| ኀለየ----ዘፈነ | ሠብሐ-----ሰባ | ሀለወ--------ኖረ |
| መሀረ-------አስተማረ | ሠዐለ-----ሣለ | ሐብለ-----ሴሰኛ ሆነ |
| መሐረ----ይቅር አለ | ሰአለ----ለመነ | ኀብለ-------ደፈረ |
| ሰረቀ-----ሰረቀ | ርኀበ-----ተራበ | ፀፈረ-------ፅፍርን ቆረጠ |
| ሠረቀ----ወጣ | ርህበ----ሰፊሆነ | ጸፈረ----ሠራ |
| ፈጸመ----ጨረሰ | ርህጸ----ተበሳጨ | |
| ፈፀመ----ዘጋ፡ለጎመ | ርህፀ----ወዛ | |

- ስምን በምንጽፍበት ጊዜም ፊደላችንን ጠንቅቀን ባለመጻፋችን ብዙ የትርጉም ለውጥ ያመጣል።
  ለምሳሌ፡-
  - ዓመት--ዘመን፡ጊዜ

አመት--ሴት አገልጋይ(ገረድ)

- ፍስሐ--ቂጣ
  ፍሥሓ--ደስታ

❖ በሥርዓተ አጻጻፍ ጊዜ መጠቀም ያለብን ሥርዓት ያለውን አጻጻፍ መሆን አለበት።ዝም ብለን የምንጽፍ ከሆነ ትርጉም አልባ (የለሽ) ሆኖ ይቀራል።እንዴት እንደምንጽፍ ከዚህ በታች ያሉትን የጥምር ፊደላት አገባብና አጻጻፍ ምሣሌዎችን እንመለከት።

ምሳሌ፡-***<u>ሀ/ሀሌታው ሀ</u>***

*ሀብታሙ፣ሀብተሥላሴ፣ሀብትሽይመር፣ሀገሪቱ፣ሀገርነሽ፡ሀላዌ፣ሀልውና፣ምሁር፣መምህር፣መምህራን፣ትምህርት፣ብርሃኑ፣ብርሃን፣ብሩህ፣ከሀሊ፣ክህሎት፣ሥነ-ላህይ፣ ሣህሉ፣ካህን፣ካህናት፣ሣህሌ፣ወሀቤ፣ተውህቦ፣ሊቀ ትጉሃን፣ወልደ ብርሃን፣ገሃድ፣ጎህ፣ጎህጽባህ፣ሃይማኖት፣ባይህ፣ዓለምነህ፣ፍርሀት፣የውሀት፣የዋህ፣የውሀን፣መሀይምን፣መሀይምናን፣ንህብ፣ዶርሆ፣ድድሆ፣ሽሀር፣መሀር፣ሀኬት፣ሁከት፣ወዘተ...የመሳሰሉት በእነዚህ ፊደሎች መጻፍ አለባቸው።*

***<u>ሐ/ሐመሩ–ሐ</u>***

*ሐምሌ፣ነሐሴ፣ሐረገወይን፣ሕይወት፣ምህረት፣መሐሪ፣ምህረት፣ሐዋርያት፣ሐዋርያ፣ወለደሐዋርያት፣ሕፃን፣ሕፃናት፣ሐውልት፣ፍትሐ ነገሥት፣ሐሜት፣መሰረተ ሐሳብ፣ንድፈ ሐሳብ፣ባሕታዊ፣ባሕታውያን፣ሕዝብ፣አሕዛብ፣ፍሥሓ፣ንቃተ ሕሊና፣ሕዋስ፣ተሕዋስያን፣ቤተልሔም፣ሐተታ፣ይስሐቅ፣ብሔር፣እግዚአብሔር፣ሐር፣ሐሰት፣ትሕዝብት፣ሐረርጌ፣ለገሐር፣ሐመረ ብርሓን፣ባሕር፣ሐረጻ፣ባሕረ ነጋሽ፣ጎህጽባሕ፣ሐማት፣ሐና፣ሕለተ ወርቅ፣ሒሳብ፣ወዘተ...የመሳሰሉት በእነዚህ ፊደሎች መጻፍአለባቸው።*

***<u>ኀ/ብዙኃኑ–ኀ</u>***

*ኃጋይ፣ኃይለሥላሴ፣ኃይሌ፣ኃይለ፣ማርያም፣ኀሙስ፣መድኃኒት፣ኃጢአት፣ኃጥእ፣ኃጥአን፣ማኅደር፣ኅቡእ፣ኅቡአን፣ኂሩት፣ኅዳር፣ታኅሣሥ፣ኅብረት፣ኅብሩ፣ማኅበር፣እኅት፣ኅብስቱ፣ማኅሌት፣ገብረመድኅን፣ደኅና፣መድኅን ድርጅት፣ረኃብ፣ኅብረ ቀለም፣ቀብሪደኃር፣ውኃ፣ኅሩይ፣ኅሩያን፣የኅትመት ሥራ፣ማኅተም፣ማኅፀን፣ደጋኅቡር፣ኃሠሣ፣አምኃ እጅ ነሣ፣ወዘተ...የመሳሰሉት በእነዚህ ፊደሎች መጻፍ አለባቸው።*

***<u>ሠ/የንጉሡ–ሠ</u>***

*ሠራዊት፣መሠረት፣ምሥረታ፡አመሠራረት፣ንጉሠ ነገሥት፣ሥምረት፣ሥምሪት፣ሤሚናር፣ሠረገላ፣ገሠሠ፣አሥማር፣ሥርጉት፣ሥሐቅ፣ሥጋ፣ዓሣ፣ሥርጋዌ፣ትዕግስት፣ንግሥት፣ሥቃይ፣ሥዩም፣ሠናይት፣ሥላቅ፣ዕሤተ፣ሥሉስ፣ሐሣር፣ሠላስ፣ወልደሥላሴ፣ተመሥጦ፣ሥሉጥ፣ሥልጣን፣ሥዕል፣ሥነልቡና፣ዓሥራት፣ምሣር፣መሣሪያ፣ሥነጽሑፍ፣ሥነጥበብ፣ሥነፀሐይ፣መሥዋዕት፣መሥፈርት፣ሠፈራ፣ሠፈር፣ሠርከ፣የሠርከ ጸሎት፣ሥራ ተሠራ፣ወዘተ...የመሳሰሉት በእነዚህ ፊደሎች መጻፍ አለባቸው።*

***<u>ሰ/የእሳቱ–ሰ</u>***

*መስፍን፣ሰፋኒት፣ስብሐት፣ሰው፣ስቡሕ፣ስሜነህ፣ስመኝ፣ሰንበት፣ወልደሰንበት፣ዓለምሰገድ፣ወሰን፣አስፋው፣አሰግድ፣ኪሮስ፣ሰማዕት፣ሰማዕታት፣ገብረክርስቶስ፣እንድርያስ፣ኤልያስ፣ኤርምያስ፣ኢሳይያስ፣ኤልሳዕ፣አስጢፋኖስ፣ቀሲስ፣መነኩሴ፣ሐዲስ፣ማቱሳላ፣አስረስ፣ስደት፣ስደት፣ስደተኛ፣መሰደድ፣ወዘተ...የመሳሰሉት በእነዚህ ፊደሎች መጻፍ አለባቸው።*

***<u>አ/የአልፋው–አ</u>***

*አበበ፣አናጋው፣ተአምሩ፣አእምረ፣አዳም፣አስቴር፣አረዳ፣አውራጃ፣ትንሣኤ፣አወጣሽ፣አያልነሽ፣እንግዳ፣አባ፣አበው፣አረጋዊ፣አዕማድ፣አዜብ፣አቀበት፣አሰብ፣አቢብ፣አሰፋ፣አንዳርጌ፣አሸብር፣ወዘተ....የመሳሰሉት በእነዚህ ፊደሎች መጻፍ አለባቸው።*

***<u>ዐ/የዓይኑ–ዐ</u>***

*ዓቢይ፣ዓለም፣ዓለሚቱ፣ዓለማየሁ፣ዐባይ፣ዓምዱ፣ዕድገት፣ዐዋቂ፣ዕውቀት፣ልዑል፣ልዕልት፣ላዕላዕ፣ዕለት፣ዓመት፣ዓሣ፣መዓዛ፣ዓቃቤ ሕግ፣ዓርብ፣ረቡዕ፣ዕሴተ፣መረዓዊ፣ሥርዓት፣ዓሥራት፣ሥዕል፣ዕድሜ፣መዋዕለ ሕፃናት፣ዓጸደ፣ዓይናለም፣ወዘተ...የመሳሰሉት በእነዚህ ፊደሎች መጻፍ አለባቸው።*

***<u>ጸ/የጸናጽሉ–ጸ</u>***

*ጽጌ፣ጺጋየ፣ጽድቅ፣ጸለምት፣ጽናጽል፣ቀጸላ፣ነጸረ፣ዓጻዊ፣መጾር፣ቅርጽ፣ተግሣጽ፣ገጽ፣አፈጻጸም፣ጽጌረዳ፣ምጽዋት፣ለምጽ፣አንቀጽ፣ጺጋ፣ፍጹም፣ጾም፣ጸሎት፣ጽልመት፣ተፍጻሜት፣ወዘተ...የመሳሰሉት በእነዚህ ፊደሎች መጻፍ አለባቸው።*

***<u>ፀ/የፀሐዩ–ፀ</u>***

ሥርፀ፣ደምጸ፣ፀር፣ፀምሩ፣ፀዳለ፣ዐፀደ፣ሕፃን፣ሕንፃ፣ዓማፅያን፣ፀወን፣ተፅዒኖ፣ምሩፅ፣ዓፄ፣ኖፃ፣ሞፃ፣ማኅፀን፣ዜው፣ፍላፃ፣ፃዕር፣ሕፀፅ፣ማዕፄ፣ዕፅ፣ዕፅዋት፣ፃፄ፣ፆታ፣ወዘተ...የመሳሰሉት በእነዚህ ፊደሎች መጻፍ አለባቸው።

## የገእዝ ቋንቋ ፊደላት እና ትርጉም

ሀ--ሄ ሆይ ሆይ ሀወይ ---------ብሂል፡ህልው እግዚአብሔር
ለ--ላሜድ ላዊ ልዑል---------ብሂል፡ልዑል እግዚአብሔር
ሐ--ሔት ሐወት ሕያው ሕይወት--------ብሂል፡ሕያው እግዚአብሔር
መ--ሜም ማይ ምዑዝ--------ብሂል ፡ምዑዝ አግዚአብሐር
ሠ--ሣምኬት ሠውት------------ብሂል፡ሰፋኒ አግዚአብሔር
ረ--ሬስ ርእስ-------------ብሂል፡ርኡስ እግዚአብሔር
ሰ--ሳን ስቡሕ-----------ብሂል፡ስቡሕ እግዚአብሔር
ቀ--ቆፍ ቅዱስ-----------ብሂል፡ቅሩብ እግዚአብሔር
በ--ቤት ባዕል-----------ብሂል፡ባዕል እግዚአብሔር
ተ--ታው ተዊ ትጉህ------ብሂል፡ትጉህ እግዚአብሔር
ኀ--ኀርሞ ኄር------------ብሂል፡ኄር እግዚአብሔር
ነ--ኖን ነሐስ ንጉሥ--------ብሂል፡ንጉሥ እግዚአብሔር
አ--አሌፍ አልፍ አብ---------ብሂል፡አብ ፈጣሬ ኵሉ ዓለም
ከ--ካፍ ከሃሊ--------ብሂል፡ከሃሊ እገዚአብሔር
ወ--ዋው ዋዌ ዋሕድ-------ብሂል፡ዋህድ እገዚአብሔር
ዐ--ዔ ዐይን ዐቢይ-------ብሂል፡ዐቢይ አግዚአብሔር
ዘ--ዛይ ዘይን ዝኩር------ብሂል፡ዝኩር አግዚአብሔር
የ--ዮድ የማን ቀኝ እጅ------ብሂል፡የማነ እግዚአብሔር
ደ--ዳሌጥ ዳ/ን/ልት ድልው-------ብሂል፡እግዚአብሔር
ገ--ጋሜል ገሞል-------ብሂል፡ግሩም እግዚአብሔር
ጠ--ጤት ጠይት ጠቢብ------ብሂል፡ጠቢብ እግዚአብሔር
ጰ--ጰይት ጴት-------ብሂል፡
ጸ--ጸዴ ጸደቀ ጻድቅ-------ብሂል፡ጻድቅ እግዚአብሔር
ፀ--ፀጰ ፀጰ ------ብሂል፡
ፈ--ፌ ፈፍ ፍቁር-------ብሂል፡ፍቁር እግዚአብሔር
ፐ--ፒ ፔ ፌ--------ብሂል፡

## የግእዝ ቋንቋ የመማር ጥቅም

፩.በግእዝ ቋንቋ የተጻፉ መጻሕፍትን አንብቦ ለመረዳት ለመተርጐም
፪.የግእዝ ቋንቋ ምንነት የአባቶችን ወግ፣ ባህል፣ታሪክ፣ሥነ-ጽሑፍና ከተለያዩ ቋንቋዎች ወደ ግእዝ የተረጎሙ መጻሕፍትን ያስተላለፉልን መሆኑን ለመረዳት ያልሞተ ቋንቋ መሆኑን ለመግለጽ በአጠቃላይ ሲያከናዉኑት የነበረውን ትውፊት ለመረከብ።
፫.አጫጭር ንግግሮችን የመግባቢያ ሃሳቦችን ፣ሥነ-ጽሑፎችን በግእዝ ቋንቋ ለማቅረብ
፬.ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመተርጐም እና ከምሥጢር ዳህጽ ለመዳን
፭.ግእዝ ቋንቋ በያዛቸው መዛግብት ላይ ችግር ከመድረሱ በፊት ለመጻኢው ትውልድ ባህሉን፣ሃይማኖቱን፣ታሪኩን፣በራሱ ባህል የሚሠራ ትውልድ መፍጠር ነው።

# ምዕራፍ---፪

## ሥርዓተ-ንባብ/ፍኖተ-ንባብ ዘልሳነ ግዕዝ

### ፪.፩ የንባብ ዐበይት ክፍሎች

የልሳነ ግዕዝ ፍኖተ ንባብ/የንባብ መንገድ በ ፬ ዐበይት ክፍሎች ይከፈላል።

፩.ተነሽ ንባብ ፫.ተጣይ ንባብ

፪.ወዳቂ ንባብ ፬.ሰያፍ ነባብ ናቸው።

- ፹ወ፩ መጻሕፍትን ሁሉም በእነዚህ የንባብ ሥልቶች ይጓዛሉ።

***፩.ተነሽ ንባብ*** በአምስት ፊደላት እየደረሰ መድረሻውን ፊደል በማንሳት ይነበባል።የሚደርስባቸው ፭ቱ ፊደላት

ግዕዝ ፊደል ካዕብ ፊደል

ሣልስ ፊደል ራብዕ ፊደል

ሳብዕ ፊደል ናቸው።

- ተነሽ ንባብ በ፪ቱ(በኃምስ እና በግዕዝ ፊደላት) አይደርስም።

ግዕዝ፡-ሐረ ገብረ ሰመየ

ወነገደ መጽአ ጸሐፈ

ድንግለ ወጽሙረ ከብረ ወዘተ ተረፈ....

ካዕብ፡-ሐሙ ወርኃቡ ሖሩ ወዐርጉ

ጸሙኡ ወተመንደቡ ንዑ ወጻኡ

ሣልስ፡-ሑሪ በእንግዳኪ ወብልዲ ጸበለ እግርኪ

ሰአሊ ወጸልዩ

ራብዕ፡-ሣህል ወርትዕ ተራከባ ጽድቅ ወሰላም ተስአማ

ሑራ ወንግራ ለአርዳዕየ

ረከባ መልአካ

አንስት ይትምሐራ በቤቶን

ሳብዕ፡-እግዚኦ ኵነኔከ ሀቦ ለንጉሥ

ይዕዜ ተስእሮ ለገብርከ

ኢመጽአ ከመ ይኰንኖ ለዓለም የሚሉትን ማየት ይቻላል

***፪.ወዳቂ ንባብ***-በሰባት ፊደላት (ከግዕዝ--ሳብዕ ባሉት)እየደረሰ መድረሻውን ፊደል ጣል በማድረግ ይነበባል።

<u>ግዕዝ</u> <u>ካዕብ</u> <u>ሣልስ</u> <u>ራብዕ</u> <u>ኃምስ</u> <u>ሳድስ</u> <u>ሳብዕ</u>

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አሐደ | ዝንቱ | ብዕሲ | ደብተራ | ሥላሴ | ዝ | ከበሮ |
| አሐተ | እሙንቱ | አሐቲ | መና | ኮነኔ | ብቻ ነው | መሰንቆ |
| ክልኤተ | አቡሁ | መሀሪ | ዕዝራ | ውዳሴ | | ባረኮ |
| እስፍንተ | እሙ | ፈታሒ | እማ | ብዕሴ | | ኢያሪኮ |
| | | በላኢ | አፍቀራ | አውሴ | | ወሀቦ |

***፫.ተጣይ ንባብ---*** በሳድስ ፊደል ብቻ የደርሳል

የመድረሻውን ቀዳማይ ፊደል በመያዝ ያዝ በማድረግ ጣል ብሎ ይነበባል።

ምሳሌ፡-ሕይወት ወሞት

አብ ወእም

ሕዝብ ወአሕዛብ

መርሕ ወዛሕን

***፬.ሰያፍ ንባብ---*** በሳድስ ፊደል ብቻ ይደርሳል፡፡

የመድረሻውን ተከታይ ፊደል በማንሳት ይነበባል።

ምሳሌ፡-አማኑኤል

የሐውር

ጤግሮስ

ስንድሮስ

❖ ተጣይ እና ሰያፍ ንባባት በግዕዝ ዜማ ጊዜ የመድረሻቸውን ፊደል በመዋጥ ሊዜሙ ይችላሉ።

## **፪.፪ የንባብ ነውሳን ክፍሎች**

እነዚህ የንባብ አይነቶች ከዐራቱ ዐበይት ናባባት ሳይወጡ ልዩ ልዩ ጠባይ የሚያሳዩ ናቸው።እነዚህ የንባብ አይነቶችም የሚከተሉት ናቸው።

***፩.ቀዋሚ/ዐራፊ/ንባብ***---ሁለት ተከታታይ ቃላትን የያዘ ሁለቱ ቃላት ሳይናበቡ እየራሳቸው የሚነበቡት ስልት ንባብ ነው።

ምሳሌ፡-አክብር አባከ ወእመከ

ኢትዝግቡ ለክሙ መዝገበ

አንበሳ መሰጠ ዘየአክሎ

***፪.ተነባቢ ንባብ----*** መድረሻፊደሉ ግዕዝ ራብዕ ኃምስ እና ሳብዕ የሆነ ስም ከተከታዩ ስም ጋር በድምጽ ንባብ እየተያዘ የሚነበብ ንባብ ነው።

ግዕዝ፡-መሰረተ ሕይወት

መጽሐፈ ልደቱ

ወልደ ዳዊት

ራብዕ፡-ደብተራ ኦሪት	መሐላ ብዕሲ

ጥቃ ቤት	መሰንቆ ዳዊት

ከበሮ ማህሌት	ተናግሮ ቃል

ኃምስ፡- ውዳሴ አምላክ

አኀዜ ኵሉ

ኵነኔ ሰማይ

- <u>የአገባብ ቀዋሚ ንባባት</u>	<u>ተናባቢ ንባባት</u>

ምሳሌ፡-አኮኑ ይመጽእ	ሰሐቢ ዘር

እፎ ይከውን	ዘመድ ዘር

ዮጊ ይመጽእ	ሣልስ ቅጽል

ኡዲ ኢመጽአ/ኢበጽሐ	ሳድስ ወዘተ

- <u>የተነባቢ አገባባት /የአገባብ ተናባቢዎች</u>

| | |
|---|---|
| አመ ይመጽእ | ኀበ የሐውር |
| ምስለ ሰብእ | መንገለ ጥቃ ቤቱ |
| ከመ ካልአን | ሶበ አኮ እግዚአብሔር |
| እስመ ሞተ | ውስተ ቤተ መቅደስ ነበረት ወዘተርፈ |

## ፫.ጠባቂ እና ልሕሉሕ /ልል/ ንባብ

- የግእዝ መካከለኛው ፊደልና ድምጽ በአካላተ ንባብ (በከንፈር፣በምላስ፣በድድ)እየጠበቀ የሚነበብ ንባብ ጠባቂ ንባብ ይባላል።
- የግዕዝ መካከለኛ ፊደልና ድምጽ ከላይ በተገለጹት አካላተ ንባብ ላልቶ የሚነበብ ንባብ ልሕሉሕ/ልል/ ንባብ ይባላል።

| <u>ጠባቂ</u> | <u>ልሕሉሕ</u> |
|---|---|
| ምሳሌ፡-ቀደሰ ይቄድስ ይቀድስ | ምሳሌ፡-ቀተለ ይቅትል |
| ይቀትል | ገብረ ይገብር |
| መካሕ | ቀተል ቅቱል |
| ጠባብ | ድኅነ ድኅን |
| ሕዳግ | ሤመ ሢመት |
| ነካር | |

**ግንዛቤ**፡-ካልአይ አንቀጽ ምንጊዜም ጠባቂ ነው።ይህም

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቀተለ ይቀትል | ሀ ወይም አ በግስ መካከል ከገቡበት ካልአይ አንቀጽ | | |
| ቀደሰ ይቄድስ | ልሕሉሕ ንባብ ይሆናል። | | |
| ገብረ ይገብር | መዐረ | ይማሕር | ሀ |
| ሤመ ይሰይም | ድኅነ | ይድኅን | |
| ተንበለ ይተነብል | ሰአለ | ይስእል | አ |
| ሴሰየ ይሴሲ | ሰዐረ | ይስዕር | |
| ጦመረ ይጦምር | | | |
| ባረከ ይባርክ | | | |

## ፩.ቆጣሪና ጠቅላይ ንባብ

❖ «ሀ» ወይም «አ» በመካከሉ የሚገኙበት የግዕዝ ንባብ የፊደል አቀማመጥም ሆነ የቁጥር መጠን ምንም ዓይነት ለውጥ ሳይኖረው መካከለኛውን ፊደል በመቁጠርም በመጠቅለልም ይነበባል።

ምሳሌ፡-አዕረገ ሰማዕት---የመሳሰሉትን ጠቅሎም ሳይጠቀልልም በመቁጠር

አዕሩግ ማንበብ ይቻላል።

አዕጹቅ

ማሕቶት

## ፪.ጐራጅ ንባብ

❖ <u>መካከለኛውን ፊደል አጥብቆ መነሻውን ፊደል የሚጐርድ</u>

ሰ፣ተ፣ዘ፣ደ፣ጸ፣ጠ የተባሉት ፊደላት በርሑቅ መደብ/ሦስተኛ መደብ/ካልአይ አንቀጽ/ትንቢት/ሣልሳይ አንቀጽ/ዘንድ/በመካከል ጠብቀው የመነበብ እና የቀዳማይ አንቀጽ መነሻ የሆነውን ፊደል«ተ»ን በማስቀረት ይነበባሉ።

| | | |
|---|---|---|
| ተሰብሐ | ይሴባሕ | ይሰባሕ |
| ተርአሰ | ይተረእስ | ይተርአስ |
| ተዘምደ | ይዛመድ | ይዘመድ |
| ተደረ | ይዴረር | ይደረር |
| ተጸምደ | ይጻመድ | ይጸመደ |
| ተጠምቀ | ይጠመቅ | ይጠመቅ |

በውእቶሙ ፣ በይእቲ እና በውእቶን እንዴት እንደሆነ አስረዳ

❖ <u>ምዕላድ ፊደልን ከመድረሻው ጐርዶ የሚያስቀር</u>

በዚህ ሥርዓተ ንባብ ከፍተኛ ሚና ያላቸው ፊደላት ቀ፣ከ፣ገ፣ነ ናቸው።

ቀ---አጥመቀ-አነተ ሠረቀ ጸረቀ ወዘተ

አጥመቁ-አነ ዖቀ

አጥመቂ--አንቲ በረቀ

አጥመቅሙ--አንትሙ

አጥመቅን--አንትን

ከ---ሰበከ--ለአንተ ሰበኩ--አነ ስበኪ--አንቲ ሰበክሙ--አንትሙ

ባረከ--አንተ ባረኩ--አነ ባርኪ--አንቲ ባረክሙ--አንትሙ

በተከ--ለአንተ በተኩ--አነ በተኪ--አንቲ በተክሙ--አንትሙ

ነክነከ--ለአንተ ነክነኩ--አነ ነክነኪ--አንቲ ነክነክሙ--አንትሙ

ገ---ሐደገ

ሐገገ

መዘገ

ሰፍነገ

ነ---ለንህነ ብቻ ነው

አምነ--አመነ

ኮነ---ኮነ

አጠነ---አጠነ

- <u>በመድበል ቅጽል መድረሻ የሚጐረድ</u>

  መድበል ቅጽል የመድረሻው ቀዳማይ ፊደልን በማጥበቅ መድረሻ የነበረውን ምዕላድ ፊደል «ት»ጐርዶ ይነበባል።

  ምሳሌ፡-መስጥት----መስጥ

  ዐጸድት----ዐጸድ

  ሰየጥት----ሰየጥ

  ጐራጅ ፊደላት ሳይጐርዱት የሚነገር ግዕዝ ንባብ የለም።

## ፮ መጠይቅ ንባብ

ኑ፣ሁ የተባሉ መጠይቅ ፊደላት በመድረሻው እየጨመረ የሚነበብ ንባብ ነው።

ምሳሌ፡-ምንትኑ

መጻእከኑ/ሁ

አኮሁ

መልዑኑ/ሁ

ሶበሁ

አምነኑ/ሁ

## ፯ የትራስ ፊደላት ሥርዓተ ንባብ

<u>፩.የ«ሰ»እና የ«መ» ሥርዓተ ንባብ</u>

- በካብዕ በሣልስ በራብዕ በኃምስ በሳብዕ ፊደላት በደረሰው ወዳቂ ንባብ መድረሻ ላይ እየወደ ቁ/እየተገኙ ወዳቂውን ንባብ ተነሽ ንባብ ያደርጉታል።

ምሳሌ፡-ዝንቱሰ ብዕሲሰ ዕዝራሰ ይእዜሰ መሰንቆሰ

ዝንቱመ ዛቲመ ደብተራመ ብእሴመ ኢያሪኮመ

- «ሰ» እና «መ» ተነሽ፣ተጣይ እና ሰያፍ ንባባትን በመድረሻ እየተገኙ ወዳቂ ያደርጓቸዋል።

ምሳሌ፡- ገብረሰ ሰብእሰ አብርሃምሰ

ተነሽ { ዓለመሰ ተጣይ { ምድርሰ ሰያፍ { ኤፌሶንሰ

ገብረመ አይሁድመ ዮናስመ

፪.ሀ፣ሂ፣ሃ፣ኒ በ፬ቱ ንባባት መድረሻ ላይ እየወደቁ ፬ቱን ንባባት ወዳቂ ንባባት ያደርጉዋቸዋል።

ምሳሌ፡- ሰማየሂ ዳዊትሃ ሙሴሀ አብርሃምሀ

ተነሽ { ሰማየኒ ዳዊትሂ ሙሴኒ አብርሃም

ተጣይ { ማርያምሃ ወዳቂ { ሳራሂ ሰያፍ { ትዕማርሃ

ዳዊትኒ ሙሴኒ አብርሃምኒ

፫.ትራስ ፊደላት አ፣ኬ፣ሰ በመድረሻ እየወደቁ ሦስቱን ንባባት ወዳቂ ያደርጓቸዋል።

እግዚእየአ ካልእአ አዝዝአ

ተነሽ { ይምጽኡኬ ተጣይ { ምንተኬ ሰያፍ { አድኅንኬ

አድኅንሰ

- የትራስ ፊደላት በአንድ ላይ ነው የሚነበቡት።
- «ሰ»በአገባብ መድረሻ ቢወድቁም ሁሉም አገባቡም አየነሱም።

## ፪.፫ የእርባታ ንባቦች

በግስ እርባታ ጊዜ የሩቅና የቅርቦች የንባብ ሒደትን እንዲሁም የወንድ እና የሴት ልዩነቶችን የሚያሳይ የንባብ ሁኔታ ነው።

ምሳሌ፡-አእመረ

አእመራት

አእመርክሙ

አእመራ(የሩቆች ሴቶች ሲያቁ)

አእመራ(የሩቁ የሩቋን ሴት ሲያውቅ)

## ፪.፬ የተጸውዖ ስሞች ንባብ

የተጸውዖ ስሞች ንባብ ከ፬ቱ የንባብ ስልቶች ባይወጡም ከአናቅጽ ንባባት የተለዩ ሕግና ሥርዓት አላቸው።

፩.ሦስቱ ቀለም ሁኖ በግዕዝ ተነስቶ በድርድሩ ውስጥ ራብዕ፣ኃምስ፣ሳብዕ ያለበት ስም ተነሽ ንባብ ነው።

ምሳሌ፡-አቤል አዜብ ----ኃምስ

አጋር አሞጽ ----ሳብዕ

ራዓብ------ራብዕ

- «አዳም»ተነስቶ አይነበብም «አደመ» ከሚለው የተገኘ ዘር ውስጠ ዘ ስለሆነ ዘር ውስጠ ዘ ደግሞ ስለማይነሳ ።«አሌፍ»የሚለው ተነሽ ነው «አሌፋት» ብሎ ሲበዛ አይነሳም።

❖ በግዕዝ ተነስቶ ቅድመ መድረሻው ሳብዕ የሆነ ስም ተነስቶ ይነበባል።

ምሳሌ፡-ሰሎሞን　　መቅዶንዮስ　　አውሳብዮስ

አርዮስ　　መርቆርዮስ　　መቃርዮስ

ፊርዖን　　አትናቴዎስ

ጰራቅሊጦስ　　ገላውዴዎስ

- የተሰመረባቸው ቅድመ መድረሻዎች ናቸው።

❖ በግዕዝ/በራብዕ ተነስቶ ቅድመ መድረሻው ሣልስ የሆነ ስም ተነስቶ አይነበብም።

አቡቀለምሲስ　　አብረክሊስ

አብጥሊስ　　ፋሲል　　ዳዊት

፪.በካዕብ ተነስቶ ድርድሩም ካዕብ፣ኃምስ፣ሳብዕ የሆነ ስም ተነስቶ ይነበባል።

ሱቱኤል

ቡኤል

ዱማቴዎስ

❖ በካዕብ ተነስቶ ደካማ ቀለም/ከግዕዝና ከሳድስ ውጭ የያዘ ስም ተነሽ ንባብ አይደለም።

ሩፋኤል

ኡራኤል

፫.በሣልስ ተነስቶ በድርድሩ ሁለት ደካማ ቀለማት የያዘ ስም ተነሽ ንባብ ነው።

ቂርቆስ　　ሚናስ　　ሲድራቅ

ሲላስ　　ጢሞቴዎስ

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ሕግ የማይመሩ ስሞች ይኖራሉ።

ምሳሌ፡-ሚሳኤል　　ሚካኤል

በሣልስ ተነስቶ ሦስት ደካማ ቀለም ሲደረደሩና ቅድመ መድረሻው ሣልስ፣ኃምስ፣ሳበዕ የሆነ ስም ተነስቶ አይነበብም።

ምሳሌ፡-ጊዮርጊስ　　ጲላጦስ

ሚካኤል　　ሊባኖስ

፬.በራብዕ ተነስቶ ድርድሩ ካዕብ፣ራብዕ፣ኃምስ፣ሳድስ እና ሳብዕ የሆነ ስም ተነስቶ ይነበባል።

ምሳሌ፡-ማቴዎስ　　ባቱኤል　　ራሄል

ጣሙኤል　　ራጉኤል　　ያሬድ

ፋኑኤል　　ባሮክ　　ሳሌም

በሕጉ የማየገዙ፡-

ናብሊስ

ራፋስቂስ

፭.በኃምስ ተነስቶ ድርድሩ እንደ፬ቱ የሆነ ስም ተነስቶ ይነበባል።

ሄኖክ ኤርምያስ ኤፍሬም

ሳሌም ቴዎፈሎስ ቄርሎስ ኬልቄዶን

በኃምስ ተነስቶ ድርደሩ ሦስት ደካማ ቀለማት የሆነ ቅድመ መደረሻው ሁለት ሳድስ ቀለም የሆነ ስም ተነስቶ አይነበብም።

ሄሮድስ

ኤልሳቤጥ ኤልዛቤል

፮.በሳድስ ተነስቶ ድርድሩ ራብዕ፣ኃምስ፣ሳድስ፣ሳብዕ የሆነ ስም ተነስቶ ይነበባል።

ጥብርያዶስ ንስጥሮስ

እንድርያስ ስምዖን

ሕዝቅያስ እስክንድሮስ

ሕግ የማይጠብቅ ----እስራኤል

- ❖ በሳድስ ተነስቶ ሦስት ደካማ ቀለም ሲኖር ተነስቶ አይነበብም
  - እስጢፋኖስ
  - እግዚአብሔር
- ❖ ድርደሩ ፍጹም ሳድስ ወይም አንድ እንኳን ቢኖር ተነስቶ አይነበብም።
  - ግብጽ እስክንድር
  - ክርስቶስ ጽርእ
  - እስክንድሮስ ግዮን ልዩ ነገር ፡ግዮን

፯.በሳብዕ ተነስቶ ድርድሩ ራብዕ፣ኃምስ፣ሳብዕ የሆነ ስም ተነስቶ ይነበባል።

ቶማስ ዮሴፍ ዮናስ

ሮቤል ሰሮንያስ ዮሐንስ

ቆሮንቶስ ዮናታን

- ❖ በሳብዕ ተነስቶ ቅድመ መድረሻው ሣልስ ከሆነ ተነስቶ አይነበብም
  - ዮዲት
  - ሆሎፎርኒስ

፰.ሁለት ቀለም የሆነ ስም ወዳቂ ወይም ተጣይ ነው።

ሙሴ ካም

ሎጥ ሩት

- ❖ ማንኛውም ስም መድረሻው ከሳድስ ውጭ ከሆነ ተነስቶ አይነበብም።
  - ዓለሙ ማርታ አምሳሉ
  - በቀለ ቢወጣ ዘለቀ

# ምዕራፍ--፫

## ስም

ስም ቃል ሲሆን «ሰመየ» ስም አወጣ ብሒ ስም ማለትም መጠሪያ መሰየሚያ ፍጥረታት ሁሉ የሚጠሩበት ማለትም ሕይወት ያላቸውም የሌላቸውም በዚች ዓለም የሚኖሩ ሁሉ የሚጠሩበት ነው ።

ስምን ከሁለት ዐበይት ክፍሎች እናገኘዋለን

ሀ.ከግስ/ውልድ ስም

ለ.ከተፈጥሮ/ነባር

## ሀ.አስማት እምነ ግስ/ውልድ ስሞች

- ግስን በመገሰስ/በማርባት ጊዜ የምናገኘውን ስም «ውልድ ስም»እንለዋለን።
- የተለያዩ ውልድ ስሞች አሉ።
- ዘመድ ዘር---ቀተለ ካለው ቀትል የሚል ዘመድ ዘር ስም ማውጣት
- ባዕድ ዘር---ቀደሰ ካለው መቅደስ የሚል ባዕድ ዘር መቀደሻ ቦታ ማለት ነው።
- ምዕላድ ዘር---ሰብሐ ካለው ስብሐት የሚል ምዕላድ ዘር ምስጋና
- ሳቢ ዘር እና ንዑስ አንቀጽ ---ድርጊት ተቀባይን ስለሚያስቡ ንዑሳን አናቅጽ ተብለው የግስነት መዓረግ ቢኖራቸውም ስሞች ናቸው።

  ምሳሌ፡- ቅትለት--መግደል/መገደል ከቀተለ የሚገኝ ሳቢ ዘር ቢሆንም ስም ነው።ቅትለተ ሰብእ ፈድፈደ--ሰውን መግደል ተበራከተ ነቢብ ጽድቅ/ነቢበ ጽድቅ ያፈደፍድ ሞገሰ።
  (እውነትን መናገር ተወዳጅነትን ያተርፋል)
- ሣልስ ቅጽሎች--ቀታሉ-ገዳይ ከቀተለ የተገኘ ሣልስ ቅጽል
- ሳድስ ቅጽሎች --ቅቱል-የተገደለ ከቀተለ የተገኘ ሳድስ ቅጽል

## ለ.አስማት እምነ ተፈጥሮ/ነባር

ነባር ማለት ከግስ እርባታ የሚገኝ እና ለግስ እርባታም ዘር የማይሆን አንድ ጊዜ ቋንቋው ሲፈጠር የሚወጣ መሰየሚያ ነው።

ምሳሌ፡- ሐመር/መቅረስ---መርከብ

ምኔት -----ገዳም

ብዕዛ-----ዋሽንት

እርጎ-----መሐል እጅ

እጠስ-----ቅንድብ

ማዑት-----አንጀት

ብሔ-----ጉማሬ

- ነባርን አስመልክቶ የሚሰጥ አስተያየት አለ፡ይህ አመለካከት ምንድን ነው ሲባል።

  ሁሉም ነባር ሲመረመር ከግስ የወጣ መሆኑ ይታወቃል/እንደሚወጣ ይገኛል ።

  ምሳሌ፡-ዓራት የሚለው ዐርገ--ወጣ ከተባለው ይገኛል፡፡

  ስእርት የሚለው ስእረ--ለመለመ

  ማይ/ሰማይ የሚለው ሰመየ--ስም አወጣ ሰየመ ከሚለው የሚገኝ ዘመድ ዘር ነው።

## ክፍላተ አስማት

የስም ክፍሎችን በተመለከተ የተለያዩ አከፋፈሎች አሉ ለምሳሌ፡--

ውልድ ስም፡-

ሕያው ልሳን
- ---ነባር ስም
- ---የተጸውዖ ስም
- ስመ ተጸውዖ

የቅኔባለሙያዎች
- ስመ ተቀብዖ
- ስመ ተፈጥሮ
- ስመ ግብር

ከሣቴ ብርሃን
- ስመ ተጸውዖ
- ስመ ኀባሬ
- ስመ ምዕላድ
- ስመ ቀኑስ
- ስመ ረቂቅ

መርኆ → ሰወሰው
- ስመ ባሕርይ
- ስመ ተጸውዖ

ከላይ የተጠቀሰው አከፋፈል የተለያየ ቢመስልም ሊተላለፍ የሚፈለገውን የቋንቋውን መልእክት ሁሉም ያስተላልፋሉ ፡እኛም ከዚህ መካከል የተሻለንን/የሚመቸንን መርጠን እንመለከታለን።

## ከሣቴ ብርሃን

### ፩.ስመ ተጸውዖ /proper noun/

ስም ሲሆን አንድን ነገር ከአንድ ነገር አንድን አካል ከአንድ አካል ወይም ሰውና እንስሳን ከወል መጠሪያቸው ለይተን የምንጠራበት ወይም የምንሰይምበት ስም ስመ ተጸውዖ ይባላል።

ምሳሌ፡-አእመረ　　ተ/ማርያም　　ኢየሱስ

ጴጥሮስ　　ጳውሎስ　　ክርስቶስ

መድኃኔዓለም　　ሥነ-ጊዮርጊስ

- ❖ ስመ ተቀብዖ የሚለው አጠራር ከስመ ተጸውዖ ጋር አንድነት አለው።ስመ ተቀብዖ ማለት ፡-
  ----በአርባ በሰማንያ የሚሰየም የክርስትና ስምን
  ----ስመ ግብር-የሹመት ስምን(ጳጳሳት፣ቀሳውስት፣ነገሥታት)
  ----ስመ ተቀብዖ-መጀመሪያ ከወጣው ስም ላይ የሚወጣ ስምን(ስምዖን በሚለው ላይ ጴጥሮስ)
  ----ዘርፍ ከባለቤት የያዙ ስሞችን ሁሉ ይይዛል(መድኃኔዓለም፣ተክለሃይማኖት)
- ❖ ስመ ተጸውዖ በሁሉም የግዕዝ ቋንቋ የቃላት ክፍሎች ሊጠራ ይችላል።
  ምሳሌ፡-አንቀጽ/ግስ/--አእመረ ፣ኮነ፣መሀሪ፣ወዘተ
  ቅጽል--ቅድስት፣ ቅዱስ፣ኂሩት
  ተውሳከ ግስ-ናሁ፣ዮም
  መስተዋድድ-አምሳል /አምሳሉ፣ተከለ/ሌ።በሌሎችም የቃላት ክፍሎችም ባለቤት ከወደደው ሊሰየምበት /ሊሰይምበት ይችላል።

### ፪.ስመ ኀባሬ/common noun/የወል ስም /ስመ መድበል

ስም ነው ነባራትን ወይም አካላትን በአንድነት ያለመለያየት የምንጠራበት እንዲሁም እንስትና ተባዕት፣እጽዋትና አዝርዕት፣እንስሳ ገዳም እና እንስሳ ዘቤት በአንድነት የሚጠሩበት ስያሜ ነው።

ምሳሌ፡-ሰብዕ　　ከልብ　　ነቢይ　　ሕዝብ

እንስሳት　　ሦር　　እብን　　ሐዋርያ

እጽዋት ጠሊ ዶርሆ ሰማዕት
በግዕ ቅዱሳን

ስመ ጉባሬ በውስጡ ስመ ተጸውዖን የያዘ ነው ፡ማለትም ሰብዕ በሚለው ውስጥ ዓለሙ፣አበበች አሉበትና ።
የተፈጥሮ ስም ፣የባሕርይ ስሞች ከስም ጉባሬ ጋር አንድነት አላቸው።

እሳት
ነፋስ
ማይ
መሬት
ሰብዕ
እንስሳ
} ስመ ተፈጥሮም ስመ ባህርይም ናቸው ማለትም ስመ ጉባሬም ናቸው።

አእባን
አእዋፍ
} ስር ዋጽ

## ፫.ስመ ምዕላድ /መድበል/collective noun /ጥቅል ስም

ስም ሲሆን ስመ ጉባሬን በመጠቅለል /በአንድነት የምንጠራበት ስም ነው ማለትም በውስጡ ስመ ጉባሬን ይዟል ማለት ነው።

ምሳሌ፡-መራዕየ አዝጉብት/አናብስት፣አናምርት፣አንህብት፣ተኩላት/
«ንህብ»--ያለው ስመ ጉባሬ ሲሆን «መራዕየ አንህብት» ሲል ምዕላድ ስም ይሆናል።

## ፬.ስመ ቀኑስ /material noun/ የነገር ስም

በቤትም በሌላ ቦታም የሚገኙ ነገሮችን ማለትም በሰው እጅ የተከናወኑ/የተሰሩ ነገሮችን የምንጠራበት ስም ነው።

ምሳሌ፡-ዓራት ደብተራ ቢረሌ መንበር
ዓርዓት ቤት አገዳ ልኅኮት ወዘተ

## ፭.ስመ ረቂቅ/abstract noun/ የረቂቅ ነገሮች ስም

ስም ሲሆን ረቂቅ ነገሮችን ለመሰየም የምንጠቀምበት ስም ነው።
ሁለት ክፍሎች አሉት።

ሀ.ነገራት ዘይትራአይ በዓይን ወዘኢይትአኀዙ በእድ
ጊሜ ጢስ
ብርሃን ፀላም
ትነት መብረቅ

ለ.ነገራት ዘኢይትራአይ በዓይን ወዘኢይትአኀዙ በእድ
ሕልም ጽድቅ ፍቅር
ትፍሥሕት ሀዘን ኃኬት
ተምኔት ኃጢያት በረከት

ስም ላይ የሚታየው ነገር ቢኖር ስመ ምዕላድ ሌሎችን ማለትም ስመ ተጸውዖን እና ስመ ጉባሬን በአንድነት ይይዛል።
ለምሳሌ፡-ጸሊም ላህም

ስም በሌላ አከፋፈል ሊከፈል ይችላል።ይህም፡-
ስም፡ ነባቢ እና ኢነባቢ

ምሳሌ-ስመ ተጸውዖ ፡-«ት»ን በመጨመር ይበዛል።
ነባቢ---ዘ ሰብዕ(አለሙ፣አበበ)
ዘ መልአክ(ሚካኤል፣ገብርኤል)
ዘ እግዚአብሔር(እግዚአብሔር፣አማኑኤል፣ኢየሱስ፣ክርስቶስ፣አዶናይ፣ኤልሻዳይ)
ኢነባቢ---ዘሀገር፣ዘደብር፣ዘፈለግ፣ዘባህር፣ዘአካል

ስመ ጉባሬም፡-

ነባቢ እና ኢነባቢ እንደላይኛው፡፡

- ስሞች/አስማት --ዋናው ተግባራቸው ባለቤትነት
  --የመሳብ ጠባይ አለቸው
  --እንደየጠባያቸው ይበዛሉ።

# ምዕራፍ--፬

## መራኅያን

መርሐ/መራ/ ከሚለው ግስ የተገኘ ሲሆን መሪዎች ፊታውራሪዎች ማለት ነው፡፡ምክንያቱም በወንድ እና በሴት ፣በሩቅና በቅርብ፣በነጠላ እና በብዙ የሚነገረውን እርባታ ስለሚያመለክቱ ግስ መሪ እርባ ዘርዛሪ ስለሆኑ ነው።በቍጥራቸው ዐሥር ናቸው።

- በመደብ ፩ኛ መደብ አነ/I/
  - ንሕነ/we/ | ነባቢ ወኃቤ ትዕዛዝ
  - ፪ኛ መደብ አንተ, አንቲ, አንትሙ, አንትን — You | ተወካፌ ትዕዛዝ ሰማኢ
  - ፫ኛ መደብ ውእቱ/He/, ይእቲ/She/, ውእቶሙ, ውእቶን | They/ | ዘ ኢሀሎ በቅጽበታዊ ሰዓት
- በሩቅ እና በቅርብ
  - ፪ኛ መደብ --ቅርቦች ይባላሉ
  - ፫ኛ መደብ--ሩቆች ይባላሉ
- በነጠላ እና በብዙ

| | |
|---|---|
| ነጠላ---አነ፣ | ብዙ---ንሕነ |
| አንቲ፣ | ---አንትሙ |
| አንተ፣ | ---አንትን |
| ውእቱ፣ | ---ውእቶሙ |
| ይእቲ፣ | ---ውእቶን |

## የመራሕያን አገልግሎት

--ሰብአዊ ተውላጠ ስም/personal pronoun/
--ነባር አንቀጽ/verb to be/
--እማሬአዊ ቅጽል/demonstrative adjective/
--ተስሐቢ/object/
--ፈጽሞተ ርእስ ቅጽል/intensive/
--ንዋያዊ ቅጽል /possessive/
--መስተዋድዳዊ ተሳቢ ምስለ መራሕያን/

## ፩.ሰብአዊ ተውላጠ ስም/personal pronoun/

ስምን ተክተው ይገባሉ፡፡

ምሳሌ፩፡-አነ ቀተልኩ አርዌ ገዳም
ንሕነ ቀተልነ አርዌ ገዳም
ውእቶሙ ቀተሉ ተመነ።

ምሳሌ፪፡---አበበ መጽአ እምብሔረ ኢየሩሳሌም
<u>ውእቱ</u> መጽአ እምብሔረ ኢሩሳሌም
---ማርያም ወማርታ ሰገዳ ለክርስቶስ
<u>ውእቶን</u> ሰገዳ ለክርስቶስ
---ጳውሎስ ወጴጥሮስ መኳንንተ ዓለም አንትሙ
<u>አንትሙ</u> መኳንንተ ዓለም አንትሙ

---አልማዝ ወጥሩሰው መጻእከን እምስያጥ

<u>አንትን</u> መጻእከን እምስያጥ

---ጊሩት ወአነ ንገብር ዘተአዘዝነ

<u>ንህነ</u> ንገብር ዘተአዘዝነ

---ማርያም ወዮሐንስ ቆማ ቅድመ መስቀል

<u>ውእቶን</u> ቆማ ቅድመ መስቀል

---ዮሐንስ ወማርያም ቆሙ ቅድመ መስቀል

<u>ውእቶሙ</u> ቆሙ ቅድመ መስቀል

መራሕያን የስም ምትክ ሲሆኑ ግስ ይከተላቸዋል።

## ፪.እንደ ነባር አንቀጽ /ከዊነ ግስ/ ኵነታዊ አንቀጽ /verb to be/

የአንድን ሁኔታ መሆን ወይም የአንድን ነገር መኖር አንቀጽ ፡

ነባር የተባለበት ኃላፊ፣ትዕንቢት ፣ትዕዛዝ አንቀጽን በእርባታ ፍች ካልሆነ በስተቀር በንባብ ስለማያስረዳ ነው።

ውእቱ --ለ፲ሩም መራሕያን ያገለግላል።

ውእቱ---ነው/is, am, are

---ነባር/was, were

---ይኑር/be, been

(ለነጠላው)

ምሳሌ፦ገበርከ አነ

አነ ወአብ አሐዱ ንሕነ

አንተሰ አንተከመ

አንተሙሰ አእርክትየ አንትሙ

አንቲ መኑ አንቲ

አንትነሰ ጠባባት አንትን

ውእቱሰ መሐሪ ውእቱ

ይእቲሰ ቅድስት ይእቲ

ውእቶን አንስት ዐብዳት እማንቱ

❖ <u>መራሕያን የውእቱ ባለቤቶች /ውእቱ ሲያሥር/</u>

ይእቲ ሰናይት ውእቱ፡፡

አንትሙ ማእምራነ ወንጌል ውእቱ፡፡

አንትሙ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም፡፡

አንተ ውእቱ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር፡፡

ውእቶሙ ውእቱ መራሕያነ ሀገር ወሜ.ክ፡፡

ሰባክያን ውእቱ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ፡፡

## ፫.አመልካች /እማሬአዊ/ ቅጽል/demonstrative adjective/ ይሆናሉ

| <u>ነጠላ</u> | <u>ብዙ</u> |
|---|---|
| ፩ኛ መደብ--<u>አንተ</u> ዝ/ዝንቱ/this/ | ---<u>አንትሙ</u>/እሉ/እሎንቱ/thes |
| -- <u>አንቲ</u> ዛ/ዛቲ /this/ | ---<u>አንትን</u>/እሎን፣እላ፣እላንቱ /thes |
| ፫ኛ መደብ--ውእቱ/ዝኩ/ዝስኩ/ዝክቱ/that/ | ---<u>ውእቶሙ</u> /እልክቱ/እሙንቱ/those |
| --<u>ይእቲ</u> /እንታክቲ/እንትኩ/that/ | ---<u>ውእቶን</u>/እልኩ/እማንቱ/those |

❖ ፩ኛ መደብ አማሪ/አመልካች የለውም ምክንያቱም እራሱ ያመለክታል እንጅ ለራሱ እራሱን አያመለክትም።

ምሳሌ፡---ውእቱ ብእሲ ፈካሬወተርጓሜ መጻሕፍት ውእቱ፡፡
---ዝኩ/ዝከቱ/ዝስኩ/ብዕሲ ፈካሬወተርጓሜ መጻሕት ውእቱ ፡፡
---ይእቲ/እንታክቲ/እንትኩ በለስ አምጽአት ብነ መርገመ በነፍስነ ወበሥጋነ፡፡
---ውእቶሙ/እማንቱ/እልኩ ሐዋርያት ሰበኩ ወንጌለ በትዕዛዘ አምላኮሙ፡፡
---አንተ/ዝ/ዝንቱ ቤ.መቅደስ ተሐንጸ በሥምረተ እግዚአብሔር ፡፡
---አንቲ ማርያም ምክነ ደናግል አንቲ፡፡
---ዛቲ/ዛ ማርያም ምክህ ደናግል አንቲ፡፡
---አንትሙ/እሉ/እሎንቱ መናብርት ተደለው ለሊ.ቃውንተ ሀገር ወቤ.ክ፡፡
---አንትን/እሉ/እለ/እለንቱ አንስት ተገልበባ ርእሶን፡፡
---ውእቶን/እልኩ/እማንቱ ጠባባት አኃዛ ቅብዐ በዓማዐዊሆን፡፡

መራሕያን የባለቤት ቅጽል/አመልካች ሲሆኑ ከስም በፊት ቀድመው ይመጣሉ።ከላይ የተሰመረባቸውን ቃላት ተመልከት፡፡

## ፬.ተሳቢ ተውላጠ ስም ይሆናሉ/Objective pronoun/

መራሕያን እንደ ተሳቢ ሆነው ያገለግላሉ ሲባልም እራሳቸውን ችለውም ተለውጠውም በሌላ መልኩ ተለውጠው ብቻ የሚሣሉ አሉ፡፡እነዚህ የገቢር አጸፋዎች ለተሳቢ ብቻ እንጅ ለባለቤት አያገለግልም፡፡

የገቢር አጻፍ እየተባሉ ይጠራሉ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ውእቱ<br>ይእቲ<br>ውእቶሙ<br>ውእቶን | እንዳሉም ተለውጠውም ይሰባሉ፡፡ | አንቲ<br>አንተ<br>አንትሙ<br>አንትን<br>ንህነ<br>አነ | ተለውጠው ብቻ ይሣባሉ፡፡ |

አነ--ኪ.ያየ/me/ ውእቱ--ኪ.ያሁ/him/

ንህነ--ኪ.ያነ/us/ ይእቲ--ኪ.ያሃ/her/

አንተ--ኪ.ያከ/you/ ውእቶሙ--ኪ.ያሆሙ/them/

አንቲ--ኪ.ያኪ./you/ ውእቶን--ኪ.ያሆን/them/

አንትሙ---ኪ.ያከሙ/you/

አንትን--ኪ.ያከን/you/

ምሳሌ፡---ውእቱ አእመረ(እርሱን አወቀ)

----አልማዝ አእመረት ውእተ/አልማዝ እርሱን አወቀች/

----አልማዝ ወገ/ማርያም አእመሩ ውእተ /አልማዝ እና ገ/ማርያም እርሱን አወቁት

----ውእቱ አእመረ ይእተ/እርሱ እርሷን አወቀ

----አኀውየ ወአኀትየ ተወከፍዋ ወመሀርዋ ይእተ ወለት

/ወንድሞች እና እህቶች ያችን ተቀበሏት አስተማሯትም/

ምሳሌ፪:---ውእቶሙ ጸሩ ውእቶን /እነርሱ እነርሷን ተሸከሟቸወው/

----ኖላዊ አቀበ ኪያሆን ከመ ኢይማስና/ጠባቂ እንዳይጠፉ እነርሱን ጠበቀ/

----አ አኀውየ ኪያዬ ተመሰሉ/ወንድሞች ሆይ እኔን ምሰሉ

## ፫.የተሳቢ ቅጽል ይሆናሉ

ምሳሌ:-ሐረየ ክርስቶስ ኪያክሙ ሐዋርያት

ወረሰ አብርሃም ኪያሃ ሀገረ

እሬኢኑ ኪያሃ ሀገረ

ንሴብሕ ኪያከ ፈጣሬ

ንሥኡ ሐዋርያት ኪያሁ መንፈሰ

ቀተሉ አሕዛብ ኪያሆሙ ሰማዕተ

ሰበከ መልአከ ኪያከን አንስተ

የባለቤት ቅጽል እና የተሳቢ ቅጽል ልዩነታቸው ምንድን ነው?

አማሪ/አመልካች ቅጽል--ባለቤት ቅጽል ነው ተገብሮ ነው፡፡

የተሳቢ ቅጽል--ገቢር ነው

ምሳሌ:--ኪያሁ መርዓዊ ፆቀ፡፡
(ኪያሁ ↓ ቅጽል; መርዓዊ ↓ ተሳቢ)

---ውእቱ መርዓዊ ተአውቀ፡፡
(ውእቱ ↓ ቅጽል; ተአውቀ ↓ ባለቤት)

## ፬.ፈጸሞተ ርእስ/intensive/

አንድ ሰው አንድን ነገር በራሱ ኢጋዥ ሳይፈልግ የሚያከናውበት ሁኔታን የምናውቅበት ነው፡፡የተገብሮ አጸፋ እየተባሉ ይጠራሉ፡፡እነዚህ የተገብሮ አጸፋዎች ለባለቤት እንጅ ለተሳቢነት አያገለግሉም፡፡

አነ---ለልየ/my self/

ንህነ--ለሊነ/our self/

አንተ--ለሊከ/your self/

አንቲ--ለሊኪ/your self/

አንትሙ--ለሊክሙ/your self/

አንትን--ለሊክን/your self/

ውእቱ--ለሊሁ/him self/

ይእቲ--ለሊሃ/her self/

ውእቶሙ--ለሊሆሙ/them self/

ውእቶን--ለሊሆን/them self/

ምሳሌ፡-ለልየ አንበብክዎ ለዛቲ መጽሐፍ በዘአልቦ መምህር ወረዳኢ፡፡

ለሊከ ተአምር በእንተ ዝንቱ ነገር እስመ ኢየአምሮ አነ በቅድም፡፡

ለሊከ ንጸውአከ በጊዜ ፺ቱ ሰዓት እንዘ ያምጽኦሙ ለቈሳቍስ፡፡

ለሊሁ አፍቀራ ለዛቲ ወለት ዘእንበለ ዘአዝማዲሁ አእምሮ፡፡

ወተፈልጠት ለሊሃ እምኔነ በዘ ኢነአምር ምክንያት

ወሖራ መንገለ ትዕይንት ጎንደር ለሊሆን ዘእንበለ መራሒ፡፡

ወአፍቀረቶ ለሊሃ እንዘ ኢየአምር፡፡

የተሳቢ ቅጽል እና ፈጽሞተ ርእስ ቅጽል ልዩነታቸው ምንድር ነው፡፡

ፈጽሞተ ርእስ --ለተገብሮ

ምሳሌ፡-ለሊሁ አምላክ ፈጠሮሙ ለፍጡራኒሁ፡፡

ተሳቢ ቅጽል --ለገቢር

ምሳሌ፡-ኪያሁ አምላክ ይቄድሱ ፍጡራን ፡፡

## ***፰ ንዋያዊ ቅጽል/possessive/ምስለ መራሕያን -- በቂ ቅጽል ይባላል፡፡***

አንድ ሥራ ወይም አንድ አካል የማን እንደ ሆነ የምናውቅበት ነው፡፡

በዚህ ዓለም ያለሰው ነገረ ሁሉ ለራሱ ባለቤት አለው፡፡

አነ--ዚአየ፣ዘዚአየ፣እንቲአየ፣እሊአየ/my, mine/

ንሕነ--ዚአነ፣ዘዚአነ፣እንቲአነ፣እሊአነ/our, ourse

አንተ--ዚአከ፣ዘዚአከ፣እንቲአከ፣እሊአከ/your, yours

አንቲ--ዚአኪ፣ዘዚአኪ፣እንቲአኪ፣እሊአኪ/your, yours

አንትሙ--ዚአክሙ፣ዘዚአክሙ፣እንቲአክሙ፣እሊአክሙ

አንትን--ዚአክን፣ዘዚአክን፣እንቲአክን፣እሊአክን

ውእቱ--ዚአሁ፣ዘዚአሁ፣እንቲአሁ፣እሊአሁ/his, his

ይእቲ--ዚአሃ፣ዘዚአሃ፣እንቲአሃ፣እሊአሃ/her, hers

ውእቶሙ--ዚአሆሙ፣ዘዚአሆሙ፣እንቲአሆሙ፣እሊአሆሙ/thies

ውእቶን--ዚአሆን፣ዘዚአሆን፣እንቲአሆን፣እሊአሆን/their, theirs

ንዋያዊ ተውላጠ ስም--በቂ ባለቤት

--በቂ ቅጽል

--በቂ ተሳቢ

--በቂ አገባብ መውጫ ይሆናሉ፡፡

ምሳሌ፡-ዘዚአየ ሞተ/ወንድሜ ሞተ/

ዚአየ ሞተ /ወንድሜ ሞተ

ዘ---የሞተ ባለቤት — በቂ ባለቤት

ዚአየ---የ«ዘ»ዘርፍ

ዘዚአየ ንዋይ/የኔንብረት የሆነ ንብረት

ዚአየ ንብረት

ዘ---የንዋይ ቅጽል — በቂ ቅጽል

ዚአየ----የ«ዘ»ዘርፍ

ዘዚአየ በላዕኩ/የወንድሜን እንጀራ በላሁ

ዚአየ በላዕኩ/የኔን እንጀራ በላሁ

ዘ---በቂ ተሳቢ — በቂ ተሳቢ

ዚአየ---በቂ ዘርፍ

በላዕኩ በቂ ሳቢ

ዚአየ መጽአ/ከኔ ወንድም ጋር መጣ/

ዘዚአየ መጽአ/ከኔ ወንድም አባት ጋር መጣ

ዘ---በቂ አገባብ የወጣበት — በቂ አገባብ

ዚአየ---በቂ ዘርፍ

መጽአ---ማሠሪያ

ምሳሌ፡-ዘዚአነ ቤት ተሐንጸ በፈቃደ መንግስት፡፡

እሊአሁ አብያት ተመስረቱ በእብን፡፡

እንቲአሃ መሰንቆ ተሰንቀወት፡፡

- ሀለውነ ካልአን ቃላት ወፈደላት ዘይረብዮን ለራስዮተንዋያዊ

----በ ዘ

----በ እንተ

----በ እለ እና ለ

ምሳሌ፡-ማኅደር ዘ ጳውሎስ ለጳውሎስ ማኅደሩ

ማኅደር እንተ ጳውሎስ      ማኅደሩ ለጳውሎስ

ማኅደር እለ ጳውሎስ

ማኅደርየ፣ማኅደሪነ፣ማኅደሪከ፡

መራሒ ሀገር---መራሒ ዘሀገር

ሐናጼ ቤት----ሐናጺ ዘቤት

ደብተራ ኦሪት----ደብተራ ዘኦሪት

ቤተ ምግብ----ቤት ዘምግብ

ዘዚአየ ሀገር ኢትዮጵያ ክብርት ይእቲ መልእልተ ኵሎን ሀገራት፡፡

## ፰.መስተዋድዳዊ ተሳቢ ምስለ መራሕያን

አንድ ነገር ለአንድ ነገር ወይም አንድ አካል ለአንድ አካል የሚገባ መሆኑን ይጠቁመናል።

| | |
|---|---|
| አነ--ሊተ/to me/ | ውእቱ--ሎቱ/to him |
| ንህነ--ለነ/to us/ | ይእቲ--ላቲ/to her/ |
| አንተ--ለከ/to you/ | ውእቶሙ--ሎሙ/to them/ |
| አንቲ--ለኪ/to you/ | ውእቶን--ሎን/to them/ |
| አንትሙ--ለክሙ/to you/ | |
| አንትን--ለክን/to you | |

---ውእቱ ቤት ዘተሐንጽ በወርቅ ወብሩር ሎቱ ለአምላክ፡፡

---ማዕጠንታት ዘወርቅ ዘያጠይሱ እጣነ ሎሙ ለመላእክት፡፡

---ሠረገላ ዘአጥረይዎ አቡየ ወእምየ ውእቱ ሊተ፡፡

## ፱.ምክንያታዊ ተውላጠ ስም

| | | |
|---|---|---|
| አነ--ብየ | አንትሙ--ብክሙ | ውእቶሙ--ቦሙ |
| ንህነ--ብነ | አንትን--ብክኖ | ውእቶን--ቦቶን |
| አንተ--ብከ | ውእቱ--ቦቱ | |
| አንቲ--ብኪ | ይእቲ--ባቲ | |

ከላይ ያሉት የሚያመለክቱት በዚህ ምክንያት እንዲህ ሆነ ለማለት የሚያስችሉ ናቸው።

ምሳሌ፡--ብኪ ወበስመ ወልድኪ ኮነ ሰላም፡፡

በምክንያተ ክርስትና ማሰነ እስልምና እምዓለም፡፡

ብከ ተገብረ ዝንቱ ሙስና በቤተ ክርስትያንነ፡፡

ብነ ትትገፈታ ሀገሪትነ ኢትዮጵያ በጸላዕትነ፡፡

ባቲ መጽአ ሞት ወበባቲ መጽአ ሕይወት

# <u>ምዕራፍ---፳</u>

# <u>ቅጽል/adjective/</u>

በስም ላይ እየተጨመረ የስምን ኩነት፣አካል፣መልከእ፣ቅርጽ፣ቅርበት፣ርቀት፣ዐይነት፣መጠን ወይም ማንነት የሚገልጥ የስምአጕልማሽ ነው፡፡

ቅጽል የተለያዬ አከፋፈል አለው፡-

፩.መርኆ ሰዋስው ፡--ዘር ቅጽል/ግሳዊ ቅጽል/

--ነባር ቅጽል

፪.ሕያው ልሳን፡--ግልጽ ዘ/አመልካች ቅጽል

--ውስጠ ዘ

፫.ከሣቴ ብርሃን፡--ከሣቲ ቅጽል

--ኍልቋዊ ቅጽል

--ንዋያዊ ቅጽል

--አማሪ ቅጽል

--ክፍላዊ ቅጽል

--ጥያቄ አዊ ቅጽል

--አጽንኦታዊ ቅጽል

እኛ ከነዚህ አከፋፈሎች የከሣቴ ብርሃንን ተከትለን እንሔዳለን፡፡

## <u>፩.ከሣቲ ቅጽል/descriptive adjective/</u>

የሰውን፣ የነገርን፣ግብር፣ኩነት፣ሕብር፣ባሕርይ፣ሕጽረትን ወይም ረጅምነትን የሚገልጽ ቅጽል ነው፡፡

ምሳሌ፡-ነዊሐ ልብስ/ሐጺረ ልብስ አጦረይኩ፡፡

መሳጢ ሰብእ ኢይረብህ ፡፡

አንባቢ ዮሐንስ አንበቦ መጽሐፍ፡፡

መዘምር ያሬድ አንበቦ /ዘመረ መዝሙረ

ጸሊም /ጸአዳ ልብስ መጽአ ሊተ፡፡

ሐካይ ገብርኄር ኢያረብሐ ንዋየ እግዚኡ፡፡

ከሣቲ ቅጽል ለራሱ በሁለት ይከፈላል፡፡

ሀ.ግስን በመገሰስ የሚገኙ ቅጽሎች /ውስጠ ዘ ቅጽሎች--፩ኛ አንቀጽ--፪ኛ አንቀጽ--፫ኛ አንቀጽ

ለ.የግሶችን ማሠሪያነት በማፍረስ የሚገኙ ቅጽሎች

## *ሀ. ግስን በማገሰስ የሚገኙ ቅጽሎች*

ውስጠ ዘ ቅጽሎች /ዘር ቅጽሎች ብለን ልንጠራቸው እንችላለን፡፡

ይህ ክፍል በውስጡ፡-

--ሣልስ ቅጽልን --ወገን ቅጽልን

--ሳድስ ቅጽልን --ነድበል ውስጠ ዘ ቅጽልን

--ሳድስ ቅጽለን --ዘር ውስጠ ዘ ቅጽልን

--መስም ቅጽልን

***<u>ሳድስ ውሰጠ ዘ ቅጽል</u>***

--በሳድስ ፊደል ይጨርሳል፡፡
--ከግስ እርባታ ይገኛል፡፡
--ከተደራጊ አንቀጽ ይገኛል፡አልፎ አልፎ  ከኢርቱዕ ግስ እና ከአድራጊ አምድ ይገኛል፡፡
--በአድራጊ /በጿቱ አእማድ ይተረጐማል፡፡

ምሳሌ፡-በጿቱ የግስ አርእስቶች ፡-

--ቀተለ---ቅቱል/የተገደለ
--ቀደሰ---ቅዱስ/የተቀደሰ
--ማህረከ---ምህሩክ/የተማረከ
--ክህለ---ክሁል/የተቻለ
--ሴሰየ---ሲሱይ/የተመገበ
--ጦመረ---ጡሙር/የተጻፈ
--ተንበለ---ትንቡል/የለመነ

ምሳሌ፡-ቅቱል አቤል ኮነ ሰማዕተ፡፡

የግብር ቅጽል
- ጻድቅ ኢዮብ ወረሰ ገነተ፡፡
- ትኩል ዐምድ ይሰውቅ ቤተ ፡፡

} ከሰዋስው ጋር ሳይናበብ ለስም ሲቀጸል

- ቅቱለ ቃኤል አቤል ኮነ ሰማዕተ፡፡
- ጻድቀ ምግባር ኢዮብ ወረሰ ገነተ ፡፡
- ትኩለ ማዕከለ አምድ ይሰውቅ ቤቱ፡፡

} ከሰዋስው ጋር ተናቦ ለስምሲቀጸል

ኲነት ቅጽል
- ሕያው እግዚአብሔር ይመልክ ዓለመ፡፡
- ምውት አላዛር ተንሥአ ፡፡
- ድኁን ኒቆዲሞስ ሰብሐ ፈጣሪሁ፡፡

ሕያው ባሕርይ እግዚአብሔር ይመልክ ዓለመ፡፡
ምውት ሥጋ አላዛር ተንስአ፡፡
ድኁነ ሕይወት ኒቆዲሞስ ሰብሐ ፈጣሪሁ፡፡

ተቀብዖ ቅጽል
- ንጉሥ ዳዊት ዘመረ መዝሙረ፡፡
- ንጉሠ ጿኤል ዳዊት ዘመረ መዝሙረ ፡፡
- ሕሩይ ኤርምያስ ተነበየ ፄዋ፡፡
- ሕሩየ አምላክ ኤርምያስ ተነበየ ፄዋ፡፡

ነዊሕ ሶምሶን ያርእድ ብዙኃነ፡፡
ነዊሐ ቁመት ሶምሶን ያርእድ ብዙኃነ፡፡ } አካላዊ ቅጽል
እውር ጤሜዎስ ርእየ ብርሃነ፡፡
እውር ዓይን ጤሜዎስ ርእየ ብርሃነ፡፡

***ሣልስ ቅጽል***

በሣልስ ፊደል ይጨርሳል፡፡
ከግስ ርባታ ይገኛል፡፡
ከ፫ቱ አእማድ ይገኛል፡
ከአድራጊነት ይተረጐማል፡፡

አድራጊ አምድ ርቱዕ/ተሻጋሪ ግስ/ግስ እና ኢርቱዕ ግስ በእርባታ ይገኛል፡፡

በ፺ቱ የግስ አርእስቶች እንመለከት

---ቀተለ-ቀታሊ ---ባረከ-ባራኪ ---ጦመረ-ጠማሪ
---ቀደሰ-ቀዳሲ ---ሴሰየ-ሴሳዪ ---ማህረከ-ማህራኪ
---ተንበለ-ተንባሊ ---ክህለ-ከሀሊ

ሣልስ ውስጠ ዘ ቅጽል ---የግብር
---የኩነት
---የተቀብዖ ተብለው ይከፈላል፡፡

ምሳሌ፡---ዜናዊ ገብርኤል ዜነወ ብሥራተ/ሳይናበብ ሰወስውንም ሳይስብ/
ዜናዊ ጥበብ ገብርኤል ዜነወ ብስራተ /ሳይናበብ ሰዋስውን እየሳበ /
ዜናዌ ጥበብ ገብርኤል ዜነወ ብስራተ/ተናቦ ሰዋስውን እየሳበ/ ዘርፍ አያያዥ ሲቀጸል /
----ቀናኢ ጳውሎስ ጸሐፈ መልእክተ
ቀናኢ ክርስቶስ ጳውሎስ ጸሐፊ መልእክተ
ቀናኤ ክርስቶስ ጳውሎስ ጸሐፈ መልእክተ
----ሠያሚ እግዚአብሔር ሤመ ነገሥተ
ሠያሜ ነገሥተ እግዚአብሔር ሤመ ነገሥተ
ሠያሜ ነገሥት እግዚአብሔር ሤመ ነገሥተ

***መስም ውስጠ ዘ ቅጽል /መስሕብ ቅጽል/***

--- በሳድስ ይጨርሳል
--- ከግስ እርባታ ይወጣል
---ባዕድ ፊደል «መ»ን በመነሻ ይጨምራል፡፡
---በአድራጊነት ይነገራል ግን መወሰን የለበትም

በ ፺ቱ የግስ አርእስቶች እንመልከት

ቀተለ--መቅትል
ቀደሰ--መቀድስ
ተንበለ--መተንብል
ጦመረ--መጠምር
ማህረከ--መማህርክ
ባረከ--መባርክ
ሴሰየ--መሴሲ /መሴስይ
ክህለ--መክህል

ምሳሌ፡--- መፈክር ዳንኤል ፈከረ ሕልመ
መፈክር ሕልመ ዳንኤል ፈከረ ሕልመ
መፈክረ ሕልም ዳንኤል ፈከረ ሕልመ
---ዮሴፍ ማዕምር ለበወ ጥበበ/ሰይናበብ ለስም ሲቀጸል/
ዮሴፍ ማዕምር ጥበብ ለበወ ጥበበ/ሳይናበብ ሰዋስውን እያሰበ ሲቀጸል/

የሴፍ ማዕምረ ጥበብ ለበወ ጥበበ /ተናቦ ሰዋስውንም እያሰበ ለስም ሲቀጸል/

***ወገናዊ ውስጠዘ ቅጽል***

---ምዕላድ ፊደላት «ዊ» «ይ» ን በመድረሻ ጨምሮ ስመ ባህርይ እና ስመ ተጸውዖን ወደ ቅጽልነት /ስምን ወደ ቅጽልነት/እየለወጠ የሚቀጸል ቅጽል ነው፡፡

---የማን ወገን እንደሆነ ያመለክታል፡፡

---ከሰዋስው ጋር ተናቦም ሳይናበብም ይቀጸላል፡፡ተናቦ አይቀጸልም የሚሉም አሉ፡፡

ምሳሌ፡-ላዕላዊ/ይ

ቀዳማዊ/ይ

አረጋዊ/ይ

ላዕላዊ/ይ ሰማይ ይርህቅ እምድር

ላዕላዌ/የ ኩሉ ሰማይ ይርህቅ እምድር

ቀዳማዊ/ይ አዳም አምጽአ ሞተ

ቀዳመዌ/የ ፍጥረት አዳም አምጽአ ሞተ

አረጋዊ አብርሃም ተወከፈ ብሥራተ

አረጋዌ እድሜ አብርሃም ተወከፈ ብሥራተ

***ዘር ውስጠ ዘ ቅጽል***

ዘርፍ እየያዘ /ከቃላት ጋር እየተናበበ /ለስም ይቀጸላል፡፡

ከግስ እርባታ ይገኛል ፡፡

በግሱ ያልነበረ ባዕድ ፊደል ይጨምራል በዚህም ዘመድ ዘር፣ባዕድ ዘር፣ምዕላድ ዘር ፣ባዕድ ከምዕላድ ዘር ሊባል ይችላል፡፡

ምሳሌ፡---ድንግል
--- አዳም
---የሰው ስም
---ምዕላድ
} እነዚህ ሁሉ ዘር ውስጠ ዘ ናቸው፡፡

---ብርሃን
---ክብር
---አክሊል
} ዘር ናቸው፡ቀጥታ ባለቤት መሆን ይችላሉ፡፡

ምሳሌ፡-ድንግል ማርያም ኮነት ምክዐ ደናግል፡፡ ሳይናበብ

ድንግለ ደናግል ማርያሞ ኮነት ምክሆሙ ለደናግል ፡፡ ተናቦ

ምሳሌ፡-ክብረ ቅዱሳን ክርስቶስ ገብረ ሰላመ
/የቅዱሳን ክብር አምላክ /ክርስቶስ ሰላምን አደረገ/፡፡
ምክሀ ደናግል ማርያም ወለደት አምላከ፡፡
} ዘመድ ዘር

አክሊለ ሰማዕት ወልድ ተሰቅለ፡
ሙላደ ክርስቶስ ቤተልሔም ኢትቴሐት፡
} ባዕድ ዘር

ምዕላድ ዘር {
ብርሃነ ዓለም ክርስቶስ አሥተርአ፡
(የዓለም ብርሃን ክርስቶስ ታዬ)
ምልክና ፈጣሪ ዓለም ያአውቅ ፈጣሪሁ ፡
(የፈጣሪ ግዛት ዓለም ፈጣሪውን ያሳውቃል)

ባዕድ ከ ምዕላድ {
ትሕርምተ መልአክ አውሰቦ ተውህቦ ለሰብ።
(የመልአክ እርም የሆነ ጋብቻ ለሰው ተሰጠ)
መስፈርተ እክል አስፈሬዳ ኢኮነ ንኡስ፡፡
(የእህል መስፈሪያ እንቅብ ትንሽ አልነበረም)

ፍቅረ -ቢጽ
ጽድቀ-አብርሃም
} እየአለ ዘርፍ ካልያዘ /ከቃላት ጋር ካልተናበበ/ ቅጽል ከመሆን ይልቅ በቂ ውስጠዘ ሆኖ

ምክረ-ጠቢባን        የአንቀጽ ባለቤት መሆን ያመዝነዋል፡፡

ምሳሌ፡---ፍቅር-ያስተማሕር -ፍቅር ያስተዛዝናል
---ወጽድቅኒ ታግዕዘከሙ -እውነትም ነጻ ታደርጋችኋለች
---ምክር ሠናይት ዘይገብራ -ለሚሰራት ምክር በጎ ናት

***<u>መድበል ውሰጠ ዘ ቅጽል</u>***

ተባዕታይ እና አንስታይ ጾታን ለማይለይ እስትጉብዕ/ስብስብ/ ስም ተባዕታይና አንስታይ ጾታን ሳይለይ የሚገልጽ ቅጽል መድብል ውስጠ ዘ ቅጽል ይባላል፡፡

ምሳሌ፡-ዐበይት    ማህረከት
ቀደምት    ሴስይት
ደሐርት    በረከት
ቀተልት    ከሐልት
ቀደስት    ጠመዐት

ምሳሌ፡--<u>ዐበይት</u> ሕዝብ ሥርዐ ሕገ፡፡
<u>ዐበይተ</u> ሀገር ሕዝብ ሥርዐ ሕገ፡፡
<u>ቀተልት</u> ሕዝብ ሠዐሩ ሕግ፡፡
<u>ቀደስት</u> ካህናት ቀደሱ ቅዳሴ፡፡
<u>ቀደስተ</u> እግዚአብሔር ካህናት ቀደሱ ቅዳሴ፡፡

ከላይ በምሳሌ እንደተመለከትነው ከሰዋስው ጋር ተናቦም ሳይናበብም ይቀጸላል፡፡

***<u>መተርጉም ቅጽል</u>***

ነባር ውስጠ ዘ ቅጽል ነው /ከግስ ግሰሳ አይገኝም/
ሁለት ስሞች በቅደም ተከተል ተደርድረው ሳይናበቡ የምናገኘው  የቅጽል ዓይነት ነው፡፡
ቅጽል ያሰኘው በአፈታቱ «የ» የሚል ሆሄ ስለ ሚያመጣ ነው

ምሳሌ፡-<u>ያዕቆብ እስራኤል</u> ወለደ ደቂቀ/<u>፲</u>ኤል <u>የ</u>ተባለ ያዕቆብ/
<u>አብራም አብርሃም</u> ሦዐ ይስሐቅሀ(አብርሃም <u>የ</u>ተባለ አብራም )
<u>ስምዖን ጴጥሮስ</u> ተስቅለ ቍልቍሊተ (ጴጥሮስ <u>የ</u>ተባለ ስምዖን)
<u>ነቢይ ሙሴ</u> መሀረ አርተ(ሙሴ <u>የ</u>ተባለ ነቢይ)
<u>ሐዋርያ ዮሐንስ</u> ሰበከ ወንጌለ(ዮሐንስ <u>የ</u>ተባለ ሐዋርያ )

ነባር ውስጠዘ ቅጽሎች ከስም ጋር ተናበው ይቀጸላሉ፡፡
<u>አድያመ ዮርዳኖስ</u> ገሊላ አስተጋብአት ነቢያተ
<u>ሀገረ አብርሃም</u> ከነአን ታውሕዝ ሐሊበ
<u>እግረ ደብር</u> ቢታንያ አውጽአት ሰርጸ (ቡቃያ)

የተሰመረባቸው መተርጉም ቅጽሎች ናቸው፡፡

## ሊ የግሶችን ማሠሪያነት እያፈረሱ የሚገኙ ቅጽሎች

ማሰሪያ አንቀጾችን የምናፈርስባቸው አገባቦች አሉ፡፡
ዘ--ለአንድም ለብዙም
እለ--ለብዙ ብቻ
እንተ--ለአንድ ብቻ ይቀጸላሉ ፡፡

በአንቀጽ/በግስ ላይ ወድቆ ማሠሪያ አንቀጽን እያስቀረ ለስም የሚቀጸል ቅጽል ግልጽ ዘ ቅጽል ይባላል፡፡
ከዚህ በላይ ያዩናቸው ቅጽሎች ከግስ የሚወጡ ስለ አልሆኑ ነባር ቅጽሎች እንላቸዋለን፡፡

ምሳሌ፡---ሰብ ዘአበሰ /እንተ አበሰ ይትኴነን
---አዳም ዘሰሐተ /እንተ ስሕተ ሰአለ ምሕረተ፡፡
---ሰዶም ዘተመዝበረት/እንተ ተመዝበረት ኮነት በድወ፡፡
---እንስሳት ዘተጋብኡ/እለ ተጋብኡ ጥሕሩ

---ሚካኤልወገብርኤል ዘኢይነውሙ /እለ ኢይነውሙ ይስእሉ ምሕረተ

---ሰሎሜ ወማርያም ዘጌሳ/እለጌሳ ረከባ መልአኮ

--- ማያት ዘርእዩከ/እለተዘርኡ ተጋብኡ(እለ የአባግዕ ግልጽ ዘ ቅጽል)

---ቅንው ወልድ ዘተሰቅለ ኮነ መድኅነ/የተሰቀለ የተቸነከረ ወልድ አዳኝ ኾነ)

❖ <u>ሦስቱንም ቅጽሎች</u> (ዘ፣እንተ፣እለ) እየደራረቡ (በዐ.ነገር) መጠቀም ይቻላል።

---እንተ እንተ አሕመልመለት በለስ በልዐ አዳም ተኮነነ።

እንተ አሕመልመለት በለስ እንተ በልዐ አዳም ተኮነነ።

(የለመለሙች እፀ በለስን የበላ አዳም ተኮነነ፡፡)

---እንተ ዘ አሕመልመለት በለስ በልዐ አዳም ወጽአ እምገነት፡፡

እንተ/ዘ አሕመልመለት በለስ እንተ/ዘ በልዐ አዳም ወጽአ እምገነት

---እንተ እለ አሕመልመሉ አእጹቀ በልዐ አዳም ተኮነነ፡፡

እለ አሕመልመሉ አእጹቀ እንተ በልዐ አዳም ተኮነነ፡፡

(የለመለሙ ቅርንጫፎችን የበላ አዳም ተኮነነ /ከገነት ወጣ)

---እንተ ዘ እለ አሕመልመሉ አዕጹቀ በልዐ አዳምሀ ፈጠረ እግዚአብሔር ተሰብሐ፡፡

ዘ/እለ አሕመልመሉ አእጹቀ ዘ/እንተ በልዐ አዳምሀ እንተ /ዘ ፈጠረ እግዚአብሔር ተሰብሐ።

የለመለሙ ቅርንጫፎችን የበላ አዳምን የፈጠረ እግዚአብሔር ተመሰገነ)

በሚከተለው መልኩ መጠቀም ይቻላል፡፡

| | |
|---|---|
| እንተ፡እንተ | እለ፡እንተ |
| እንተ፡እንተ፣ዘ | እለ፡እንተ፣ዘ |
| እንተ፡እለ | እለ፡እንተ፣እለ |
| እንተ፡ዘ | እለ፡ዘ፣እንተ፣ዘ |
| እንተ፡እለ፣ዘ | ዘ፡ዘ፣ዘ፣እንተ፣ዘ |
| ዘ፡እለ፣ዘ | እለ፡ዘ፣እንተ፣እለ፣ዘ፣እለ |
| እንተ፡ዘ፣እለ | |

## <u>፪.ኍልቋዊ ቅጽል/adjective quantity/</u>

ሁል ጊዜ ስሞችን፣ነገሮችን በቍጥር መልክ መግለጽ ኍልቋዊ ቅጽል ይባላል፡፡

ሦስት ክፍሎች አሉት፡-

ሀ.ኍልቋዊ ቅጽል ዘ ተባዕታይ ጾታ

ለ.ኍልቋዊ ቅጽል ዘ አንስታይ

ሐ.ኍልቋዊ ቅጽል ዘ ዕለት ናቸው፡፡

### *ሀ.ኍልቋዊ ቅጽል ዘ ተባዕታይ*

ሦስት ክፍሎች አሉት፡-

፩.ደሞላዊ ኍልቋዊ ቅጽል

፪.ኆላቊ ኍልቋዊ ቅጽል

፫.መዓርጋዊ ኍልቋዊ ቅጽል

***<u>፩.ደሞላዊ ኍልቋዊ ቅጽል/nominal number/</u>***

መድበል አኀዝ ቅጽል ይባላል/ልዩነት ሳይኖረው ጠቅልሎ)

ደሞላዊ ማለት ጀምሎ ፣ጠቅልሎ እንደ ማለት ነው፡፡

----ብዙኃ/ለሴት ለወንድ

----ውሑድ/ለሴ፡ለወ

----ኵሉ ኵሎሙ /ኵሎን

----ሕፍን-ኵልነ/ኵልክሙ/ክን

----ሙብዝኅቱ ሙብዝኀቶሙ/ተነ/ቶን/ክሙ/ክን

ሕቅ---ለወንድም ለሴትም
ንስቲት---ለሴት
ንዑስ----ለወንድ
ንዕስት---ለሴት

ምሳሌ፡-ብዙሕ ሕዝብ ተጋብአ ኵሎሙ አግብርት ተቀነዩ ለእግዚአሙ
ብዙሐን ኖሎት መጽኡ ንዑስ ወልድ ይጠቡ ሐሊበ እሙ
ኵሉ ብርከ ይሰግድ ለስሙ
ኵሎሙ ሕዝብ ይሴብሑ ኪያሁ
ሕዳጥ ዓሣ አጽገበ ብዙኀነ ንዕስት ወለት ትጠቡ ሐሊበ እማ
ንስቲት ልሳን ታውዒ ሰብአ

***፪.ኖላቍ ኍልቋዊ ቅጽል/cardinal number/***

ዝርዝር አኀዝ ቅጽል ተብሎ ይጠራል፡፡
በ«ወ» ተጫፍረውም ሳይጫፈሩም ይቀጸላሉ
ጉልት አኀዝ ተብለውም ይጠራሉ/የማይቀየሩ ቁጥሮች

ምሳሌ፡--

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ፩ | አሐዱ | 1 | ፷ | ስድሳ | 60 |
| ፪ | ክልኤቱ | 2 | ፸ | ሰብዓ | 70 |
| ፫ | ሠለስቱ | 3 | ፹ | ሰማንያ | 80 |
| ፬ | ዐርባዕቱ | 4 | ፺ | ተስዓ | 90 |
| ፭ | ኃምስቱ | 5 | ፻ | አሐዱ ምዕት | 100 |
| ፮ | ስድስቱ | 6 | ፪፻ | ክልኤተ ምዕት | 200 |
| ፯ | ሰባቱ | 7 | ፫፻ | ሠለስቱ ምዕት | 300 |
| ፰ | ስምንቱ | 8 | ፬፻ | ዐርባዕቱ ምዕት | 400 |
| ፱ | ተሳቱ | 9 | ፭፻ | ኃምስቱ ምዕት | 500 |
| ፲ | ዐሥርቱ | 10 | ፮፻ | ስድስቱ ምዕት | 600 |
| ፲፩ | ዐሠርቱ ወአሐዱ | 11 | ፯፻ | ሰባቱ ምዕት | 700 |
| ፲፪ | ዐሠርቱ ወክልኤቱ | 12 | ፰፻ | ስመንቱ ምዕት | 800 |
| ፲፫ | ዐሠርቱ ወሠለስቱ | 13 | ፱፻ | ተሳቱ ምዕት | 900 |
| ፲፬ | ዐሠርቱ ወዐርባዕቱ | 14 | ፲፻ | ዐሠርቱ ምዕት | 1000 |
| ፲፭ | ዐሠርቱ ወኃምስቱ | 15 | ፳፻ | እሥራ ምዕት | 2000 |
| ፲፮ | ዐሠርቱወስድሰቱ | 16 | ፴፻ | ሠላሳ ምዕት | 3000 |
| ፲፯ | ዐሠርቱወሰባቱ | 17 | ፵፻ | ዐርብዐ ምዕት | 4000 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ፲፰ | ዐሥርቱወስምንቱ | 18 | ፶፻ | ሃምሳ ምዕት | 5000 |
| ፲፱ | ዐሥርቱወተሳቱ | 19 | ፷፻ | ስድሳ ምዕት | 6000 |
| ፳ | እስራ | 20 | ፸፻ | ሰባቱ ምዕት | 7000 |
| ፴ | ሠላሳ | 30 | ፹፻ | ስምንቱ ምዕት | 8000 |
| ፵ | ዐርብዐ | 40 | ፺፻ | ተሳዐ ምዕት | 9000 |
| ፶ | ሃምሳ | 50 | ፻፻ | እልፍ | 10000 |
| ፪፻፻ | ክልኤቱ እልፍ | 20000 | ፫፻፻ | ሠለስቱ እልፍ | 30000 |
| ፬፻፻ | ዐርባዕቱ እልፍ | 40000 | ፭፻፻ | ኃምሰሰቱ እልፍ | 50000 |
| ፮፻፻ | ስድስቱ እልፍ | 60000 | ፯፻፻ | ሰባቱ እልፍ | 70000 |
| ፰፻፻ | ስምንቱ እልፍ | 80000 | ፱፻፻ | ተሳቱ ዕልፍ | 90000 |
| ፲፻፻ | አእላፍ 10ቱ እልፍ | 100000 | ፳፻፻ | እሥራ እልፍ | 200000 |
| ፴፻፻ | ሠላሳ እልፍ | 300000 | ፵፻፻ | ዐርብዐ እልፍ | 400000 |
| ፶፻፻ | ሃምሳ እልፍ | 500000 | ፷፻፻ | ስሳ እልፍ | 600000 |
| ፸፻፻ | ሰብአ እልፍ | 700000 | ፹፻፻ | ሰማንያ እልፍ | 800000 |
| ፺፻፻ | ተስዓ እልፍ | 900000 | ፻፻ | አእላፍት/ምዕትእልፍ | 1000000 |
| ፲፻፻፻ | አእላፍ አእላፍት | 1000000 | ፻፻፻ | ትእልፊት | 100000000 |
| ፪፻፻፻ | ክልኤቱ ትእልፊት | 200000000 | ፫፻፻፻ | ሠለስቱ ትዕልፊት | 300000000 |
| ፬፻፻፻ | ዐርባዕቱ ትእልፊት | 400000000 | ፭፻፻፻ | ኃምስቱ ትዕልፊት | 500000000 |

ምሳሌ፡-፩ እውር ጸርሐ ኀበ እግዚአብሔር

፲ወ፪ ሐዋርያት ሰበኩ ወንጌለ

፴ወ፮ቱ ቅዱሳት ተለዎ ለክርስቶስ

፸ወ፪ቱ አርድዕት ተፈነው ምስለ ሐዋርያት

በዚህ ቅጽል በመሠረታዊ የሒሳብ ስሌቶች ሒሳብ መሠረት ይቻላል፡፡

የዚህ ቊጥር /ቅጽል ከእልፍ በኋላ ያለው የተለያዬ አሰያየም በየመጻሕፍቱ ስለሚኖር በጥንቃቄ ተመለከት፡፡

***<u>፫.መዓርጋዊ ቅጽል/ordinal number/</u>***

ወገን አኀዝ ይባላል።

ሁልጊዜም የሚያሳየው መዓርግን /ደረጃን ነው፡፡

ምሳሌ፡--ቀዳማይ/ዊ---፩ይ/ዊ    ሣልሳይ/ዊ--፫ይ/

ካልአይ/ዊ--፪ይ/ዊ    ራብዓይ/ዊ----፬ይ

ኃምሳይ/ዊ----፶ᵉ
ሳድሳይ/ዊ----፷ᵉ
ሳብዓይ/ዊ----፸ᵉ
ሰምናይ/ዊ----፹ᵉ
ተስዓይ/ዊ----፺ᵉ
ዐሥራይ/ዊ----፻ᵉ
ዐሥርቱ ወቀዳማይ----፻ወ፩ᵉ

እስራአዊ/ይ----፳ᵉ
እስራ ወቀዳማይ/ዊ----፳ወ፩ᵉ
እስራ ወተስዓዊ/ይ----፳ወ፱ᵉ
ሠላስያዊ----፴ᵉ
ሠላሳ ወኃምሳዊ/ይ----፴ወ፭ᵉ
ዓርብአወሳድሳዊ/ይ----፵ወ፮ᵉ

ሃምሳዊ-----፶ᵉ
ምሳሌ፡---ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ቀንየ ብዙኃ
ስሳአዊ-----፷ᵉ ----ካልአዊ መጽሐፍ ሀለወኒ በእንተ ሥነ-ፍጥረት
ሰብአዊ-----፸ᵉ ----ሣልሳየ ወጽአ በትምህርቱ
ሰማንያዊ----፹ᵉ ----ቀዳማዊ ኃልቀ ወደኃራዊ ተጠምቀ፡፡
ተስዓዊ-----፺ᵉ
ምዕታዊ/ይ -----፻ᵉ

፩ አሐዱ ብሎ አንድ ፣አንደኛ ይላል እንዲህ እያለ እንዲህ እያለ እስከመጨረሻው መሄድ ይችላል።

<u>ፍጹም ውስጠ ዘ ን ብንመለከት</u>

ውኁድ/እሑድ ሰቡዕ/ሰብዕ
ሥሉስ/ሳልስ ስሙን/ስምን
ርቡዕ/ራብዕ ትሱዕ/ታስዕ
ኀሙስ/ኀምስ ዕሡር/ዐሥር
ሰዱስ/ሳድስ

ውስጠ ዘ ስለተባለ ሁለጊዜም «የ»ን ይዞ ይፈታል ማለት አይቻልም፡፡
ምሳሌ፡--<u>በኀምስ</u> ኀብስት አጽገበ ብዙኀነ
--<u>በሳብዕ</u> ብሩር ተሰይጠ ዝንቱ ወይን
የተሰመረባቸው ቃላት ቅጽሎች ናቸው፡፡

## ሊ ጉልቋዊ ቅጽል ዘ አንስታይ ጾታ

ከሴት ጾታ በፊት እየገባ ቅጽልነቱን ያሣያል
ሦስት ክፍል አለው፡--

### *<u>፩.ደምላዊ ቅጽል ዘአንስት</u>*

ምሳሌ፡-ብዙኃት አንስት ሖራ ኀበ ቤ.ክ
ውሒዳት አንስት ደናግል መጽአ እምነ ገዳመ ዋልድባ
ኵሎን አንስት በዜ.ክ የሐውራ በሕገ ቤ.ክ
ሕቅ ደናግል ተደለዋ ለሥርዓተ ተክሊል
ንስቲት ልሳን ታውኢ ሰብአ
ሕዳጥ ዓሣ ዐጽገበት ብዙኀነ
ንእስት ወለት ትጠቡ ኀሊበ እማ

### *<u>፪.ኖለቍ ቅጽል ዘ አንሰታይ ጾታ</u>*

| | |
|---|---|
| አሐቲ | ዐሥሩ ወአሐቲ |
| ክልኤቲ | ዐሥሩ ወክሌቲ |
| ሠላስ | ዐሥሩ ወሠላስ |

አርብዕ　　　　　ዐሥሩ ወዐርባዕ
ኃምስ　　　　　ዐሥሩ ወኃምስ

ምሳሌ፡-ሰብኡ አንስት በከያ ዮም በምክንያት ፵ተ አሐዱ ህፃን፡፡
ዐሥሩ ወክሌቱ አልሕምት ተቀንያ ለበያለ መስቀል
ዕሥራ ወአሐቲ አባግዕ ሞታ በበሊአ ተኵላ፡፡

እንደ ወንዱ ኆለቊ ቅጽል እስከ እልፍ ይዘልቃል፡፡ከ፳ ጀምሮ ለሴትም ለወንድም አንድ አይነት ነው።

### *፫.መዓርጋዊ ቅጽል ዘአንስታይ ጾታ*

ከመዓርጋዊ ቅጽል ዘተባዕታይ የሚለየው «ት» የሚባል ምዕላድ ስለ ተጨመረ ነው፡፡

ምሳሌ፡-ቀዳማዊት/ይት -፩ ^ይት^
ካልአዊት/ይት-፪ ^ይት^

ምሳሌ፡-ቀዳማይት ብእሲት መጸአት /በጽሐት በጊዜ ፩ ሰዓት፡፡
ካልዓይት ብእሲት ሖረት መንገለ ቤተ ትምህርት
ዐሥራይት/ዊት ዐለትዘወርኃ መጋቢት መዓለ መስቀል ይእቲ፡፡

ኆለቊ ቅጽል ዘተባዕታይ እንደ መዓርጋዊ ቅጽል እንደ ኆለቊ ቅጽልም እንደ አገለገለው ሁሉ ኆለቊ ቅጽልም ዘ አንስታይም እንደ ኆለቊም እንደ መዓርጋዊም ያገለግላል።

| | | |
|---|---|---|
| ምሳሌ፡-አሐቲ | አንዲቱ | አንደኛይቱ |
| ሠላስ | ሦስቲቱ | ሦስተኛይቱ |

አሐቲ ብእሲት መጽአት /አንዲት ሴት/አንደኛይቱ ሴት/መጣች፡፡
ክልኤቲ አንስት ተመይጣ/ተመየጠት /ሁለት ሴቶች/ሁለተኛይቱ ሴት ተመለሰች፡፡

የሴት ፍጹም ውስጠ ዘ የሚባለው
ውኀድ/ዋሕድ/እሕድ/አሐድ--አንድ አንደኛ
ክልዕት/ካልዕት--ሁለት　ሁለተኛ
ሥልስት/ሣልስት
ርብዕት/ራብዕት
ስምንት/ሳምንት
ትስዕት/ታስዕት
ዕሥርት/ዓሥርት

ምሳሌ፡---ዋሕድ ማርያም ወላዲተ ኮነት ለአምላክ
---ክልዕት ብዕሲት ወለደት እጓለማውታ

## *ሐ.ኍልቋዊ ቅጽል ዘዕለት*

ከዕለታት በፊት እየተገኘ ቅጽልነቱን ያሳያል፡፡
ሦስት ክፍላት አለው፡፡

### *፩.ደምላዊ ቅጽል ዘዕለት*

የተባዕታይ/የአንስታይ ጾታን አንዱን መጠቀም ይቻላል፡፡

ምሳሌ፡- ብዙኃን/ት ዕለታት ዘወርኀ መስከረም ውእቶሙ ውእቶን፡፡
ውኍዳን/ት መዓልታት ዘወርኀ ጥር ውእቶሙ ውእቶን ፡፡ኵሎሙ (ሎን አውራኀ ምሉኣን /ት ውእቶሙ/ውእቶን፡፡

### *፪.ኆለቊ ቅጽል ዘዕለታት*

| | | | |
|---|---|---|---|
| አሚር | አንድ | አንደኛ | ምሳሌ፡- |
| ሰኑይ | ሁለት | ሁለተኛ | -- ዓመ አሚሩ/፩/ ለመስከረም |
| ሠሉስ | ሦስት | ሦስተኛ | -- ዓመ ፴ሁ ለግንቦት |
| ረቡዕ | አራት | አራተኛ | -- ዓመ ዕሥራ ወአሚሩ /፲፩/ ተዝካረ በዓለ |
| ሐሙስ | አምስት | አምስተኛ | ለማርያም እመ አምላክ፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሰዱስ | ስድሰት | ስድስተኛ | ---ዓመ ስሙኑ/፷/ለሐምሌ ተዝካረ በዓሉ |
| ሰብዕ | ሰባት | ሰባተኛ | ለአቡነ ኪሮስ |
| ሰሙን | ስምንት | ስመንተኛ | ---ዓመ ተሥዐ ለኀዳር ጉባኤ ኤጺስ ቆጶሳት |
| ተሡዕ | ዘጠኝ | ዘጠኛ | ዘ፫፻ወ፳ ርቱዐነ ሃይማኖት |
| ዐሡር | አስር | አስረኛ | |

***፫.መዓርጋዊ ቅጽል ዘዕለታት***

መዓርጋዊ ዘተባዕት /ዘአንስት ከሁለቱ አንዱን መጠቀም ይቻላል፡፡

ቀዳማዊት/ዊ መዓልት በጽሐት/በጽሐ

ኃምሳይ/ይተ ወርኅ ኮነ/ኮነት ዮም፡፡

ኆለቍ ቅጽል ዘተባዕት ፣ዘአንስት ፣ዘዕልት፣አንድ አይነት ምሳል አላቸው፡፡

ምሳሌ፡--አሐዱ, አሐቲ, አሚር -- ፩ ; ክልኤቱ, ክልኤቲ, ሰኒይ -- ፪

## ፫.ንዋያዊ ቅጽል/possessive adjective/

## ፬.አማሪ/አመልካች ቅጸል/demonstrative adjective/--ደቂቅ ቅጽል ነው፡፡

ከዚህ በላይ ሁለቱ ቅጽሎችን /፫ እና ፬/ከመራሕያን ጋር ተመለከት፡፡

## ፭.ከፍላዊ ቅጽል

በክፍፍል መልኩ ስሞችን የሚገልጽ ቅጽል ነው፡በየክፍል በየከፍሉ ስሞችን የሚገልጽ ነው፡፡ወኢኮነ እምድሩ/አካቶ ፈጽሞ አይደለም /

ለእለ አሐዱ---each

አሐዲሆሙ---either

በበ አሐዱ----individual

ብዙኃን-----some of them

ኵሎሙ----all of them

አልቦ እምውስቴቶሙ----none of them

አሐዲሆሙ----each of them

አልቦ አሐዲሆሙ----niether of them

ክልኤሆሙ----two of them

ሠለስቲሆሙ-----three of them

ምሳሌ፡-ለእለ አሐዱ መጽሐፍ አንብቦሙ

አሐዲሆሙ ማኅደራት ተወጥኑ ዮም

አልቦ አሐዲሆሙ ማኅደራት ዘተወጥኑ

የም ተዘግበ በበ አሐዱ  ማኅደር

## ፮.ጥያቄአዊ ቅጽል /ንኡስ ቅጽል/introgative adjective

ንኡስ ቅጽል የተባለበት ምክንያት መጠይቃዊ ንኡስ አገባቦችን ስለሚይዝ ነው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| አይ | ምክንያት | እፎኑ |
| መኑ | ማዕዜ | እፎሁ |
| አይቴ | እስፍንቱ | ስፍን |

[WH] ጥያቄዎችም እዚኹው አሉበት

መኑ፡እለመኑ፡------who/which

ለምንት/አያት/አይ-----what

በይነ ምንት -------why

አይቴ-------where

ማዕዜ-ማዕዜያት-----when

ዘመኑ-----whose

መኑ እለመኑ-----whome

እስፍንት ጊዜ-----how aften

እፎሁ/ኑ------how

እስፍንቱ/ስፍን------how mony /how much

እስፍንተ ማዋዕል------how long

እስከ እይ መካን-----how far

መኑ ብእሲ ተሰይመ ኤጲስቆጶስ ዘተምህረ መጻሕፍተ----who be come epskopose

መኑ ቀኑስ ማሰነ ትማለም ትማለም ዘተሰይጠ/ዘአጥረይዎ/----which thing loses yesterday

አይኑ መጽሐፍ ዘተጽሕፈ በእደ ሙሴ ዘኦሪት----what book is written by muse?

እስፍንቱ መዋዕል ኮነ ህንጸተ ዝንቱ ቤ.መ----how long has been this building of church

እስኩ አይ መካን ተለውዎሙ ፳ኤል ለሕዝበ ኢትዮጵያ ሶበ መጽአት ጽላተ ሙሴ፡፡

## ፯.አጽንዖታዊ ቅጽል/Inphasise adjective/

በርዕሱ ዘርእሱ ለርእሱ

በርእሳ ዘር እሳ ለርእሳ

በርእስክሙ ዘርእስክሙ ለርእስክሙ

በርእስከን ለርእስከን ዘርእስከን

የቀረውን እንደዚሁ ብለሕ ከዚህ ከተዘረዘሩት መካከል መቀጸል የሚችለው ዘርእስየ የሚለው እና መሰሎች ናቸው፡፡

በርእስየ --አድራጊ /ማድረጊያ የወጣበት ስለሆነ

ለርእስየ---አቀባይ የወጣበት ስለሆነ

ምሳሌ፡-ጥቀ ጳውሎስ ክቡር ውእቱ ፡፡

ጥቀ ክቡር ጳውሎስ ውእቱ፡፡

ዘርእስየ ዚአየ መጽሐፍ ውእቱ፡፡

ዘርእሱ ዚአሁ መጽሐፍ ውእቱ፡፡

ዘርእሳ ዚኣሃ መጽሐፍ ውእቱ፡፡

ብዝኀት ኃጢያት በህየ ትፈደፍድ ፀጋ እግዚአብሔር

የቅጽል ቅርብና ሩቅ መደቡን ለይቶ የሚያሣየው አንቀጽ ነው፡፡

ሞሳሌ፡--ምኑን ሄሮድስ ቀተልከ ህፃናተ

ደኀርት ሕዝብ ኮነ ቀደምተ

ፅርዓዊ አንቲ ኮንኪ ጠቢበ፡፡ — ቅርብ

ምኑን ሄሮድስ ቀተለ ህፃናተ

ደኀርት ሕዝብ ኮኑ ቀደምተ

ፅርዓዊ ውእቱ ሐሰሰ ጥበበ — ሩቅ

የቅጽል ተባዕታይና አንስታይ ጾታ የሚለው ቅጽል + ት /የሴት/ ስለሚሆን ነው፡፡

ምሳሌ፡- ምኑን----ምንንት

መናኒ----መናኒት

መፍርሕ----መፍርሕት

እድ----አንስት

እጓል---እጕልት

ወልድ----ወለት

<u>ስርዋጽ ቅጽል</u> ---ባዕድ ፊደላን በመድረሻ ሳይጨምር ተባዕታይንና አንስታይ ጾታን አስተባብሮ ለሁለቱም ጾታዎች የሚነገር ቅጽል ነው፡፡

ፈራሕ/ፈሪ የፈራ ፡የፈራች /

ሕድግ/የተባለ/ች የተቀረጸ /የተቀረጸች/

ጸዋግ/የከፋ/የከፋች

ነቋር /ዓይነ ስውር ወንድ ሴት/

❖ <u>የቅጽል አንድ ና ብዙ ቍጥር</u>

በመነሻ ባዕድን ፊደላት «አ»፣«እለ» ን
በመድረሻ ምዕላድ ፊደላት ን፣ዊ/ይ፣ያ፣ት፣ው በመጨመር
«እለ» ን በመተካት ይበዛል፡፡

ሳድስ፡--

| | | |
|---|---|---|
| ሳድስ | ፍንው | ፍንዋን |
| | ፍቁር | ፍቁራን |

| | | |
|---|---|---|
| ዐማዒ | ዐማጽያን | ሣልስ |
| ሠራዒ | ሠራዕያን | |

| | | |
|---|---|---|
| መስም | መምህር | መምህራን |
| | መተንብል | መተንብላን |

| | | |
|---|---|---|
| ሰማያዊ | ሰማያውያን | ወገን |
| ፅርአዊ | ፅር አውያን | |

| | | |
|---|---|---|
| ምንት | ምንታት | ንዑስ ቅጽል |
| አይ | አያት | |
| መኑ | ዕለመኑ | |

| | | |
|---|---|---|
| ደቂቅ ቅጽል | ዝንቱ | ዕሉ |
| | ውእቱ | ውእቶሙ |

| | | |
|---|---|---|
| ሀገር | አህጉር | ነባር ው.ቅ |
| አብ | አበው | |

# ምዕራፍ--፮

## ዝርዝር

በግስ ላይ ወይም በነባር ላይ በፊደል ተጨምረው ወይም በድምጽ ብቻ የሚነገሩ የባለቤትን ወይም የተሳቢን አንድ እና ብዙ ቁጥር ፣ቅርብና ሩቅ መደብን ፣ወንድ እና ሴት አንቀጽን የሚያስለዩ ፊደላት ወይም ድምጾች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ዝርዝር ማለት አመልካች ፣ጠቃሽ ፣ቅርጽና ፊደል ድምጽ ማለት ነው፡፡

ዝርዝር----ነባራዊ ዝርዝር

***----ግሳዊ ዝርዝር***----ተሳቢ ዝርዝር

***----የባለቤት ዝርዝር***----የባለቤት ዘመድ

----የባለቤት ባዕድ

## የባለቤት ዘመድ ዝርዝር

በፊደል ሳይገለጽ /ምዕላድ ፊደልን በግስ ላይ ሳይጨምር በግስ መድረሻ ላይ ሆኖ በድምጽ ብቻ ባለቤትን/ግስን የሚያመለክት የሚጠቅስ ድምጸ ግዕዝ ነው፡፡

ከመራሕያን ---በውእቱ

---በውእቶሙ

---በውእቶን ላይ ሌላፊደል ሳጨምር የፊደል ቅርጽና ድምጽ ብቻ በመለወጥ የሚነገር ነው፡፡

ምሳሌ፡-ቀተለ---ግእዝ ድምጽ -ውእቱ

ቀተሉ---ካዕብ ድምጽ-ውእቶሙ

ቀተላ---ራብዕ ድምጽ

መጽአ ቀተሎ--ዘመድ ዘር

መጽኡ

መጽኣ

ሁለቱም ላይ የቅርጽ እና የድምጽ ለወጥ ብቻ መካሔዱን ልብ ይሏል፡፡

## የባለቤት ባዕድ ዘር

በቀዳማይ ኃላፊ አንቀጽ መድረሻ ላይ በምዕላድ ፊደል ተገልጸ ባለቤትን የሚያመለክት /የሚጠቅስ ድምጽ ባለቤት ነው፡፡

ከመራሕያን ከሩቆች ሴቷን እና ሌሎችን በሙሉ በመያዝ ይገልጻል፡፡

ቀተለ----ቀተል<u>ኩ</u>

----ቀተል<u>ነ</u>

----ቀተል<u>ከ</u>

----ቀተል<u>ኪ</u>

----ቀተል<u>ክሙ</u>

----ቀተልክን   ሁሉም ላይ ስንመለከት ባዕድ /ከግሱ ያልነበሩ ፊደላትን ጨምረዋል

----ቀተለት      ወይም ኩ፣ነ፣ከ፣ኪ፣ክሙ፣ክን፣ እና ት ጨምረዋል፡፡

## ግሳዊ ተሳቢ ዝርዝር

ፊደል ተጨምሮ ሳይጨምር በድምጽ ብቻ በባለቤት ዝርዝር ላይ ተደራቢ እየሆነ የሚነገር ድምጽ ወይም ፊደል ነው፡፡ይህም ተሳቢን የሚያመለክት ነው፡፡

፯ ቀመሮች አሉት

ቀመር-፩ ፩ᵉ ለ፪ᵉ   አነ   ንህነ

ቀተልኩከ/እኔ አንተን ገደልሁ   ቀተልናከ/እኛ አንተን ገደልንህ

ቀተልኩኪ/እኔ አንችን ገደልሁሽ   ቀተልናኪ

ቀተልኩክሙ/እኔ እናንተን ገደልኋችሁ   ቀተልናክሙ

ቀተልኩክን   ቀተልናክን

ቀመር-፪ ፪ᵉ ለ፫ᵉ   አነ ቀተልክዎ   ንህነ ቀተልናሁ

ቀተልክዎ   ቀተልናሃ

ቀተልክዎሙ   ቀተልናክሙ

ቀተልክዎን   ቀተልናክን

ቀመር-፫ ፪ᵉ ለ፩ᵉ   አንተ----ቀተልከኒ   አንቲ----ቀተልክኒ

----ቀተልከነ   ----ቀተልክን

አንተሙ----ቀተልክሙኒ   አንትን----ቀተልክናኒ

----ቀተልክሙነ   ----ቀተልክናነ

ቀመር-፬ ፪ᵉ ለ፫ᵉ   ቀተልካሁ   ቀተልኪዮ

ቀተልካሃ   ቀተልኪያ

ቀተልካሆሙ   ቀተልኪዮሙ

ቀተልካሆን   ቀተልኪያዮን

ቀተልክምዎ   ቀተልክናሁ

ቀተልክምዋ   ቀተልክናሀ

ቀተልክምዎሙ   ቀተልክናሆሙ

ቀተልክምዎን   ቀተልክናሆን

ቀመር-፭ ፫ᵉ ለ ፩ᵉ   ቀተለኒ   ቀተልክምዎ

ቀተለነ ቀተልክምዋ

ቀተለተኒ ቀተልክምዎሙ

ቀተለተነ ቀተልክምዎን

ቀተሉኒ ቀተልክናሁ

ቀተሉነ ቀተልክናሀ

ቀተላኒ ቀተልክናሆሙ

ቀተላነ ቀተልክናሆን

<u>ቀመር-፮ ፫ኛ ለ ፪ኛ</u> ቀተለከ ቀተሉከ

ቀተለኪ ቀተሉኪ

ቀተለክሙ ቀተሉክሙ

ቀተለክን ቀተሉክን

ቀተለተከ ቀተለከ

ቀተለተኪ ቀተለኪ

ቀተለተክሙ ቀተላክሙ

ቀተለተክን ቀተላክን

<u>ቀመር-፯ ፫ኛ ለ ፫ኛ</u>

ቀተሎ -- ቀተለቶ ቀተልዎ -- ቀተላሁ

ቀተላ -- ቀተለታ ቀተልዋ -- ቀተላሃ

ቀተሎሙ -- ቀተለቶሙ ቀተልዎሙ -- ቀተላሆሙ

ቀተሎን -- ቀተለቶን ቀተልዎን -- ቀተላሆን

## <u>የተሳቢ ድርብ ዝርዝር</u>

ከተሳቢ ዝርዝር ጋር እየተደረቡ በግስ መድረሻ ገብተው ተሳቢን ብቻ የሚጠቅሱ ዝርዝሮች ናቸው፡፡

አንድ ቍጥር --ሁ፣ሃ፣ዮ፣ያ

ብዙ ቍጥር --ሆሙ፣ሆን፣ዮሙ፣ዮን

የተሳቢ ድርብ ባዕድ ዝርዝሮች ፡-

--የቅርብ ሩቅ መደብን

--የተባዕታይና የአንስታይ ጾታን ወሰነ ሰዋስው ያላ ደባለቁ መስለው ይገባሉ፡፡

ምሳሌ፡-አብርሃም ወሰዳሁ ለይስሐቅ/አብርሃም ይሳቅን ወሰደው/---ሩቅ መደብ

አብርሃም ወሰድካሁ ለይስሐቅ /አብርሃም ይስሐቅን ወሰድከው/---ቅርብ መደብ

ያዕቆብ ወለዳሆሙ ለደቂቁ ----ሩቅ

ያዕቆብ ወለዶሙ ለደቂቁ

ያዕቆብ ወለድካሆሙ ለደቂቅከ----ቅርብ

## <u>ነባራዊ ዝርዝር</u>

እርባታ የሌለው ፩፣፪(ትንቢት) ፡ ፫(ትዕዛዝ) አንቀጽ አንድ አይነት የሆነ (ለውጥ የሌለው) ነባር ይባላል።

በነባር ሰዋስው መድረሻ ላይ ገብተው የተሳቢና የባለ ገንዘብ

---አንድና ብዙ ቊጥርን

---ተባዕታይና አንስታይ ጾታን

---ቅርብና ሩቅ መደብን የሚያመለክቱ ነባር ዝርዝር ይባላሉ፡፡

<u>እነዚህም</u>፡- --በነባር አንቀጽ (ኩነት፣ሕልው)

---በስም

---በደቂቅና በንዑስ አገባብ ይገባሉ፡፡

<u>በነባር አንቀጽ ሲገቡ</u> ----ብከ ማኅደር ዘበሰማያት

----አልብከ ማኅደር ዘበሰማያት

----ቦቱ አዋልድ መውልድ እምጽጌ ሐዲስ

----አልቦቱ አዋልድ መውልድ እምጽጌ ሐዲስ

<u>በስም ሲገባ</u> --- የነባር ሰዋስው ዝርዝሮች ከተጸውዖ ስም በቀር በገቢርና በተገብሮ ስልት በሚነገረው ስም መድረሻ ላይ ገብተው ባለገንዘብ /ባለንብርትን/በማመልከት ይዘረዘራሉ ድምጻቸውን ያሰማሉ፡፡

ምሳሌ፡---ተሐንጸ ቤትየ / ጥቅምየ

<u>ቤት</u> እና <u>ጥቅም</u> ስም ሲሆኑ <u>የ</u> ፣<u>የ</u> የሚሉት ደግሞ ዝርዝር ናቸው፡፡

<u>በንዑስ አገባብ</u> --በንዑስ አገባብ መድረሻ ላይ በመግባት ይዘረዘራሉ

ምሳሌ፡-አብርሃም ምንትየ ሊተ፡፡ምንት--ንዑስ ሲሆን የ--ደግሞ አገባብ ነው

<u>በደቂቅ አገባብ--</u> እንደ ንዑስ አገባብ መድረሻ ላይ ገብተው ይዘረዘራሉ፡፡

ተፈነወ ኀቤነ/ኀቤየ/ኀቤከሙ

መጽአ መንገሌየ/መንገሌየ/መንጋሌከ

<u>ነባራዊ ዝርዝሮች በዐሥሩ መራሕያን</u>

| | |
|---|---|
| ብየ/አለኝ | ባቱ/አለው |
| ብነ/አለን | ባቲ/አላት |
| ብከ/አለህ | ቦሙ/አላቸው |
| ብከሙ/አላችሁ | ቦቶን/አላቸው |
| ብከን /አላችሁ | |

በዚህ መሰረት የሚከተሉትን በዐሥሩ መራሕያን ዘርዝር

--- አልቦ/ነባር ---ሃይማኖት /ስም/ ---ጠሊ/ስም/ ---ጥበብ/ስም

---ኀበ/አገባብ ---መና/ስም/ ---ነጌ/ስም/

# <u>ምዕራፍ--፯</u>

# <u>ባዕድ ፣ምዕላድ እና ባዕድ ከምዕላድ</u>

# <u>ባዕድ ሰዋስው/prefixes/</u>

የሰዋስው መደበኛ ዘር ያልሆነ ባዕድ ፊደል በመነሻ የገባበት ሰዋስው ባዕድ ዘር ሰዋስው ይባላል፡፡ባዕድ ፊደል የተጨመረበት ሰዋስው ማለት ነው፡፡

| | |
|---|---|
| ምሳሌ፡--መቅድስ | መቀደሻ |
| ሙጻዕ | መውጫ |
| አስካል | ፍሬ |
| አግበረ | አስደረገ፣አሠራ |
| አስቈረረ | አጸየፈ አስፀየፈ |

## <u>ክፍላተ ባዕድ ዘር ሰዋስው</u>

ሀ.ብትን ባዕድ ዘር ሰዋስው

ለ.ግስ ባዕድ ዘር ሰዋስው

### ሀ.ብትን ባዕድ ዘር ሰዋስው

ባዕድ ፊደል በመነሻ የገባበት የግብር (ድርጊት) የቦታና የነገር ስም ብትን ባዕድ ዘር ሰዋስው ይባላል፡፡

ብትን የተባለበት ምክንያት እንደ ግስ ቅርብና ሩቅ መደብን ፣ተባዕታይንእና አንስታይ ጾታን ፣ኃላፊና ትንቢት ጊዜያትን ለይቶ ስለ ማያስረዳ ነው፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| መስቀል | --- መሰቀያ፣መስቀያ | ምቅዋም | ---መቋሚያ |
| ሞጻፍ | ----ወንጭፍ | ትርጋድ | ---ግርጌ |
| አስካል | -----ፍሬ | ተግሳጽ | ---ምክር |
| መቅደስ | -----መቀደሻ | ተምያጥ | ---መልስ |
| ሙጻእ | -----መውጫ | ታሕጻጽ | ---ጉድለት |

***<u>፩.የብትን ሰዋስው ተገብሮ/ተደራጊ/ስልቱ</u>***

ብትን ባዕድ ዘር ሰዋስው መድረሻ ፊደሉን ሳይለውጥ በተገብሮነት/በተደራጊነት/ስልት የማሰሪያ አንቀጽ ባለቤት ሆኖ ይነገራል፡፡

ምሳሌ፡-አብርሃ መስቀል ----መስቀል አበራ

ተሐንጸ መርጡል/መቅደስ ----መቅደስ ታነጸ

ርሕበ ሙጻዕ ----መውጫ ሰፋ

አልቦ ተምያጥ ----መልስ የለም

አስተርአየ አስካል ----ፍሬ ታየ
↓
ባዕድ ዘር ሰዋስው

***፪.ገቢር /ተገቢነት/ ስልቱ***

ብትን ባዕድ ዘር ሰዋስው መድረሻው ሳድስ የነበረውን ወደ ግዕዝ ፣ካዕብ የነበረውን ወደ ሳብዕ፣ሣልስ የነበረውን ወደ ኃምስ ፣ኃምስ ፡ራብዕና ሳብዕ የነበረውን እንዳለ ሳይለውጥ የማሰሪያ አንቀጽ ተሳቢ በመሆን ይነገራል።

ምሳሌ፡-ሐነጸ ሰሎሞን መቅደሰ

ይከሪ አንበሳ ሙጻአ

ኀለየ ኪሩብ ማኅሌተ

ያፈቅር ጠቢብ ተግሳጸ

ፈረይ ዕጸው አሰካለ

## ***ሊ. ግሳዊ ባዕድ ዘር ሰዋስው***

ባዕድ ፊደል /መደበኛ ዘር ያልሆነ/ በመነሻ የገባበት ዐቢይ አንቀጽ (፩ᵉ አንቀጽ(ኃላፊ ጊዜ)፣፪ᵉ አንቀጽ (ትንቢት ሕልው)፣፫ᵉ አንቀጽ(ትዕዛዝ) እና ንዑስ አንቀጽ (አርዕስት፣ዘንድ፣ቦዝ እና ውስጠ ዘ ቅጽል) ግሳዊ ባዕድ ዘር አንቀጽ ሰዋስው ይባላል።

***፩.ባዕድ ዘር ዐቢይ አንቀጽ***

ቀዳማይ ---ተሰማ ዜናከ (ዜናህ ተሰማ )

--- አስቄረረ ፄናሁ(ሽታው አጸየፈ)

---አስተጋብዐ ብዙኃነ (ብዙዎችን ሰበሰበ)

---አንፈርዐጸ እጓል ውስተ ከርሳ እሙ(በእናቱ ሆድ ዘለለ)

ካልዐይ ----ይገብር መንክረ(ድንቅን ያደርጋል)

----ይሰምር መሬቶ(መሬቱ ይወደድለታል)

----ይቄድስ ቅዳሴ (ቅዳሴ ይቀድሳል)

----ይመጽእ በሌሊት(በሌሊት ይመጣል)

----ይከሥት ምሥጢረ(ምሥጢርን ይገልጣል)

ሣልሳይ ----ይግበር መንክረ (ድንቅን ያደርግ)

----ይቀድስ ቅዳሴ(ቅዳሴ ይቀድስ)

----ይምጽአ በሌሊት (በሌሊት ይምጣ)

----ይክሥት ምሥጢረ (ምሥጢርን ይግለጥ)

***፪.ባዕድ ዘር ንዑስ አንቀጽ***

አርእስት---ተጋብአ/ተጋብአት

---ቀቲል/ቀቲሎ

---ገቢር/ገቢሮት

---ነዊም/ነዊሞት

---ጽሒፍ/ጽሒፎት

---ወድስ/ወድሶት

ቦዝ አንቀጽ---አቅቲሎ--አስገድሎ

---አቀዲሶ--አስቀድሶ/አመስግኖ

---ተጽሒፈ---ተጽፎ

መጺአ---መጥቶ
ተበሊኦ---ተበልቶ
አስትዮ---አጠጥቶ
አፍቀሮ---ወዶ

ባዕድ ናቸው።

ዘንድ አንቀጽ ---ሣልሳይ አንቀጽ በገባበት ስለሚገባ ከቦታው ተመልከት

ሣልስ ውስጠ ዘ ----ተጋባኢ

----አግባኢ

----አስተጋባኢ

----እስትግቡእ

----መስተጋብዕ

----አንፈርአጺ

የንዑስ አንቀጽ ባዕድን በደንብ ተመልከት፡፡

## ምዕላድ ሰዋስው

መደበኛ ያልሆነውን ፊደል በመድረሻው እየጨመረ የሚነገር ሰዋስው ምዕላድ ሰዋስው /ምዕላድ ዘር

ምዕላድ ማለት አለደ ሰበሰበ ከሚለው ወጥቶ የባዕድ ፊደል መሰብሰቢያ የባዕድ ፊደል ማከማቻ የሚለውን ትርጉም ይይዛል።

### የምዕላድ ዓይነቶች

ጥሬ ዘር ምዕላድ ---ምልክና

---ብርሃን

---ውዳሴ

---ስባሔ

ቅጽል ምዕላድ ---ጻድቃን

---ብእሲት

---አበው

ሳቢ ዘር ምዕላድ---ሕርመት

---ጽንነት

---ግብረት

አርእስት ምዕላድ---ነቢሮት

----ባርኮት

---ጸውዖት

ዐቢይ አንቀጽ ምዕላድ--ሰመርኩ

---ሰመርናሁ

---ሰመርክሙ

## <u>ክፍላተ ምዕላድ ሰዋስው</u>

ሀ.ስማዊ ምዕላድ

ለ.ግሳዊ ምዕላድ

### *ሀ.ስማዊ ምዕላድ*

ባዕድ ፊደልን በመድረሻ እየጨመረ የሚነገር ጥሬ ዘር ሰዋስው፣ውስጠ ዘ ቅጽል ሰዋስው፣የባህርያዊ ጾታ ስም፣ተውላጠ ስም ስማዊ ምዕላድ ሰዋስው ይባላል።

በሌላ አገላለጽ የስም ወገን፣ስም መሰል፣ስም አብል የባዕድ ፊደልና ድምጽ መሰብሰቢያ ሰዋስው ማለት ነው።

ምሳሌ፡-ብርሃን---ብርሃን

ምልክና ---ግዛት

ጻድቃን---እውነተኞች፣ከቡራን

አበው---አባቶች

ሐዋርያት---መልዕክተኞች ሂያጅ

ናዝራዊ---የናዝሬት ወገን

ኵሎሙ---ኹሉ

ብእሲት---ሴት

አንትሙ---እናንት

ውእቶሙ---እነሱ

<u>፩.የአንቀጽ ባለቤት እየሆነ ይነገራል</u>

ምሳሌ፡-መጽአ ብርሃን---ብርሃን መጣ

ቦቱ ምልክና---ግዛት ነበረው

ተለው ጻድቃን አሰሮ----ጻድቃን ኮቴውን /ዱካውን/ተከተሉ

ይባርኩ አበው ደቂቀ---አባቶች ልጆችን ይባርኩ።

<u>፪.በገቢር/የአንቀጽ ተገቢ በመሆን /ስልት ሲነገር</u>

መድረሻውን ፊደልና ድምጽ ሳድስ የነበረውን ግዕዝ ፣ካዕብ የነበረውን ሳብዕ፣ሣልስ የነበረውን ወደ ኃምስ ፡ራብዕ ፣ኃምስ እና ሳብዕ የሆነውን ደግሞ እንዳለ ሳይለውጥ የማሰሪያ አንቀጽ ተሳቢ ሆኖ ይነገራል፡፡

ምሳሌ፡--ውእቱ ከሰተ ብርሃነ

ኵሉ ይትሜነይ ምልክና

አንትሙ ኢትሜንኑ ጻድቃነ

ሔራን ይትዌከፍ ሐዋርያ

<u>አይሁድ</u> <u>ኢያከብሩ</u> <u>ናዝራዊ</u>

↓ ↓ ↓

ባለቤት አንቀጽ ተሳቢ ስማዊ ምዕላድ

### ሊ ግሳዊ ምላድ ሰዋስው

ባዕድ ፊደልን በመድረሻው እየጨመረ የሚነገር ዐቢይ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ግሳዊ ምላድ ሰዋስው ወይም የግስ ወገን ረቢና ሳቢ የባዕድ ፊደለና የባዕድ ፊደልና የድምጽ መሰብሰቢያ መከማቻ ሰዋስው ማለት ነው። ምሳሌ፡--

ሳቢ ዘር ምዕላድ:
- ሢመት----መሾም
- ምርዓት---መዳራት
- ዕርገት----መውጣት

ንዑስ አንቀጽ ምዕላድ:
- ገቢሮት---መስራት
- ተወክፎት---መቀበል
- ጐንድዮት---መዘግየት
- ፍርሃት----መፍራት

ዐቢይ አንቀጽ ምዕላድ:
- ሰመርኩ----ወደድሁ
- ፈነዎሙ---ላካቸው
- ፈታሕኩሙ---ፈታችሁን

<u>*ሀ.ሳቢዘር እና አርእስት ምዕላድ ሰዋስው /ንዑሳን ምዕላድ ሰዋስው/*</u>

<u>፩.በተገብሮ/በባለቤትነት ስልት ሲነገሩ</u>

ምሳሌ፡---<u>ምርዓት</u> ተረኩሰ ለሰብዕ/መዳራት ሰውን ታረክሰዋለች /

<u>ቅናት</u> አኅዞሙ ለአብዳን/ቅናት ሰነፎችን ያዘች/

<u>ምሕረት</u> አልቦሙ ለአሕዛብ/ለአሕዛብ ይቅርታ የላቸውም/

<u>አክብሮት</u> ይትሀየይ ልሒቀ/ታላቅን ማክበር ቸል አይባልም/

<u>ተወክፎት</u> ይደሉ ነግደ /እንግዳን መቀበል ይገባል/

ኢይትከሐል <u>አግርሮት</u> ልሳነ/አንደበትን መግዛት አይቻልም//

የተሰመረባቸው ቃላት ምዕላድ ንዑሳን አናቅጽ ሰዋስው እንደባለቤት ሲያገለግሉ፡፡

<u>፪.በገቢር/በተሳቢነት ስልት ሲነገሩ</u>

ምሳሌ፡--ሠምረ ቃየን <u>ቅትለተ</u> አቤልሀ/አቤልን መግደልን ወደደ
ተአገሰ እግዚእ <u>ኵረተ</u> ርዕስ/ራስን መደብደብን ታገሰ
ያበዝኍ አይሁድ <u>ሁሰተ</u> ርዕስ/ራስን መነቅነቅን ያበዛሉ
ፈቀደ አብርሃም <u>ተኪሎተ</u> ሐይመተ /ድንኳን መትከልን
ኢይጸርዕ ኪሩብ <u>ቀድሰተ</u> ቅዳሴ/ምስጋና ማመስገንን አያቋርጥም
ያበድሩ ጻድቃን <u>መንኖተ</u> ዓለም/ዓለምን መናቅን ይመርጣሉ

↓

ምዕላድ ሰዋስው እንደ ተሳቢ ሆነው ሲያገለግሉ

***ሊዐቢይ አንቀጽ ምዕላድ ሰዋስው***

ምሳሌ፡-ነበብከ ጽድቀ /እኔ እውነትን ተናገርኩ

ፈወስናሃ ንህነ ለባቢሎን /እኛ ባቢሎንን ፈወስናት

ቀባዕካሁ አንተ ለዳዊት /አንተ ዳዊትን ቀባሀው

በደርከናሆሙ አንትን ለአርድዕት/እናንተ ተማሪዎችን ቀደማችኋቸው

<u>ባዕድ ከምዕላድ</u>

ባዕድ ሰዋስውን እና ምዕላድ ሰዋስውን በአንድ ላይ እንደ አቀማመጣቸው የሚይዝ ሰዋስው ባዕድ ከምዕላድ ሰዋስው ተብሎ ይጠራል።

ምሳሌ፩፡-

| | | |
|---|---|---|
| መሥዋዕት | አንቃዕድዎት | እንደባለቤት |
| መሥፈርት | አስተፋጠንከሙ | |
| ማኅሌት | አስቆቀውዎሙ | |
| ትምህርት | ትሕርምት | |
| አስተብቍዖት | | |

ምሳሌ፪፡-አስተምሕሪ መስተምሕርት ኀበ ወልድኪ

ተሦዐ መሥዋዕት ለአምላክነ

የሐርስዎ አግብርት ለምድር

ታስተፌስሕ <u>ትዕግስት</u> ተዐገሰ

ምሳሌ፫፡- ይትመሐጸን ኤፍሬም <u>መስተምሕርተ</u>

ሦዐ አብርሃም <u>መስዋዕተ</u>

ያዘልፍ ኢዮብ <u>ትዕግስተ</u>

ያፈቅር ጠቢብ <u>ትምሕርተ</u>

ይጽብት ኖትየ <u>አብሕርተ</u>

ይፌኑ ባዕል <u>አግብርተ</u>

↓

ባዕድ ከምዕላድ ሰዋስው

# ምዕራፍ--፫

## ረብሓ ግስ

ግስ ማለት የተሰሩ ወይም የተሰበሰቡ ቃላትን መልእክት እንዲያስተላልፍ በዐ.ነገር ውስጥ በመገኘት የሚያሥር የሚሠበስብ ማለት ነው።

ረብሓ ግስ፡-ማለት ዘማች ግሶችን ከቀዳማይ አንቀጽ ጀምሮ እስከ ዐርዕስት እና ከዚያ በላይ ያሉትን ቅጽሎችን የሚያገሰግስ ማለት ነው፡(ቀዳማይ አንቀጽን ማርባት መተንተን ማለት ነው)

- *መራኁተ ግስ፡ፊደላት ሲሆኑ ሁል ጊዜ በግሱ መጀመሪያ ላይ የሚገኙ ናቸው።*
  *መንስኤ ግስ ወይም አርኀውያን/ወጣንያን ተብለው ይጠራሉ።*
  *ግስ የሚያስነሱ ቀለማት ተብለውም ይጠራሉ እነዚህም፡-*

*ግዕዝ* *ኃምስ*

*ራብዕ* *ሳድስ እና ሳብዕ ናቸው።*

ምሳሌ፡-*ግዕዝ*---*ቀተለ፣ቀደሰ፣ተንበለ*

*ራብዕ*---ባረከ፣ማሕረከ

*ኃምስ*----ሴሰየ

ሳድስ---ክህለ

ሳብዕ---ጦመረ

- *መሠረታዊ ግስ (ዘማች ቀዳማይ አንቀጽ) ተመስርቶ የሚገኘው በሦስተኛ መደብ ወንድ ነጠላ ቁጥር ነው(ውእቱ)*
- *ግስ የማያስነሱ ቀለማቶች ሁለት ናቸው ማንማን ናቸው ቢሉ ካዕብ እና ሣልስ ናቸው።*

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ምሳሌ፡-*ሖረ* | } | | *ሑረ* | } |
| *ቴሀ* | } ይላል እንጂ | | *ቲሀ* | } አይልም |

- *የግስ መድረሻ ቀለማቶች ሁለት ናቸው እነዚህም ግእዝ እና ኃምስ ናቸው።*
- *የግእዝ ማስረጃ ከሀ--ፐ የሚገኙ ግሶች በሙሉ ናቸው።*
- *የኃምስ ግን አንድ «ይቤ» ብቻ ነው፡፡ነባር አንቀጽ አይደለም ቢሉ ካልአዩን፣ዘንዱን፣ትእዛዙን ይዞ ስለተገኘ ነው።*

## የረብሓ ግስ ዓይነቶች

*ግስ የሚረባበት ሁለት ዓይነት መንገድ አለው።እነዚህም፡-*

*ሀ.የዋሕ ረብሓ ግስ*

*ለ.መሠሪ ረብሓ ግስ*

### *ሀ.የዋሕ ረብሓ ግስ*

*ግስን በውእቱ ባለቤትነት (ዘማች አንቀጽ በውእቱ ስለሚጠሩ ስለሚመሠረቱ) በመራሕያን ባለቤትነት በግስ አርስቶች ተመስርቶ መገሰስ/ማገስገስ የዋሕ ረብሓ ግስ ተብሎ ይጠራል።*

| ምሳሌ፡- | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ቀተለ | ቀደሰ | ተንበለ |
| | | ይቀትል | ይቄድስ | ይተነብል |
| | | ይቅትል | ይቀድስ | ይተንብል |
| በውእቱ | | ይቅትል | ይቀድስ | ይተንብል |
| | | ቀቲል/ቀቲሎት | ቀድስ/ቀድስት | ተንብሎ/ተንብሎት |
| | | ቀታሊ/ልያን | ቀዳሲ/ሳያን | ተንባሊ/ልያን |
| | | ቀታሊት/ልያት | ቀዳሲት/ሳያት | ተንባሊት/ልያት |
| | | | ቅዱስ/ቅዱሳን | መተንብል/ላን |
| | | | ቅድስት/ሳት | መተንብልት/ላት |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ቀተልኩ | ቀተልነ | ቀተልከ | ቀተልኪ |
| በመራሕያን | እቀትል | ንቀትል | ትቀትል | ትቀትሊ |
| | እቀትል | ንቅትል | ትቅትል | ትቅትሊ |
| | | ቅትል | ቅትሊ | |

ሌሎችን ግሶችም በዚህ መልክ እና በመራሕያን ሙሉ ለሙሉ መዘርዘር ይቻላል፡ማለትም አውጣሓቸው ማገስገስ ይቻላል፡፡

***ሊ.መሠሪ ረብሓ ግስ***

መሰሪ ግስ የሚረባበት የርባታ ስልት መሠሪ ረብሓ ግስ ይባላል፡መሠሪ የሚል የስያሜ ቅጽል የተቀጸለበትም ምክንያት የግስ መደበኛ ዘር በባለቤት ዝርዝር ላይ ሎቱን፣ቦቱን፣የተሳቢ ዝርዝርን እየጨመረ በበጎ እና በክፉ ነገር ስለሚነገር ስለሚተረጎም ነው።

ምሳሌ፡-ተለውኩ ቦቱ--ተከተልኩበት

ተለውኩ ሎቱ---ተከተልኩለት

ተለውኩ ላቲ---ተከተልኩላት

ተለውኩ ባቲ---ተከተልኩባት

ተለውኩ ሎሙ---ተከተልኩላቸው

ተለውኩ ቦሙ---ተከተልኩባቸው

ሎቱ---የበጐ ነገር አመልካች

ቦቱ---የክፉ ነገር አመልካች ናቸው።

የተሳቢ ዝርዝርን ጨምሮ ሲነገር

ሎቱ እና ቦቱ በንባብ ሳይገለጹ በተሳቢ ዝርዝር ድምጽ ብቻ እየተነገሩ በጐንና ክፉ ነገርን ያመለክታሉ።

በዚህ ጊዜ የመሠሪ ግስ በጐና ክፉ ስሜት በንባብ ተለይተው አይታቁም።

ምሳሌ፡-ተለውኩኮ---ተከተልኩህ(በጐም ክፉም)

ተለውኩከ--- ተከተልኩልህ(በጐኛ)

ተለውኩከ---ተከተልኩብህ(ክፉኛ)

----አሐየው ኢየሱስ ለመጸጉዕ(ኢየሱስ ሽባውን አዳናው)ሎቱ

----ወአሐብአሙ ሞክሮሙ ለመካርያን

(የመካሪዎችን ምክራቸውን እሸሽግባቸዋለሁ)-ቦቱ

እያንዳንዱ ግስ በዚህ አማርኛ ተፈቶ በበጎና በክፉ በመናገር በሁለት ሙቶ ዐርባ ወይም በሁለት ሙቶ ሰማንያ የዓበይት አናቅጽ ዐቢይ ቀመር ርባሕ ይባላል።

| | |
|---|---|
| ቀዳማይ---80 | ቀዳማይ----96 |
| ካልአይ---80 | ካልአይ----96 |
| ሣልሳይ---80 | ሣልሳይ----96 |
| ጠቅላላ---240 | ጠቅላላ----288 |
| 3*80----240 | 96*3---288 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ፡--ተለኩከ | ተለውኩኪ | አእመርኩከ | አእመርኩኪ |
| እተልወከ | እተልወኪ | አአምረከ | አአምረኪ |
| እትሉከ | እትሉኪ | አእምርከ | አእምርኪ |
| --ተለዉኩክሙ | ተለውኩክን | አእመርኩክሙ | አእመርኩክን |
| እተልወክሙ | እተልዎክን | አአምረክሙ | አእምርክን |
| እትሉክሙ | እትሉክን | አእምርክሙ | አእምርክን |

❖ ከዚህ ላይ ይህን ቁጥር ልናመጣው የቻልንበት ሁኔታ ምንድን ነው ቢሉ አንዱ መራሂ ሌሎችን 8ቱን ሲያውቃቸው ወይም ሲከተላቸው 10 መራሕያን እያንዳንዳቸው 80 ይሆናሉ ይህን በቀዳማይ

በካልኣይ ፣በሣልሳይ አንቀጽ ስንመለከተው 240 ይሆናል።ይህ የሚሆነው በቅርቦች እና በኣነ፣በንህነ ነው።

❖ በሩቆች ግን አንዱ/ውእቱ የቅርቦችን ፣የሩቆችን እና የንህነ የአነንን ስለሚያውቅ ወይም ስለሚያሰማ 12 ይሆናል በዚህም መሠረት ቀዳማይ አንቀጽ 96 ካልኣይ 96 እና ሣልሳይ 96 ይሆንና በጠቅላለው 288 ይሆናል ማለት ነው።

❖ የዋት ግስ እና መሠሪ ግስ ልዩነታቸው ምንድን ነው?

ምሳሌ፦ <u>የዋሐ</u> <u>መሠሪ</u> <u>መሠሪ</u> <u>የዋሕ</u>

| | |
|---|---|
| ረስየ--------ረስዮ | መሀርኩከ------መሀርኩ |
| ረስዐ-------ረስዖ | ማህርክዎ-------ማህረኩ |
| ርእየ------ርእዮ | መለክናከ-----መለክን |
| ሰምዐ-----ሰምዖ | መላእክናሁ----መላእክን |
| ቀደመ------ቀደሞ | መስጥከሙ----መስጠከ |
| ቀጥቀጠ----ቀጥቀጦ | መነንክሙኒ----መነንክሙ |
| ቀጸበ-----ቀጸቦ | ከፈለተኒ-----ከፈለት |

## <u>የግስ አረእስት እና ሠራዊቶች ከነርባታ ዝርዝራቸው</u>

በግዕዝ ሰዋስው ግሶች አርእስት እና ሠራዊት በመባል በሁለት ምድብ ይከፈላሉ።

❖ አርእስት የሚባሉት በእርባታቸው እና በሰዋስዋዊ አገባባቸው ለጠቅላላው ግስ ተጠሪዎች ወይም ወካዮች ሆነው በመመረጣቸው ነው፡ይህም የሆነበት ምክንያት ዐሥሩን መራሕያን መሠረት አድርጎ የአንድ ግስ እርባታ እስከ ሰማንያ እርከን ስለሚደርስ እና ይህንም በመዝገበ ቃላት ውስጥ ማስፈር እጅግ አታካች ስለሚሆን ስምንት አለቆች/አርእስቶች/ምሳሌ አድርጎ ለማሳየት ተፈልጎ ነው፡፣

❖ ሠራዊት የሚባሉት በከፊልም ሆነ በሙሉ እየአንዳንዱን ርእስ መስለው በመገኘታቸው እንደ አለቃቸው የሚገሰሱና የሚረቡ ናቸው፡፡

❖ ሥረይ ግስ እነዚህ ግሶች እንደ ርእስ እንዳይቆጠሩ አለቃ አላቸው እንደ ሠርዌ/ሠራዊት እንዳይቆጠሩ ከአለቃቸው የተለዩ ወይም ለአለቃቸው የማይገዙ ግሶች ሥረይ ግስ ይሏቸዋል፡፡

### *ሀ.የግስ አርእስቶች-*

ከላይ የተመለከትነው ትንታኔ እንዳለ ሁኖ ቍጥራቸውን እንመለከታለን።

የግስ አርእስቶች በየመጻሕፍቱ በየሊቃውንት የተለያዩ ናቸው፡ለምሳሌ፦

<u>፩.ሊቀ ሊቃውንት ያሬድ ሽፈራው</u>

| | |
|---|---|
| ቀተለ | ማህረከ |
| ቀደሰ | ሴሰየ |
| ተንበለ | ጦመረ |
| ባረከ | ክህለ |

«ቀደሰ»---የ«ቀተለ»ሠራዊት ነው ይላሉ፡፡

«ማህረከ»የ«ተንበለ»ሥራዊት ነው፡፡

፪.ኪዳነ ወልድ ክፍሌ

| | |
|---|---|
| ቀተለ | ማህረከ |
| ቀደሰ | ዴገነ |
| ደንገጸ | ኖለወ |
| ባረከ | |

«ደንገጸ»---ተንበለ «ዴገነ»---ሴሰየ «ኖለወ»----ጦመረ ስለሆነ ችግር የለውም።

፫.ሰዋስወ ግዕዝ

| | |
|---|---|
| ቀተለ | ባረከ |
| ቀደሰ | ሤመ |
| አእመረ | ብህለ |
| ገብረ | ቆመ |

- አእመረ---በቀተለ ቤት ለመገሰስ ቀተለ የ«አ»አመል ስለሌለው እና አእመረ ደግሞ የ«አ»አመል ስላለው በአመሉ ለመገሰስ ነው።
- ገብረ---በቀተለ ቤት መገሰስ ይቻላል ግን በመግለጫው ለመገለጽ ተፈልጎ ነው ፡ቀትለ የሚል የገብረ ጠባይ አለው።
- ሤመ---ሴሰየ ነው ግን ለራሱ የተለየ አመል አለው አመለኛውን ለማስቀመጥ ፈልጎ ነው ያስቀመጠው።
- ብህለ---ክህለ ስለሆነ ችግር የለውም
- ቆመ---ጦመረ ስለሆነ ችግር የለውም
- ቆመ እና ሤመ---ሁለቱም ቀተለ ቤት ናቸው በፊደል ስለተለዩ ርእስ አድርጓቸዋል።

፬.ሕያው ልሳን

| | |
|---|---|
| ቀተለ | ማህረከ |
| ቀደሰ | ዴገነ(ሴሰየ) |
| ተንበለ | ክህለ |
| ባረከ | ጦመረ |

- በአጠቃላይ የአርእስት መለያየት ምክንያቱ፡-
  - ✓ አንዱ የግስ አርእስት የአንዱን አመል ይዞ ስለሚገኝ

✓ የተለየ አመል ያለውን ለይቶ ለማወቅ/ለማሣወቅ እንዲረዳ ነው

ከዚህ በላይ በተመለከትነው መሠረት እኛም የግስ አርእስቶችን ስምንት ብለን እንመለከታለን ፡፡

| | የፊደል ደረጃ | | | አነባብ |
|---|---|---|---|---|
| ቀተለ | ግዕዝ | ግዕዝ | ግዕዝ | የላላ |
| ቀደሰ | ግዕዝ | ግዕዝ | ግዕዝ | የጠበቀ «ደ»ይጠብቃል |
| ተንበለ | ግእዝ | ሳድስ | ግእዝ | የላላ |
| ባረከ | ራብዕ | ግእዝ | ግእዝ | የላላ |
| ማህረከ | ራብዕ | ሳድስ | ግእዝ | የላላ |
| ሴሰየ | ኃምስ | ግዕዝ | ግዕዝ | የላላ |
| ጦመረ | ሳብዕ | ግእዝ | ግእዝ | የላላ |
| ክህለ | ሳድስ | ሳድስ | ግእዝ | የላላ |

***ገሲሰተ ግስ ዘልሳነ ግእዝ***

መሠረታዊ ግሱ(ዘማች አንቀጹ)በተለያየ መንገድ ሲረባ /ሲተነተን ይህ ሁኔታ ገሲሰተ ግስ ይባላል።

ከአንዱ መሠረታዊ ግስ (ዘማች አንቀጽ) ብዙዎች ግሶች፣ቅጽሎች፣አስማት፣ተውሳከ ግሶች ይፈጠራሉ/ይገኛሉ።

***ክፍላተ ገሲሰተ ግስ***

--በሦስት ይከፈላል፡እነዚህም ክፍሎች፡-

፩.ቀዳማይ(፩ᵉ)ገሲሰተ ግስ

፪.ካልአይ(፪ᵉ)ገሲሰተ ግስ

፫.ሣልሳይ(፫)ገሲሰተ ግስ ናቸው።

***፩.ቀዳማይ(፩ᵉ) ገሲሰተ ግስ***

ይህ የመገሰስ ስልት ከመሠራታዊ ግሱ የሚገኙ ግሶችን ፣ቅጽሎችን ፣ስሞችን፣እየአወጡ እስከ መጨረሻው መዝለቅ ፩ᵉገሲሰተ ግስ ተብሎ ይጠራል።

ለምሳሌ፡-ተከለ
ይተክል
ይትክል
} አቢይ አንቀጽ (ዐቢይ እርባታ)

ይትክል(ዘ አ)
ተኪል/ተኪሎት
} ንዑስ አንቀጽ (ንዑስ እርባታ)

ተካሊ/ልያን
ተካሊት/ተካልያት
ተከልት
ትኩል(ላን)
ትክልት(ላት)

} ቅጽለት

ተክል
ምትካል
(መትከያቦት)

} አስማት

} ደቂቅ እርባታ

ከዚህ ላይ ሊሰተዋል የሚገባው ነገር ቢኖር አድራጊው እና ተደራጊው የተቀለቀለ መሆኑ ነው።

ምሳሌ፡-ቀተለ

ይቀትል
ይቅትል

} ዐናቅጽ

ይቅትል(ዘ አ)
ቀቲለ/ቀቲሎት

} ንዑስ ዐንቀጽ

ቀታሊ(ልያን)
ቀታሊት(ልያት)

} ገቢር ቅጽለት

ቀተልት
ቅቱል/ላን
ቅትልት/ላት

} ተገብሮ ቅጽለት

ቀትል
ቀትለት
መቅትል

} አስማት

ምሳሌ፡-ቀደሰ----አመሰገነ

ይቄድስ----ያመሰግናል

ይቀድስ----ያመሰግን ዘንድ

ይቀድስ----ያመስግን

ቀድሰ/ቀድሰት----ማመስገን

ቀዳሲ/ሳያን----ያመሰገነ

ቀዳሲት/ስያት----ያመሰገነች

ቅዱስ/ሳን----የተመሰገነ

ቅድስት/ሳት----የተመሰገነች

መቅደስ----መቀደሻቦታ /ማመስገኛ ቦታ

ቅዱስ----ምስጉን

ቀዳሲ----አመስጋኝ

ቅዳሴ----ምስጋና

| | |
|---|---|
| ምሳሌ፡- ተንበለ----ለመነ | መተንብል(ላን)-----ለማኝ(የወንድ) |
| ይተነብል----ይለምናል | መተንብልት(ልት)-----ለማኝ(ሴት) |
| ይተንብል----ይለምን ዘንድ | ተንቢሎ-----ለምኖ |
| ይተንብል----ይለምን | ተንባል-----አማላጅ |
| ተንብሎ/ተንብሎት----መለመን | ተንባላት-----እስላማውያን |
| ተንባሊ(ልያን)-----የሚለምን/የሚለምኑ | ተንባላታዊ/ይ-----እስላም |
| ተንባሊት(ልያት)-----የምትለምን/የሚለምን | ትንባሌ------ልመና/ምልጃ |

| | | |
|---|---|---|
| <u>ማህረከ</u> | ማህርኮ/ማህርኮት | ምህርክት/ምህሩካት |
| ይመህርክ | ማህራኪ/ማህራክያን | ምህርካ |
| ይማህርክ | ማህራኪት/ክያት | |
| ይማህርክ | ምህሩክ/ምህሩካን | |

| | | |
|---|---|---|
| <u>ሴሰየ</u> | ሴስዮ/ሴስያት | ሲሱይ/ሲሱያን |
| ይሴሲ | ሴሳይ/ሴሳያን | ሴስይት/ሴስያት |
| ያሴሲ | ሴሳይት/ሴሳያት | መሴስይት/መሴስያት |

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ምሳሌዎች መሠረት ግሶችን መገሰስ ቀዳማይ ገሲሶተ ግስ ይባላል።ግሶችን በምንገስስበት ጊዜ ሁሉም ዘማች አንቀጾች እኩል ሆነው የሚገሰሱት እስከ አርእስት ነው፡ከዚህ ውጭ ባሉት ግን ሊመሳሰሉም ሊለያዩም ይችላሉ።

***<u>፪.ካልአ ገሲሰተ ግሰ</u>***

*መሠረታዊ ግስን በዐሥሩ መራሕያን እየዘረዘሩ እስከ ትእዘዝ አንቀጽ (ቀዳማይ አንቀጽን ፡፪ዩአንቀጽን፣፫ዩ(ትእዛዝ)አንቀጽ) የሚደረግ እርባታ/የግሰሳ ዓይነት ፪ዩ ተብሎ ይጠራል።*

**ምሳሌ፡-<u>ቀዳማይ አንቀጽ</u>**

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አነ | ንህነ | አንተ | አንትሙ | አንቲ | አንትን | ውእቱ | ውእቶሙ | ይእቲ | ውእቶን |
| ቀተልኩ | ቀተልነ | ቀተልከ | ቀተልክሙ | ቀተልኪ | ቀተልክን | ቀተለ | ቀተሉ | ቀተለት | ቀተላ |
| ተንበልኩ | ተንበልነ | ተንበልከ | ተንበልክሙ | ተንበልኪ | ተንበልክን | ተንበለ | ተንበሉ | ተንበለት | ተንበላ |

ባረኩ ባረክነ ባረከ ባረክሙ ባረኪ ባረክን ባረከ ባረከት ባረከት ባረካ

ክህልኩ ክህልነ ክህልከ ክህልክሙ ክህልኪ ክህልክን

ማህረኩ ማህረክነ ማህረከ ማህረክሙ ማህረኪ ማህርክን ማህረከ ማህርኩ ማህረከት ማህርካ

ሴሰየኩ ሴሰይነ ሴሰይከ ሴሰይክሙ ሴሰይኪ ሴሰይክን ሴስየ ሴሰዩ ሴሰየት ሴስያ

ጦማረኩ ጦመርነ ጦመርከ ጦመርክሙ ጦመርኪ ጦመርክን ጦመረ ጦመሩ ጦመረት ጦመራ

**ምሳሌ፡-**<u>**ካልኣይ ኣንቀጽ**</u>

እቀትል ንቀትል ትቀትል ትቀትሉ ትቀትሊ ትቀትላ ይቀትል ይቀትሉ ትቀትል ይቀትላ

እቄድስ ንቄድስ ትቄድስ ትቄድሱ ትቄድሲ ትቄድሳ ይቄድስ ይቄድሱ ትቄድስ ይቄድሳ
እተነብል ንተነብል ትተነብል ትተነብሉ ትተነብሊ ትተነብላ ይተነብል ይተነብሉ ትተነብል ይተነብላ

---

---

**ምሳሌ፡-** <u>**ሣልሳይ ኣንቀጽ**</u>

እቅትል ንቅትል ቅትል ቅትሉ ቅትሊ ቅተላ ይቅትል ይቅትሉ ትቀትል ይቅትላ

---

---

መርኆ ሰዋስው ገጽ <u>፩፻፪</u>

<u>*፫.ሣልሳይ ገሲሰተ ግስ*</u>

*መሠሪ ግሶችን ወይም ድርብ ግስን ማርባት ማለትም እነዚህም ግሶች የባለቤት እና የተሳቢ ዝርዝር የያዙ በተጨማሪም ድረጊት ተቀባይ እና አድራጊ/ፈጻሚ ያላቸው ናቸው።*

አካሔዱ እንደ ተሳቢ ዝርዝር ሲሆን እስከ ሣልሳይ አንቀጽ ድረስ የሚዘምት ነው።

ለአጠናን ይመች ዘንድ በሰባት ቀመር ቀምረን እንመለከተዋለን (ከቀመር፩-----ቀመር፯)

*ቀመር ፩..<u>አንደኛ መደብ ለሁለተኛ መደብ(፩ᵉ ለ፪ᵉ)</u>*

| | |
|---|---|
| አነ--- አእመርኩከ | አእመርኩክሙ |
| አእምረከ | አእምረክሙ |
| አእምርከ | አእምርክሙ |
| ---አእመርኩኪ | አእመርኩክን |
| አእምረኪ | አእምረክን |
| አእምርኪ | አእምርክን |

ንህነ--- አእመርናከ አእመርናክሙ

ነአምረከ ነአምረክሙ

ናእምረከ ናእምርክሙ

--- አእመርናኪ አእመርናክን

ነአምረኪ ነአምረክን

ናእምርኪ ናእምርክን(ዘንድ እና ትእዛዝ)

ቀመር ፪..<u>አንደኛ መደብ ለሦስተኛ መደብ(፩ዩ ለ፫ዩ)</u>

አነ--- አእመርክዎ አእመርክዎሙ

አአምሮ አአምሮሙ

አእምሮ አእምሮሙ

--- አእመርክዋ አእመርክዋን

አአምራ አአምሮን

አእምራ አእምሮን

ንህነ--- አእመርኖ/አእመርናሁ አእመርኖሙ/አእመርናሆሙ

ነአምሮ/ነአምራሁ ነአምሮሙ/ናእምራሆሙ

ናእምሮ/ናእምራሁ ናእምሮሙ/ናእምራሆሙ

---- አእመርና/አእመርናሃ አእመርኖን/አእመርናሆን

ነአምራ/ነአምራሃ ነአምሮን/ነአምራሆን

ናእምራ/ናእምራሃ ናእምሮን/ናእምራሆን

ቀመር ፫..<u>ሁለተኛ መደብ ለአንደኛ መደብ(፪ዩ ለ፩ዩ )</u>

አንተ--- አእመርከኒ[ፐ]/አእመርከኒ[^] አንትሙ---አእመሩኒ

ተአምራኒ[ፐ]/ተአምራኒ[^] የአምሩኒ

ታእምረኒ/ታእምራኒ[^] ያእምሩኒ

---- አእመርከነ/አእመርከነ ---- አእመሩነ

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ተአምራነ/ተአምራነ | | የአምሩነ |
| | ታእምረነ/ታእምራነ | | ያዕምሩነ |
| አንቲ---- | አእመርኪኒ/አእመርክኒ | አንትን--- | አእመርክናኒ |
| | ተአምርኒ | | ተአምራኒ |
| | ታእምሪኒ/ታእምርኒ | | ታእምራኒ |
| | አእምሪኒ/አእምርኒ | | አእምራኒ |
| ---- | አእመርኪነ/አእመርክነ | | አእመርክናነ |
| | ተአምሪነ/ተአምርነ | | ተአምራነ |
| | ታእምሪነ/ተአምርነ | | አእምራነ |

ቀመር ፬..<u>ሁለተኛ መደብ ለሦስተኛ መደብ(፪</u> ለ፫ )

| | | | |
|---|---|---|---|
| አንተ--- | አእመረከ/አእመርካሁ | | አእመርክሙ/አእመርካሆሙ |
| | ተአምሮ/ተአምራሁ | | ተአምሮሙ/ተአምራሆሙ |
| | ታእምሮ/ታእምራሁ | | ታእምሮሙ/ታእምራሆሙ |
| | አእምሮ/አእምራሁ | | አእምሮሙ/አእምራሆሙ |
| ---- | አእመረካ/አእመርካሃ | --- | አእመርከን/አእመርካሆን |
| | ተአምራ/ተአምራሃ | | ተአምሮን/ተአምራሆን |
| | ታእምራ/ታእምራሃ | | ታእምሮን/ታእምራሆን |
| | አእምራ/አእምራሃ | | አእምሮን/አእምራሆን |
| አንቲ--- | አእመርኪዮ/አመርክዮ | --- | አእመርኪዮሙ/ክዮሙ |
| | ተአምሪዮ/ተአምርዮ | | ተአምራዮሙ/ተአምርዮሙ |
| | ታእምሪዮ/ታእምርዮ | | ታእምሪዮሙ/ታእምርዮሙ |
| | አእምሪዮ/አእምርዮ | | አእምሪዮሙ/አእምርዮሙ |
| ---- | አእመርኪያ/አእመርክያ | ---- | አእመርኪዮን/አእመርክዮን |
| | ተአምሪያ/ተአምርያ | | ተአምሪዮን/ተአምርዮን |
| | ታእምሪያ/ታእምርያ | | ታእምሪዮን/ታእምርዮን |

| | | |
|---|---|---|
| | አእምሪያ/አእምርያ | አእምሪዮን/አእምርዮን |
| አንትሙ-- | አእመርከምዎ | ---- አእመርከምዎሙ |
| | ተአምርዎ | ተአምርዎሙ |
| | ታእምርዎ | ታእምርዎሙ |
| | አእምርዎ | አእምርዎሙ |
| ---- | አእመርከምዋ | ---- አእመርከምዎን |
| | ተአምርዋ | ተአምርዎን |
| | ታእምርዋ | ታእምርዎን |
| | አእምርዋ | አእምርዎን |
| አንትን---- | አእመርከናሁ | ---- አእመርከናሆሙ |
| | ተአምራሁ | ተአምራሆሙ |
| | ታእምራሁ | ታእምራሆሙ |
| | አእምራሁ | አእምራሆሙ |
| --- | አእመርከናሃ | ----- አእመርከናሆን |
| | ተአምራሃ | ተአምራሆን |
| | ታእምራሃ | ተእምራሆን |
| | አእምራሃ | አእምራሆን |

ቀመር ፳..<u>ሦስተኛ መደብ ለአንደኛ(፫[ዩ] ለ፩[ዩ])</u>

ውእቱ--- አእመረኒ/አእመራኒ

የአምረኒ/የአምራኒ

ያእምራኒ[ተ]/ያእምራኒ[ላ]

--- አእመረነ/አእመራነ

የአምረነ/የአምራነ

ያእምረነ/ያእምራነ

ይእቲ--- አእመረተኒ --- አእመረተነ

ተአምረኒ ተአምራነ

ታእምረኒ ታእምረነ

ውእቶሙ--- አእመሩኒ ---- አእመሩነ

የአምሩኒ የአምሩነ

ያእምሩኒ ያእምሩነ

ውእቶን--- አእመራኒ --- አእመራነ

የአምራኒ የአምራነ

ያእምራኒ ያእምራነ

ቀመር ፺..<u>ሦስተኛ መደብ ለሁለተኛ መደብ(፫ዩ ለ፪ዩ )</u>

ውእቱ--- አእመረከ/አእመራከ

የአምረከ/የአምራከ

ያእምርከ/ያእምራከ

---- አእመረኪ/አእመራኪ

የአምረኪ/የአምራኪ

ያእምርኪ/ያእምራኪ

---- አእመረክሙ/አእመራክሙ

የአምረክሙ/የአምራክሙ

ያእመርክሙ/ያእምራክሙ

---- አእመረክን/አእመራክን

የአምረክን/የአምራክን

ያእመርክን/ያእምራክን

ይእቲ---- አእመረተከ --- አእመረተክሙ

ተአምረከ ተአምረክሙ

ታእመርከ ታእምርክሙ

---- አእመረተኪ --- አእመረተክሙ

| | | |
|---|---|---|
| | ተአምረኪ | ተአምራክን |
| | ታእምርኪ | ታእምርክን |
| ውእቶሙ--- | አእመሩከ | ---- አእመሩክሙ |
| | የአምሩከ | የአምሩክሙ |
| | ያእምሩከ | ያእምሩክሙ |
| | አእመሩኪ | አእመሩክን |
| | የአምሩኪ | የአምሩክን |
| | ያእምሩኪ | ያእምሩክን |
| ውእቶሙ---- | አእመራከ | አእመራሆሙ |
| | የአምራከ | የአምራሆሙ |
| | ያእመራከ | ያእመራሆሙ |
| | አእመራኪ | አእመራክን |
| | የአምራኪ | የአምራክን |
| | ያእምራኪ | ያእምራክን |

ቀመር ፯..<u>ሣስተኛ መደብ ለሣስተኛ መደብ(፫ዩ ለ፫ዩ)</u>

ውእቱ--- አእመሮ/አእመራሁ

የአምሮ/የአምራሁ

ያእምሮ/ያእምራሁ

አእመሮሙ/አእመራሆሙ

የአምሮሙ/የአምራሆሙ

ያእምሮሙ/ያእመራሆሙ

--- አእመረ/አእመራሃ

የአምራ/የአምራሃ

ያእምራ/ያእምራሃ

አእመሮን/አእመራሆን

የአምሮን/የአምራሆን

ያእምሮን/ያእመራሆን

| | | |
|---|---|---|
| ይእቲ---- | አእመረቶ | አእመረቶሙ |
| | ተአምሮ | ተአምሮሙ |
| | ተእምሮ | ታእምሮሙ |
| --- | አእመረታ | --- አእመረቶን |
| | ተአምራ | ተአምሮን |
| | ታእምር | ታእምሮን |
| ውእቶሙ--- | አእመርዎ | --- አእመርዎሙ |
| | የአምርዎ | የአምርዎሙ |
| | ያእምሮዎ | ያእምርዎሙ |
| --- | አእመርዋ | አእመርዎን |
| | የአምርዋ | የአምርዎን |
| | ያእምርዋ | የእምርዎን |
| ውእቶን--- | አእመራሁ | አእመራሆሙ |
| | የአምራሁ | የአምራሆሙ |
| | ያእምራሁ | ያእምራሆሙ |
| --- | አእመራሃ | አእመራሆን |
| | የአምራሃ | የአምራሆን |
| | ያእምራሃ | ያእምራሆን |

❖ አምስቱ አእማድ ማለት አድራጊ፣አስደራጊ፣አደራራጊ፣ተደራጊ እና ተደራራጊ ናቸው።

## የግዕዝ አርስቶች በአምስቱ አእማድ ቀለማት ሲገሰሱ

### ፩.አድራጊ አምድ

| ርእስ(ግሥ) | ፍች | ሰዋሰዋዊ ሙያ |
|---|---|---|
| ቀተለ | ገደለ | ኀ.አ |
| ይቀትል | ይገድላል | ትንአ. |
| ይቅትል | ይገድል ዘንድ | ዘአ. |
| ይቅትል | ይግደል | ት.አ |
| ቀቲል/ቀቲሎት | መግደል | ን.አ |
| ቀታሊ/ልያን | ገዳይ | ሣ.ቅ |
| ቀታሊት/ልያት | የምትገድል | አን.ቅ |
| ቀትል | ገድያ | ዘዘ. |
| ቀቲሎ/ሙ | ገድሎ | ቦአ. |
| ቀቲላ/ሎን | ገድላ | አን. |

### ፪.ተደራጊ አምድ

| | | |
|---|---|---|
| ተቀትለ | ተገደለ | ኀአ. |
| ይትቀተል | ይገደላል | ትንአ. |
| ይትቀተል | ይገደል ዘንደ | ዘአ. |
| ይትቀተል | ይገደል | ትአ. |
| ተቀትሎ/ተቀትሎት | መገደል | ንአ. |
| ቅቱል/ላን | የተገደለ | ሳቅ. |
| ቅትልት/ቱላት | የተገደለች | አን. |
| መቅትል/ላን | መግደያ መሰሪያ | ባዘ. |
| ምቅታል/ላት | መግደያ ቦታ | ባዘ. |

***፫.አስደራጊ አምድ***

| | | |
|---|---|---|
| አቅተለ | አስገደለ | ኀአ. |
| ያቀትል | ያስገድላል | ትንአ |
| ያቅትል | ያስገድል ዘንድ | ዘአ. |
| ያቅትል | ያስገድላል | ተአ. |
| አቅትሎ/አቅትሎት | ማስገደል | ንአ. |
| አቅታሊ/ልያን | አስገዳይ | ሣቅ. |
| አቅታሊት/ልያት | የምታስገድል | አን.ቅ |

***፬.ተደራጊ አምድ***

| | | |
|---|---|---|
| ተቃተለ | ተጋደለ | ኀአ. |
| ይትቃተል | ይጋደላል | ትንአ. |
| ይትቃተል | ይጋደል ዘንድ | ዘአ. |
| ይትቃተል | ይጋደል | ትአ. |
| ተቃትሎ/ተቃትሎት | መጋደል | ንአ. |
| ተቃታሊ(ልያን) | ተጋዳይ | ሣቅ. |
| ተቃታሊት | የምትጋደል | አን.ቅ. |

***፭.ሊደራጊ አምድ***

| | | |
|---|---|---|
| አስተቃተለ | አጋደለ | ኀአ. |
| ያስተቃትል | ያጋድላል | ትንአ. |
| ያስተቃትል | ያጋድል ዘንድ | ዘአ. |
| ያስተቃትል | ያጋድል | ትአ. |
| አስተቃትሎ/አስተቃትሎት | ማጋደል | ንአ. |
| አስተቃታሊ/ልያን | የሚያጋድል | ሣቅ. |
| አስተቃታሊት/ልያት | የምታጋድል | አን.ቅ. |
| መስተቃትል/ላን | አጋዳይ | ባቅ. |
| መስተቃትልት/ላት | የምታጋድል | አን.ቅ. |

***የቀደሰ እርባታ***

❖ <u>አድራጊ አምድ</u>

| <u>ርዕስ(ግሥ)</u> | <u>ፍች</u> | <u>ሰዋሰዋዊ ሙያ</u> |
|---|---|---|
| ቀደሰ | አመሰገነ | ኀአ. |
| ይቄድስ | ያመሰግናል | ትንአ. |
| ይቀድስ | ያመሰግን ዘንድ | ዘአ. |
| ይቀድስ | ያመስግን | ትአ. |
| ቀድሶ/ቀድሶት | ማመስገን | ንአ. |
| ቀዳሲ/ስያን | የሚያመሰግን | ሣቅ. |
| ቀዳሲት/ስያት | የምታመሰግን | አን.ቅ. |
| ቀዲሶ/ሙ | አመስግኖ | ቦአ. |
| መቅደስ | ማመስገኛ ቦታ | ባዘ. |
| ቅዳሴ | በቁሙ ምስጋና | ዘዘ. |
| ቅድስና | ቅዱስነት፣ንጽሕና | ምዘ |

❖ <u>ተደራጊ አምድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| ተቀደሰ | ተመሰገ | ኀአ. |
| ይትቄደስ | ይመሰገናል | ትንአ. |
| ይትቀደስ | ይመሰገን ዘንደ | ዘአ. |
| ይትቀደስ | ይመስገን | ትአ. |
| ተቀድሶ/ተቀድሶት | መመስገን | ንአ. |
| ቅዱስ(ሳን) | የተመሰገነ | ሳቅ. |
| ቅድስት/ዱሳት | የተመሰገነች | አን.ቅ. |
| ቅድሳት | ክብር፣መሥዋዕት | ምዘ. |

❖ <u>አስደራጊ አምድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| አቀደሰ | አስመሰገነ | ኀአ. |
| ያቄድስ | ያስመሰግናል | ትንአ. |
| ያቀድስ | ያመሰግን ዘንድ | ዘአ. |
| ያቀድስ | ያስመስግን | ትአ. |
| አቀድሶ/አቀድሶት | ማስመስገን | ንአ. |
| መቀድስ/ሳን | አስመስጋኝ | ሳቅ. |
| መቀድስት/ሳት | የምታስመሰግን | አን. |

❖ <u>ተደራጊ አምድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| ተቃደሰ | ተመሰጋገነ | ኀአ. |
| ይትቃደስ | ይመሰጋገናል | ትንአ. |
| ይትቃደስ | ይመሰጋገን ዘንድ | ዘአ. |
| ይትቃደስ | ይመሰጋገን | ትአ. |
| ተቃድሶ/ተቃድሶት | መመሰጋገን | ንአ. |
| ተቃዳሲ/ስያን | ተመሰጋገኝ | ሣቅ. |
| ተቃዳሲት/ስያት | ዝከ. | አን. |

❖ <u>አድራጊ አምድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| አስተቃደሰ | አመሰገነ | ኀአ. |
| ያስተቃድስ | ያመሰግናል | ትንአ. |
| ያስተቃድስ | ያመሰግን ዘንድ | ዘአ. |
| ያስተቃድስ | ያመሰግን | ትአ. |
| አስተቃድሶ/አስታቃድሶት | የመመስገን | ንአ. |
| አስተቃዳሲ/ስያን | የሚያመሰግን | ሣቅ. |
| አስተቃዳሲት/ስያት | የምታመሰግን | አን.ቅ |

## የተንበለ እርባታ

❖ <u>አድራጊ አምድ</u>

| ርዕስ | ፍች | ሰዋሰዋዊ ሙያ |
|---|---|---|
| ተንበለ | ለመነ | ኀአ. |
| ይተነብል | ይለምናል | ትንአ. |
| ይተንብል | ይለምን ዘንድ | ዘአ. |
| ይተንብል | ይለምን | ትአ. |
| ተንብሎ/ተንብሎት | መለመን | ንአ. |
| ተንባሊ/ልያን | ለማኝ | ሣቅ. |
| ተንባሊት/ልያት | የምትለምን | አን.ቅ. |
| መተንብል/ላን | የሚያላምን | አን.ቅ. |
| መተንብልት/ላት | የምታላምን | አን.ቅ. |
| ተንቢሎ | ለምኖ | ቦአ. |
| ተንባል/ላት | አማለጅ | ሳቅ. |
| ተንባላታዊ/ታይ | | ወቅ. |
| ትንባሌ | ልመና፣ምልጃ | ዘዘ. |

❖ <u>ተደራጊ አምድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| ተተንበለ | ተለመነ | ኀአ. |
| ይተነበል | ይለመናል | ትንአ. |
| ይተንበል | ይለመን ዘንድ | ዘአ. |
| ይተንበል | ይለመን | ትአ.. |
| ተተንብሎ/ተተንብሎት | መለመን | ንአ. |
| ትንቡል/ላን | የሚለመን | ሳቅ. |
| ትንብልት/ቡላን | የምትለምን | አን.ቅ. |
| ትንብልና | ልመና፣ምልጃ | ምዘ. |

❖ <u>አስደራጊ አምድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| አተንበለ | አስለመነ | ኀአ. |
| ያተነብል | ያስለምናል | ትንአ. |
| ያተንብል | ያስለምን ዘንደ | ዘአ. |
| ያተንብል | ያስለምን | ትአ. |
| አተንብሎ/አተንብሎት | ማስለመን | ንአ. |

| | | |
|---|---|---|
| አተንባሊ/ልያን | የሚያስለምን | ሣቅ. |
| አተንባሊት/ልያት | የምታስለምን | አንቅ. |

❖ ተደራጊ አምድ

| | | |
|---|---|---|
| ተተናበለ | ተለማመነ | ኀአ. |
| ይተናበል | ይለማመነናል | ትንአ. |
| ይተናበል | የለማመን ዘንድ | ዘአ. |
| ይተናበል | ይለማመን | ትአ. |
| ተተናብሎ/ተተናብሎት | መለማመን | ንአ. |
| ተተናባሊ/ልያን | ተለማማኝ | ሣቅ. |
| ተተናባሊት/ልያት | ዝ.ኮ | አንቀጽ |

❖ አደራጊ አምድ

| | | |
|---|---|---|
| አስተተናበለ | አላመነ | ኀአ. |
| ያስተተናብል | ያላምናል | ትንአ. |
| ያስተተናብል | ያላምን ዘንድ | ዘአ. |
| ያስተተናብል | ያላምን | ትአ. |
| አስተተናብሎ/አስተተናብሎት | ማላመን | ንአ. |

***የባረከ እርባታ***

❖ አድራጊ አምድ

| | | |
|---|---|---|
| ባረከ | በቁሙ መረቀ አመሰገነ | ኀአ. |
| ይባርክ | ይባርካል | ትንአ. |
| ይባርክ | ይባርክ ዘንድ | ዘአ. |
| ይባርክ | ይባርክ | ትአ. |
| ባርኮ/ባርኮት | መባረክ | ንአ. |
| ባራኪ/እያን | የሚባርክ | ሣቅ. |
| ባራኪት/እያት | የምትባርክ | አንቅ. |
| ባረኮ/ሙ | ባርኮ፣መርቆ | ቦአ. |
| ባሪካ/ኮን | መርቃ | ዝኮ. |

❖ ተደራጊ አምድ

| | | |
|---|---|---|
| ተባረከ | ተመረቀ፣ተባረከ | ኀአ. |
| ይትባረክ | ይመረቃል | ትንአ. |
| ይትባረክ | ይመረቅ ዘንደ | ዘአ. |
| ይትባረክ | ይመረቅ | ትአ. |
| ተባርኮ/ተባርኮት | መመረቅ | ንአ. |
| ቡሩክ/ካን | የተመረቀ | ሳቅ. |
| ቡርክት/ሩካት | የተመረቀች | አንቀ. |
| ቡራኬ | በቁሙ መባረክ | ዘዘ. |
| በረከት/ታት | መበርከት፣ማበርከት | ምዘ. |

❖ አዳራጊ አምድ

| | | |
|---|---|---|
| አስተባረከ | አባረከ፣አማረቀ | ኀአ. |
| ያስተባርከ | ያባርካል | ትንአ. |
| ያስተባርክ | ያባርክ ዘንድ | ዘአ. |
| ያስተባርክ | ያባርክ | ትአ. |
| አስተባርኮ/አስተባርኮት | ማባረክ | ንአ. |
| አስተባራኪ/እያን | አባራኪ | ሣቅ. |
| አስተባራኪት/እያት | የምታባርክ | አንቅ. |

***የማህረከ እርባታ***

❖ <u>አድራጊ አምድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| ማህረከ | ማረከ፣ዘረፈ | ኀአ. |
| ይማህርከ | ይማርካል | ትንአ. |
| ይማህርክ | ይማርክ ዘንድ | ዘአ. |
| ይማህርክ | ይማርክ | ትአ. |
| ማህርኮ/ማህርኮት | መማረክ | ንአ. |
| ማህራኪ/ኪያን | የሚማርክ | ሣቅ. |
| ማህራኪት/እያት | የምትማርክ | አንቅ. |

❖ <u>ተደራጊ አምድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| ተመህረከ | ተማረከ፣ተዘረፈ | ኀአ. |
| ይትመህረከ | ይማርካል | ትንአ. |
| ይትመህረክ | ይማርክ ዘንድ | ዘአ. |
| ይትመህረክ | ይማረክ | ትአ. |
| ተማህረኮ/ተማህረኮት | መማረክ | ንአ. |
| ምህሩክ/ካን | የተማረከ | ሳቅ. |
| ምህርክት/ሩካት | የተማረከች | አንቅ. |
| ምህርካ | ምርኮ፣ዘረፋ | ዘዘ. |

❖ <u>አስደራጊ አምድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| አማህርከ | አስማረከ | ኀአ. |
| ያመህርከ | ያስማርካል | ትንአ. |
| ያማህርክ | ያስማርክ ዘንድ | ዘአ. |
| ያማህርክ | ያስማርክ | ትአ. |
| አማህርኮ/አማህርኮት | ማስማረክ | ንአ.. |

❖ <u>አዳራጊ አምድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| _ አስተማህረከ | አማረከ፣አዛረፈ | ኀአ. |
| ያስተማህርከ | ያማርካል | ትንአ. |
| ያስተማህርክ | ያማርክ ዘንደ | ዘአ. |
| ያስተማህርክ | ያማርክ | ትአ. |
| አስተማርኮ/አስተማህርኮት | ማማረክ | ንአ. |

***የዴገነ እርባታ/ሴሰየ ማለት ነው/***

- <u>አድራጊ አምድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| ዴገነ | ተከተለ፣አባረረ | ኀአ. |
| ይዴግን | ይከተላል | ትንአ. |
| ይዴግን | ይከተል ዘንድ | ዘአ. |
| ይዴግን | ይከተል | ትአ. |
| ዴግኖ/ዴግኖት | መከተል | ንአ. |
| ዴጋኒ/ንያን | ተከታይ | ሣቅ |
| ዴጋኒት/ንያት | የምትከተል | አንቅ. |
| ዴግኖ | ተከትሎ | ቦአ. |
| ዴጋን | ቀስት ፣ደጋን | ዘዘ. |

- <u>ተደራጊ አምድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| ተዴገነ | ተከተለ | ኀአ. |
| ይትዴገን | ይከተላል | ትንአ. |
| ይትዴገን | ይከተል ዘንድ | ዘአ. |
| ይትዴገን | ይከተል | ትአ. |
| ተዴግኖ/ተዴግኖት | መከተል | ንአ. |
| ተዴጋኒ/ንያን | ተከታይ | ሣቅ. |
| ተዴጋኒት/ንያት | የምትከተል | ዝኮ. |

- <u>አስደራጊ አምድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| አዴገነ | አስከተለ | ኀአ. |
| ያዴግን | ያስከትላል | ትንአ. |
| ያዴግን | ያስከትል ዘንድ | ዘአ. |
| ያዴግን | ያስከተል | ትአ. |
| አዴግኖ | ማስተካከል | ንአ. |

***የከሀለ እርባታ***

- <u>አድራጊ አምድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| ከሀለ | ቻለ | ኀአ. |
| ይክሀል | ይችላል | ትንአ. |
| ይክሀል | ይችል ዘንደ | ዘአ. |
| ይክሀል | ይቻል | ትአ. |
| ክሂል/ክሂሎት | መቻል | ንአ. |
| ከሃሊ/ልያን | ቻይ፣ታገሽ | ሣቅ |
| ከሃሊት/ልያት | የምትችል | አንቅ. |

- <u>ተደራጊ አምድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| ተከሀለ | ተቻለ፣ተመቸ | ኀአ. |
| ይትከሀል | ይቻላል | ትንአ. |
| ይትከሀል | ይቻል ዘንድ | ዘአ. |

| | | |
|---|---|---|
| ይትክህል | ይቻል | ትአ. |
| ተክህሎ/ተክህሎት | መቻል | ንአ. |
| ክሁል/ላን | የተቻለ | ሣቅ. |
| ክህልት/ላት | የተቻለች | አንቅ. |

❖ <u>አስደራጊ አምድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| አክህለ | አስቻለ | ኀአ. |
| ያክህል | ያስችላል | ትንአ. |
| ያክህል | ያስችል ዘንድ | ዘአ. |
| ያክህል | ያስችል | ትአ. |
| አክህሎ/አክህሎት | ማስቻል | ንአ. |
| አክሃሊ/ልያን | የሚያስችል | ሣቅ. |
| አክሃሊት/ልያት | የምታስችል | አንቅ. |
| መክህል | የሚያስችል | ባቅ. |

❖ <u>ተዳራጊ አምድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| ተካህለ | ተቻቻለ | ኀአ. |
| ይትካህል | ይቻላል | ትንአ. |
| ይትካህል | ይቻቻል ዘንድ | ዘአ. |
| ይትካህል | ይቻቻል | ትአ. |
| ተካህሎ/ተካህሎት | መቻቻል | ንአ. |

❖ <u>አዳራጊ አምድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| አስተካህለ | አቻቻለ | ኀአ. |
| ያስተካህል | ያቻችላል | ትንአ. |
| ያስተክህል | ያቻችል ዘንድ | ዘአ. |
| ያስተክህል | ያቻችል | ትአ. |
| አስተካህሎ/አስተካህሎት | ማቻቻል | ንአ. |
| መስተካህል/ላን | የሚያቻችል | ባቅ. |

***የጦመረ እርባታ***

❖ <u>አድራጊ አምድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| ጦመረ | ጻፈ፣ተከተበ | ኀአ. |
| ይጦምር | ይጽፋል | ትንአ. |
| ይጦምር | ይጽፍ ዘንድ | ዘአ. |
| ይጦምር | ይጻፍ | ትአ. |
| ጦምሮ/ጦምሮት | መጻፍ | ንአ. |
| ጦማሪ/ርያን | የሚጽፍ | ሣቅ. |
| ጦማሪት/ርያት | የምትጽፍ | አንቅ. |
| ጦማር | ክታብ፣ደብዳቤ | ዘዘ. |

❖ <u>ተደራጊ አምድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| ተጦመረ | ተጻፈ፣ተከተበ | ኀአ. |

| | | |
|---|---|---|
| ይጦመር | ይጻፉል | ትንአ. |
| ይጦመር | ይጻፍ ዘንድ | ዘአ. |
| ይጦመር | ይጻፍ | ትአ. |
| ተጦምሮ/ተጦምሮት | መጻፍ | ንአ. |

❖ <u>ተዳራጊ አምድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| ተጡዋመረ | ተጻጻፈ | ኀአ. |
| ይጡዋመር | ይጻጻፉል | ትንአ. |
| ይጡዋመር | ይጻጻፍ ዘንድ | ዘአ. |
| ይጡዋመር | ይጻጻፍ | ትአ. |
| ተጡዋምሮ/ | መጻጻፍ | ንአ. |

❖ <u>አዳራጊ አምድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| አስተጡዋመረ | አጻጻፈ | ኀአ. |
| ያስተጡዋምር | ያጻጽፉል | ትንአ. |
| ያስተጡዋምር | ያጻጽፍ ዘንድ | ዘአ. |
| ያስተጡዋምር | የጻጽፍ | ትአ. |
| አስተጡዋምሮ/አስተጡዋምሮት | ማጻጻፍ | ንአ. |

❖ <u>አስደራጊ አምድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| አጦመረ | አጻጻፈ | ኀአ. |
| ያጦምር | ያጽፉል | ትንአ. |
| ያጦምር | ያጽፍ ዘንድ | ዘአ. |
| ያጦምር | የጽፍ | ትአ. |
| አጦምሮ/አጦምሮት | ማጻፍ | ንአ. |

## <u>ሥረይ ግሶች</u>

በቅርጻቸው(የግስ እግር) እና በእርባታቸው ስምንቱን አርእስተ ግሶች መስለው የምናገኛቸው ግሶች «ሠራዊት» በመባላቸው ተገቢ መሆኑን ካላይ ለማሳየት ሞክሬአለሁ።ይሁን አንጂ የማንቁርት ድምጾች/ንባበ ጉርዔ «ሐ፣ኀ እና ዐ»ከፊል አናባቢ ድምጾች (ወ፣የ)ወይም መሣግር ድምጾች (ሀ፣ረ፣አ፣ወ፣ዘ) በግሥ እርባታ ላይ በሚያመጡት ለውጥ ምክንያት በቅርጽ ወይም በእርባታ ለስምንት አለቆች የማይበዙ ግሶች አሉ።እነዚህ ግሶች እንደ ሠራዊት መቆጠር ስለሌለባቸው የእነሱ አምሳያ ለሆነው ጠቅላላ ግስም ምሳሌ ስለሆነ ሥረይ ግሶች የሚል ስያሜ ተሰጥቧቸዋል፡«ሥረይ»የሚለው ቃል በቅዱስ ያሬድ ጽዋትወ ዜማዎች የተለመደ ነው።ቀለል ባለ (ትውልዱ በሚገባው)ሌላ ምሳሌ በሀገራችን ባህላዊ የዘፈን ቅኝት «አምባሳል፣ባቲ፣ትዝታ፣አንቺ ሆዬ ለኔ»ሥራዮች ናቸው ማለት ይቻላል።ምክንያቱም የሙዚቃ እውቀት ያለው ሰው ሁሉ አንድ ሀገራዊ ዘፈን ሲሰማ «ይህ አምባሰል ፣ይህ የባቲ ቅኝት ነው»ብሎ ማለት ይቻላልና።በዚህ መጽሐፍ ሠላሳ ሰባት ሥረይ ግሶች አሉ።እነርሱም በስምንት አርእስት ሥር ተመድበው እርባታቸው እንደሚከተለው ቀርቧል።

***፮ በቀተለ ሥር የሚመደቡና የእርባታ አመል ያላቸው ሥረይ ግሶች***

| ሥረይ ግስ | ፍች | ሰዋሰዋዊ ሙያ |
|---|---|---|
| ሐተተ | መረመረ | ኃላፊ አንቀጽ |
| የሐትት | ይመረመራል | ትንቢት አንቀጽ |
| ይሕትት | ይመረመር ዘንድ | ዘንድ አንቀጽ |
| ይሕትት | ይመርመር | ትእዛዝ አንቀጽ |
| ሐቲት/ሐቲቶት | መመርመር | ንዑስ አንቀጽ |
| ሐታቲ/ሐታትያን | መርማሪ | ሣልስ ቅጽል |
| ሐታቲት/ትያት | የምትመረምር | አንስታይ ቅጽል |
| መሐትት | የሚያስመረምር | ባዕድ ቅጽል |
| ሐቲቶ/ሙ | መርምሮ | ቦዝ አንቀጽ |
| ሐተታ | ምርመራ ፣ፍተሻ | ዘመድ ዘር |

ደጊመ ድምጽ ያላቸው የ«ሐተተ»ዘሮች መድረሻ ድምፃቸውን ጐርደው ቅድመ መድረሻቸውን ያጠብቃሉ እርባታቸው ግን እንደ «ሐተተ»ነው ፡፡ምሳሌ፡-

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሐፀ | የሐፅፅ | ይሕፅፅ | ይሕፅፅ |
| ሐመ | የሐምም | ይሕምም | ይሕምም |

| | | |
|---|---|---|
| መሐለ | ማለ፣ተፈጠመ | ኀአ. |
| ይምሕል | ይምላል | ትንአ. |
| ይምሐል | ይምል ዘንድ | ዘአ. |
| ይምሐል | ይማል | ትአ. |
| ምሒል/ምሒሎት | መማል | ንአ. |
| መሓሊ/ልያን | የሚምል/ማይ | ሣቅ |
| ምሒሎ/ሙ | ምሎ | ቦአ. |
| መሐላ | ማላ፣ውሎ | ዘዘ. |
| ነቀወ | ጮኸ | ኀአ. |
| ይነቁ | ይጮሀል | ትንአ. |

| | | |
|---|---|---|
| ይንቁ | ይጮህ ዘንድ | ዘአ. |
| ይንቁ | ይጩኸ | ትአ. |
| ነቂው/ነቂዎት | መጮኸ | ንአ. |
| ነቃዊ/ውያን | የሚጮኸ | ሣቅ. |
| ነቃዊት/ውያት | የምትጮኸ | አን.ቅ. |
| ነቂዎ/ሙ | ጩኾ | ቦአ. |
| ንቃው | ጩኹት | ዘዘ. |

«ወ» እና «የ» የግስ መድረሻ ሲሆኑ በትንቢት፣በዘንድና በትዛዝ አናቅጽ ይጐርዳሉ።ያም ሆኖ ቅድመ መድረሻ እና መድረሻ ድምጻቸው ደጊመ ድምጽ ሲኖረው አይጐርድም።እሱም እንደሚከተለው ነው፡-

| | | |
|---|---|---|
| ከወወ | ቀለጠፈ፣ፈጠነ | ኀአ. |
| ይከውው | ይቀለጥፋል | ትንአ. |
| ይከውው | ይቀለጥፍ ዘንድ | ዘአ. |
| የከውው | ይቀልጠፍ | ትአ. |
| ከዊው/ከዊዎት | ቀልጥፎ | ንአ. |
| ከዊዎ/ሙ | ቀልጣፋ | ሳቅ. |
| ወሀበ | ሰጠ | ኀአ. |
| ይውህብ(ይሁብ) | ይሰጣል | ትንአ. |
| የሀብ | ይሰጥ ዘንድ | ዘአ. |
| የሀብ | ይስጥ | ትአ. |
| ውሂብ/ውሂቦት | መስጠት | ንአ. |
| ወሃቢ/ብያን | የሚሰጥ፣ሰጪ | ሣቅ. |
| ወሃቢት/ብያት | የምትሰጥ | አንቀ. |
| ወሁብ/ባን | የተሰጠ | ንቅ. |
| ወሂቦ/ሙ | ሰጥቶ | ቦአ. |
| ሀብት | በቁሙ ስጦታ | ዘዘ. |

/ወ/ የግስ መነሻ ሲሆን በዘንድና በትእዛዝ ይጐርዳል፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ወረደ | ወረደ፣ተወረደ | ኀአ. |
| ይወርድ | ይወርዳል | ትንአ. |
| ይረድ | ይወርድ ዘንድ | ዘአ. |
| ይረድ | ይውረድ | ትአ. |
| ወሪድ/ወሪዶት | መውረድ | ንአ. |
| ወራዲ/ድያን | የሚወርድ፣ወራጅ | ሣቅ. |
| ወራዲት/ድያት | የምትወርድ | አን. |
| ርደት | መውረድ፣አወራረድ | ሳዘ. |
| ወሪዶ/ሙ | ወርዶ | ቦአ. |
| ወርድ | ስፋት፣ጐን | ዘዘ. |

ገብረ ፣ቅድመ መድረሻው ሳድስ ድምጽ የሆነ ግስ

| | | |
|---|---|---|
| ገብረ | አደረገ፣ሠራ | ኃአ. |
| ይገብር | ያደርጋል | ትንአ. |
| ይግበር | ይደረግ ዘንድ | ዘአ. |
| ይግበር | ያድርግ | ትአ. |
| ገቢር/ገቢሮት | ማድረግ | ንአ. |
| ገባሪ/ያን | አድራጊ | ሣቅ. |
| ገባሪት/ርያት | የምታደረግ | አን. |
| ግቡር/ራን | የተደረገ | ሳቅ. |
| ግብረት | ማድረግ ፣መሥራት | ሳዘ. |
| ገቢሮ/ሙ | አድርጎ | ቦአ. |
| ግብር | ሥራ፣ተግባር | ዘዘ. |
| ገብር | አገልጋይ፣ረዳት | ስም. |
| ምግባር/ተግባር | በቁሙ ሥራ | ባዘ. |

ሜመ«ሠየመ»በማለት ፈንታ (የ) ን ጐርዶ ባለሁለት እግር የሆነ ግስ ነው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሜመ | ሾመ | ኃአ. |
| ይሠይም | ይሾማል | ትንአ. |
| ይሚም | ይሾም ዘንድ | ዘአ. |
| ይሚም | ይሹም | ትአ. |
| ሠይም/ሥይምት | መሾመ | ንአ. |
| ሠያሚ | ሹዋሚ | ሣቅ. |
| ሥዩም/ማን | የተሾመ | ሳቅ. |
| ሠይም | ሹም | ቦአ. |
| ሢመት | ሹመት | ሞዘ. |
| ምሥያም | መሾሚያ | ባዘ. |

ቆመ«ቀወመ» በማለት ፈንታ (ወ) ን ጐርዶ ሁለት እግር ያለው ግስ፡-

| | | |
|---|---|---|
| ቆመ | ቆመ፣ተነሳ | ኀአ. |
| ይቀውም | ይቆማል | ትንአ. |
| ይቁም | ይቆም ዘንደ | ዘአ. |
| ይቁም | ይቁም | ትአ. |
| ቀዊም/ቀዊሞት | መቆም | ንአ. |
| ቀዋሚ/ምያን | የሚቆም | ሣቅ. |
| ቀዋሚት/ምያት | የምትቆም | አንቅ. |
| ቅውም/ማን | የቆመ | ሳቅ. |
| ቁመት | መቆም | ሳዝ. |
| ቀዊሞ/ሙ | ቁሞ | ቦአ. |
| ተቅዋም | መቅረዝ፣ማብሪያ | ባዘ. |
| ምቅዋም | መቆሚያ | ባዘ. |

*፪.በቀደሰ ሥር የሚመደቡና የእርባታ አመል ያላቸው ሥረይ ግሶች።*

| <u>ሥርይ ግስ</u> | <u>ፍች</u> | <u>ሰዋሰዋዊ ሙያ</u> |
|---|---|---|
| ለበወ | አስተዋለ | ኀአ. |
| ይሌቡ | ያስተውላል | ትንአ. |
| ይለቡ | ያስተውል ዘንድ | ዘአ. |
| ይለቡ | ያስተውል | ትአ. |
| ለብዎ/ለብዎት | ማስተዋል | ንአ. |
| ለባዊ/ውያን | የሚያስተውል | ሣቅ. |
| ለባዊት/ዋን | የምታስተውል | አንቅ. |
| ልባዌ | አስተዋይ | ሳቅ. |
| ልቡና | አስተውሎት | ዘዘ. |
| መለብው | ዝኮ. | ምዘ. |
| ለቢዎ/ሙ | የሚያስተውል | ቦአ. |
| ልብ | በቁሙ | |

| | | |
|---|---|---|
| ሰብሐ | አመሰገነ | ኀአ. |
| ይሴብሕ | የመሰግናል | ትንአ. |
| ይሰብሕ | ያመሰግን ዘነድ | ዘአ. |
| ይሰብሕ | ያመስግን | ትአ. |
| ሰብሖ/ሰብሖት | ማመስገን | ንአ. |
| ሰባሒት/ሕያት | አመስጋኝ | ሣቅ. |
| ስቡሕ/ሐን | የምታመሰግን | አንቅ. |
| ስብሕት/ቡሐት | የተመሰገነች | ዘዘ. |
| ስባሔ | ማመስገን | ቦአ. |
| ሰቢሖ/ሙ | አመስግኖ | ቦአ. |

| | | |
|---|---|---|
| ስብሐት | ምሥጋና፣ክብር | ሞዘ. |
| ተወከለ | ታመነ | ኀአ. |
| ይትዌከል | ይታመናል | ትንአ. |
| ይትወከል | ይታመን ዘንድ | ዘአ. |
| ይትወከል | ይታመን | ትአ. |
| ተወክሎ/ተወክሎት | መታመን | ንአ. |
| ዉኩል/ላን | የሚታመን | ሳቅ. |
| ተወኪሎ/ሙ | ታምኖ | ቦአ. |
| ትውክልት | እምነት | ሞዘ. |
| ሐለየ | አሰበ | ኀአ. |
| ይሔሊ | ያስባል | ትንአ. |
| የሐሊ | ያስብ ዘንድ | ዘአ. |
| የሐሊ | ያስብ | ትአ. |
| ሐልዮ/ሐልዮት | ማሰብ | ንአ. |
| ሐላዪ/ይያን | አሳቢ | ሣቅ. |
| ሕሉይ/ያን | የታሰበ | ሳቅ. |
| ሐልዮ/ሙ | አስቦ | ቦአ. |
| ሕሊና | ኀሳብ | ሞዘ. |
| ነገለገ | ተሰበሰበ | ኀአ. |
| ያንጌልግል | ይሰበሰባል | ትንአ. |
| ያንገልግ | ይሰበሰብ ዘነድ | ዘአ. |
| ያንገልግ | ይሰብሰብ | ትአ. |
| ነገልጎ/ነገልጎት | መሰብሰብ | ንአ. |
| ነገላጊ | የሚሰበስብ | ሣቅ. |
| ነገሊጎ/ሙ | ተስብስቦ | ዘዘ. |

*፫.በተንበለ ሥር የሚመደቡ ሥረይ ግሶች*

| ሥረይ ግስ | ፍች | ሰዋሰዋዊ ሙያ |
|---|---|---|
| ቀበያውበጠ | ቀላወጠ | ኀአ. |
| ይቀበያወበጥ | ይቀላውጣል | ትንአ. |
| ይቀበያውብጥ | ይቀላውጥ ዘንድ | ዘአ. |
| ይቀበያውብጥ | ይቀላውጥ | ትአ. |
| ቀበያውብጦ/ቀበያውብጦት | መቀላወጥ | ንአ. |
| ቀበያውባጢ/ጥያን | ቀላዋጭ/ጮች | ሣቅ. |
| ቀበያውባጢት/ጥያት | ቀለዋጭ | አንቅ. |
| ቀበያውቢጦ/ሙ | ቀላውጦ | ቦአ. |
| ቀንጦሰጠ | ተሰለፈ | ኀአ. |
| ይቀነጦስጥ | ይሰለፋል | ተንአ. |
| ይቀነጦስጥ | ይሰለፍ ዘንድ | ዘአ. |
| ይቀነጦስጥ | ይሰለፍ | ትአ. |
| ቀንጦስጦ/ቀንጦስጦት | መሰለፈ | ንአ. |
| ቀንጦሳጢ/ጥያን | ተሰላፊ፣ሰልፈኛ | ሣቅ. |
| ቀንጦሳጢት/ጥያት | የምትሰለፍ | አንቅ. |
| ቀንጦሲጦ/ሙ | ተሰልፎ | ቦአ. |
| አስፌድለወ | ቆጠቆጠ | ኀአ. |
| ያስፌደሉ | ይቆጠቁጣል | ትንአ. |
| ያስፌድሉ | ይቆጠቁጥ ዘንድ | ዘአ. |
| ያስፌድሉ | ይቆጥቁጥ | ትአ. |
| አስፌድልዎ/አስፌድልዎት | መቆጥቆጥ | ንአ. |
| አስፌድላዊ/ውያን | የሚቆጠቁጥ | ሣቅ. |
| አስፌድላዊት/ውያት | የምትቆጠቁጥ | አንቅ. |

| | | |
|---|---|---|
| አስፌድሊዎ/ሙ | ቆጥቁጦ | በአ. |
| ዜርዜርቀ | ነፋ፣አበጠረ | ኀአ. |
| ይዜረዚቅ | ይነፋል | ተንአ. |
| ይዜርዚቅ | ይነፋ ዘንድ | ዘአ. |
| ይዜርዚቅ | ይንፋ | ትአ. |
| ዜርዚቆ/ዜርዚቆት | መንፋት | ንአ. |
| ዜርዚያቂ/ቅያን | የሚነፋ፣ነፊ | ሣቅ. |
| ዜርዚያቂት/ቅያት | የምትነፋ | አንቅ. |
| ዜርዜቅ | ወንፊት፣የወርቅ ሀብል | ዘዘ. |
| ዜርዚቆ | ነፍቶ | ቦአ. |
| ጸምሐየ | ጠወለገ፣ደረቀ | ኀአ. |
| ይጸመሒ | ይጠወልጋል | ትንአ. |
| ይጸምሒ | ይጠወልግ ዘንደ | ዘአ. |
| ይጸምሒ | ይጠውልግ | ትአ. |
| ጸምሕዮ/ጸምሕዮት | መጠውለግ | ንአ. |
| ጽምሑይ/ያን | የተጠወለገ፣ጠውላጋ | ሳቅ. |
| ጽምሕይት/ሀያት | የጠወለገች | አንቅ. |
| ጸምሒዮ | ጠውል | ቦአ. |

### ፬.በባረከ ሥር የሚመደቡ ሥርይ ግሶች

| <u>ሥርይ ግስ</u> | <u>ፍች</u> | <u>ሰዋሰዋዊ ሙያ</u> |
|---|---|---|
| ሣቀየ | አሰቃየ፣አስጨነቀ | ኀአ. |
| ይሣቂ | ያሰቃያል | ትንአ. |
| ይሣቂ | ያሰቃይ ዘንድ | ዘአ. |
| ይሣቂ | ያሰቃይ | ትአ. |
| ሣቅዮ/ሣቅዮት | ማሰቃየት | ንአ. |

| | | |
|---|---|---|
| ሣቃዩ/ይያን | የሚያሰቃይ | ሣቅ. |
| ሣቀዩት/ይያት | የምትሰቃይ | አንቅ. |
| ሥቅይት/ቁያት | የተሰቃየች | አንቅ. |
| ሣቅዮ | አሰቃይቶ | ቦአ. |
| ሥቃይ | ጭንቅ፣መከራ | ዘዘ. |

| | | |
|---|---|---|
| ፃመወ | ጭንቅ ፣መከራ | ኀአ. |
| ይፃሙ | ደከመ፣ታከተ | ትንአ. |
| ይፃሙ | ይደከም ዘንድ | ዘአ. |
| ይፃሙ | ይድከም | ትአ. |
| ፃምዎ/ፃምዎት | መድከም | ንአ. |
| ፃማዊ(ውያን) | የሚደክም | ሣቅ. |
| ፃማዊት/ውያት | የምትደክም | አንቅ. |
| ፃሚዋ/ው | ለፍቶ | ቦታ. |
| ፃማ | ልፋት፣ጥረት | ዘዘ. |

### ፭. በማህረከ ሥር የሚመደቡ ሥረይ ግሶች

| | | |
|---|---|---|
| ሰካዕለዋ | ቆጠቆጠ | ኀአ. |
| ይሰካዓሉ | ይቆጠቁጣል | ትንአ. |
| ይሰካዕሉ | ይቆጠቁጥ ዘንድ | ዘአ. |
| ይሰካዕሉ | ይቆጥቁጥ | ትአ. |
| ሰካዕለዊ/ውያት | መቆጥቆጥ | ንአ. |
| ሰካዕሊዊ/ውያት | የሚቆጠቁጥ | አንቅ. |
| ሰካዕሊዋ | ቆጥቁጦ | ቦአ. |

| | | |
|---|---|---|
| ጻሕየየ | አረመ፣አጠራ | ኀአ. |
| ይጻሓይይ | ያርማል | ትንአ. |
| ይጻሕይይ | ያርም ዘንድ | ዘአ. |

| | | |
|---|---|---|
| ይጻሕይይ | ያርም | ትአ. |
| ጻሕይዮ/ጻሕይዮት | ማረም | ሣቅ. |
| ጻሕያዪ/ይያን | የሚያርም | አንቅ. |
| ጻሕያይት/ይያት | የምታርም | ሣቅ. |
| ጽሕዩይ/ያን | የታረመ | ሳቅ. |
| ጽሕይይት/ዩያት | የታረመች | አንቅ. |
| ጽሕያይ | አረም፣አራሙቻ | ዘዘ. |
| ጻዕደወ | ነጣ፣ጠራ፣በራ | ኀአ. |
| ይጸዓዱ | ይነጣል | ትንአ. |
| ይጸዕዱ | ይነጣ ዘንድ | ዘአ. |
| ይጸዕዱ | ይንጣ | ትአ. |
| ጻዕድዋ/ጻዕድዋት | መንጣት | ንአ. |
| ጻዕዳዊ/ውያን | የሚነጣ | ሣቅ. |
| ጻዕዳዊት/ውያት | የምትነጣ | አንቅ. |
| ጽዕድው/ዋን | የነጣ | ሳቅ. |
| ጽዕዱት/ድዎት | የነጣች | አንቅ. |
| ጽዕዳዌ | ንጣት /መጥራት | ዘዘ. |
| ጸዐዳ/ጸዐድዓድ | ነጭ/ነጭማ/ነጫጭ | ቅ. |
| ጻዕዲዎ/ሙ | ነጭ ሆኖ | ቦአ. |
| ጻዕዲዋ/ዋን | ነጭ ሆኖ | ዘከ. |

***፮ በዴገነ/ሴሰየ ሥር የሚመደቡ ሥረይ ግሶች***

| | | |
|---|---|---|
| አቅዜዘየ | ቅዝዘ አለ | ኀአ. |
| ያቅዜዚ | ቅዝዝ ይላል | ትንአ. |
| ያቅዜዚ | ቅዝዝ ይል ዘንድ | ዘአ.. |
| ያቅዜዚ | ቅዝዝ ይበል | ትአ. |

| | | |
|---|---|---|
| አቅዜዝዮ/አቅዜዝዮት | ቅዝዝ ማለት | ንአ. |
| አቅዜዛዪ/ይያን | ቅዝዝ የሚል | ሣቅ |
| አቅዜዛዪት/ይያት | ቅዝዝ የምትል | አንቅ. |
| አቅዜዝዮ/ሙ | ቅዝዝ ብሎ | ቦአ. |
| አንጌገየ | ተቅበዘበዘ | ኀአ. |
| ያንጌጊ | ይቅበዘበዛል | ትንአ. |
| ያንጌጊ | ይቅበዘበዝ ዘንድ | ዘአ.. |
| ያንጌጊ | ይቅበዝበዝ | ትአ. |
| አንጌግዮ/አንጌግዮት | መቅበዝበዝ | ንአ. |
| አንጌጋዪ/ይያን | የሚቅበዘበዝ | ሣቅ. |
| አንጌጋይት/ይያት | የምትቅበዘበዝ | አንቅ. |
| እንጊጉይ/ያን | የተቅበዘበዘ | ሳቅ. |
| እንጊጉይት/ያት | የተቅበዘበዘች | አንቅ. |
| አንጌግዮ/ሙ | ተቅበዝብዞ | ቦአ. |
| አንጌግያ/ያን | ተቅበዝብዛ | ዝኮ. |

ከዚህ በታች ያሉት ሥረይ ግሶች የትንቢት ዘንድ እና ትእዛዝ አንቀጽ በቅርጽ አንድ ሆነው በመጥበቅና በመላለት ነው የሚለዩ።የትንቢታቸው መድረሻ ድምጽ ይጠብቃል ዘንድ እና ትእዛዛቸው ይላላል።

| | | |
|---|---|---|
| ዜነወ | ነገረ ፣አወራ | ኀአ. |
| ይዜኑ | ያወራል | ትንአ. |
| ይዜኑ | ያወራ ዘንድ | ዘአ. |
| ይዜኑ | ያውራ | ትአ. |
| ዜንዎ/ዜንዎት | ማውራት | ንአ |
| ዜናዊ/ውያን | ነጋሪ ወሬኛ | ሣቅ. |
| ዜናዊት/ውያት | የምታወራ | አንቅ. |
| መዜንው/ዋን | ዝኮ | ባቅ. |

| | | |
|---|---|---|
| መዜንውት | ዝከ. | ዘከ. |
| ዜና | በቁሙ፣ወሬ | ዘዘ. |
| ዜንዎ/ሙ | አውርቶ | ቦአ |

| | | |
|---|---|---|
| ጌገየ | በደለ፣ሳተ | ኀአ. |
| ይጌጊ | ይበድላል | ትንአ. |
| ይጌጊ | ይበድል ዘንድ | ዘአ. |
| ይጌጊ | ይበድል | ትአ. |
| ጌግዮ/ጌግዮት | መበደል | ንአ. |
| ጌጋዪ/ይያን | በዳይ/የሚበድል | ሣቅ. |
| ጊጉይ/ያን | የተበደለ | አን. |
| ጊግይት/ጉያት | የተበደለች | ዝኮ. |
| ጌጋይ | ስህተት፣በደል | ዘዘ. |
| ጌግዮ/ሙ | በድሎ | ቦአ. |

## ፷ በከህለ ሥር የሚመደቡ ሥርይ ግሶች

| | | |
|---|---|---|
| ስሕወ | ተሳበ፣ተጐተተ | ኀአ. |
| ይስሑ | ይስባል | ትንአ. |
| ይስሐው | ይሳብ ዘንደ | ዘአ. |
| ይስሐው | ይሳብ | ትአ. |
| ስሒው/ስሒዎት | መሳብ | ንአ. |
| ስሐዊ/ውያን | የሚሳብ | ሣቅ. |
| ስሐዊት/ውያት | የምትሳብ | አን. |
| ስሕው | የጉም ሽንት ካፊያ | ዘዘ. |
| ስሒዎ | ተስቦ፣ተጎትቶ | ቦአ. |

| | | |
|---|---|---|
| ጥዕየ | ዳነ፣ተፈወሰ | ኀአ. |
| ይጥዒ | ይድናል | ትንአ. |

| | | |
|---|---|---|
| ይጥዓይ | ይድን ዘንድ | ዘአ. |
| ይጥዓይ | ይዳን | ትአ. |
| ጥዕይ/ጥዕዮት | መዳን | ንአ. |
| ጥዑይ/ያን | የዳነ | ሳቅ. |
| ጥዕይት/ዑያት | የዳነች | ዝኮ. |
| ጥዒና | ጤና፣ደህንነት | ዘዘ. |
| ጥዕዮ/ሙ | ድኖ | ቦአ. |
| ጥዕያ/ዎን | ድኖ | ዝኮ. |

***፰.በጠመረ ሥር የተመደቡ ሥረይ ግሶች***

| | | |
|---|---|---|
| ሎለወ | ጠበሰ፣ለበለበ | ኀአ. |
| ይሎሉ | ይጠብስ | ትንአ. |
| ይሎሉ | ይጠብስ ዘንድ | ዘአ. |
| ይሎሉ | ይጥበስ | ትአ. |
| ሎልዋ/ሎልዎት | መጥበስ | ንአ. |
| ሎላዊ/ውያን | የሚጠብስ፣ጠባሽ | ሣቅ. |
| ሎላዊት/ውያት | የምትጠብስ | አንቅ. |
| ሎሊዋ/ሙ | ጠብሶ | ቦአ. |
| ሞርቅሐ | ላጠ | ኀአ. |
| ይሞረቅሕ | ይልጣል | ትንአ. |
| ይሞርቅህ | ይልጥ ዘንድ | ዘአ. |
| ይሞርቅህ | ይላጥ | ትአ. |
| ሞርቅሖ/ሞርቅሖት | መላጥ | ን አ. |
| ሞርቃሒ/ሒያን | የሚልጥ | ሣቅ. |
| ሞርቃሒት/ሒያት | የምትልጥ | አንቅ. |
| አልኆሰሰ | ሹክ አለ | ኀአ. |

| | | |
|---|---|---|
| ያልኖስስ | ሹክ ይላል | ትንአ. |
| ያልኖስስ | ሹክ ይል ዘንድ | ዘአ. |
| ያልኖስስ | ሹክ ይበል | ትአ. |
| አልኖስሶ/አልኖስሶት | ሹክ ማለት | ንአ. |
| አልኖሳሲ/ስያን | አሾከሹዋኪ | ሣቅ. |
| አልኖሳሲት/ስያት | ሹክ የምትል | አንቅ. |
| ለኖሳስ | ቀስታ፣ሹክሹክታ | ዘዘ |
| አልኖሲሶ/ሙ | ሹክ ብሎ | ቦአ. |
| አልኖሲሳ/ሶን | ሹክ ብላ | ዝኮ. |
| አከሞሰሰ | ፈገገ፣ፈገግ አለ | ኀአ. |
| ያከሞስስ | ይፈጋል | ትንአ. |
| ያከሞስስ | ይፈግ ዘንድ | ዘአ. |
| ያከሞስስ | ይፍገግ | ትአ. |
| አከሞስሶ/አከሞስሶት | መፍገግ | ንአ. |
| አከሞሳሲ/ስያን | የሚፈግ | ሳቅ. |
| አከሞሳሲት/ስያት | የምትፈግ | አንቅ. |
| አከሞሲሶ/ሙ | ፈገግ ብሎ | በአ. |
| ኀርየመ | አገመ፣አከመ | ኀአ. |
| ይኀረይም | ያግማል | ትንአ. |
| ይኀረይም | ያግም ዘንድ | ዘአ. |
| ይኀርይም | ይገም | ትአ. |
| ኀርይሞ/ኀርይሞት | ማገም | ንአ. |
| ኀሬም | ዋገምት | ዘዘ. |
| ኀርይሞ/ሙ | አግሞ | ቦአ. |
| ኀርይማ/ሞን | አግማ | ዘከ. |

## <u>አንቀጽን የሚስብ አንቀጽ(ይቤ)</u>

- ዐበይት አናቅጽን እንደ ስም የሚስብ አንቀጽ ወይም ዐበይት አናቅጽን እንደ ዐቢይ አገባብ ከማሠሪያነት የሚያስቀር አንቀጽ ይህም አንቀጽ ከነዘራዝርቱ «ይቤ» ነው።
- «ይቤ»የ«ቤለ» ካልአይ አንቀጽ ነው እንጅ «ይቤ» እራሱን የቻለ ቀዳማይ አንቀጽ አይደለም ።«ይብል»የሚለውም የ«ብሐለ»ካልአይ አንቀጽ ነው። እንጂ የ«ይቤ» ካልአይ አንቀጽ አየደለም።
- አገሳሰሱም ---ቤለ ይቤ ይብል ይበል

ብህለ  ይብል ይብሀል ይብሀል ነው የሚሉ ሊቃውንት አሉ ነበሩ።

- በመጽሐፍ ውስጥ «ይቤን»እንደ ቀዳማይ አንቀጽ አድርገው ይብል ደግሞ እንደ ካልአይ አንቀጽ የሚተረጉሙ።ምሳሌ፡-ይቤ መጽሐፍ «ብላዕበሐፈ ገጽከ »በላብህ ብላ »አለ መጽሐፍ ይብል መጽሐፍ።«ዘቦ ክልኤ ክዳናት የሀብ አሐደ»«ሁለት ልብስ ያለው አንዱን ይሰጥ»ይላል መጽሐፍ።
- ከዚህ በመቀጠል የይቤ እርባታ ከዐሥር መራሕያን አንጻር እንመለከታለን።

<u>አንደኛ መደብ</u> ፡-እቤ---አልሁ

እብል---እላለሁ/እያልሁ

እበል---እል ዘንድ

እበል---ልበል

ንቤ---አልን

ንብል---እንበል

ንበል---እንል ዘንድ

ንበል---እንበል

<u>ሁለተኛ መደብ</u>፡- ትቤ---አልክ  ትቤሊ---አልሽ

ትብል---ትላለህ  ትብሊ---ትያለሽ

ትበል---ትል ዘንድ  ትበሊ---ትይ ዘንድ

በል---በል  በሊ---በይ

ትቤሉ---አላችሁ  ትቤላ---አለችሁ

ትብሉ---ትላላችሁ  ትብላ---ትላላችሁ

ትበሉ---ትሉ ዘንድ　　በላ---በሉ

በሉ----በሉ

<u>**ሦስተኛ መደብ**</u>፡-ይቤ---አለ　　ትቤ---አለች

ይብል---ይላል　　ትብል---ትላለች

ይበል---ይል ዘንድ　　ትብል---ትል ዘንድ

ይበል---ይበል　　ትበል---ትበል

ይቤሉ---አሉ　　ይቤላ---አሉ

ይብሉ---ይላሉ　　ይብላ---ይላሉ

ይበሉ----ይበሉ　　ይብላ---ይሉ ዘንድ

ይበላ---ይበሉ

❖ ሰማኒያው መደብ የ«ይቤ»እርባታ /በዐሥሩ መራሕያን ተውላጠ ስሞች ሲዘምት

<u>**፩.፩ᵖ ለ፪ᵖ መደብ፡-**</u>

<u>አነ</u> እቤለከ---አልሁህ　　እቤለኪ---አልሁሽ

እብለከ--እልሃለሁ　　እብለኪ---እልሻለሁ

እበልከ---እልህ ዘንድ　　እበልኪ---እልሽ ዘንድ

እበልከ---ልበልህ　　እበልኪ---ልበልሽ

እቤለክሙ---አልኋችሁ　　እቤለክን---አልኋችሁ

እብለክሙ---እላችሁ አለሁ　　እብለክን---እለችሁ አለሁ

እበልክሙ---እላችሁ ዘንድ　　እበልክን---እላችሁ ዘንድ

እበልክሙ---ልበላችሁ　　እበልክን---ልበላችሁ

<u>ንህነ</u>፡- ንቤለከ---አልንህ　　ንቤለኪ---አልንሽ

ንብለከ---እንልሃለን　　ንብለኪ---እንልሻለን

ንበልከ---እንበልህ ዘንድ　　ንበልኪ---እንልሽ ዘንድ

ንበልከ---እንበልህ　　ንበልኪ---እንበልሽ

ንቤለክሙ---አልናችሁ　　ንቤለክን---አልናችሁ

ንብለክሙ---እንላችሁ አለን        ንብለክን---እንላችሁ አለን

ንበልክሙ---እንላችሁ ዘንድ        ንበልክን---እንላችሁ ዘንድ

ንበልክሙ---እንበላችሁ        ንበልክን---እንበላችሁ

**፪..፩ዩ ለ፫ዩ መደብ**

አነ....እቤሎ---አልሁት        እቤለ---አልኋት

እብሎ---እለዋለሁ        እብላ---እላታለሁ

እበሎ---እለው ዘንድ        እበላ---እላት ዘንድ

እበሎ---ልበለው        እብላ---ልበላት

እቤሎሙ---አልኋቸው        እቤሎን---አልኋቸው

እብሎሙ---እላቸዋለሁ        እብሎን---እላቸዋለሁ

እበሎሙ---እላቸው ዘነድ        እበሎን---እላቸው ዘንድ

እበሎሙ---ልበላቸው        እበሎን---ልበላቸው

ንህነ፡-ንቤሎ---አልነው        ንቤላ---አልናት

ንብሎ---እንለዋለን        ንብላ---እንላታለን

ንበሎ---እንለው ዘንድ        ንበላ---እንላት ዘንድ

ንበሎ---እንበለው        ንበላ---እንበላት

ንቤሎሙ---አልናቸው        ንቤለክን---አልናቸው

ንብሎሙ---እንላቸዋለን        ንብለክን---እንላቸዋለን

ንበሎሙ---እንላቸው ዘንድ        ንበልክን---እንላቸው ዘንድ

ንበሎሙ---እንበላቸው        ንበልክን---እንበላቸው

**፫..፪ዩ ለ ፩ዩ መደብ**

አንተ..ትቤለኒ---አልኸኝ        አንቲ..ትቤልኒ---አልሽኝ

ትብለኒ---ትለኛለህ        ትብልኒ---ትይኛለሽ

ትበለኒ----ትለኝ ዘንድ        ትበልኒ---ትይኝ ዘንድ

በለኒ----በለኝ        በልኒ---በይኝ

| | |
|---|---|
| ትቤለነ---አልኸን | ትቤልነ---አልሽን |
| ትብለነ---ትለናለህ | ትብልነ---ትይናለሽ |
| ትበለን---ትለን ዘንድ | ትበልነ---ትይን ዘንድ |
| በለነ---በለን | በልነ---በይን |
| አንትሙ..ትቤሉኒ---አላችሁኝ | አንትን..ትቤለኒ---አላችሁ |
| ትብሉኒ---ትሉኛላችሁ | ትብለኒ---ትሉኛላችሁ |
| ትበሉኒ---ትሉኝ ዘንድ | ትበሊኒ---ትለኝ ዘንድ |
| በሉኒ---በሉኝ | በለኒ---በሉኝ |
| ትቤሉነ---አላችሁን | ትቤለነ---አላችሁን |
| ትብሉነ---ትሉናላችሁ | ትብለነ---ትሉናላችሁ |
| ትበሉነ---ትሉን ዘንድ | ትበለነ---ትሉን ዘንድ |
| በሉነ---በሉን | በለነ---በሉን |

**፬..፪ዩ ለ ፫ዩ መደብ**

| | |
|---|---|
| አንተ..ትቤሎ---አልኸው | ትቤላ---አልኸት |
| ትብሎ---ትለዋለህ | ትብላ---ትላታለህ |
| ትበሎ---ትለው ዘንድ | ትበላ---ትላት ዛንድ |
| በሎ---በለው | በላ---በላት |
| ትቤሎሙ----አልኋቸው | ትቤሎን---አልኸቸው |
| ትብሎሙ---ትላቸዋለህ | ትብሎን---ትላቸዋለህ |
| ትበሎሙ---ትላቸው ዘንድ | ትበሎን---ትላቸው ዘንድ |
| በሎሙ---በላቸው | በሎን---በላቸው |
| አንቲ..ትቤልዮ---አልሽው | ትቤሊያ---አልሻት |
| ትብሊዮ---ትይዋለሽ | ትብሊያ---ትያታለሽ |
| ትበሊዮ---ትይው ዘንድ | ትበሊያ---ትያት ዘንድ |
| በሊዮ---በይው | በሊያ---በያት |

ትቤሊዮሙ---አልሻቸው　　ትቤሊዮን---አልሻቸው

ትብሊዮሙ---ትያቸዋለሽ　　ትብሊዮን---ትያቸዋለሽ

ትብሊዮሙ---ትያቸው ዘንድ　　ትብሊዮን---ትያቸው ዘንድ

በሊዮሙ---በያቸው　　በሊዮን---በያቸው

አንትሙ.. ትቤልዎ---አላችሁት　　ትቤልዋ---አላችኋት

ትብልዎ---ትሉታላችሁ　　ትብልዎ---ትሏታላችሁ

ትብልዎ---ትሉት ዘንድ　　ትብልዋ---ትሏት ዘንድ

በልዎ---በሉት　　በልዋ---በሏት

ትቤልዎሙ---አላችሁአቸሁ　　ትቤልዎን---አሏችኋቸው

ትበልዎ---ትሉት ዘንድ　　ትበልዋ---ትሏት ዘንድ

በልዎ---በሉት　　በልዋ---በሏት

አንትን.. ትቤላሁ---አላችሁት　　ትቤላሃ---አላችኋት

ትብላሁ---ትሉታላችሁ　　ትብላሀ---ትሏታላችሁ

ትብላሁ---ትሉት ዘንድ　　ትበላሃ---ትሏት ዘንድ

በላሁ---በሉት　　በላሃ---በሏት

ትቤላሆሙ---አላችኋቸው　　ትቤላሆን---አላችኋቸው

ትብላሆሙ---ትሏቸዋላችሁ　　ትብላሆን---ትሏቸዋላችሁ

ትበላሆሙ---ትሏቸው ዘንድ　　ትበላሆን---ትሏቸው ዘንድ

በላሆሙ---በሏቸው　　በላሆን---በሏቸው

**፩..፫ᵉ ለ ፩ᵉ መደብ**

ውእቱ..ይቤለኒ---አለኝ　　ይእቲ..ትቤለኒ---አለችኝ

ይብለኒ---ይለኛል　　ትብለኒ---ትለኛለች

ይበለኒ---ይለኝ ዘንድ　　ትበለኒ---ትለኝ ዘንድ

ይበለኒ---ይበለኝ　　ትበለኒ---ትበለኝ

ይቤለነ---አለን　　ትቤለነ---አለችኝ

ይብለነ---ይለን ትብለነ---ትለኛለች

ይበለነ---ይለን ዘንድ ትበለነ---ትለን ዘንድ

ይበለነ---ይበለን ትበለነ---ትበለን

ውእቶሙ.. ይቤሉኒ---አሉኝ ውእቶን.. ይቤላኒ---አሉኝ

ይብሉኒ---ይሉኛል ይብለኒ---ይሉኛል

ይበሉኒ---ይሉኝ ዘንድ ይበላኒ---ይሉኝ ዘንድ

ይበሉኒ---ይበሉኝ ይበለኒ---ይበሉኝ

ይቤሉነ---አሉን ይቤለነ---አሉን

ይብሉነ---ይሉናል ይብለነ---ይሉናል

ይበሉነ---ይሉን ዘንድ ይበለነ---ይሉን ዘንድ

ይበሉነ---ይበሉን ይበለነ---ይበሉን

**፮..፫ᵉ ለ ፪ᵉ መደብ**

ውእቱ..ይቤለከ---አለህ ይቤለኪ---አለሽ

ይብለከ---ይልሀል ይብለኪ---ይልሻል

ይበልከ---ይልህ ዘንድ ይበልኪ---ይልሽ ዘንድ

ይበልከ---ይበልህ ይበልኪ---ይበልሽ

ይለክሙ---አላችሁ ይቤለክን---አላችሁ

ይብለክሙ---ይላችኋል ይብለክን---ይላችኋል

ይበልክሙ---ይላችሁ ዘንድ ይበልክን---ይላችሁ ዘንድ

ይበልክሙ---ይበላችሁ ይበልክን---ይበላችሁ

ውእቶሙ.. ይቤሉከ---አሉህ ይቤሉከ---አሉሽ

ይብሉከ---ይሉኃል ይብሉኪ---ይሉሻል

ይበሉከ---ይሉህ ዘንድ ይበሉኪ---ይሉሽ ዘንድ

ይበሉከ---ይበሉህ ይበሉኪ---ይበሉሽ

ይቤሉክሙ---አሏችሁ ይቤሉክን---አሏችሁ

ይበሉክሙ---ይሏችሁ ዘንድ    ይበሉክን---ይሏችሁ ዘንድ

ይበሉክሙ---ይበሏችሁ    ይበሉክን---ይበሏችሁ

ይእቲ..    ትቤለከ---አለችህ    ትቤለኪ---አለችሽ

ትብለከ---ትልሀለች    ትብለኪ---ትልሻለች

ትበልከ---ትልህ ዘንድ    ትበልኪ---ትልሽ ዘንድ

ትበልከ---ትበልህ    ትበልኪ---ትበልሽ

ትቤለክሙ---አለቻችሁ    ትቤለክን---አለቻችሁ

ትብለክሙ---ትላችኋለች    ትብልክን---ትላችሁ አለች

ትበልክሙ---ትላችሁ ዘንድ    ትበልክን---ትላችሁ ዘንድ

ትበልክሙ---ትበላችሁ    ትበልክን---ትበላችሁ

ውእቶን.. ይቤለከ---አሉህ    ይቤለኪ---አሉሽ

ይብለከ---ይሉኃል    ይብለኪ---ይሉሻል

ይበለከ---ይሉህ ዘንድ    ይበለኪ---ይሉሽ ዘንድ

ይበለከ---ይበሉህ    ይበለኪ---ይበሉሽ

ይቤላክሙ---አሏችሁ    ይቤለክን---አሏችሁ

ይብለክሙ---ይሏችኋል    ይብለክን---ይሏችኋል

ይበለክሙ---ይሏችሁ ዘንድ    ይበለክን---ይሏችሁ ዘንድ

ይበለክሙ---ይበሏችሁ    ይበለክን---ይበሏችሁ

**፺..፫ኛ ለ ፫ኛ መደብ**

ውእቱ..  ይቤሎ---አለው    ይቤላ---አላት

ይብሎ---ይለዋል    ይብላ---ይላታል

ይበሎ---ይለው ዘንድ    ይበላ---ይላት ዘንድ

ይበሎ---ይበለው    ይበላ---ይበላት

ይቤሎሙ---አላቸው    ይቤሎን---አለችው

ይብሎሙ---ይላቸዋል    ይብሎን---ይላቸዋል

| | | |
|---|---|---|
| | ይበሎሙ---ይላቸው ዘንድ | ይበሎን---ይላቸው ዘንድ |
| | ይበሎሙ---ይበላቸው | ይበሎን---ይበላቸው |
| ውእቶሙ.. | ይቤልዎ---አሉት | ይቤልዎ---አሏት |
| | ይብልዎ---ይሉታል | ይብልዎ---ይሏታል |
| | ይበልዎ---ይሉት ዘንድ | ይበልዎ---ይሏት ዘንድ |
| | ይበልዎ---ይበሉት | ይበልዎ---ይበሏት |
| | ይቤልዎሙ---አሏቸው | ይቤልዎን---አሏቸው |
| | ይብልዎሙ---ይሏቸዋል | ይብልዎን---ይሏቸዋል |
| | ይበልዎሙ---ይሏቸው ዘንድ | ይበልዎን---ይሏቸው ዘንድ |
| | ይበልዎሙ---ይበሏቸው | ይበልዎን---ይበሏቸው |
| ይእቲ.. | ትቤሎ---አለችው | ትቤለ---አለቻት |
| | ትብሎ---ትለዋለች | ትብላ---ትላታለች |
| | ትበሎ--ትለው ዘንድ | ትበላ---ትላት ዘንድ |
| | ትበሎ---ትበለው | ትበላ---ትበላት |
| | ትቤሎሙ---አለቻቸው | ትቤለሆን---አለቻቸው |
| | ትብሎሙ---ትላቸዋለች | ትብለሆን---ትላቸዋለች |
| | ትብሎሙ---ትላቸው ዘንድ | ትበለሆን---ትላቸው ዘንድ |
| | ትበሎሙ---ትበላቸው | ትበለሆን---ትበላቸው |
| ውእቶን.. | ይቤላሁ---አሉት | ይቤላሃ---አሏት |
| | ይብላሁ---ይሉታል | ይብላሃ---ይሏታል |
| | ይበላሁ---ይሉት ዘንድ | ይበላሃ---ይሏት ዘንድ |
| | ይበላሁ---ይበሉት | ይበላሃ---ይበሏት |
| | ይቤላሆሙ---አሏቸው | ይቤላሆን---አሏቸው |
| | ይብላሆሙ---ይሏቸዋል | ይብላሆን---ይሏቸዋል |
| | ይበላሆሙ---ይሏቸው ዘንድ | ይበላሆን---ይሏቸው ዘንድ |

ይበላሆሙ---ይበሏቸው ይበላሆን---ይበሏቸው

## አመላተ ሰዋስው

ሕግን የሚጐርዱ/የሚጥሉ ፊደሎችን የሚጐርዱ የመጀመሪያ ፊደልን የሚያወጡ ናቸው።እነዚህም አራት ፊደላት ናቸው።

| | |
|---|---|
| አ | ወ |
| ሀ | የ |

***፩.የ«ሀ» እና የ«አ» አመል***

«አ»እና «ሀ» ንኡስ አንቀጽን ቀቲል ከፊል ይል የነበረውን በመካከል እየተገኙ መነሻውን ሳድስ ፊደል ሳድስ ድምጽ ያደርጋሉ።

| | |
|---|---|
| ወሀበ | ውሂብ/ውሂቦት |
| ወዐለ | ውዒል/ውዒሎት |
| ሰዓለ | ስዒል/ስዒሎት |
| መሐለ | ምሒል/ምሒሎት |

የተሰመረባቸው ፊደላት ወደሳድስ መለወጣቸውን ልብ ይሏል።

የእነዚህ ግሶች እና መሠሎቻቸው አርእስታቸው/ቤታቸው «ቀተለ» ነው ንዑስ አንቀጽ ደግሞ ቀቲል/ቀቲሎት ነው ከዚህ ላይ የተሠመረበትፊደል ግዕዝ መሆኑን ያስተውሉ።ከላይ ያሉት ወደሳድስ የተለወጡበት ምክንያት የ አ እና የ ሀ አመል ስላላቸው ነው።

- «ሀ» እና «አ» በመካከል ሲገቡ የቀዳማይ አንቀጽን መነሻ ራብዕ፣ሳድስ ፊደል ያደርጋሉ።
  ምሳሌ፡-ተሣሐለ
  ተላአለ
  ብህለ
- «ሀ» ኦና «አ» የጥሬ ዘርን መነሻ ራብእ ያደርጋሉ፡፡
  ምሳሌ፡-ከሀለ---ባህል
  ስእነ----ሳእን
  ቀደሰ----ቅዳሴ
  ባረከ----ቡራኬ } ሕጉን የሚያፈርሱ ግሶች እንዳሉ የሚያመለክቱ ናቸው።
- «ሀ» እና «አ» በግስ መድረሻ እየተገኙ የግሱን መሐል ሳድስ ያደርጋሉ፡፡

| ምሳሌ፡- | | |
|---|---|---|
| በልዐ | ጸርሐ | ቀንዐ |
| ከልሀ | መርሐ | |
| ወግአ | ኰርሐ | |

ከዚህ ላይ የተጠቀሱት ምሳሌዎች ቤታቸው/አርእስታቸው «ቀተለ» ነው፡፡የቀተለ ደግሞ ሦስቱም ፊደላት ግዕዝ ናቸው ግን በ«ሀ» እና በ«አ» አመል ምክንያት መሐል ፊደላቸው ወደ ሳድስ ተለወጠ።**አስታውሱ፡**-ጥሬ ዘር ማለት ባለቤት ፣ተሳቢ፣ተናባቢ ሊሆን የሚችል በራብዕ፣በኃምስ እና በሳብዕ ሊደርስ የሚችል ነው።

ምሳሌ፡-ፍግዓ ቅዳሴ መሰንቆ

ምምዓ ቡራኬ ከበሮ

ደብተራ ስባሔ

***፪.የ«ወ» አመል***

በካእብና በሳብዕ ይደርሳል።

በቀዳሚ አንቀጽ በመካከል ይገኝ የነበረ«ወ» መነሻውን ሳብዕ በማድረግ ይቀራል።

ምሳሌ፡-ቀወመ ቆመ

ሐወረ ሖረ

በመደረግ አመል ያለ ግስን /ተግባር ግስን /መድረሻ በትንቢት እና በትእዛዝ አንቀጽ ሳብዕ ያደርጋል።

ምሳሌ፡-ተፈነወ----ይትፌነው

ተሰፈወ----ይሴፈው የተሰመረባቸው ፊደላት ሳድስ ናቸው።

ተፈነወ---ይትፌኖ

ተስረወ---ይሴፎ የተሰመረባቸው ፊደላት ሳብዕ ናቸው።

በተደራራጊ እና በተደራጊ አመል ግን ሊቀጥል እንደ ሚችል ልብ በል።

ይትፌነው

ይሴፈው

ሳብዕ እንዲሆን ያደረገው በመጨረሻ ላይ «ወ» ስላለ ነው።

በማድረግ አመል ያለ ግስን /ገቢር ግስን/መድረሻ በትንቢት በትእዛዝ ካዕብ ያደርጋል።

ምሳሌ፡-ሀለወ----ይሄልው *ይሄሉ (4 ጊዜ)

ፈነወ----ይፌንው *ይፌኑ (2) ይፈኑ (2)

ነቀወ----ይነቅው *ይነቁ፣ይንቁ (2)

ለበወ---ይለብው *ይሌቡ (4)

ከላይ «*» ምልክት የተደረገበት በማንኛውም ሰዓት አገልግሎት አይሰጥም ማለትም ከላይ በመደረግ ላየ ያለ ግስን እንደ ተመለከትነው ማለት ነው።

የወንድ ሳድስ ውስጠዘ ቅጽልን መካከሉ ካዕብ ይሆን የነበረውን ሳድስ ያደርጋል።

ምሳሌ፡-ፈነወ ----ፍኑው * ፍንው

ከወወ----ክውው *ክውው

የሴት ሳድስ ውስጠዘ ቅጽል መካከሉ ሳድስ ይሆን የነበረውን ካዕብ ያደርጋል።

ምሳሌ፡-ሠርገወ----ሥርግውት * ሥርጉት (የተሸለመች)

የ«ወ» ግስ የሴት ሳድስ ውስጠዘ ቅጽል በሙሉ በዚህ መንገድ ይሄዳል ማለት ነው።

በሳቢ ዘር መነሻ ሳድስ ይሆን የነበረውን ካዕብ አድርጐ ይናገራል።

ምሳሌ፡-ዖደ----ዐወደ---ዕውደት* ዑደት +

ሖረ----ሐወረ--ሕውረት* ሑረት +

ቆመ----ቀወመ--ቀውመት * ቁመት +

«ወ» በደጊመ ቃል ከመጣ አይጐርድም

ምሳሌ፡- ከወወ---ይከውው

---ይክውው

---ይክውው

***፫.የ«የ» አመል***

በኃምስና በሳብዕ መጉረድ ልማዱ ነው።

በቀዳማይ አንቀጽ መሀል ላይ ይገኝ የነበረው «የ»ቀርቶ መነሻውን ኃምስ ያደርጋል።

ምሳሌ፡-ጸገየ---ጽጊት/ጽግይት

ሠየመ---ሤመ

አየለ---ዔለ

«የ»በመድረሻ ላይ ሲገኝ በትንቢት እና በትእዛዝ አንቀጽ በሣልስ ይጐርዳል።

ምሳሌ፡-ሴሰየ----ይሴሲ (4)

----ይሴስይ *

ሰነየ----ይሴኒ (4)

----ይሴንይ *

በከየ----ይበኪ (4)

----ይበክይ *

በአንድ ግስ ላይ «የ» በተደጋጋሚ ቢገኝ ልክ እንደወ አጐርድም ።

በቦዝ አንቀጽ መካከሉ ሣልስ ይሆን የነበረውን ሳድስ ያደርጋል፤

ምሳሌ፡- ሴሰየ---ሴሲዮ *

---ሴስዮ + ይህም ማለት ቦዝ አንቀጹን እና ንዑስ አንቀጹን/አርእስት/አንድ ያደርጋል፡፡ሴስዮ/ሴስዮት፥ንዑስ መዝገብ

አስተውሉ፡-የደጊመ ቃል ሲያወጣ አይጎርድም።

ምሳሌ፡-የሕየየ---ይየሀይይ

---ይየሕይይ

«የ»የሴት ሳድስ መስም ውስጠዘ ቅጽል መካከል ሳድስ ይሆን የነበረውን ሣልስ ያደርጋል።

ምሳሌ፡-ኅረየ--ኃራይት *

---ኅርየት + የተመረጠች

ጸረየ---ጽርይት *

ጽሪት + የጠራች

የ«የ» ን ግስ በዚህ መሠረት ተመለከት

*ዐሥራው ቀለማት፡*-- በእርባታ ጊዜ ከቀዳማይ አንቀጽ ቀጥሎ በካልአይ፣ በትዕዛዝ አንቀጽ፣ በዘንድ አንቀጽ በመነሻ ላይ/በቅድመ መነሻ ላይ የሚገኙ ባዕዳን ቀለማት ዐሥራው ቀለማት ይባላል።የአንቀጽ ሥሮች ማለት ነው።ቀለማቱም ተ፣አ፣የ፣ነ ናቸው።

| | |
|---|---|
| የ---ለውእቱ | ተ---ለይእቲ |
| ለእሙንቱ | ለአንተ ለአንትሙ |
| ለእማንቱ | ለአንቲ ለአትን |
| አ--- ለአነ | ነ--- ለንህነ |

ምሳሌ፡- ቀተለ--ይቀትል ቀተሉ---ይቀትሉ ቀተላ---ይቀትላ

| | | | |
|---|---|---|---|
| የ፡- | ይቅትል | ይቅትሉ | ይቅትላ |
| | ይቅትል | ይቅትሉ | ይቅትላ |

ተ፡- ቀተለት---- ትቀትል

ትቅትል

ትቅትል

ቀተልከ----ትቀትል ቀተልክሙ----ትቀትሉ

ትቅትል--ዘንድ ትቅትሉ

ቅትል--ትዕዛዝ ቅትሉ--ትዕዛዝ

ቀተልኪ---- ትቀትሊ ቀተልክን--- ትቀትላ

ትቅትሊ ትቅትላ

ቅትሊ ቅትላ

ዐሥራው በቅርብ መደቦች ሲነገሩ በትዕዛዝ አንቀጽ ላይ ተነጥለው ተለይተው ይቀራሉ ይሻሻሉ፡ማለትም

ቅትል ቅትሊ ቅትሉ እና ቅትላ

አ፡-ቀተልኩ---እቀትል

እቅትል

እቅትል

ነ፡-ቀተልነ--- ንቀትል

ንቅትል

ንቅትል

## የዐሥራው ቀለማት ሕጐች

፩.«ሀ» ወይም «አ» በመነሻና በመካከል በሌሉባቸው ግሶች ዐሥራው ቀለማት ፍጹም ሳድስ ይሆናሉ።

ምሳሌ፡-ቀተለ--ይቀትል መጽአ---ይመጽእ

ይቅትል ይምጻእ

ይቅትል ይምጻእ

ቀድሐ--- ይቀድሕ

ይቅዳሕ

ይቆዳሕ

የ«ሀ» እና የ«አ» ከዘሮቻቸው ጋር በመጨረሻ ሲመጡ ሳድስ የመሆን ችሎታ አላቸው፡፡

፪. «ሀ» ወይም «አ» በመነሻ ያሉባቸው ባለ ዓራት ፊደላት ግሶች ዐሥራው ቀለማት ፍጹም ግዕዝ ይሆናሉ፡፡

ምሳሌ፡--ሀይመነ----የሀየምን (2) የሀይምን (2)

አንዘራ----የአነዝር (2) የአንዝር (2)

ሀርበደ----የሀረብድ (2) የሀርብድ (2)

፫. ባለ ሁለት እና ሦስት ፊደላት ግሶች «ሀ» ወይም «አ» መነሻ ሲሆኑ ዐሥራው ቀለማት በትንቢት ግዕዝ ፣በትእዛዝ ሳድስ ይሆናሉ፡፡

ምሳሌ፡- ኤመ---የአይም ይኢም

የአይም ይኢም

ሄበ--- የሀይብ ኀረየ----የኀሪ

ይሂብ ይህረይ

ይሂብ ይህረይ

ሖረ--- የሀውር ሐተተ--- የሀትት

ይሁር ይህትት

ይሁር ይህትት

፬.በመካከል «ሀ» ወይም «አ» የተገኙበት ግስ በትንቢት ሳድስ ፣በትዕዛዝ ግእዝ ይሆናሉ፡፡

ምሳሌ፡- ወሀበ---ይሁብ

የሀብ

የሀብ

- መሀሉ የጠበቀ ፍጹም ግዕዝ ሦስት ቀለማት የሆነ ግስ በ«ሀ» በ«አ» ሲነሳ በትንቢት ሳድስ ፣በትእዛዝ/ዘንድ/ ግዕዝ ይሆናል፡፡

ምሳሌ፡- ኀየለ----ይኄይል አመረ---ይኤምር

የኀይል የኣምር

የኀይል የኣምር

ዐሠየ----ይዔሲ

የዓሲ

የዓሲ

❖ ላልቶ ፍጹም ግዕዝ ሦስትለው ቀለማት የሆነ ግስ በ«አ» ሲነሳ «ሀ» ሲከተለው ሳድስና ግዕዝ ይሆናል።ማለትም ትዕዛዝ ሳደስ ዘንድ ግዕዝ ማለት ነው።

አኀዘ---ይእኀዝ

የአኀዝ(ቆጥር)

የአኀዝ

❖ በ«ወ» ወይም «ው» የትነሣ ሦስት ቀለማት የሆነ ግስ «ሀ» ወይም «አ» በመካከሉ ያሉበት ግስ በትንቢት ሳድስ ፣በዘንድ እና ትእዛዝ ግእዝ ይሆናል።

ምሳሌ፡-ወሀበ----ይውህብ ውሕዘ----ይውህዝ

የሃብ የሃዝ

የሃብ የሃዝ

ወዐለ---- ይውዕል ውሕጠ----ይውሕጥ

የዓል የሃጥ

የዓል የሃጥ

❖ «አ» ን «እ» ሲከተለው በትንቢት ግዕዝ እና በዘንድ ራብዕ ሆነው የመናገር ጠባይ አላቸው ።

ምሳሌ፡-አእመረ----የአምር

ያእምር

ያእምር

፫.«አ» ፣«አስተ»፣«አን» የሚባሉ ባዕድ ፊደላት በመነሻ ላይ ሲጨመሩ ዐሥራው ቀለማት ራብዕ ሆነው ይነገራሉ።

ምሳሌ፡-አቅተለ----ያቀትል

ያቅትል

ያቅትል

አስተሀቀረ---ያስተሀቅር (አጥብቅ)

ያስተሀቅር(አላላ)

ያስተሀቅር

አንገለገ-----ያንጌልግ

ያንገልግ

ያንገልግ

አንቀልቀለ---ያንቀለቅል

ያንቀልቅል

ያንቀልቅል

አስተቃተለ--- ያስተቃትል

ያስተቃትል

ያስተቃትል

አቅተለት---- ታቀትል

ታቅትል

ታቅትል

**ቱሱሐን እርባታ**

«ቶስሐ» ጨመረ ፣ደባለቀ፣ቀላቀለ ከሚለው የግዕዝ ግስ የወጣ ሲሆን የግስ እርባታን ወደ ተለያዩ ግሶች የማቀያይሩ የሚለውጡ ናቸው፡፡በዚህም ውስጥ ዓምስት ነጥቦችን እናያለን።

፩.የቀተለን ፣የባረከን እና የከህለን ተገብሮ የመሰሉ በእርባታ ጊዜ ፍጹም የቀደሰን አካሔድ ይሔዳሉ።

ምሳሌ፡-ተዐወረ/ቀተለ ቤት ተልዕለ/ክህለ

ተዋነየ/ባረከ ቤት ተሥዕለ/ክህለ

ተዝህረ/ክህለ ቤት ተጽዕረ/ክህለ

ተኀየየ/ቀተለ ቤት

ተወዐረ---ይትዌዐር ተልዕለ---ይትሌዐል

ይትወዐር ይትለዐል

ይትወዐር ይትለዐል

ተዝኀረ---ይዜኅር ተሥዕለ---ይሤዐል

ይዘኅር ይሠዐል

ይዘኅር ይሠዐል

ተዋነየ--- ይትዌነይ ተኀየየ---- ይትኄየይ

ይትዋነይ ይትኀየይ

ይትዋነይ ይትኀየይ

፪.ወረወ፣ፀዐለ፣ወጠነ፣ገረመ፣ን የመሳሰሉ ግሶች በኃላፊ የ«ቀተለን»በትንቢት የ«ቀደሰ»ን ከዚያ በታች የ«ቀተለን»አካሔድ ይሔዳሉ።

ምሳሌ፡-ወረወ---ይዌሩ ወጠነ---ይዌጥን

ይውሩ ይውጥን

ይውሩ ይውጥን

ፀዐለ--- ይፄዐል ገረመ--- ይጌርም

ይፅዓል ይግርም

ይፅዓል ይግርም

፫.ጠፈረ፣ጸፈረ፣የመሣሰሉት ግሶች በኃላፊ የቀደሰን ፣በትንቢት የቀተለን በዘንድ እና ትዕዛዝ የቀደሰን ከዚያ በታችም ቀደሰን አካሔድ ይሔዳሉ።

ምሳሌ፡-ጠፈረ---ይጠፍር---ቀተለ

ይጠፍር
ይጠፍር } ቀደሰ

ጠፍሮ/ጠፍሮት---ቀደሰ

ጸፈረ---- ይጸፍር---ቀተለ

ይጸፍር
ይጸፍር
ጸፍሮ/ጸፍሮት } ቀደሰ

፬.«ወገረ» ፣«መሐረ»ን የመሳሰሉ ግሶች በኃላፊ ፍጹም የቀተለን ሲሆን በአንድ ቃል ሁለት ነገር እየፈቱ በመጀመሪያው የቀደሰን በሁለተኛው ፍች ደግሞ የቀተለን እርባታ አካሔድ ይሔዳሉ።

ምሳሌ፡-መሀረ መሐረ---ይምሕር ?

ይሜህር ይምሐር ?

ይምህር ይምሐር ?

ይምህር

ወገረ---ይዌግር ስህተ----ይስህት/ሳተ

ይገር/ይውግር ይስሐት

ይገር/ይውግር ይስሐት

ወገረ--- ይወግር
ይውግር
ይውግር } ቀተለ

ሥኀተ---ይሤህት/አሣረፈ

ይሥኀት

ይሥኀት

ቀስመ----ይቴስም                ቀርበ/ቀረበ---ይቀርብ

ይቀስም                ይቅርብ

ይቀስም                ይቅርብ

ቀስመ---ይቀስም

ይቅስም

ይቅስም

ቀረበ/ቆረበ---ይቴርብ

ይቀርብ

ይቀርብ

ወሀከ---ይዌህክ        ወሀከ---ይውህክ

የሀክ        የሀክ

የሀክ        የሀክ

ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው ግሶች መካከል የተወሰኑት መሣግር የላቸውም /የቀተለ ወደ ቀደሰ የቀደሰ ወደ ቀተለ መረማመድ አይችሉም

፫.በአንድ ቃል ሁለት እየፈቱ በመጠበቅ የቀደሰን በማላላት የቀተለን የሚሆኑ ግሶች አሉ።

ምሳሌ፡-መልሐ/አጣፈጠ        መልሐ/መዘዘ

ሰብሐ/አመሰገነ        ሠብሐ/ሰብ ሆነ ሰባ

ሰበከ/ጣዖት ሠራ        ሰበከ/አስተማረ

ፈጸመ/ጨረሰ        ፈጸመ/ዘጋ ለጎመ

ሐለየ/አሰበ        ኀለየ/ዘመረ

ሠርሐ/አቅናና፡አሠለጠነ        ሠርሐ/ደከመ

መሰለ/ምሳሌ ሰጠ        መሰለ/መሰለ

| | |
|---|---|
| ጸብሐ/ቀረጥ ቀረጠ | ጸብሐ/ነጋ |
| መከረ/ፈተነ | መከረ/መከረ |
| ጸለለ/ጋረደ | ጸለለ/ተንሳፈፈ |
| ነስሐ/ተጸጸተ | ነሥሐ/ሸተተ |

በ፫ኛው ትዕዛዝ ላይ የተቀመጡ ግሶች በቤታቸው /በቀደሰና በቀተለ ቤት/መሠረትነት ግሰስ።

## <u>ተመኩሳይያን/ሞግሾዎች</u>

፩.በምሥጢር የማይገናኙ በየራሳቸው የቆሙ ሲሆን አድራጊ አስደራጊ የመሰሉ ተመኩሳይያን ናቸው።

በሌላ አገላለጽ በንባብ አንድ ሆነው በዐውደ ንባብ  የሚለያዩ ናቸው።

ምሳሌ፡-  ሠርሐ--ሠራ    ፡በእንተ እለ ይሠርሑ ትባርክ ፍሬ ምድሮሙ ።

ሠርሐ--አቅናና   ፡አርትሕ ተሠራሕ ።

ርእየ--አየ     ፡አሥተርአ በሥጋ ሰብእ።

ራዐየ--ጠበቀ    ፡ራዐይኬ አባግዕየ።

ኀለየ--ዘፈነ፣አመሰገነ     ፡ምሕረተ ወፍትሐ አኀሊ ለከ።

ሐለየ---አሰበ   ፡ አሕለይኪዮሙ ይምጽኡ ኀቤኪ።

፪.አንድ ቃል ሁነው በመጠበቅ እና በመላለት ለውጥ የሚያመጡ ናቸው።

ምሳሌ፡-ይሜርሐከ እግዚአብሔር ፍናዊከ/ያከናውንልሐል።

ሠርሐ---አቅናና   ፡ ይሜርሐከ በኩሉ ግብርከ።

ሠርሐ--ሠራ      ፡ይሠርሕ  እስከ ያገርር ተያፊኒሁ።

፫.በአንድ ድምጽ ተነበው በብዙ የሚፈቱ ናቸው፡

ምሳሌ፡-ለስሐ (በ፰)

ኮነ(በ፺)

ወደየ(በ፫)   ይፈታሉ።

፬.ከአገባብ ፣ከዘር ፣ከነባር የሚገኙ በንባብ አንድነት  በነገር ልዩነት ያላቸው  ናቸው።

፮.በእርባታ ጊዜ ፍጹም አንድ የሚሆኑ በአወጣጥ በምሥጢር አንድ የማይሆኑ ።

ምሳሌ፡-<u>ውእቱ  ይእቲን ሲዘረዝር</u>

አእመራ /አወቃት

የአምራ /ያውቃታል

ያዕምራ/ያውቃት ዘንድ

ያዕምራ/ይወቃት

ውእቶን ሲያውቁ

አእመራ/እነርሱ ሴቶች አወቁ

የአምራ/ እየአወቁ ነው

ያዕምራ/ያውቁ ዘንድ

ያዕምር/ይወቁት

ምሳሌ፡-ኢይመውት --አልሞትም

አይሞትም

ኢትመውት---አትሞትም/ሴቷ

አትሞትም/እርሱ

ትቤ---አልህ/እሱ

አለች/እሷ

ይቤ ዘማች ነው የተባለበት ምክንያት ስለሚዘምት ነባር አንቀጽ የተባለበት ምክንያት ከነባር አንቀጽ ስለ ሚገኝ ነው፡፡

፪.ነባር ከአገባብ ተዋርሰው የሚገኙበት በፊደል ተመሣሣይ ቢሆኑም በመጥበቅ እና በመላለት ይለያያሉ።

ምሳሌ፡- እም---ከ/አገባብ

እም--እናት/ነባር

እምነ---እናታችን/ነባር

እምነ---ከ/አገባብ

ከመዝ---እንደዚህ/አገባብ

ከመዝ---የውኃ እናት/ነባር

ምሳሌ፡- ከመዝ ከመዝ/የውኃ እናት እንደዚህ ናት

፫.ዘር ከዘር ነባር ከዘር በማጥበቅና በማላለት

ምሳሌ፡-ስቡሕ---የተመሰገነ

ስቡሕ---የሰባ የወፈረ

ማዕብል---ሠይፍ

ማዕበል---ማዕበል ሞገድ

አጸድ---አጫጆች

አፀድ---የወይን ዛፍ

ቅሳሜ---ዓይንት

ቅሳሜ---ሧርት

## ምዕራፍ ---፱

## ገቢር ተገብሮ /active & passive

ገቢር/ሦጋሪ ግስ/ተሻጋሪ/transitive verb እና ተገብሮ ኢሦጋሪ/ኢተሻጋሪ/intransitive verb በአጠቃለይ ግሶች በተግባር ኺደታቸው በሁለት ይከፈላሉ ፡

እነዚህም ገቢር እና ተገብሮ ናቸው።

የሚሻገሩ ግሶች --ግሶች ከባለቤቱ ወይም ከድርጊት ፈጻሚው ድርጊቱን በማሦለፍ በድርጊት መፈጸሚያቸው ላይ ማረፍን የሚያመለክቱ ግሶች ናቸው።በግዕዙ የገቢር ግሶች ይባላሉ።ተሻጋሪ ግሶች ለማለት ነው።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ፡-አቅረበ | አንበረ | አጥረየ | መለከ |
| ጸፍአ | ቀተለ | ዘመረ | ሰብሐ |
| ሰበረ | ባረከ | ሰበከ | መሀረ |
| አኀዘ | ሐነጸ | ሰቀለ | መሐረ |
| | ቀደሰ | ዜነወ | ሐለመ |

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ግሶቾ ፈጻሚ አካል እና ተወካፌ ግብር በውስጣቸው የያዙ ናቸው።

የገቢረ ግሳት ምንጫቸው እራሳቸው እና ተገብሮ ግሳት ናቸው።

ምሳሌ፡-ሰቀለ---ስቅለት፣ሰቀሉሰቀላ፣እየአለ በ፲ሩ መራኅያን ሲዘረዘር እራሳቸው የሚለውን ያሣያል።

| | |
|---|---|
| ቆመ | አቀመ |
| ገብአ | አግብአ |
| ወጽአ | አውጽአ |
| ወዓለ | አውዓለ |
| ሰከረ | አሰከረ ወዘተ እያለ ከተገብሮ ግሳት ገቢር ግሳትን ማግኘት ይቻላል። |

በግዕዝ ቋንቋ የሚሻገሩ ግሶች ወሰነ ሰፊ ናቸው ለዚህም ሰሐቢነታቸው የጎላ ነው ማለት ይቻላል።በሌላ አገላለጽ የሚሳቡ እና የማይሳቡ ማለት ነው።

ተሳቢው ተውላጠ ስም እና ባለቤት ተውላጠ ስም  ያላቸውን ልዩነት እና አንድነት ለይተን የምናውቅበት ነው።

### ተገብሮ/ኢሰጋሪ/ኢሰሐቢ ግስ

ኢተሻጋሪ ግሶች የሚባሉት መሳብ የማይችሉ ናቸው ድርጊት ፈጻሚ እንጅ ድረጊት የሚቀበል አካል የለውም።ስለ ተሳቢ አይጨነቅም ፡፡

ምሳሌ፡--ገብአ ተንተነ ሞተ

ቆመ ወአለ ነበረ

ማሰነ መጸአ ሖረ

ከወወ ተወይጠ ወረደ

የተገብሮ ግሳት ምንጫቸው እራሳቸው እና ገቢር ግሳት ናቸው።

ምሳሌ፡-ገብአ፣ገባእኩ፣ገባእኪ፣ገብአት ወዘተ እያለ ከራሳቸው እናገኛለን

ምሳሌ፡-ቀተለ ተቀትለ

ቀደሰ ተቀደሰ

ተንበለ ተተንበለ

ባረከ ተባረከ

ሴሰየ ተሴሰየ ወዘተ እያለ ከገቢር ግሳት ተገብሮ ግሳትን ማግኘት ይቻላል።

በዚህ መሰረትም ገቢር ግሳት ወደ መሠረታውያን ተገብሮ ግሳት መለወጥ ይቻላል።እንዲሁም ተገብሮ ግሳት ወደ ገቢር ግሳት ይለወጣሉ ሁሉም ማለት አይቻልም ።

በግእዝ የማይሻገሩ /የተገብሮ ግሶች የሚመስሉ አንዳንዶች ተሻጋሪ የሚሆኑበት ጊዜ አለ ።ያም እንደ ዐ.ነገሩ ይወሰናል ማለትም ይሳባሉ ማለት ነው።

ነባር አንቀጽ እና የማለት አንቀጾች የማይሻገሩ ግሶች ናቸው።

## ተሻጋሪ ግሶች በተሳቢነት ያላቸው ደንብ

ተሳቢ -- በዐ.ነገር ውስጥ የድርጊቱ መፈጸሚያ ነው ይኸውም በድረጊት መሪ የሚለይ «ን» የሚለው ቃል በግልጽም ሆነ በውስጠ ታዋቂነት የሚያስቀምጥልን የሰዋሰው ተ/ክፍል ነው፡፡

***ሀ.ፊደልን በመለወጥ***

ቃላት በገቢር እና በተገብሮ ግሶች ሲገለጹ ባህርያቸውን ይለውጣሉ ይኸውም በተገብሮ የነበሩ ቃላተ በገቢር ግሶች ሲነገሩ ራሳቸውን ይለውጣሉ ።

፩.ተቃሉ የመጨረሻ ፊደል ስድስተኛ ፊደል የሆነ ወደ ግእዝ ይለወጣል ።

| ምሳሌ፡-ገቢር | ተገብሮ |
|---|---|
| አንተ ሰበርከ ሐመረ | ተሰብረት ሐመርየ ውስተ ባሕር |
| አቅረበ ለነ እሳተ | ቀረብከ አንተ ውስተ እሳት |

አቅረበ ለነ ማየ ቀረብኩ አነ ኀበ ማይ

የሚከተሉት ቃላት ከሳድስ ወደ ግዕዝ እንዴት እንደተለወጡ ያሳያል።

| ባለቤት ስም | ትርጉም | ተሳቢ | ትርጉም |
|---|---|---|---|
| ቤት | ቤት | ቤተ | ቤትን |
| ሀገር | ሀገር | ሀገረ | ሀገርን |
| እም | እናት | እመ | እናትን |
| አብ | አባት | አበ | አባትን |
| ወልድ | ልጅ | ወልደ | ልጅን |
| ዕብን | ድንጋይ | እብነ | ድንጋይን |
| ለብስ | ልብስ | ልብሰ | ልብስን |
| ልብ | ልብ | ልበ | ልብን |
| ዕፅ | እንጨት | ዕፅ | እንጨትን |
| ነገር | ነገር | ነገረ | ነገርን |
| ቅድስት | ቅድስት | ቅድስተ | ቅድስትን |

ምሳሌ፡-ገ/ማርያም ተደረ ኀብስተ

ኀብስት ተደረ በእኁነ ገ/ማርያም

ከላይ የዘረዘርናቸው ቃላት የመጨረሻ ፊደላቸውን በመለወጣቸው «ን»ተሳቢ አመልካች መስተአምር አስገኝተዋል፡በተጨማሪም በ፣ከ፣ወደ የሚል መስተአምር ሊያወጡ ችለዋል፡፡

ምሳሌ፡-ቤተ---ቤትን ፣ወደ ቤት፣ከቤት ፣በቤት ወዘተ

እምከ----እናትሽ እመከ----እናትኸን

እምኪ----እናትሽ እመኪ----እናትሽን

ወልድከ---ልጅህ ወልደከ----ልጅህን

አይ---ምን አየ-----ምንን

ምንት----ምን ምንተ----ምንን /በምን

መዓልት----ቀን መዓልተ----ቀንን/በቀን

ዐመት---ዓመት ዓመተ---- ዓመትን/በዓመት

፪.በቃሉ መጨረሻ ፊደል ሦስተኛ ፊደል የሆነ ወደ አምሥተኛ ይለወጣል።

ምሳሌ፦ከይሲ ------- እባብ ከየሴን ---- እባብን

ብእሲ ------ሰው ብእሴ ----ሰወን

ሰራቂ -----ሌባ ሰራቄ ----ሌባን

ሰባኪ-----አስተማሪ ሰባኬ------አስተማሪን

ነጋዲ ------ነጋዴ ነጋዴ------ነጋዴን

ምሳሌ፦ገቢር፡አነ ቀተልኩ ከይሴ /እኔ እባብ ገደልሁ/---ሲስብ

ተገብሮ፡መጽአ ብየ ከይሲ/እባብ መጣብኝ/---ሳይስብ

ገቢር፡አንተ ፈጠርከ ብእሴ/አንተ ሰውን ፈጠርህ/

እግዚእ ኀረየ ሰባኬ /ጌታቸን ሰባኪን መረጠ/

ሰባኪ ውእቱ አቡዩ/አባቴ አስተማሪው /

<u>ዜግነትን የሚያመለክት</u>

| ስመ ሀገር | ቅጽል | |
|---|---|---|
| ኢትዮጵያ | ኢትዮጵያዊ | ኢትዮጵያዌ |
| እስራኤል | እስራኤላዊ | እስራኤላዌ |
| ሮም | ሮማዊ | ሮማዌ |
| ኤርትራ | ኤርትራዊ | ኤርትራዌ |

፫.ካእብ ፊደል ወደ ሳብእ ፊደል ይለወጣል።

| | |
|---|---|
| ቤቱ | ቤቶ |
| እሙ | እሞ |
| ዘመዱ | ዘመዶ |
| ባሕቲቱ | ባሕቲቶ |
| ንብረቱ | ንብረቶ |

ቅጽል ከንቱ ከንቶ

ኵሉ ኵሎ

ሕጽሪቱ ሕጽረቶ

አመልካች--- ዝኩ ዝኮ

እልኩ እልኮ

ገቢረ ኰሎ ዘፈቀደ ገብረ እግዚአብሔር/እግዚአብሔርን የወደደውን አደረገ

ሀደገ ቤቶ ወንብረቶ/ቤቱንና ንብረቱን ተወ

ከንቶ ይመስል ዝንቱ ዓለም/ይህ ዓለም ከንቱን ይመስላል

ተገብሮ መጽአ ኀበ ቤቱ ወተከፈ ንብረቱ /ወደ ቤቱ መጣ ንብረቱንም ተረከበ/

ከንቱ ውእቱ ዓለም /ይህ ዓለም ከንቱ ነው

ኵሉ ተፈጥረ በፈቃደ እግዚብሔር/ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃደ ተፈጠረ

ለማጠቃለል፡--የቃሉ መጨረሻ ፊደል ሳድስ----ግዕዝ

ሣልስ---ኃምስ

ካእብ-----ሳብእ

***ሊፈደልን ባለመለወጥ***

የቃሉ የመጨረሻ ፊደል ራብእ፣ኃምስ፣ሳብዕ እና ግእዝ ከኾነ በተሳቢም /ገቢር/በተገብሮም ጊዜ የቃሉ ፊደል አይለወጥም።

፩.ምሳሌ የቃሉ የመጨረሻ ፊደል ሳብእ ሲሆን

አንበሳ ---አንበሳ አንበሳ----አንበሳን

ደብተራ----ድንኳን ደብተራ -----ድንኳን

ሠረገላ ----መኪና ሠረገላ -----መኪናን

መጽአ አንበሳ አንትሙ ቀተልከሙ አንበሳ

አነ መጻእኩ በሠረገላ አንተ ገብርከ ሠረገላ

፪.የቃሉ የመጨረሻ ፊደል ኃምስ ፊደል ሲሆን

ሥላሴ ---- ሥላሴ ----ሥላሴን

ውዳሴ ---- ውዳሴ ----ምስጋና ፡ምስጋናን

ስንዳሴ ----- ስንዳለ ስንዴ ስንዴን

ሉዓሌ ------ ሉዓሌ --- ከፍታ ፣ከፍተኛን/ከፍታን

ምሳሌ፡-ነአምን በሥላሴ----በሥላሴ እናምናለን

አምን ሥላሴ ----ሥለሴን እናምናለን

ውደሴ ዘማርያም----- የማርያም ውዳሴን

አነ ጸሐፍኩ ውዳሴ ዘማርያም ---የማርያምን ምስጋና ጻፍኩ

ኢታፍቅሩ ውዳሴ -----ውዳሴን አትውደዱ

አብርሃም ተወክፈ ሥላሴ-----አብርሃም ሥላሴን ተቀበለ

፫.ሳብእ እና ግእዝ ሲሆን

ደርሆ----ደሮን፣ደሮ

አንቆቅሆ---እንቁላል፣እንቁላልን

መርዓ----መክፈቻ ፡መክፈቻን

ደራሞ፡ጸራሞ----የእንቅልፍ ጋኔን

***ሐ.የተጸውዖ ስም ላይ የገቢር ግሶች«ሀ» ን ይጨምራሉ***

አንዳንድ ሰዎች /መጻሕፍት «ሃ» የሚሉ አሉ ሁሉም ችግረ የለባቸውም።

ጴጥሮስ ----ጴጥሮስሀ

ሙሴ ----ሙሴሃ

ዐለሙ ---ዐለመሃ

ምሳሌ፡-እግዚአብሔር ኀረየ ጴጥሮስሀ

አይሁድ ሰቀሉ ክርስቶስሀ

አነ አፍቀርኩ ዘካርያስሃ

***መ.ባለቤት ተውላጠ ስም ወደ ተሳቢ ተውላጠ ስም ይለወጣል***

አነ----ኪያየ እኔ እኔን

አንተ----ኪያከ አንተ፡አንተን

አንትን----ኪያክን አንቺ፣እናንተን እያለ ይዘልቃል።

ምሳሌ፡-አንትሙ አፍቀርክሙ ኪያዬ/እናን እኔን ወደዳችሁ

ዘተወክፈ ኪያክሙ ተወክፈ ኪያየ/እናንተን የተቀበለ እኔን ተቀበለ

ኪያከ ንሴብሕ እግዚኦ/አቤቱ አንተን እናመሰግናለን

ተጠቃሽ እና አመልካች ተውላጠ ስሞች እንደ ተሳቢ ተውላጠ ስም ያገለግላሉ።

### *ሠ.በአመልካች ጊዜ*

ዝ-----ዘ ይኽ፣ይኽንን

ዝንቱ-----ዘንተ ይኽ፣ይኽንን

ዛቲ----ዛተ ይኽች፡ይኽችንን

ዝከቱ----ዝከተ ያ፡ያንን

ውእቱ-----ውእተ ያ፣ያንን

ይእቲ----ይእተ ያች፣ያችንን

ቃላቱ እራሳቸውን የሚቀይሩት /የሚለውጡት እንደ ግሱ ተሻጋሪነት ነው።

ምሳሌ፡-ዝንቱ <u>ውእቱ</u> ወልድየ /ይህ ልጄ ነው ፡፡የተሰመረበት የማይሻገር ግስ

አነ ወለድኩ ዘንተ ወልደ/ይህንን ልጅ እኔ ወለድኩት

ዛቲ ይእቲ መርያትዬ/ያቺ እህቴ ናት

<u>ባርክ</u> ለነ ዘንተ ኅብስተ /የህንን ኅብስት ባርክ ።የተሰመረበት የሚሻገር ግስ

### *ረ.አንዳንድ ልዩዎች*

አንዳንድ ቃላት ለተሳቢም ለተገብሮም ይችላሉ።

፩.የቃሉ የመጨረሻ ፊደል ግእዝ ሲሆን

ዮኽን ስንል ግን ግስሱ ተገብሮ ሆኖ ድርጊት መፈጸሚያው ቃል እንደ ተሳቢ ይነበብ ማለታችን አይደለም።

ምሳሌ፡-«ዘመድከ»ሲል ዘመድኽ እንጂ የመጨረሻ ፊደሉ ግእዝ ስለሆነ ዘመድኽን ተብሎ አይነበብም

፪.በዝርዝር ሲነገር አንድ ቃል እንደ ዐ.ነገሩ ገቢርም ተገብሮም ይኾናል/ሊሳብም ላይሳብም ይችላል።/

ምሳሌ፡-እምየ----እናቴ

እምከ----እናትህ ----እመከ

እሞን ---እናታችሁ/ን

እሞሙ---እናታቸው/ን

ዚአየ---እኔ/ን

ዚአከሙ----እናንተ/ን

ዚአኪ-----አንቾ/ን

ዚአነ----ዚአከን

የመስተዋድድ፣የመስተጻምር ፣የተናባቢ፣ቃላት ሳይለወጡ እንዳለ ይሳባሉ።

# ምዕራፍ ---፲

## አንቀጽ

የአድራጊ ፣የድረጊት እና የሁኔታ አንድና ብዙ ቁጥሩን ቅርብና ሩቅ መደብ ፣ተባዕታይ እና አንስታይ ጾታን ፣ኃላፊ አሁንተና ትንቢት ጊዜያትን ወዘተ የሚያስረዳ ሰወስው አንቀጽ ይባላል።አንቀጽ ማለትም መግቢያ መውጫ መመላለሻ በር ማለት ነው።

አንቀጽ በሁለት ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል።

ሀ.ዘርእ/ዘማች /አንቀጽ

ለ.ነባር አንቀጽ

### ሀ.ዘማች አንቀጽ--

ለራሱ በሁለት ይከፈላል።

፩.ዐበይት አናቅጽ(፭ᵉ ፣፪ᵉ ፣፫ᵉ አናቅጽ)

፪.ንዑሳን አናቅጽ(ዘንድ፣ርዕስ፣ቦዝ፡ሳቢ ዘር፣ቅጸል፣)

### ፩.ዐበይት አናቅጽ /main verb/

- ዐበይት አናቅጽ የሚባሉት/የተባሉት ያለ ውእቱ የአንቀጽ ረዳትነት ራሳቸውን ችለው ማሠር ስለሚችሉ/ማሠሪያ አንቀጽ ስለሆነ ነው።
- ዐበይት አናቅጽ የሚባሉት
  ---ቀዳማይ/past tense /

  ---ካልአይ/Present & future/

  ---ሣልሳይ/ Command/ ናቸው።

ምሳሌ፡----ወጽአ----ወጣ

ይወጽእ----ይወጣል፡እየወጣ

ይጻእ----ይውጣ

---- ቀደሰ----አመሰገነ

ይቄድስ----ያመሰግናል/እያመሰገነ

ይቀድስ----ያመስግን

---- ተንበለ----ለመነ

ይተነብል----ይለምናል

ይተንብል----ይለምን

---- ቀተለ----ገደለ

ይቀትል----ይገድላል፡እየገደለ

ይቅትል----ይግደል

---- ባረከ----ባረከ

ይባርክ[ፕ]----ይባርካል፤እየባረከ

ይባርክ[ለ]----ይባርክ

---- ማህረከ----ማረከ

ይመህርክ----ይማርካል፤እየማረከ

ይማህርክ----ይማርክ

---- ሴሰየ---መገበ

ይሴሲ[ፕ]---ይመግባል፡እየመገበ

ይሴሲ[ለ]----ይመግብ

---- ጦመረ-----ጻፈ

ይጦምር[ፕ]----ይጽፋል፤እየጻፈ

ይጦምር----ይጻፍ

---- ክህለ----ቻለ

ይክህል/ይክል---ይችላል

ይክህል/ይክህል----ይቻላል

ምሳሌ፡-ቀደሰ ካህን ሰቦ ኮነ ተባርየቱ።

ይቄድስ ካህን ሶበ ይጠመቁ ህፃናት።

ይቀድስ ካህን ሶበ ኮነ ፺ቱ ሰያት።

ምሳሌ፡--አቡየ መጽአ እምደብረ ሊባኖስ

/my father came from libanos monastery/

አቡየ ይመጽእ እምደብረ ሊባኖስ

/my father comes from libanos monastery/

አቡየ ይምጽአ እምደብረ ሊባኖስ

/my father should come from libanos monastery

/my father must come from libanos monastery/

ምሳሌ፡--ሐደፈ ዘቤ.ክ መሀረ አርድእተ ሰዋስዎ ግእዝ ለ፪ ዓመታት

/teach of church tought students of geez last 2 years/

ሐደፍ ዘቤ.ክ ይሜህር አርድእተ ሰዋስዎ ግእዝ ለ፪ ዓመታት

/teach of church will teach students geez for 2 years

ሐደፍ ዘቤ.ክ ይምህር አርድእተ ሰዋስዎ ግእዝ ለ፪ቱ ዓመታት

/ teach of church should teach students of geez for 2 years

***፪.ንኡሳን አንቀጽ***

ንኡሳን አንቀጽ ተብለው የተሰየሙበት /የሚሰየሙበት ምክንያት «ውእቱ»በውስጣቸው ካልገሰገሰባቸው /በውስጣቸውም ሆኖ የመሆን ማሠሪያ አንቀጽ ካልሆነ /በቀር እንደ ዐበይት አናቅጽ እራሳቸውን ችለው ማሠሪያ አንቀጽ ሆነው መነገር ስለ ማይችሉ ነው።

አናቅጽ፡-ተብለው የተሰየሙበት ምክንያት እንደ ዐበይት አናቅጸ ሰዋስውን ስለሚሰቡ ነው።

ንኡሳን አናቅጽ ተብለው የሚጠሩትም የሚከተሉት ናቸው።

---ርእስ ንኡስ አንቀጽ
---ሳድስ እና ሣልስ ቅጽል ንኡስ } ተናባቢ ንኡሳን አንቀጽ
---ሳቢ ዘር ንኡስ አንቀጽ

---ቦዝ አንቀጽ
---ዘንድ አንቀጽ } ኢ-ተናባቢ

ከዚህ የምንረዳውም ንኡሳን አናቅጽ ፡-1.ተናባቢ እና 2.ኢ-ተናባቢ ተብለው እንደ ሚከፈሉ ነው።

ወጽአ---ይጻእ ---ይወጣ ዘንድ--ዘንድ

ወጺእ/ወጺዓት---መውጣት---አርእስት

ወጺአ---ወጥቶ---ቦዝ አንቀጽ

ወጻኢ---የሚወጣ---ሣልስ ቅጽል

ውጹእ---የወጣ---ሳድስ ቅጽል

ጻአት---መውጣት---ሳቢ ዘር

ቀተለ---ይቅትል--ዘንድ

ቀቲል/ቀቲሎት--አርእስት

ቀታሊ----ሣልስ ቅጽል

ቅቱል---ሳድስ ቅጽል

ቅትልት----ሳቢ ዘር

ቀቲሎ---- ቦዝ አንቀጽ

ምሳሌ፡--

ዘንድ--አስተጋብአ እጸወ ሰሎሞን ይህንጽ መቅደሰ/ሰሎሞን መቅደስን ይሠራ ዘንድ እንጨቶችን ሰበሰበ።

አርዕስት---አርሐዎ ኆኅተ አብርሃም ለተወክፎ ነግደ/አብርሃም እንግዳን ለመቀበል በሩን ከፈተ።

ቦዝ አንቀጽ ---ደንገጸ ሙሴ ሰሚዖ ድምጸ/ሙሴ ድምጽን ሰምቶ ደነገጠ።

ሳቢ ዘር---ተሐርየ ዳዊት ለሢመት መንግስተ/ዳዊት መንግስትን ለመሸከም ተመረጠ።

ሳድስ ቅጽል---ይነሥእ ማዕጠንተ አሮን ሥዩም ክህነተ/ክህነትን የተሾመ አሮን ማዕጠንትን ይይዛል።

ሣልስ ቅጽል---ኢፈርሐ ሞተ ሙሴ ቀታሊ ግብጻዊ/ግብጻዊን የገደለ ሙሴ ሞትን አልፈራም።

## <u>ኢተናባብያን ንዑሳን አናቅጽ/ዘንድ እና ቦዝ አንቀጽ</u>

ከሚከተላቸው ሰዋስው ጋር ሳይናበቡ በፊት ሆነው ኋለኛውን በኋላ ሁነው የፊተኛውን ሰዋስው ይስባሉ።

- <u>ፊት ሆነው ኋለኛውን ሲስቡ</u>
  ፈነወ ሄሮድስ ሐራሁ ይቅትሉ ህፃናተ/ሄሮድስ ሕፃናትን እንዲገድሉ ወታደሮችን ላከ።
  ተጸውዐ ዳንኤል ይፈክር ሕልመ/ዳንኤል ህልምን ሊተረጉም ተጠራ።
  ወረሱ ጿኤል ርስቶሙ ስሊጦሙ ግብሮሙ/ጿኤል ርስታቸውን ጨርሰው ርስታቸውን ወረሱ።
  ዘመረ ዳዊት መዝሙረ ነሢአ መሰንቆ /ዳዊት መሰንቆን ይዞ መዝሙርን ዘመረ።
- <u>በኋላ ሆነው ፊተኛውን ሲስቡ</u>
  ዘንድ --ፈነወ ሄሮዶስ ሐራሁ ሕፃናተ ይቅትሉ።
  ተጸውአ ዳንኤል ሕልመ ይፈክር።
  ቦዝ---- ወረሱ ጿኤል ርስቶሙ ግብሮሙ ስሊጠሙ።
  ዘመረ ዳዊት መዝሙረ መሰንቆ ነሢአ።
  ሙያው --ይቅትሉ----------
  ይፈክር-----የተጸውዐ ምክንያትን የሚያስረዳ ዘንድ

ስሊጦሙ----»»»»»»»»

ኑሂአ----የዘመረን ምክንያት የሚያስረዳ ቦዝ

**፪.የተናባብያን ንዑሳን አናቅጽ**

ከሚከተላቸው ሰዋስው ጋር እተናበቡ /ዘርፍ እየያዙ /ወይም ዘርፍ ሳይዙ ሰወስውን በመሳብ ይነገራሉ።

ዘርፍ ሳይዙ ሰዋሰውን በመሳቡ ሲነገሩ

ርዕስ ንዑስ አንቀጽ:
- ተመነዩ ዳዊት ቀቲለ ጐልያድ።
- ኢያጸርእ አብርሃም ተወክፎተ ነግድ።
- ያፈቅር ዳዊት ዘምሮ መዝሙረ።

ሳቢ ዘር ንዑስ አንቀጽ:
- ኢሐደገ ሄሮድስ ቅትለተ ሕፃናት ።
- ፈቀዱ አይሁድ ስቅለተ አምላክ
- ተአደወ ለንጊኖስ ርግዘተ እግዚእ።

ውስጠዘ ቅጽል:
- ተሐርየ ሰሎሞን ሐናጼ መቅደስ።
- ጻድቀ አብርሃም ሰዋኤ ይስሐቅ።
- ተሰቅለ እግዚእነ ቅጹለ አስዋክ ።

ዘርፍን ይዘው ሰዋስውን በመሳብ ሲነገሩ

ተመነየ ዳዊት ቀቲለ ምጻፍ ጐልያድሀ/ዳዊት ጐልያድን በወንጭፍ መግደልን ተመኘ።

ኢያጸርእ አብርሃም ተወክፎተ ሐይመት ነግደ/አብርሃም እንግዳን በድንኳን መቀበልን አያቋርጥም ነበረ።

ያፈቅር ዳዊት ዘምሮ መሰንቆ መዝሙረ/ዳዊት መዝሙርን በመሰንቆ መዘመርን ይወድ ነበር።

ፈቀዱ አይሁድ ስቅለተ መስቀል አምላክ።

ተዐደወ ለንጊኖስ ርግዘተ ኵናት እግዚእ ።

ተሐርየ ሰሎሞን ሐናጼ አእናቍ መቅደሰ/መቅደስን በእንቁዎች የሠራው ሰሎሞን ተመረጠ።

ጻድቀ አብርሃም ሰዋኔ መጥባሕት ይስሐቅሀ/ይስሐቅን በቢላ የሰዋ አብርሃም ጻደቀ።

ተሰቅለ እግዚእነ ቅጹለ አይሁድ አስዋክ/እሾኾችን በአይሁድ የተቀዳጀ ጌታችን ተሰቀለ።

## ለ.ነባር አንቀጽ

ነባር አንቀጽ ማለት ሳይለወጥ የኖረ ኗሪ አንቀጽ ማለት ነው።በሌላ በኩል ኃላፊ ፣ትንቢት እና አሁንተ ጊዜያትን ፣በእርባታ ፍች ካልሆነ በቀር በንባብም ንዑስ አንቀጽ /አርእስት፣ሳቢ ዘር ፣ጥሬ ዘር፣ቅጽል/ስለሌለው።

ነባር አንቀጽ ፡- ሀ.የከዊን አንቀጽ/verb to be

ለ.ህልው አንቀጽ /verb to have

## *ሀ.ከዊን አንቀጽ /verb to be*

አንድ ነገር እንደ ሆነ፣እንደሚሆን፣እየ ሆነ እንደ ሆነ የምንገልጽበት ነው።

እነዚህም፡-

ውእቱ---ነው፣ሆነ/ሆኗል ይሆናል ይሁን

አኮ----አይደለም ፣አልሆነም ፣አይሆንም

ሐሰ---»»»                »»»

ኢ---ከማፍረስ አንጻር

ውእቱ፡-ውእቱ በንባብ ተገልጾ የሁኔታ መሆን ማሰሪያ አንቀጽ ሆኖ ሲነገር

ምሳሌ፡-ኵነኔየ ጽድቅ ውእቱ /ፍርዴ እውነት ነው።

ኢዮብ ጻድቅ ውእቱ /ኢዮብ ጻድቅ ነው።

ቃልየ እሙን ውእቱ/ቃሌ የታመነ ነው፡፡

ውእቱ በንባብ ሳይገለጽ በሰዋስው ውስጥ ሆኖ በመገሰስ የሁኔታ ነባር ማሠሪያ አንቀጽ በመሆን ይነገራል።

ምሳሌ፡-ዓቢይ እግዚአብሔር /እግዚአብሔር ታላቅ ነው።

ጻድቅ ኢዮብ /ኢዮብ እውነተኛ ነው።

ክህን አሮን/አሮን ካህን ነው፡፡

ንጽሕት ማርያም /ማርያም ንጽሕት ናት።

ውእቱ በ፴ሥሩ መራሕያን ይዘረዘራል

ውእቱ ንባቡን ሳይለውጥ የቀዳማይ፣የካልአይ እና የሣልሳይ አናቅጽ ማታን በፍች በ፴ሥሩ መራሕያን እየዘረዘረ ብቻ ይረባል።ማለትም ውእቱ ለ፲ሩ መራሕያን እንደ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል።

አነ--ውእቱ፡እኔ ነኝ --ኾንኩኝ--እሆናለሁ፣ልሁን

ንህነ--ውእቱ ፡እኛ ነን ሆን /ሆነናል፣እንሆን እንሆናለን ፣እንሁን

አንተ--ውእቱ --አንተ ነህ --ሆንህ/ሆነሀል፣ትሆን/ትሆናለህ፣ሁን

Was, were ---ቀዳማይ አንቀጽ

Is, am, are, be---ካልአይ አንቀጽ

ምሳሌ፡-ጸድቀ ኢዮብ፣ኢዮብ ጻድቅ ውእቱ

/Eiyob was paitint/Eiyob is paitint/Eiyob will be paitint

አነ ጻድቅ ውእቱ ።

/I was paitint/I am paitint/I will be paitint/I should be paitint

ገ/ማርያም ወእህቱ ነዳያን ውእቱ።

/G/mariyam and his sister were poor/G/mariyam and his sister are poor

/G/mariyam >> >> will be poor/G/mariyam>> >> should be poor

አኮ--በንባብ ተገለጸ ከሰዋስው በፊትና በኋላ ሆኖ የአንድን ነገር አለመሆን /አለ መፈጸም የሚስረዳ አሉታ ማሰሪያ አንቀጽ ነው።

ምሳሌ፡-አኮ ሙታን ንህነ /እኛ ሙታን አይደለም

ሙታን አኮ ንህነ/ሙታን እኛ አይደለንም

አኮ ሒጣን ቃል/ቃሌ ሸንገላ አይደለም

ሒጣን አኮ ቃልየ /ሸንገላ ቃሌ አይደለም

አኮ ዝንቱ ግእዘንነ/ልማዳችን ይህ አይደለም

ዝንቱ አኮ ግእዘንነ/ይህ ልማዳችን አይደለም

አኮ ጽድቅ ይሁዳ /ይሁዳ ጻድቅ አይደለም

ጽድቅ አኮ ይሁዳ /ጻድቅ ይሁዳ አይደለም

አኮ--በዐሥሩ መራሕያን እንደ ውእቱ እየተዘረዘረ ቀዳማይ ፣ካልአይ፣ሣልሳይ አንቀጽን በፍች ያመጣል።

ለምሳሌ፡-አነ--አኮ/አይደለሁም

ውእቱ--አኮ/አይደለም

ውእቶሙ--አኮ/አይደሉም እያለ በ፲ሩ ይዘልቃል።

አነ--አኮ/አይደለሁም

አልሆንኩም -፩ᵉ ኃላፊ/past tense

አልሆንም--፪ᵉ ትንቢት/future

አልሁን--፫ᵉ ዘንድ/command

ምሳሌ፡-አኮ ኃጥእ(ኃጢያተኛ አልነበረሁም ፣አልሆንም፣አልሁን)

አኮ ሰዋስወ ግእዝ(የግእዝ ቋንቋ አልነበረም ፣ይኖራል፣ይኑር)

አኮ ኀብስተ ሰማይ ።

አኮ ወልደ እጓለ እመሕያው

/He was not the son's of the person/

/He isn't the son's of the person/

/He isn't the son's of the person/

/He will ben't the son's of the man/

/He should be not the son's of the man/

## ሊ ህልው አንቀጽ /verb to have

- «ሀለዎ»ማለት መኖር ማለት ነው ።በዚህም መሠረት «በ» እና «አልቦ» ን በውስጡ ይዟል።ማለትም መኖርን እና አለመኖርን ማለት ነው።
- «በ» ከሰዋስው በፊትና በኋላ እየገባ መኖርን ይገልጻል።

ምሳሌ፡-

በፊት:
- ቦ ሕይወት ዘለዓለም /የዘላለም ህይወት አለ።
- ቦ አሕርው ውስተ ሐቅል /በበርሐ ውስጥ እሪያዎች ነበሩ።
- ቦ ሰብእ ውስተ ይእቲ ቢት/በዚህ ቤት ሰው ይኖራል፣ነበር።

በኋላ:
- ሕይወት ዘለዓለም ቦ።
- አሕርው ውስተ ሐቅል ቦ።
- ሰብእ ውስተ ይእቲ ቤት ቦ።

ትርጉም ከላይኛው ጋር ተመሳሳይ

<u>«በ» በዐሥሩ መራሕያን መዘርዘሩ /መነገሩ/</u>

የተቀባይ ዝርዝርን ሳይዘረዝር ወይም ዘርዝሮ ይነበባል።

በንባብ የማይገልጻቸው ቀዳማይ፣ካልአይ እና ሣልሳይ አናቅጽን በፍች ይገልጻቸዋል።

ቦ-----ብየ/አለኝ-----ኖረኝ/ነበረኝ፩ዩ----ይኖረኛል፪ዩ ----ይኑረኝ፫ዩ

-----ብነ/አለን------ »» ----- »» ----- »»

-----ብከ/አለህ------ »» ----- »»» ----- »»

-----ብክሙ/አላችሁ---- »» ---- »» ---- »»

-----ብኪ/አለሽ ---- »» ---- »» ---- »»

----ብክን/አለችሁ ----»» ---- »» ----»»

----ቦቱ/አለው ---- »» ---- »» -----»»

----ቦሙ፣ቦቶሙ/አላቸው-----»» ----»» ----»»

----ባ/ባቲ/አላት -----»» ----»» ----»»

----ቦን/ቦቶን/አላቸው -----»» -----»» -----»»

ምሳሌ፡-ብየ መዝገብ፡/ደብተር ነበረኝ ፣ይኖረኛል፣ይኑረኝ/

/I had a book/I have a book/I will have abook /I should have a book

----ቦቱ ሕይወት ወሞት/ሕይወት እና ሞት ነበረው ፣ይኖራል፣ይኑረው።/

----ቦቱ ምሕረት /ይቅርታ ነበረው ፣ይኖረዋል፣ይኑረው/

አልቦ----ከሰዋስው በፊት ወይም በኋላ እየገባ የ«ቦ» አሉታ ሆኖ አለመኖርን በመግለጽ ይነገራል።

ምሳሌ፡-አልቦ ማህለቅት/ማህለቅት አልቦ---መጨረሻ የለውም

አልቦ ጠቢብ/ጠቢብ አልቦ----ጥበበኛ አይኖርም

አልቦ ሁከት/ሁከት አልቦ----ሁከት አልነበረም

----በዐሥሩ መራሕያን ይዘረዝራል።

----የተቀባይ ዝርዝርን ሳይዘረዝር/ዘርዝሮ ይነበባል፡፡

----በንባብ የማይገልጸቸው ፳ᵉ ፣፪ᵉ ፣፫ᵉ አናቅጹን በፍች ይገልጻል።

| | <u>ቀዳማይ</u> | <u>ካልአይ</u> | <u>ሣልሳይ</u> |
|---|---|---|---|
| አልብየ---የለኝም | ---አልነበረኝም | ----አይኖረኝም | -----አይኑረኝ |
| አልብነ---የለንም | ----አልነበረንም | -----አይኖረንም | -----አይኑረን |
| አልበከ---የለህም---- | »» | ----- »» | ----- »» |
| አልብኪ---የለሽም-----»» | | ------ »»»» | ----- »» |
| አልብከሙ---የላችሁም----»» | | ------ »» | ---- »» |
| አልብክን---የላችሁም---- | »» | ----- »» | ---- »» |
| አልቦቱ---የለውም ----»» | | -----»» | ----»» |
| አልቦሙ/አልቦቶሙ----የላቸውም-----»» | | -----»» | ----»» |
| አልባ/አልባቲ--- --የላትም | ---- »» | ----- »» | ----»» |

አልቦን/አልቦቶን----የላቸውም ---- »» ---- »» ----»»

ምሳሌ፦-አልቦቱ መልበስ ዘእንበለ ዘተውኀበቶ።

(ከተሰጠችው ውጭ ልብስ የለውም ነበር፣አይኖረውም ፣አይኑረው)

He hadn't cloth with out gifted

He hasn't >> >>

He will not >> >>

He should >> >>

# ምዕራፍ--፲፩

## ዘርፍ ሰዋሰው

ከተናባቢ ሰዋስው ጋር ተያይዞ /ተጠብቆ የሚነገር ሰዋስው ዘርፍ ይባላል።በሌላ አገላለጽ ዘርፍ ማለት ዘፈር፣ቅርንጫፍ ማለት ነው።ውስጣዊ ሐሳቡ /ጠባዩ ተሳቢነት /ተሳቢ መሆን ነው።

ዘርፍ ባለንብረትነትን/ገንዘብነትን ያመለክታል።ይህም፡-

በግእዝ ፊደል

በራብዕ ፊደል

በሐምስ ፊደል

በሳቢ ፊደል

በዘ፣እንተ፣እለ እና ለ እየተያያዘ የሚነገር ነው።

ምሳሌ፡-ንጉሠ እስራኤል /የ፷ኤል ንጉሥ/---ግእዝ

ተስፋ ሕይወት /የሕይወት ተስፋ /----ራብዕ

ውዳሴ ማርያም/የማርያም ውዳሴ/----ኃምስ

መሰንቆ ዳዊት/የዳዊት መሰንቆ/---ሳበዕ

ምሳሌ፡-ዘ/እንተ፡-

ንጉሥ ዘ/እንተ ፷ኤል-----   ተስፋ ዘ/እንተ ሕይወት

መሰንቆ ዘ/እንተ ዳዊት

እለ፡-ነገሥት እለ ምድር---ነገሥተ ምድር

እጽዋት እለ አድባር ---እጽዋተ አድባር

አርድእት እለ ጉባኤ

ተስፍሃ ለሕይወት
ውዳሴሃ ለማርያም
ንጉሦሙ ለእስራኤል    } አያያዥ
መሰንቆሁ ለዳዊት

ለሕይወት ተስፍሃ

ለማርያም ውዳሴሃ

ለጀኤል ንጉሦሙ ደፊ

ለዳዊት መሰንቆሁ

- ❖ እንተ እና ዘ በአንድ ላይ ለመግባት ነጠላ ቁጥር ሊሆን ይገባል።
- ❖ እለ እና ዘ በአንድ ላይ ለመግባት ብዙ ቁጥር ሊሆን ይገባል።
- ❖ ለ ሊያያይዝ የሚችለው ስሙ መዘርዘር ከተቻለ ብቻ ነው ካልዘረዘረ አይችልም።

  ምሳሌ፡-መሰንቆ ለዳዊት *

  መሰንቆሁ ለዳዊት +

## ክፍላተ ዘርፍ ሰዋስው

ሀ.የባለቤት ዘርፍ

ለ.የተሳቢ ዘርፍ ተብለው በሁለት ይከፈላል።

### ሀ.የባለቤት ዘርፍ --የማሠሪያ አንቀጽ ባለቤት ሰወስው

ከዚህ በላይ በተመለከቱት አናባብያን ግእዝ ፣ራብዕ ፣ኃምስ እየተናበበ(እየተያያዘ፣እየተጠበቀ) የሚነገር ሰዋስው የባለቤት ዘርፍ ሰዋስው ይባላል፡፡የባለቤት ቅርንጫፍ ማለት ነው።ውስጣዊ ሐሳቡ ባለቤት የሚስበው ሰዋስው ማለት ነው።

ምሳሌ፡-ሰማዕተ ሐሰት ኢይድኅን/የሐሰት ምስክር አያድንም።/

ልሳነ አማጽያን ኢይትሐጐል/የአመጸኞች አንደበት ይጠፋል/።

ብእሲ ዘጥበብ የአምር ብዙሐ/የጥበብ ሰው ብዙን ያውቃል/።

አፉሁ ለጻድቅ ይትሜሐር ጥበብ/የጻድቅ አፍ ጥበብን ይማራል/።

ከናፍር እለ ጻድቃን ይውሕዝ ሞገሰ/የጻደቃን ከንፈሮች ሞገስን ያወጣሉ።

እንስሳ እንተ ገዳም ይገብሩ በዓለ/የበርሐ እንስሳ በዐልን ያደርጋሉ።

- ❖ ተናባቢው ሰዋስው ሳቢ ንዑስ አንቀጽ ከሆነ ዘርፍ ሰዋስው ተሳቢ ዘርፍ ይባላል።ተናባቢ ሰዋስው ስም ከሆነ ግን ዘርፍ እንጅ ተሳቢ የሚለው አይስማማውም።
- ❖ ባለቤት ዘርፍ የሚሆን ቀለማት ሰባት ናቸው ፡እነዚህም ከግእዝ እስከ ሳብእ ያሉት ናቸው

  ግእዝ፡-ባለቤት እንጅ ዘርፍ አይሆንም

  ምሳሌ፡-ማዕደ መሶበ--አይልም

  ማዕደ መሶብ---ይላል

  አርድእተ ደብረ---አይልም

  አርድእተ ደብር----ይላል

  ቤተ ማኅበረ ----አይልም

  ቤተ ማኅበር ----ይላል

- ❖ ካእብ፣ሣልስ እና ሳድስ ዘርፍ እንጅ ባለቤት አይሆኑም

  ምሳሌ፡-ተቀብዐ ቅብዐ ናርዱ ++

  ተቀብዐ ናርዱ ቅብዐ ብእሲ ገጽ **

  ተቀብዐ ቅብዐ ገጸ ብእሲ++

  ተቀብዐ ገጸ ብእሲ ቅብዐ**

ተቀብዐ ቅብዐ ገጸ ሰብዕ

ተቀብዐ ገጸ ሰብዕ ቅብዐ

- ሦስቱ (ራብዕ ፣ኃምስ፣እና ሳብእ) ባለቤትም ዘርፍም ይሆናሉ።

ምሳሌ:-አውታረ ደብተራ } ራብዕ
ደብተራ አሪት

ሥነ-ጽጌ } ኃምስ
ጽጌ-ወይን

መሰንቆ ዳዊት } ሳብዕ
ድምጸ መሰንቆ

- ዘርፍ እና ባለቤት በአገባብ ሲያያዙ በተለያዩ መጠን ባላቸው ፊደላት ሲናበቡ የሚያሳዩት ምሥጢር /ቁም ነገር ብዙ ነው።

<u>፩.ገንዘብን እና ባለገንዘብነትን</u>

ሀ.ምሳሌ:-መዝሙረ ዳዊት

መዝሙሩ ለዳዊት } የዳዊት መዝሙር--ባለቤትነት

መዝሙር ዘዳዊት

→ ተነባቢ ዘርፍ ባለ ገንዘብ

→ ኢነባቢ ባለቤት ገንዘብ

ለ.መልአከ ሰማይ /መልአኩ ለሰማይ /የሰማይ መልአክ

ብእሴ ምድር/ብእሲሃ ለምድር

→ ኢነባቢ ዘርፍ

→ ነባቢ ባለቤት

መልአክ እና ብእሴ ወገን ናቸው።እንዲሁም ሰማይ እና ምድር ባለወገን ናቸው።

መናበብ ሲቀር --መልአክ ሰማያዊ

--ብእሲ ምድራዊ እያሰኘ ይቀጥላል።

ሐ.ዘርፍ እና ባለቤት ሁለቱም ኢነባቢ ሲሆኑ በአንድ አገባብ ብቻ በ«ዘ»፣በ«እለ»እና በ «እንተ» ተያይዘው በአራት ፊደላት ተናበው ሲዘርፉ እና ሲነገሩ ቅጽልና ባለቤት ሁነው ሥራን እና መሣሪያን ያሣያሉ።

ምሳሌ:-ተቅዋም ዘወርቅ ፣ተቅዋመ ወርቅ /ከወርቅ የተሠራ መቅረዝ

ልብሰ ወርቅ፣ልብሰ ዘወርቅ

አርዌ ብርት ፣አርዌ ዘብርት

ወልታ ወርቅ        ወልታ ዘወርቅ

↓ ዘርፍ ኢነባቢ

ባለቤት   ኢነባቢ

ተቅዋማት እለ ወርቅ /ከወርቅ የተሰሩ መቅረዞች /

አርዌ እለ ብርታት /ከብረቶች የተሠሩ እባቦች /

መ.የባሕርይ ስም ከህላዌ ስም ተናቦ ሲዘረፍ የህላዌ ስም ለባህርይ ስም መፍቻና ቅጽል እየሆነ ባህርይ እና መልክን የሚያሳይ።

ህላዌ ስም ---ስመ ተጸውዖ

የባህርይ ስም---ስመ ኁባሬ

ምሳሌ፡-ዕፅ አውልዕ ---ወይራ የሚባል እንጨት

---የወይራ እንጨትነት

---ወይራው እንጨት

ሠ.የግብር ስም ከተጸውዖ ስም ሲናበብ ዘርፍ ባለቤት ቅጽል እየሆነ እንዲሁ ይፈታል።

ምሳሌ፡--ነቢየ ሙሴ /ነቢዩ ሙሴ / ሙሴ የተባለ ነቢይ

ካህን አሮን / ካህኑ አሮን /አሮን የተባለ ካህን

የሚነገረው ሕይወት ላለቸው ነገሮች ነው።ማንኛውም የተጸውዖ ስም ተናቦ ዘርፍ ይሆናል እንጂ እርሱ በሌላ ስም ተናቦ የዘርፍ ባለቤት አይሆንም ።ይህም፡-ኢየሱስ ናዝሬት

ዳዊተ መንግስት

አሮን ካህን።አይልም

ስም ሀገር /የሀገር ስሞች የባለቤት ዘርፍ መሆን ይችላሉ እንጅ የዘርፍ ባለቤት መሆን አይችሉም።

ምሳሌ፡-ናዝረተ ኢየሱስ **

ናዝሬት እንተ ኢየሱስ ++

ኢየሱስ ናዝራዊ ++

ኢየሱስ ናዝሬት **---ስም ተጸውዖ

ጠምዛዥ ---ሦስት ስሞች ሲየያዙ ጠምዛዥ እንለዋለን።

ምሳሌ፡-መና ዘባዕል መሶብ /የባዕል መሶብ የመሶብ እንጀራ /መና እንተ ባዕል መሶብ።

ኀበው ዘ እለ ባዕል መሰውብ /መሰባት

ኀባው ዘ መስውብ ባዕል

፭.መሰንቆ መዝሙሩ ለዳዊት ለሰሎሞን መንበረ ክብሩ --አይልም ምክንያቱም

--የደቂቅ አገባብ የድፋት ድፋት ስለሌለው ማለትም «ለ»ደቂቅ አገባብ ስለሆነች ።

፪.እንተ ሰሎሞን መንበረ ክብር /ዘ ሰሎሞን መንበረ ክብር እለ ሰሎሞን መንበረ ክብራት --ይቻላል።

ምክንያቱም «እለ»፣«እንተ»፣«ዘ» ዐቢያን እና ንዑሳን አገባቦች ስለሆኑ ወይም ደቂቃት ስለሌላቸው ከዚህላይም እንደ ንዑስ አገባብ አገልግለዋል።

## ለ.የተሳቢ ዘርፍ ሰዋስው

የማሰሪያ አንቀጽ ተሳቢ ሰዋስው ከዚህ በላይ በተመለከትናቸው አንባብያን እየተናበቡ /እየተያያዙ ፣እየተጠበቁ የሚነገሩ ሰዋስው የተሳቢ ዘርፍ ሰዋስው ይባላል።

የተሳቢ ዘርፍ ፣የተሳቢ ቅርንጫፍ ማለት ነው ።

ውስጣዊ ሐሳቡ የተሳቢ ተሳቢ ማለት ነው።

ምሳሌ፡-ኢይክል ሰብእ ሙሂአ ፀጋ/ ሰው ጻጋን መቀበልን አይችልም።

ይሜንን አብድ ቃለ ጥበብ /ሰነፍ የጥበብን ቃል ይንቃል ።

ባረከ እግዚእነ ዓመተ ጻድቃን /ጌታችን የጻድቃንን ዓመት አከበረ

ይትሜሐሩ ደቂቀ ፈሪሆት ለእግዚአብሔር /ልጆች እግዚአብሔርን መፍራትን ይማሩ።

አገባብ የወደቀበት የተናባቢ ሰዋስው ዘርፍ ከባለቤት ዘርፍ ይመደባል።

ይእሕዝ ኵሎ <u>በ</u>ኃይለ ቃሉ /ቃሉ/ በ--አገባብ

ሰአሮ ውእቱ ለመልአከ ሞት/

ኡቅዎሙ ለ <u>ገብረተ እኪት</u>/ እኪት

↓ ተናባቢ ሰዋስው ዘርፍ ነው ግን አገባብ

ስለ ወደቀበት ባለቤት ዘርፍ ሆኗል።

# ምዕራፍ ---፲፪

## አገባብ

በሰዋስው መነሻ ፣በመካከል እና በመድረሻ ላይ እየገባ ሰዋሰውን ነጂ ወይም ተነጂ ሆኖ የሚነገር ብትን ነገር ሰዋሰው አገባበብ ተብሎ ይጠራል።በሌላ አገላለጽ አገባብ ማለት የሰወስው አሰባሰብ የሰዋስው አሰካክ ማለት ነው።ለቅርጸ ፊደሉ ተሰጥቶ ሰዋሰውን ሰብሳቢ ማዣኪያና በማያያዣ ማለት ይሆናል።

የአገባብ ጠባዩ ሰወሰውን መሰብሰብ ማያያዝ እና ማሳካት ዐ.ነገርን ማሰማት ነው።ቀደምት መምህራነ ግዕዝ ይህን የአገባብ ጠባይ በጭቃ ይመስሉታል ማለትም አናጺ ድንጋይን ከድንጋይ ጋር ለማያያዝ የሚጠቀመው ጭቃን ስለሆነ ይህም ወደ አገባብ ስንቀይረው ሰዋሰው ሁሉ አገባብ ገብቶ ካላያያዘው በቀር ያልተሰበሰበ፣ያልተሳካና ያልተስማማ ብትን ይሆናል ማለት ነው።

## ክፍላተ አገባብ

የአገባብ ክፍሎችን በዐራት ክፍለን ማየት እንችላለን።

ሀ.ተውሳከ ግስ /አንቀጽ አጐላማሽ /adverb

ለ.ዓቢይ አገባብ /መስተጻምር/conjunction

ሐ.ንኡስ አገባብ /መስተዋድድ/priposion

መ.ደቂቅ አገባብ /መስተዋድድ /priposition

### ሀ.አንቀጽ አጐላማሽ/ተውሳከ ግስ

ተውሳከ ግስ ማለት ከሁለት ቃላት የተገኘ ሲሆን እነዚህም «ተውሳክ» እና «ግስ» ናቸው።ተውሳክ ማለትም /ወሰከ፣ተወሰከ---ጨመረ፣ተጨመረ/ከሚለው የግዕዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ተውሳክ ማለት የተጨመረ፣የተደረበ ማለት ነው ።ተውሳከ ግስ ስንል ደግሞ ከግሱ ላይ እየተጨመረ የግሱን እንዴት ፣መቸ፣ለምን፣የት ወዘተ የሚሉትን የትርጉም ሁኔታ የሚወስኑ አንቀጽ አጐላማሾች ማለት ናቸው። የግስ ረዳት/ኢጋዥ እየተባለም ይጠራል።

- ❖ አንቀጽ አጐላማሽ የምንለው ተግባሩ/ሥራው ፡-
  - ---አንቀጽ/ግስን መግለጽ /ማጐላመስ
  - ---ሌሎችን ተውሳከ ግሶች መግለጽ/ማጐላመስ
  - ---ቅጽሎችን መግለጽ
  - ---ሐረጋትን መግለጽ
  - ---ዐ.ነገሮችን መግለጽ ናቸው።

***ክፍላተ ተውሳከ ግስ***

ተውሳከ ግስ የተለያዩ ክፍላት አሉት እነዚህም የሚከተሉት ናቸው።

፩.ተውሳከ ግስ ዘ ኵነት/ሁኔታ/adverb of manner/

፪.ተውሳከ ግስ ዘ መካን/የቦታ /adverb of place/

፫.ተውሳከ ግስ ዘ ጊዜ /adverb of time/

፬.ተውሳከ ግስ ዘ ደጊሞት/adverb of frequency/

፭.ተውሳከ ግስ ዘ እሙን/adverb of certainity/

፮.ተውሳከ ግስ ዘ መልዕል/adverb of degree/

፯.ተውሳከ ግስ ዘ ጥያቄ /adverb of introgative/

፰.ተውሳከ ግስ ዘ ምክንያት/adverb of reasone

***ሀ. ተውሳከ ግስ ዘ ጊዜ***

የጊዜ፣የግስ ተውሳኮች ጊዜን የሚገልጹ ወይም አንድ ድርጊት መቸ እንደተከናወነ የሚጠቁሙ ናቸው ።when የሚለውን ጥያቄ የምንመልስበት ማለት ነው።

እነዚህ የተውሳከ ግስ ዓይነቶች ፡-

---ዮም-ዛሬ/to day

---ትማለም-ትላንት/yester day

---ጌሰም-ነገ/tomorrow

---ቅድም ትማለም-ከትላንት በፊት/before yester day

---ድኅረ ጌሰም-ከነገ በስቲያ /after tomorrow

ምሳሌ እና የቀሩትን ትንሣኤ ግዕዝ ገጽ ፻፶፬ ተመልከት

***ለ ተውሳከ ግስ ዘ ኩነት***

የኩነት ተውሳከ ግሶች አንድ ድርጊት በምን ሁኔታ እንደ ተፈጸመ የሚያሳይ /አንቀጽ አጉልማሽ ነው።በሌላ መልኩ How የሚሉ ጥያቄዎችን የምንመልስበት ነው።

በዚህ ተውሳከ ግስ ውስጥ የሚገኙትን ለምሳሌ፡-

ፍጡነ--በፍጥነት /quickly/fastly

ጽሚተ-በቀስታ/slowly

ደኅና-በደና /well

ምሳሌ፡-ተጽኢኖ ዲበ እዋል ቦአ ሀገረ ኢየሩሳሌም፡

በሊአ ኅብስተ መና ኖመ ወደቀሰ፡

መጽአ ውስተ ዓለም ተፈኒዎ እምነ አቡሁ፡

ሖረ ያንብብ መጽሐፈ፡

ተንሥአ ይሁር ትእንተ፡

ፈቀደ እግዚእ ያግዞ ለአዳም፡

መጽአ ፍጡነ ሶበ ሰምአ ሞተ እሙ፡

መጽአ ይሁዳ ጽሚተ ምስለ አይሁድ ስመ የሀብዎ ለወልደ እጓለመሕያው፡፡

ኵነታዊ ተውሳከ ግስ ዘንድ አንቀጽን እና ቦዝ አንቀጽን እንደ ገላጭ ይጠቀማቸዋል።ከላይ የተሰጡትን ምሳሌዎች ተመልከት።

በግእዝ ቋንቋ በሳድስ ፊደል የሚጨርሱ ቃላትን ግእዝ በማናገር /በግዕዝ እንዲጨርሱ በማድረግ በ፣ወደ እና ከ የሚሉትን የአማርኛ ፍቺ ማምጣት ይቻላል።ሌሎችም እንዲሁ፡፡

ምሳሌ፡-ዐርገ ሰማየ--ወደሰማይ ዐረገ

ወሖረ ብሔረ--ወደ ሐገር ሔደ

ሖረት ብሔረ ርሑቀ--ወደ ሩቅ ሀገር ሄደች

ሖረ ቤቶ--ወደ ቤቱ ሄደ

ወአኀዙ ኪያሁ ይእተ ሰዓተ--እርሱን በዚያች ሰዓት ያዙት

ይገብር ግብሮ መዓልተ ወሌሊተ/በመዓልት ወበሌሊት --በቀንም በሌሊትም ሥራውን ይሠራል።

ወልድ ተንሥአ ቤተ አቡሁ /ተንሥአ እምቤተ አቡሁ --ከአባቱ ቤት ተነሣ

***ሐ.ምክንያትን የሚፈልጉ***

አስረጂ ተብሎ ይጠራል።«ና» የሚለውን ፊደል የሚወልድ ነገሩ ወይም ሁኔታው ለምን እንደተፈጸመ የሚያመለክት የተውሳከ ግስ ዓይነት ነው።

ምሳሌ፡-እስመ---------ና

አምጣነ-------ና

አኮኑ ---------ና

ምሳሌ፡-ሖረ        እስመ/አምጣነ/አኮኑ ሖረ----ሒዷልና

»»        »»»ሖርነ----ሒደናልና

»»        »» ሖርከ----ሒደሐልና

»»        »»ሖርክሙ----ሒዳችኋልና ወዘተ

ምሳሌ፡- አምጣነ ተወለድ መድኅን ለክብረ ቅዱሳን ፡፡

እስመ ሖረ ኀበ ምኔተ ዋልድባ ተወከፈ ብዙኃ በረከተ፡፡

ፈቀደ እግዚእ ያግእዞ ለአዳም አኮኑ/እስመ ቦአ ምድረ ፋይድ፡፡

አኮኑ በግስ ይወሰናል፡፡    አኮኑ አልቦ --አይባለም አኮ --ይባላል፡፡

*መ.ሁኔታን የሚገልጽ*

እመ/ለእመ---ምንም እንኳን/although/

ለእመ/እመ---ኢካለ/if not/

ባሕቱ ----ነገር ግን/but/

አላ ----ይኹን እንጂ/neverthelese, how ever/

ምሳሌ፡-<u>ለእመ መጽአ</u> ኢተመይጠ ልቡ/ቢመጣም እንኳ ልቡ አልተመለሰም /although he came, did not come his heart.

<u>ለእመ ኢሖረ</u> ተመጽአ እሙ /ካልሔደ እናቱ ትመጣለች/if he did not go , his mather will come.

ለእመ ቅዱስ አንተ ረድእ እመስቀልከ /ቅዱስ ከሖንሕስ ከመስቀል ውረድ/

*ሠ.ውጤትን አመልካች*

አንድ የተፈጸመን ድርጊት በመደረጉ የሚገኘውን ውጤት የሚያሳይ ነው፡፡

በእንተዝ----ስለዚህ/therefore, hence, as a result/

በእንተ ዝንቱ---ስለዚህ/>> >>

በእንተ ውእቱ----ስለሱ/sothat

ወበእንተ ዝ ----ስለዚህ/ም /

ምሳሌ፡-አነ ሖርኩ ኀበቤተ እግዚአብሔር ፣በእንተዝ ረከብኩ በረከተ ቅዱስ /እኔ ወደ ቤተ እግዚአብሔር ሔድኹ ስለዚሆ/ም የቅዱሳንን በረከት አገኘሁ/

--ዮም ተወልደ መድኃኔዓለም ፣በእንተዝ ተፈሥሓ ኵሉ ዓለም፡፡

--ኦ ማርያም በእንተዝ ናፈቅረኪ እስመ ወለድኪ ለነ መብልአ ጽድቅ /ማርያም ሖይ እናመሰግንሻለን የእውነት መብልን ወልደሽልናል እና፡፡

በእንተ ዛቲ/because of this

በእንተ ዝንቱ/because of this

በእንተ እሙንቱ/እማንቱ/because of these

በእንተ ኵሉ/for all

በእንተ ዝስኩ/because of that

በእንተ ይእቲ/because of that

*ረ.ቦታ ገላጭ*

አንድ ነገር የት ወይም ወዴት እንደተፈጸመ የሚያመለክት ነው ፡፡

ህየ/ካሃ----እዚየ

ዝየ-----ከዚህ

በላዕለ----በቅድመ

በውስተ----በድኅረ

ውሳጤ----ውስተ

አፍአ----

ዲበ-----

በዲበ-----

ታህት----

ቅድመ----

ምሳሌ፡--መጽሐፍየ ሀሎ በውሳጤ ቤት ምስለ ካልአኒሁ፡፡

ሑር ኀበ መርቄ ከመ ታምጽእ እጸመ፡፡

መጽኡ እምነ እስክንድርያ ከመ ይትመሀሩ ጥበበ፡፡

ንበር ዝየ ከመ ትንግረነ ግብሮሙ ለሐቃልያን፡፡

ብእሲሁ ነበረ አፍአ ቤት እስመ ኀዘነ በእንተ ሞተ ብእሲቱ፡፡

ዝንቱ ሆባይ ተጽዕነ ዲቤሁ ለዝኩ ተክል፡፡

ዘአጽንአ ለምድር ዲበ ባህር /በላዕለ ባህር በክሂሎቱ፡፡

ንህነ ሖርነ ኀበ ገዳመ ሐይቅ ፣ወበህየ ረከብነ ሳለመ ቅዱሳን/እኛ ወደ ሐይቅ ገዳም ሔድን በዚህም/በዚያም የቅዱሳንን ሰላም አገኘን፡፡

ክርስቶስ ተሐተተ ቅድመ ጲላጦስ /በቅድመ ጲላጦስ

ሰ.ተውሳከ ግስ ዘጸዊምት

በጊዜ ውስጥ ምን ያህል ጊዜ/የሚለውን ጥያቄ የምንመልስበት ነው፡፡

ኵለሄ---ሁልጊዜ /usually

ዳግመ---ሁለተኛ ጊዜ/secondary

ክልኤ ጊዜ---ሁለት ጊዜ /twice

ዋሕድ ዋሕድ ጊዜ ---አንዳንድ ጊዜ/some times

ዘልፈ/ወትረ ----ኹል ጊዜ /always

ምሳሌ፡-ኵለሔ የሐውር ኀበ ቤ.ክ፡፡

መብዝኀት ጊዜ ነሐውር ኀበ ፈለግ፡፡

አሐደ አሐደ ጊዜ ነሐውጽ መካናተ ቅዱሳተ፡፡

አርባዕተ ጊዜያተ ተወክፈ ቁርባነ፡፡

ወዘ አዝለፈ ትዕግስቶ ውእቱ ይድኀን፡፡

ወትረ ይሴብሑ ፈጣሪሆሙ፡፡

ዳግመ ይትነሥኡ ሙታን አመ ይመጽእ ክርስቶስ፡፡

## ለ.ዐቢይ አገባብ /መስተጻምር/

በሰዋስው ላይ /በአንቀጽ እና በስም /ላይ እየወደቀ /እየገባ/የሚነገር ብትን ነገር ሰወሰው ዐቢይ አገባብ ይባላል፡፡ዐቢይ ታላቅ ጽኑ ብርቱ ማለት ነው፡፡

ዐቢይ የተባለበት ምክንያት በሰወስው በአንቀጽ፣በነባር፣በዘማች እና በስም ላይ ወድቆ የአንቀጽን ማሰሪያነት ስለሚያፈርስ ነው፡፡

አገባብ የተባለበት ምክንያት በሰወስው በአንቀጽና በስም ላይ እየወደቀ ሰወስውን ስለሚያሳካ፣ዐ.ነገርን ስለሚያስማማ ነው፡፡

በአጠቃላይ ዐቢይ አገባብ ----በአንቀጽ

----በባለቤት<br>
----በተሳቢ<br>
----በሌሎች አገባብ

} ላይ እየወደቀ ሥራውን ይሠራል፡፡

ምሳሌ፡--አምጣነ/አኮኑ ተሰቅለ አምላከ ፀሐይ ጸልመ /በአንቀጽ ላይ/

ከመ ጸሐፈ ሙሴ በእደዊሁ አነሂ ጸሐፍኩ፡፡

ዮሐንስ ጸሐፈ ከመ ሙሴ ወእዝራ /ስም ውይም ባለቤት/

እስራኤል ወሙሴ አበው እሙንቱ ፡፡

በጊዜ ተሰቅለ ወልድ ፀሐይ ጸልመ /በአገባብ ላይ/

በከመ ኮነ በማየ አኅ ይከውን ብነ ለኃጢያትነ

ወበከመ ሙሴ ሰቀሎ ለአርዌ ምድር በገዳም ከማሁ ይሰቀል ክርስቶስ በእጸ መስቀል፡፡

ዐቢይ አገባብን በሦስት ታላላቅ ክፍሎች ከፍሎ መመልከት ይቻላል፡፡

ሀ.ምክንያት አስረጂ /ገላጭ/ዐቢይ አገባብ

ለ.ማንጸሪያ/ማነጻጸሪያ ዐቢይ አገባብ

ሐ.አሉታ/አፍራሽ ዐቢይ አገባብ

### *ሀ.ምክንያት አስረጅ ዐቢይ አገባብ*

በአንቀጽ ላይ እየወደቀ /እየገባ/የነገር፣የድርጊት፣የሁኔታና የጊዜ ምክንያትን የሚያስረዳ አስረጅ ዐቢይ አገባብ ይባላል፡፡

ይህ ክፍል በውስጡ ብዙ አገባቦችን ይዟል

---«ና» የሚሆኑ አገባቦችን

---«ስለ» የሚሆኑ አገባቦችን

---«ዘንድ» የሚሆኑ አገባቦችን

---«ጊዜ» የሚሆኑ አገባቦችን

---«ኋላ፣በኋላ» የሚሆኑ አገባቦችን

---«እስኪ፣እስከ፣እስክ» የሚሆኑ አገባቦችን

---«ከ-ጀምሮ የሚሆኑ አገባቦችን ወዘተ ይዟል፡፡

፩.«ና» የሚሆኑ አገባቦችን- አምስት ናቸው፡፡

እስመ፣አምጣነ፣አኮኑ፣ስ፣ወ ናቸው፡፡

ምሳሌ፩፡-እስመ/አምጣነ/አኮኑ አኮ ዛቲ ዓለም ዘትነብር ለዓለም፡፡

ይሬእይዋ ጻድቃን ከመ ውሉደ እግዚአብሔር ይትዔገሡ፡፡

በእንተ ክርስቶስ መከራ አኮኑ/እስመ/አምጣነ ውእቱ አርአያሆሙ ለዛቲ ትዕግስት ዝንቱ ክርስቶስ፡፡

/ጻድቃን ይህችን ዓለም ለዘለዓለም የምትኖር እንዳይደለች ያይዋታልና እንደ እግዚአብሔር ልጆች ስለ ክርስቶስ መከራን ይታገሣሉ ይህ ክርስቶስ ለዚች መከራ ምሳሌአቸው ነው፡፡

፪.ብጹአን ጻድቃን እስመ እሙንቱ በየማነ ክርስቶስ ዘይቀውሙ ወአኮ ዘይቀዉሙ በጸጋሙ፡፡

/ጻድቃን የተመሰገኑ ናቸው እነርሱ በክርስቶስ ቀኝ ይቆማሉና በግራውም አይደለም/

፫.ሰማዕት ኢፈርሑ ሞተ ሥጋ እስመአምጣነ/አኮኑ ይሬእይዋ በዓይነ ተሥፋ ለመንግስተ ሰማያት ዘበምክንያተ ይወርስዋ፡፡/ሰማዕት የሥጋ ሞትን አልፈሩም በሞታቸው ምክንያት ሊወርሷት እንዳላቸው በተስፋ ዓይን መንግስተ ሰማያትን ያዩአታልና፡፡

፬.እስመ/አምጣነ ልዑል እግዚአብሔር ይሴባሕ በኀበ ልዑላን፡፡/እግዚአብሔር ታላቅ ነውና በታላለቆች ዘንድ ይመሰገናል፡፡/

አምጣነ ባዕል እግዚአብሔር ኢየኀጥአ ዘይሁቦሙ ለነዳያን

አኮኑ ማዕምር እግዚአብሔር ይትነከር በኀበ ማእምራን፡፡

፭.ኢንረክቦ ለኤልያስ እስመ ሀገሩ ገነት፡፡

፮.ጻድቃን ይብልዎ ለክርስቶስ እንዘ ይመጽእ ላዕሌሆሙ መከራ ሥጋ ኄር ውእቱ አምጣነ ይኩን ዝ መከራ ሕይወተ ነፍሳቲሆሙ /ጻድቃን የሥጋ መከራ በላያቸው ሲመጣባቸው ይህ መከራ የነፍሳቸው ድኅነት ይሆን ዘንድ ነውና ክርስቶስ ቸር ነው ይላሉ፡፡

በኃላፊና በትንቢት መግባት ይችላሉ፡፡ኢፈጸሙ አይሁድ ሕገ ወንጌል ይትረሳዕሰ /ይዘንጋዕሰ/ይጽናሕሰ/ይትጎድግሰ/ይትርፍሰ ዝንቱ፡፡ሕገ ኦሪትኒ/ጥቀ/ን ወሕገ ኦሪት ኢፈጸሙ፡፡/አይሁድ ሕገ ወንጌልን አልፈጸሙም ይህስ ይቅርና የኦሪትን ሕግ ስንኳ አልፈጸሙም ፡፡

መጽኡ ሚካኤል ወገብርኤል /ሚካኤልና ገብርኤል መጡ፡፡/--በስም

ከብሩ አዳም ወሔዋን ፡፡

፪.ስለ የሚሆኑ አገባቦች ፡-

ስለ የሚሆኑ አገባቦች ብዙ ናቸው፡ከእነዚህም ውስጥ--

---በእንተ ተውላጠ ቤዛ

---በይነ አስበ/ደምስነትን ሳይለቅ/ ተክለ/ምትክነትን ሳይለቅ

---እንበይነ እስመ ዓይነ

---ህየንተ መጠነ በቀለ

---ፍዳ/ብድራትን ሳይለቅ/ አምጣነ እሜተ/ዋጋነትን ሳይለቅ/

እነዚህ አገባቦች ብዙዎቹ

---በኃላፊ አንቀጽ ነግባት

---በስም መግባት

---በዐሥሩ መራሕያን መዘርዘር

---በአርእስት/በንዑስ አንቀጽ መግባት/

ምሳሌ፡-ፈደይዎ አይሁድ ለእግዚእነ ህየንተ /ተውላጠ/በእንተ ዘገብረ ሠናየ/አይሁድ ጌታችን በጎ ስላደረገ ክፉን ከፈሉት/፡፡

---ብጻእ ዘይትቤቀለኪ በቀለ/መጠነ/አቅመ/በይነ/እንበይነ ተበቀልክነ፡፡/ስለተበቀልሽን የሚበቀልሽ ንኡድ ክቡር ነው/

---ጸልዩ በእንተ ሀገሪትነ ኢትዮጵያ /ስለ ሀገራችን ኢትዮጵያ ጸልዩ፡፡/

---በእንተ ተአርቆቱ ገ/መንፈስ ቅዱስ ለብሰ ጸጉረ፡፡/ገብረ መንፈስ ቅዱስ ስለ መራቆቱ/መታረዙ ጸጉርን ሰበሰበ፡

---በይነ ዘተዋረደ አዳም ሞተ እግዚእ /አዳም ስለተዋረደ ጌታ ሞተ/፡፡

፫.ዘንድ የሚሆኑ አገባቦች

በዚህ ርዕስ ስር የሚመደቡ አገባቦች የሚከተሉት ናቸው ፡-

---ኀበ

---መንገለ

---ወ/ውእደ/በኃላፊ ብቻ ይላሉ/

---ከመ/ሣልሳይ አንቀጽ ይገባል/

---ሣልሳይ አንቀጽ

እነዚህ አገባቦች ብዙዎቹ --በኃላፊና በትንቢት ይገባሉ

--በስም ላይ ይገባሉ

--በዐሥሩ መራሕያን ይዘረዘራሉ፡፡

ምሳሌ፡-ኀበ ለብሰ ሥጋሃ ለማርያም አምላክ ዘሀሎ በአርያም ሞተ ከመ አበዊሁ እለ አዳም፡፡

/በሰማይ በከፍታ ያለ አምላክ የማርያምን ሥጋ ከለበሰ ዘንድ እንደ አባቶቹ እንደነ አዳም ሞተ/

--ኀበ ሠርዐ--ከሠራ ዘንድ

ኀበ ሠራዕከ --ከሠራህ ዘንድ -----እያልህ ዝለቅ

--ወእደ ተናገረ ገብርኤል አውሥኦት ማርያም እንዘ ትብል እፎ ይከውነኒ ዝንቱ እንዘ ኢየአምር ብእሴ፡፡/ገብርኤል ከተናገረ ዘንድ ማርያም ይህ እንዴት ይሆንልኛል ወንድ ሳላውቅ ስትል መለሰች/

---መኑ ውእቱ እግዚአ ከመ እእመን ቦቱ፡፡/ማነው አቤቱ አምንበት ዘንድ/

---አመ እፍታሕ/ትፍታሕ/ይፍትሑ/ትፍትሑ.....

---ኢይከውነከ ታውስብ ብእሲተ እኁከ /የወንድምህን ሚስት ታገባ ዘንድ አይገባህም፡፡/

<u>፬.ጊዜ የሚሆኑ አገባቦች</u>

በዚህ ርዕስ ሥር የሚጠቃለሉ አገባቦች ፡-

| | | |
|---|---|---|
| አመ | መዋዕለ | አፈ |
| ሶበ | ሰዓተ | ግዕዝ |
| ጊዜ | ዕለተ | ፍና |
| ዓመተ | ስዓ | በ |

እነዚህ አገባቦች በሚገቡበት ጊዜ ብዙዎቹ፡-

---በኃላፊና በትንቢት አንቀጽ ይገባሉ፡፡

---በዐሥሩ መራሕያን ይዘረዘራሉ፡፡

---በስም ላይ በተወሰነ ይገባሉ፡፡

ምሳሌ፡-አመ ተሰቅለ ክርስቶስ ፀሐይ ጸልመ ወርኅኒ ደመ ኮነ/ክርስቶስ በተሰቀለ ጊዜ ፀሐይ ጨለመ ጨረቃም ደም ሆነ፡፡/

--አመ ይነግሥ ቴዎድሮስ በመንበረ ዳዊት ወልደ እሤይ ይትፌሥሑ ግፉዓን፡፡

/በእሤይ ልጅ በዳዊት ዙፋን ቴዎድሮስ በሚነግሥበት ጊዜ የተበደሉ የተገፉ ደስ ይላቸዋል፡፡/

-- ሶበ ቀሰመ/ይቀስም/ቀሰምከ/ትቀስም/ቀሠሙ/ይቀሥሙ

---አመ ሰበረ/ይሰብር/ሰበርከ/ትሰብር/ሰበሩ/ይሰብሩ

---በዓመተ ነግ /ይነግሥ ዳዊት ኢየሩሳሌም ረከበት ሰላመ

---በመዋዕለ ነግሠ ሰሎሞን ተፈሥሑ በሕቁ ፳ኤል /ሰሎሞን በነገሠ ጊዜ እስራኤል እጅግ ደስ አላቸው፡፡

---ፍና ሠርክ ቦአ አዳም ውስተ ገነት ፡፡

---በአፈ ጽባሕ ወጽአ ሎጥ እምሀገሩ፡፡

---በምንዳቤከ ጸማዕከኒ ወአደንኩከ፡፡

---ወተወሊደ ኢየሱስ በቤተ ልሔም /በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ/፡፡

ፎ.ኋላ፤በኋላ የሚሆኑ አገባቦች

በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኙ አገባቦች፡---ድኅረ/ወደን በትርፍ አማርኛ ያመጣል/

---ከዋለ

---እምዝ ናቸው፡፡

እነዚህ አገባቦች ፡---በዐሥር ሠራዊት ይዘረዘራሉ ፡፡

---ከነገር በፊት እየገቡ ማሠሪያ ያስቀራሉ፡፡

---ከነገር በኋላ ሲገቡ ማሠሪያ አያስቀሩም ፡፡

---በስም በግብር ለብቻ /ተለይቶ/ይገባል፡፡

ምሳሌ፡--ዝናብ ኃለፈ ወገባ ድኅሬሁ /ዝናም አለፈ ወደኋላውም ተመለሰ/፡፡

---ተኖልወኒ በፍጽም ወዕቀበኒ በከዋለ/በፊት እና በኋላ ጠብቀኝ/

---ወያገብኦሙ ለኵሎሙ ፀርነ/ጠላቶቻችንን ሁሉ ወደኋላ ይመልሳቸወል/፡፡

---ድኅረ ነግሠ ዳዊት ነግሠ ሰሎሞን/ዳዊት ከነገሠ በኋላ ሰሎሞን ነገሠ፡፡

---እምዘረወዩ አግማሊሁ ሖረ ኢያውብር ውስተ ቤተ ባቱኤል/ኢያቡር ግመሎች ከጠጡ በኋላ ወደ ባቱኤል ቤት ሔደ/፡፡

ጂ.የ የሚሆኑ አገባቦች

በዚህ ሥር የሚገኙ አገባቦች ፡-

--ዘ ውስጠዘ አመ

--እንተ ኀበ ተናባቢ ቀለማት

--እለ ወእደ/ለቦታ ብቻ ይቀጸላሉ/

እነዚህ አገባቦች ብዙዎቹ፡-

--በትንቢት ፡ኃላፊ ይገባሉ--በነባር አንቀጽ

--በዐሥሩ መራሕያን ይዘረዘራል

--በስም፣በቅጽል፣ይገባሉ፡፡

ምሳሌ፡--ተሰቅለ እግዚእ ዘፈጠረ መላእክተ/መላእክትን የፈጠረ እግዚአብሄር /ጌታ ተሰቀለ

--አምላክ ዘለብሰ ሥጋ አድኃነ ዓለመ /ሥጋን የለበሰ አምላክ ዓለምን አዳነ/

--ሀቡ ዘነጋሢ ለነጋሢ ወዘ እግዚአብሔር ለእግዚአብሔር/የንጉሥን ለንጉሥ የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ሥጡ፡፡

--ዘሂ በልዐ ለእግዚአብሔር በልዐ ወአኰቶ ለእግዚአብሔር ወዘሂ ኢበልአ ለእግዚአብሔር ኢበለዐ ወአኰቶ ለእግዚአብሔር/የበላም ለእግዚአብሔር በላ እግዚአብሔርን ያመሰግነዋል ያልበላም ለእግዚአብሔር አልበላም እግዚአብሔርን ያመሰግነዋል፡፡

---ዚአየ ውእቱ ገለአድ ወዚአየ ምናሴ /ገለአድ የኔ ነው ምናሴም የኔ ነው //ገለአድም ምናሴም የኔ ነው፡፡

---ዘአየ/ከ/ኪ/ሆሙ....

---ሰትየ እንተ ወይን ሠይፎ ጊዮርጊስ ጽሙ/የተጠማ ጊዮርጊስ ውይን ሰይፍን ጠጣ/፡፡

---አርድዕት እለ ተምህሩ ሰወስዎ ግዕዝ ተርጐሙ መጻሕፍት /የግእዝን ቋንቋ የተማሩ ተማሪዎች መጻሕፍትን ተረጐሙ፡፡

---ናክብር ኀበ ተሰቅለ /ወእደ ተሰቅለ እግዚእነ /ጌታችን የተሰቀለበትን ቦታ እናክብር

---ተዘርው ሐዋርያት በዕለት አመ ተእህዘ እግዚእነ/ጌታችን በተያዘ እለት/ጊዜ ሐዋርያት ተበተኑ፡፡

---ወልደ እግዚአብሔር /የእግዚአብሔር ልጅ

---ብእሴ እግዚአብሔር /የእግዚብሔር ሰው

<u>፯.ወደ የሚሆኑ አገባቦች</u>

በውስጡ የሚይዛቸው አገባቦች ፡-

| | | |
|---|---|---|
| --ኀበ | ግእዝ | ተናባቢ ቀለማት |
| መንገለ | ራብዕ | ለ፣ዘ |
| እንተ | ኃምስ | እሞ |
| ውስተ | ሳብዕ | |

ከ ኀበ እና መንገለ ውጭ ያሉት በቦታ ይገባሉ

ምሳሌ፡-ተፈነወ ሙሴ ኀበ/መንገለ ፈርኦን፡፡/ወደ ፈርዖን ተላከ

ሖረ እንተ ገዳም /ወደ ዱር ሔደ/

ጸውአ ዮሐንስ አሕዛበ ውስተ ንስሐ /ወደ ንስሐ/

ተመይጠ ለብሔረ ግብጽ /ወደ ግብጽ ሀገር ተመለሰ

አርገ ኤልያስ ሰማየ/ኤልያስ ወደ ሰማይ ወጣ

አርገ ዘሰማይ/ወደ ሰማይ ወጣ

ወረደ ዘምድር/ወደ ምድር

ሖረ ኢየሱስ ገሊላ/ኢየሱስ ወደ ገሊላ ሔደ

ሖረ ጳውሎሶ ተሰሎንቄ/ወደ ተሰሎንቄ

ሖረ ጳውሎስ ደማስቆ/ወደ ደማስቆ

ዐፍቀረ ዕርገተ ሰማይ /ወደ ሰማይ መውጣትን ወደደ

በዘይነቅዕ እምሥራቅ የሐውር እምእራብ ከመ ይሰቂ ህየ

/ከምሥራቅ የሚመነጨው ወደ ምዕራብ ይሔዳል በዚያ ያጠጣ ዘንድ/

<u>፰.እየ የሚሆኑ አገባቦች</u>

እነዚህ አገባቦች በሚከተለው መንገድ ይቀመጣሉ ፡-

--ለለ --በበ

--እንዘ --ኀበኀበ

--እንተ --ከመከመ

--ዘዘ --አምጣነ ናቸው፡፡

እነዚህ አገባቦች --በኃላፊ ፣በትንቢት ይገባሉ፡፡

--በስም ይገባሉ /የተጸውዖን ስም ላይጨምሩ ይችላሉ፡፡

ምሳሌ፡--ለለ ጸብሐ ሌሊት ወለለ መስየ መዓልተ ተሰብሐ እግዚአብሔር በአፈ ኵሉ ፍጥረት፡፡

/ሌሊቱ እየነጋ ቀኑ እየመሸ እግዚአብሔር በፍጥረት አንደበት ሁሉ ተመሰገነ፡፡/

ኵሉ ሰብ የሐውር ለለ ሀገሩ /ሁሉ ሰው /ሰው ሁሉ እየ ሀገሩ ይሔዳል፡፡

ለለ እለቱ/ዓመቱ እየ ዕለቱ ፣እየ ሰዓቱ

በጽሐ ዮሐንስ እንዘ ይሰብክ በገዳሞ /ዮሐንስ በገዳም እየሰበከ መጣ /ደረሰ

ነፍሰ ርኀብተ እንተ ጸግበት ተአኰተከ /የተራበች ሰውነት እየጠገበች ታመሰግንህአለች፡፡/

እንተ ጸብሐት የሀበነ ምሕረቶ /እየዕለቱን ምሕረቱን ይስጠን

ለኵሉ ዕፅ ፍሬሁ ዘዘዚአሁ/የእንጨት ሁሉ ፍሬው በየብቻ ነው

ወረዱ መላእክት በበ ጾታሆሙ /በየነገዳቸው

ፍጥረት ይነብር በበመካኑ /በየቦታው

በበዕለቱ፣ሰዓቱ/ሰዓት/፣በበወርኁ፡በበዓመት/በየዕለቱ ወሩ ሰዓቱ ዓመቱ/

የሐምዮ ሰብእ ለእግዚአብሔር አምጣነ ይሁቦ ሲሳዮ ወልበሰ/ምግቡና ልብሱን እየሰጠው ሰው እግዚአብሔርን ያማዋል፡፡

<u>፱. ያህል የሚሆኑ አገባቦች</u>

እነዚህ አገባቦች ---መጠነ

---አምጣነ

---አቅመ ያጠቃልላሉ፡፡

እነዚህ አገባቦች ---በኃላፊ

---- በትንቢት

---በስም

---በግብር  ይገባሉ፡፡

ምሳሌ፡-ነግሠ ሰሎሞን መጠነ /አምጣነ/አቅመ ዘነግሠ ዳዊት አቡሁ/ሰሎሞን አባቱ ዳዊት የነገሠውን ያህል ነገሠ/፡፡

---ተወከፈ እም እኁኩ መጠነ/አምጣነ/አቅመ ዘወኀብኮ/ለወንድምህ የሰጠኸውን ያህል ከወንድምህ ተቀበል/

---ነግሠ ቴዎድሮስ መጠነ ምኒልክ ቀዳማዊ /የምኒልክ ቀዳማዊን ያህል/

---አ ዳዊት ነግሠ ሰሎሞን መጠነ አንተ ላዕለ ፟ኤል /ዳዊት ሆይ ሰሎሞን ያንተን ያህል በ፟ኤል ላይ ነገሠ/

---ይነግሡ ሐዋርያት አቅመ ዘወኀቦሙ ዓመ ይመጽእ ዳግመ /ሐዋርያት ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ በሰጣቸው መጠን ይነግሣሉ/

ፊት የሚሆኑ አገባቦች /ቅድመ፣ቅድም፣ፍጽም፣ፍጽመ/

መኻከል የሚሆኑ አገባቦች /ማዕለ፣ውስተ/

የእስከ አገባብ

## ሊ ማንጻሪያ/ ማነጻጸሪያ/ ዓቢይ አገባብ

በአንቀጽ ላይ እየወደቀ/እየገባ/ነባርን፣ድርጊትን፣ሁኔታን፣ጊዜን ያነጻጽራል፡፡

በዚህ ክፍል ውስጥ የምንመለከታቸው አገባቦች «እንደ» የሚሆኑ አገባቦችን ነው፡፡እነዚህም አገባቦች የሚከተሉት ናቸው፡-

| | | |
|---|---|---|
| ከመ | ጽላሎተ | ወ |
| መጠነ | አያተ | ሶበ |
| ሕገ | በዘ | ግእዝ |
| አርአያ | እምዘ | ራብዕ |
| ምስለ | ቦ | ኃምስ |

አምሳለ ሳቢ ዘር ሳብዕ

ህየንተ አርእስት መዋዕለ/በስም በግብር ገብቶ/

እነዚህ አገባቦች ብዙዎቹ ፡---በኃላፊ እና በትንቢት አንቀጽ ይገባሉ

---በዐሥሩ ሥራዊት ይዘረዘራሉ

---በስሞች ላይ ይገባሉ/ይጫናሉ/

ምሳሌ፡-ማየሰ ዐረፍተ በይምን ወአረፍተ በጽግም፡፡/ውኃው ግን በቀኝናበግራ እንደ ግድግዳ ቆመላቸው/

---ተክለ ሃይማኖት ተሰብረ እጸ/ተ/ሃይማኖት እንደ እንጨት ተሰበረ/

---ያርብሕ ያፍርህ አንበሳ/ኃይለኛ እንደ አንበሳ ያስፈራል/

---ጊዮርጊስ ተረግዘ አርዌ/ጊዮርጊስ እንደ አውሬ ተወጋ/

---ሱራፌ ይነቁ መሰንቆ /ሱራፌ እንደ መሰንቆ ይጮሐል/

---አእምሩ ድኩማን ወተመውኡ ኃያላን/ኃይለኞች እንደተሸነፉ ደካሞች እወቁ/

---ጽድቅ በወልታ የአውደከ/ጽድቅ እንደ ጋሻ ይከብሃል/

---ተመትረ ጊዮርጊስ ምትረተ ጳውሎስ /ጊዮርጊስ እንደ ጳውሎስ ተቆረጠ/

---ተመትረ ጊዮርጊስ ተመትሮ ጳውሎስ/

***ሒአሉታ/አፍራሽ/ ዓቢይ አገባብ***

በአንቀጽ ላይ እየወደቀ /እየገባ/ ነባርን፣ድርጊትን፣ሁኔታን፣ጊዜን ወዘተ ያፈርሳል፡፡

በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኙ አገባቦች «እንጂ» የሚሆኑት በሙሉ ናቸው፡፡

እንጂ የሚሆኑ አገባቦች ---አስ

---ዳዕሙ

---ባሕቱ

---እንበለ ናቸው፡፡

ምሳሌ፡---ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት አላ አድኅነነ ወባልሐነ እምኵሉ እኩይ

/አቤቱ ወደፈተና አታግባን ከክፉ ሁሉ አድነን እንጅ/

---ኵሉ ዘየአምን በወልድ ኢይትኃጐል አላ ይረክብ ሕይወት ዘለዓለም

/በወልድ የሚያምን ሁሉ አይጠፋም የዘለዓለም ሕይወት ያገኛል እንጂ/

---አኮ ጻድቅ ልዮን ዳዕሙ ኃጥእ/ልዮን ጻድቅ አይደለም ኃጢያተኛ እንጅ/

---አኮ ኃጥእ ጊዮርጊስ ዳዕሙ ጻድቅ/ጊዮርጊስ ኃጥእ አይደለም ጻድቅ እንጅ/

---ኢሠዐረ እግዚእነ ሕገ ኦሪት ባሕቱ ፈጸመ/ጌታችን የኦሪትን ሕግ አልሻረም ፈጸመ እንጅ/

---ኢይመውት ዘእንበለ ዘአሐዩ/አልሞትም እኖራለሁ እንጅ/

---ኢተሰቅለ ወልድ ከመ ያድኅን መላእክተ ዘእንበለ ከመ ያድኅን ሰብአ

/ወልድ መላእክትን ሊያድን አልተሰቀለም ሰውን ሊያድን እንጅ/

---ኢተወልደ አምላክ አመ ዳዊት እንበለ አመ ቄሳር /አምላክ በዳዊት ጊዜ አይደለም በቄሳር ጊዜ እንጅ/

---ኢበጽሐ ሙሴ እስከ ኢየሩሳሌም እንበለ እስከ ደብረ ሲና

/ሙሴ እስከ ኢሩሳሌም አልደረሰም እሰከ ደብረ ሲና እንጅ/

---ኢተወልደ ወልድ በዘጸልአ እንበለ በዘአፍቀሮ/ወልድ ስለ ጠላው አልተወለደም ስለ ወደደው እንጅ/

---ኢተሰቅለ ወልድ በእንተ መልአክ እንበለ በእንተ ሰብእ/ወልድ ስለ መልአክ አልተሰቀለም ስለ ሰው እንጅ/

---ኢነግሠ ሰሎሞን መጠነ ኪራም እንበለ መጠነ ዳዊት

/ሰሎሞን የኪራምን ያህል አልነገሠም የዳዊትን እንጅ/

---ኢሞተ ቃል ኀበ ተወልደ እምአብ እንበለ ኀበ ተወልደ እምድንግል

/ወልድ ከአብ ከተወለደ ዘንድ አልሞተም ከድንግል ከተወለደ ዘንድ እንጅ/

---ኢተወልደ ወልድ ቅድመ ዮሐንስ እንበለ ድኅረ ዮሐንስ

/ወልድ ከዮሐንስ በፊት አልተወለደም ከዮሐንስ በኋላ እንጅ/

---ኢተኀዘ ወልድ እንዘ ይሰርቅ ንዋየ እንበለ እንዘ ይሰግድ ስግደተ

/ወልድ ገንዘብን ሲሰርቅ አልተያዘም ስግደትን ሲሰግድ እንጅ/

---አኮ ሰንበት ባሕቲቶ ዘይስዕር አዲ አባሁ ይሬስዮ ለእግዚአብሔር

/እግዚአብሔርን አባቱን ያደርገዋል እንጅ ስንብትን ብቻ የሚሽር አይደለም/

## <u>ሐ.ንዑስ አገባብ</u>

አገባቡ-ንዑስ አገባብን በተለያዩ ክፍሎች ልንመለከተው እንችላለን፡፡

### *ሀ.መጠይቅ ንዑስ አገባቡ-*

የተለያዩ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ የምንጠቀምበት ክፍል ነው ፡፡ማለት፡-

- የነገር ስም -ምንት ፣አይ፣ት፣ሁ(ምን፣ማን፣ማንን) መጠይቅ
- የስም-መኑ(ማን) መጠይቅ
- የሁኔታና የድርጊት -እፎ፣ኑ፣ሁ(እንዴት፣እንዴታ፣ምን) መጠይቅ
- የጊዜ መጠይቅ-ማዕዜ፣አይ(መቼ)
- የቦታ መጠይቅ-አይቴ፣አይ(የት፣የትኛው፣ወዴት)
- የቀጥር መጠይቅ-ስፍን፣እስፍንት(ስንት/ቱ፣ስንተኛው)

ምሳሌ፡-<u>፩.መጠይቅ ባለቤት እና የአንቀጽ አጎላማሽ ሆኖ ሲገባ</u>

-ምንት ተገብረ(ምን ተደረገ?)

-አይ ይሰምዕ ቃለከ (ቃልህን ማን ይሰማል)

-መኑ የአምር ሕሊናከ(ሐሳብህን ማን ያውቃል)

-ማዕዜ ይከውን ምጽአትከ(መምጫህ መቸ ይሆን)

<u>፪.መጠይቅ ተሳቢ ሆኖ ሲገባ</u>

-ምንተ እነግር አነ (እኔ ምን እናገራለሁ?)

-አይ ይሴፎ ነዳይ(ደኻ ምንን ተስፋ ያደርጋል?)

-መነ የሐስሱ አይሁድ (አይሁድ ማንን ይፈልጋሉ?)

-እፎ ይከውን ዝንቱ (ይህ እንዴት ይሆናል?)

-ኢያከኑ/ሁ አዕበየ እግዚአብሔር (እግዚአብሔር አንተ ከፍ ከፍ አድርገን)

-እስፍንተ ቀተለ ሐራዊ(ወታደሩ ስንቱን ገደለ?)

<u>፫.መጠይቅ (የባለቤት ቅጽል) ሲሆን</u>

-ምንት ግብር ይበቁዖ ለሰብእ(ምን ሥራ ሰውን ይጠቅማል?)

-አይ ብእሲ ይረክብ ክብረ (ማን ሰው ክብርን ያገኛል?)

-መነ ነቢየ ጸውዐ እግዚአብሔር(እግዚአብሔር ማንን ነቢይን ጠራ?)

<u>፬.መጠይቅ የተሳቢ ቅጽል ሲሆን</u>

-ምንተ ግብረ ንግበር ንህነ(እኛ ምን ሥራን እንሥራ?)

-አየ ብእሴ ቀተለ ዳዊት(ዳዊት ማን ሰውን ገደለ?)

-ማዕዜ ዕለተ ቀደሰ እግዚአብሔር (እግዚአብሔር መቸን ቀን አከበረ?)

-አይቴ ሀገረ ወረሰ አብርሃም(አብርሃም የትኛይቱን ሀገር ወረሰ?)

-እስፍንተ ሕፃናተ ቀተለ ሄሮድስ(ሄሮድስ ስንት ህፃናትን ገደለ?)

ምንት ፥አይ፣መኑ፣የሰዋስው ዘርፍ ሲሆኑ

ምሳሌ፡-ብዕሴ ምንት ያስቆርር እግዚአብሔር (እግዚአብሔር የምን ሰውን ይጸየፋል?)

-ምክረ አይ ሰምዐ አዳም (አዳም የማንን ምክር ሰማ?)

-ምጽአተ መኑ ይፈርሕ አርዌ(አውሬ የማንን መምጣት ይፈራል?)

በመጠይቅ አገባቦች በመነሻ እና በመድረሻ አገባብ ሲገባባቸው

ሀ.በመነሻ -ምሳሌ፡-ለምንት ትቴክዚ ነፍስየ(ነፍሴ ለምን ታዝኛለሽ?)

-ምስለ አይ ተሰደተ ማርያም (ማርያም ከማን ጋር ተሰደደች?)

-ኀቤከኑ/ሁ ተፈነወ ገብርኤል (ገብርኤል ወደአንተ ተልኳልን?)

-አማሰለ መኑ ይትሜሰል ወልድ (ወልድ በማን አምሳያ ይመሰላል?)

-እስከ ማዕዜኑ ይዜሀሩ ኃጥአን (ኃጢያተኞች እስከ መቸ ይኮራሉ?)

ለ.በመድረሻ -ምሳሌ፡- ምንትኑ ግብርከ (ሥራህ ምንድን ነው?)

-አይኑ ፈውስ ተገብረ(ምን ድኅነት ተደርጐ ነበር?)

-እፎኑመ እመአምላክ በከየት(የአምላክ እናት ምንኛ አለቀሰች?)

-አይቴኑ ብሔርከ (ሐገርህ የት ነው?)

መጠይቅ አገባቦች የውእቱ ነባር አንቀጽ ሲሆኑ

ምሳሌ፡- ምንት ውእቱ ምክሮሙ (ምክራቸው ምንድን ነው?)

-አይ/መኑ ውእቱ ዝንቱ(ይህ ምንድን ነው?)

-እፎ ውእቱ ብእሲሁ(ሰውየው እንዴት ነው?)

-አይቴ ውእቱ ብሔራ ለጥበብ (የጥበብ ሀገሯ ወዴት ነው?)

-ማዕዜ ውእቱ ዕለተ ልደቱ(የልደቱ ቀን መቸ ነው?)

ማስታወሻ፡- ምንት ብቻ በ0ሥሩ መራሕያን ይዘረዘራል

ምንትየ/ምንትነ/ምንትከ/ኪ/ክሙ/ክን/ቱ/ታ

(ምንየ/ምናችን/ምንህ/ምንሽ/ምናችሁ/ምኑ/ምኗ)

-ምንት እና አይ ብቻ ከነጠላነት ወደ ብዙነት ይለለወጣሉ፡፡

ምንት/ምንታት--ምን/ምኖች

አይ/አያት---ምን፣ማን/ምኖች፣ማኖች

***ሊ ትእምርተ አንክሮ/ ፍሥሐ እና ሐዘን ንዑስ አገባብ***

- ትእምርተ አንክሮ --እፎ፣አ(ምን፣ምንኛ፣እንዴት/ታ)
- ትእምርተ ፍሥሓ--ዕንቋዕ(እንኳን እሰይ)
- ትእምርተ ሐዘን--አሌ፣ሰይ፣ዬ፣አ(ወዮ፣ወየው፣ወዮታ፣ይብላኝ)

አንክሮ

ምሳሌ፡--እፎ ተሴሰየ እግዚእ ሐሊበ(ጌታ ወተትን እንዴት ተመገበ!)

-እፎ አምስጥዎ ጻድቃን ለመጸብብ(ጻድቃን ጠባቡን እንዴት አመለጡት!)

-አ እሙቅ ብዕለ ጥበቡ ለእግዚአብሔር(የእግዚአብሔር የጥበቡ ምላት ስፋት ምን ጥልቅ ነው!)

-አ መንክር ልደተ አምላክ (የአምላክ ልደት ምን ድንቅ ነው!)

ደስታ

-እንቋዕ ርኢናሁ ንህነ ለህፃን (እኛ ህፃኑን እንኳን አየነው፡፡)

-እንቋዕ ተወልደ መድኅን (መድኅኒት እሰይ ተወለደ)

ሐዘን

-እንቋዕ ይቤሉኒ ጸላዕትየ /ጠላቶቸ እስይ እሰይ ይሉኛል፡፡)

-አሌ ለክሙ ሰዶም ወገሞራ (ሰዶምና ገሞራ ወዮታ ይገባችኋል/ወዮላችሁ)

-ሰይ/የ ለከ ይሁዳ ሰያጤ እግዚእ(ጌታን የሸጥህ ይሁዳ ወዮልህ)

-ዬ ዬ ዬ (ወየው ወየው ወየው)

-እፎ እፎ (እረግ እረግ /እንዴት እንዴት)

***ሐ.ትእምርተ ጽዋዔ /ጥሪ ንዑስ አገባብ***

አ---ትእምርተ ጽዋዔ አገባብ ተብሎ ይጠራል።

ምሳሌ፡- -አ እግዚአ አድኅን ሶ(አቤቱ አድና /አቤቱ አድን)--አክብሮ

-አ ደቂቅየ ተመሀሩ እምኔየ(ልጆቸ ሆይ ከኔ ተማሩ)--ምክር

-አ ማርያም ናፈቅረኪ (ማርያም ሆይ እንወድሻለን)

-አ ወልደ ዳዊት ተሣሃለኒ(የዳዊት ልጅ ሆይ ይቅር በለኝ)--አራኅርኖ

-አ ወልድየ ይዕቀብከ እግዚአብሔር (ልጄ ሆይ እግዚአብሔር ይጠብቅህ)

አ---በምሥጢር/ውሳጣዊ/ጠባዩ የስም ቅጽል ነው።

***መ.ትእምርተ እማሔ፡አቤቱታ ፤እሽታናመልእክት ንዑስ አገባብ***

- ትእምርተ እማሔ/ሰላምታ---በሀ(ደስታ፤ሰላም፤እንዴት አደርህ )
- ትእምርተ አቤቱታ ---ነዬ/እነሆኝ /አቤት፤አለሁኝ)
- ትእምርተ እሽታ---ኦሆ(እሽ፤በጀ)
- ትእምርተ መልእክት---ኣ(ራብዕ ድምጽ)

ምሳሌ፩. --በሀ በልዎ አንትሙ ለቤ.ክ(እናንተ ቤ.ክንን ሰላም በሏት)

--በሀ ኢትበልዎ አንትሙ ለዘኢየአምን(እናንተ የማያምንን ሰው ሰላም አትበሉት)

ምሳሌ፪ --ነየ እሰምዕ አነ ቃለከ(እነሆኝ እኔ ቃልህን እሰማለሁ)

--ነየ እትፌኖ አነ(አኖት/እነሆኝ እኔ እልካለሁ

ምሳሌ፫ --ኦሆ በልዎ አንትሙ ለእግዚአብሔር(እግዚአብሔርን እሽ በጀ በሉት)

--ኦሆ ኢትበልዎ አንትሙ ለሰይጣን(ሠይጣንን እሽ፤በእጀ አትበሉት)

--ኦሆ ኢበልዎሙ ሕዝብ ለደቂቅ /ሕዝቡ ልጆችን እሽ በእጀ አሰኞአቸው)

ምሳሌ፬. --ተሰአሎሙኣ አንተ ለሕዝብ (አንተ ሕዝቡን ጠይቃቸው)

--ተመየጡኣ አንትሙ ኀቤየ(እናንተ ወደኔ ተመለሱ)

***ሠ.ትእምርተ አዎንታ እና አሉታ ንኡስ አገባብ***

- ትእምርተ አዎንታ ---እወ(አዎን)
- ትእምርተ አሉታ ---እንዳኢ/እንጋ(እንጃ)
- ትእምርተ አሉታ ---ሐሰ (አይደለም ፤አየሁን)
- ትእምርተ አሉታ ---ሰ(ግን፤ና፤ስ፤ሳ፤ማ)

ምሳሌ፡-  --እወ እብለከሙ አነ(እኔ አወን እላችኋለሁ )

--እወ ይኩን ቃልከሙ (ቃላችሁ አዎን ይሁን )

--እንዳኢ ይቤሉ አሕዛብ (አሕዛብ እንጃ ይላሉ)

--እንጋ የሐዩኑ ወልድየ (ልጄ ይድናልን እንጃ)

--ሐሰ ኢይዜጎር አነ(እኔ አልታጀርም አይሁንብኝ )

--ማርያምሰ ኀርየት ሠናየ(ማርያም ግን/ስ/ማ በጎውን መረጠች)

--እንከሰ ተገብሩ ግብረ(እንግዲህስ/ማ ሥራን ሥሩ )

--አንተሰ ጸላዕከ ተግሣጽየ (አንተስ/ግን፣ማ ምክሬን ጠላህ)

--ሕድግሰ ዕበደ ተገበር ጽድቀ(ስንፍናን ተውና እውነትን አድርግ)

***ሬ ትእምርተ ጊዜ ንዑስ አገባብ***

- ❖ ትእምርተ አሁንታ ጊዜ---ናሁ/አሁን/
- ❖ ትእምርተ አሁንታ ጊዜ ---ዮም፣ይእዜ/ዛሬ፣አሁን፣ዘንድሮ)
- ❖ ትእምርተ አሁንታ ጊዜ---እንከ(እንግዲህ፣ከእንግዲህ ወዲህ)
- ❖ ትእምርተ ወትራዊ ጊዜ---ከመ ፣ዓለም(መቶ፣መች፣ዘወትር)
- ❖ ትእምርተ መጻኢ ጊዜ ---ጌሰም፣ሳኒታ(ነገ፣ነጋታ)
- ❖ ትእምርተ ኃላፊ ጊዜ ---ትካት ፣ትማለም፣ቅድም(ድሮ፣ቀደም፣ጥንት)

ምሳሌ፡--ናሁ እሁብ አነ መንፈቀ ንዋይየ(እኔ የገንዘቤን እኩሌታ አሁን እሰጣለሁ)

--ዮም ተወልደ መድኃኔዓለም (የዓለም መድኃኒት ዛሬ ተወለደ)

--ከመ እሰምዕ አነ ዘንተ (እኔ ይህንን መቸ /መች እሰማለሁ)

--እንከ ፈንዎሙ አንተ ለሕዝብከ (አንተ እንግዲህ ሕዝቡን አሰናብታቸው)

--ይእዜ ብንከሙ አንትሙ ሕዝበ (እናንተ ዛሬ ወገኖቼን ሆናችሁ)

--ጌሰሙ ታገብኡ አንትሙ ወርቅየ (እናንተ ከርሞ ወርቄን ታስገባላችሁ )

--ሳኒታ ይመጽእ መርዓዊ (ሙሽራው ነገ ይመጣል)

--ትካት ዘንመ ማየ አይኅ (የንፍር ውኃ ድሮ ዘንሞ ነበር)

--ትማለም ፈነውክዎ አነ ለወልድየ (እኔ ትላንትና ልጄን ልኬው ነበር)

በጊዜ ንዑስ አገባብ ላይ መነሻና መድረሻ አገባብ ይወድቅበታል፡፡

በመነሻ፡--ወከመ ውእቱ እግዚእ(መቸ መች ጌታ ነው)

--ኢትበሉ አንትሙ ለጌሰም (እናንተ ለነገ አትበሉ )

--ወእመሳኒታ ርእዮ ዮሐንስ ለኢየሱስ (በነጋታውም ዮሐንስ ኢየሱስን አየው)

--እምትካት ሀለወት ይእቲ(ያች ከጥንት ጀምሮ ነበረች)

በመድረሻ፡--ናሁኬ በጽሐ ጊዜሁ (አሁን ጌዜው ደርሷል )

--ዮምሰ አበርሕ አነ በመስቀልየ(ዛሬስ እኔ በመስቀሌ አበራላችኋለሁ)

--ይእዜሰ ትሬዕዩኑ አንትሙ(አሁን ግን እናንተ ታዩኛላችሁ)

--እንከሰ ግብር አንተ ዘትገብር (እንግዲህ አንተ የምታደርገውን አድርግ)

***ሰ.ትእምርተ ጥርጣሬ /አማራጭ እና አብላጫ ንዑስ አገባብ***

- ❖ ትእምርተ ጥርጣሬ---ዮጊ(ምናልባት)
- ❖ ትእምርተ አማራጭ---አው/ሚመ(ወይ፣ወይም፣ወይስ)
- ❖ ትእምርተ አብላጫ---ጥቀ፣ፈድፋደ(እጅግ፣በእጅጉ)

ምሳሌ፡- --ዮጊ ይመጽእ ዘይከብረከ (ምን አልባት ከአንተ ይልቅ የሚከብር ይመጣል )

--ተሣየጥ ዘንፈቅድ ለበዓል አው ዘንሁብ ለነድያን (ለበዓል የምንፈልገውን ወይም ለድሆች የምንሰጠውን ግዛ)

--ምንተ ንብሎ ለመድኃኒነ አርዌ ገዳምኑ ወሚመ አንበሳ(መድኃኒታችንን ምን እንለዋለን የበርሐ አውሬን ወይስ አንበሳን)

--ጥቀ አእበዮ እግዚአብሔር (እግዚአብሔር እጅግ ከፍ ከፍ አድረጎታል)

--ፈድፋደ ይትቀነዩ ሎሙ (በእጅጉ ይገዙላችኋል

--ሰሎሞን ጥቀ ኢለብሰ(ሰሎሞን እንኳን አለበሰም)

***ቀ.ትእምርተ ጸጸት/ተምኔት፡መጠን እና ቀስታ /ሥውር ንዑስ አገባብ***

- ❖ ትእምርተ ጸጸት/ተምኔት---በ-ነበር
- ❖ ትእምርተ መጠን ---ሕቅ፣ንስቲት፣ሕዳጥ(ጥቂት በጠቂት )
- ❖ ትእምርት ቀስታ/ሥውር---ጽሚተ/ጽመ(ቀስ በቀስታ በሥውር)

ምሳሌ፡- --እም ሐሰ ለሰብእ ሶበ ይምሕር ነዳየ(ለድኃ ቢራራ ለሰው በተሻለው ነበር)

--እምሐየሰ ለውእቱ ብእሲ ሶበ ኢተፈጠረ (ለዚህ ሰው ባልተፈጠረ በተሻለው ነበር)

--አዕይንቲክሙ መሊሐክሙ እምወሀብኩክሙኒ(ዓይኖቻችሁን መዛችሁ /አውጥታችሁ በሰጠችሁኝ ነበር)

--ሕቀ አሕጸጽኮ እመላእክቲከ(ከአለቆችህ/ከመላእክቶችህ ጥቂት አሳነስከው )

--ንስቲት ይእቲ ልሳን(አንደበት ትንሽ ናት)

--ሕዳጥ የአክል (ጥቂት ይበቃል)

--ሐተቶ ጲላጦስ ለኢየሱስ ጽሚተ(ጲላጦስ ኢየሱስን በቀስታ መረመረው)

--ቀተሎ ኃጥእ ለንጽሕ ጽሚተ(ኃጢያተኛ ንጹሑን በሥውር ገደለው)

--ተናገር ጽድቀ ጽመ(ዝም ብለህ እውነትን ተናገር)

ንስቲት እና ሕዳጥ ተለይተው ተገብሮ እና ገቢር ቅጽል ይሆናሉ።

ምሳሌ፡- <u>ተገብሮ ቅጽል</u>

--ንስቲት ኅብስት ተጸግበ ለርሑብ (ትንሽ እንጀራ ረሐብተኛን ታጠግባለጭ

--ሕዳጥ አሣ ብነ(ጥቂት አሣ አለን )

<u>ገቢር ቅጽል</u>

--ንስቲት ሕብስት ግበሪ ሊተ(ትንሽ ዳቦ ጋግሪልኝ)

--ሕዳጠ መዋዕል ሀሎኩ ምስሌክሙ (ጥቂት ቀን ከእናንተ ጋር ኖሬአለሁ)

***ቢእስኩ፣አዲ፣ጓ፣እስመ፣ቅድመ፣ሂ፣ኒ ንዑስ አገባብ***

| | |
|---|---|
| እስኩ---እስኪ | ቅድመ---ሳ |
| አዲ---ዳግመኛ፣ሞ፣ገና | ሂ----ም |
| ጓ---እኮ | ኒ----ም |
| እስመ---እኮ | |

ምሳሌ፡- --እስኩ ንግረኒ ምንትኑ ዝ ነገር ዘእስምዕ በእንቲአከ

(እስኪ ንገረኝ ይህ ስለ አንተ የምሰማው ነገር ምንድን ነው?)

--አዲ ናቁርብ ለከ ዘንተ(ዳግመኛ ይህን እናቀርብልሃለን)

--ከለባትኒ ጓ ይበልዑ እምፍርፍርተ እግዚኦሙ(ውሾችም አኮ ከጌታቸው ፍርፋሪ ይበላሉ)

--እስመ ነሣዕናከሙ አስተብቋዕየነ ለኀበ እግዚአብሔር

(ወደ እግዚአብሔር ማላጆች አድርገን ተቀብለናችኋል እኮን)

--እምቅድመ ይትወለድ አብርሃም ሀሎኩ አነ (አብርሃም ሳይወለድ እኔ ነበርሁ)

--እመሂ በባሕር ወእመሂ በቀላያት ወእመሂ በአፍላግ

(በባሕርም ቢሆን በጥልቁም ቢሆን በወንዙም ቢሆን )

--ሙሴኒ ርእያ ወተናገራ(ሙሴም አይቶ ተናገረላት )

## <u>መ.ደቂቅ አገባብ</u>

በስም ላይ ወድቆ ሰዋስውን የሚያሳካ /የሚያያዝ/ዐ.ነገርን የሚያስማማ ብትን ነባር ሰዋስው ደቂቅ አገባብ ይባላል፡፡ይህም ማለት ደቂቅ አሰካከ /አያያዝ ማለት ነው ለቅርጸ ፊደሉ ተሰጥቶ ሲፈታ ደቃቃ ማሣኪያ (ማያያዣ ደቃቃ የዐ.ነገር ማስማሚያ ማለት ነው።

ደቂቅ የተባለበት ምክንያት በአንቀጽ ላይ ስለማይወድቅ የአንቀጽን ማሰሪያነት ስለሚያስቀር ነው፡፡

አገባብ የተባለበት ምክንያትም ምክንያት በስም ላይ እየወደቀ ሰዋስውን ስለሚያሳካ ፣ዐ.ነገርን ስለ ሚያስማማ ነው፡፡ደቂቅ አገባብ በተለያዩ ሁኔታ ስለሚገባ በተለያየ ክፍል ከፍሎ ማየት ይቻላል

### *ሀ.ትምህርተ ላዕል መታሕት/ላይ እና ታች ደቂቅ አገባብ*

ይህ ክፍል ጠባዩ ማንጸሪያ/ማመልከቻ ፣አመልካች መሆን ነው በውስጡም

ላይ ላዕለ----በ...ላይ፣በላይ፣ስለ

መልዕልተ----በ...ላይ ፣በላይ፣ስለ

ዲበ----በ...ላይ፣በላይ፣ስለ

ታች ታሕተ----ከታች፣በታች

መትሕተ----ከታች፣በታች

እነዚህ አገባቦች ሌላ አገባብ ወድቆባቸው ሳይወድቅባቸውም በዐ.ነገር ውስጥ ይገባሉ።

<u>፩.አገባብ ሳይወድቅባቸው</u>

---ኢትደይ እዴከ ላዕለ ወልድከ (በልጅህ ላይ እጅህን አታንሳ)

---ጸልዩ ላዕሌየ(ስለኔ ጸልዩ /ለምኑ

---ወተለዓለ ማይ መልዕልተ ምድር (ውኃ በምድር ላይ ከፍከፍ አለ)

---ወዐርጉ ሐዋርያት መልዕልተ ሐመር(ሐዋርያት በመርከብ ላይ ወጡ)

---መልአ አመጻ ዲበ ምድር(ዓመጽ በምድር ላይ ሞላ)

---ኢይደልዎ ከመትባዕ አንተ ታሕተ ጠፈረ ቤትየ(ከቤቴ ጣሪያ በታች ትገባ ዘንድ አይገባኝም)

---ወእደመሰስ ኩሉ ዘሥጋ ዘሀሎ መትሕተ ሰማይ(ከሰማይ በታች ያለውን ሥጋዊ ፍጥረት ሁሉ አጠፋለሁ)

፪.አገባብ ሲወድቅበት

---አሐዱ ይሳለቅ በላዕለ ካልዑ(አንዱ በሌላው ይዘብታል)

---ርኡደ መደንጉጸ ኩን በመልዕልተ ምድር(በምድር ላይ ተንቀጥቃጭ እና ተቅበዝባዥ ሁን)

---ርኢኩከ በታሕተ ዕፀ በለስ (ከበለስ ቅጠል በታች አይቸሃለሁ)

ይህ የደቂቅ አገባብ ክፍል በዐሥሩ መራሕያን ይዘረዘራል።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ላዕሌየ | መልዕልቴየ | ዲቤየ | ታሕቴየ | መትሕቴየ |
| ላዕሌነ | መልዕልቴነ | ዲቤነ | ታሕቴነ | መትሕቴነ |
| ላዕሌከ | መልዕልቴከ | ዲቤከ | ታሕቴከ | መትሕቴከ |
| ላዕሌኪ | መልዕልቴኪ | ዲቤኪ | ታሕቴኪ | መትሕቴኪ |
| ላዕሌክሙ | መልዕልቴክሙ | ዲቤክሙ | ታሕቴክሙ | መትሕቴክሙ |
| ላዕሌክን | መልዕልቴክን | ዲቤክን | ታሕቴክን | መትሕቴክን |
| ላዕላሁ | መልዕልቴሁ | ዲቤሁ | ታሕቴሁ | መትሕቴሁ |
| ላዕሌሃ | መልዕልቴሃ | ዲቤሃ | ታሕቴሃ | መትሕቴሃ |
| ላዕሌሆሙ | መልዕልቴሆሙ | ዲቤሆሙ | ታሕቴሆሙ | መትሕቴሆሙ |
| ላዕሌሆን | መልዕልቴሆን | ዲቤሆን | ታሕቴሆን | መትሕቴሆን |

***ሊ.ትዕምርተ ማዕከል ወውስጥ ደቂቅ አገባብ***

የዚህ አገባብ ጠባዩ እንደላይኛው ማንጸር/ማመልከት ነው፡፡

ማዕከል---መካከል፣በ-መካከል

ውስተ---ውስጥ፣መካከል ፣በ፣ወደ

ውሳጤ---ውስጥ፣መካከል፣በ፣ወደ

አገባብ ሳይወድቅበት ወድቆበትም ሊገባ ይችላል፡፡

፩.ሣይወድቅበት

ምሳሌ፡-ቆመ ማዕከለ ባሕር(በባሐር መካከል ቆመ)

-- ወትበውእ አንተ ውስተ ታቦት (አንተ በመርከብ ውስጥ ትገባለህ)

--ውስተ በድው አኀድኀሙ ለሕዝብየ(በምድረ በዳ መካከል ሕዝቤን እተዋቸዋለሁ)

--ወወጽአ ስሙኣተ ነገሩ ውስተ ኲላ ሶርያ/ኢትዮጵያ

(የተአምራቱ ነገር በመላዋ ኢትዮጵያ ተሰማ)

--ወወጻእኩ ውስተ ዓለም/ወደዓለም መጥቻለሁ)

--ወኢትሐብኡ አራዊተ ውሳጤ ግብ(አራዊቶችን በጉድጓድ ውስጥ አትሸሽጉ)

<u>፪.አገባብ ሲወድቅበት</u>

ምሳሌ፡-በማዕከለ ፪ እንስሳ ርኢኩከ(በሁለት እንስሶች መካከል አየሁሕ)

--ተሕው በውስተ አድባር ወብከዩ በውስተ ፍና

(በተራሮች ላይ አልቅሱ በመንገድም መካከል አልቅሱ)

--አውጽአ ሠርዌ እምውስተ ዓይንከ(ምሶሰውን ከዓይንህ አውጣ /ከዓይንህ ውስጥ አውጣ)

--ወቦው ደቂቁ እምውሳጤ ታቦት (ልጆቹ ከታቦቱ ውስጥ ገቡ)

<u>በዐሥሩ መራኁያን ሲዘረዘሩ</u>

| | | |
|---|---|---|
| ማዕከሌየ | ውስቴትየ | ውሳጤየ |
| ማዕከሌነ | ውስቴትነ | ውሳጤነ |
| ማዕከሌከ | ውስቴትከ | ውሳጤከ |
| ማዕከሌሁ | ውስቴቱ | ውሳጣሁ ወዘተርፈ |

***ሐ.ትምሕርት መነሻ ፣መገሰገሻ እና መድረሻ ደቂቅ አገባብ***

የዚህ አገባብ ጠባዩ የነገሮችን መነሻቸውን መድረሻቸውን እንዲሁም ሂደታቸውን ማሣየት ነው፡፡

- መነሻ---እም(ከ፣ካ፣ከ፣ቦዝ፣ከፊል፣ይልቅ የተነሣ)
- መገስገሻ---ኀበ ፣መንገለ፣ለ፣እንተ(ወደ)
- መድረሻ---እስከ(እስከ ድረስ)

እንደሌሎቹ አገባቦች ሌላ አገባብ ሳይወድቅበት ወድቆበትም ይገባል፡፡

ምሳሌ፡-ወእንዘ የሐልፍ እም ህየ ርእየ ብዕሴ(ከዚያ አልፎ ሲሄድ ሰውን አየ)

--አውጽእወ እደው እም ሀገር(ወንዶች ከሐገር አስወጡት)

--አንሥአ ለነ ቀርነ መድኀኒትነ እምቤተ ዳዊት ገብሩ

(ከአገልጋዩ ከዳዊት ወገን ተወልዶ የድሕነታችንን ሥልጣን አነሳልን)

--ወኮነ አጽመ ያዕቆብ እምግብጽ ለከነአን(የያዕቆብ አጽም ከግብጽ ወደከነአን ተወሰደ)

--ደይ እዴከ እንተ ስቁረት (እጅህን ወደ ቀዳዳ አስገባ )

--ወእስከ አጽናፈዓለም በጽሐ ነቢቦሙ(ነገራቸው እስከ ዓለም ዳርቻ ደረሰ)

በዐሥሩ መራኅያን ሲዘረዘር

| | | | |
|---|---|---|---|
| እምኔየ | ኀቤኪ | ምንገልየ | እስከኔየ |
| እምኔከ | ኀቤክን | መንገሌነ | እስከኔነ |
| እምኔከሙ | ኀቤሆን | መንገሌከ | እስከኔሁ |
| እምኔሆሙ | ኀቤከሙ | መንገሌከሙ | እስከኔከ |

***መ.ማድረጊያ አቀባይ/ተጠቃሽ አጫፋሪና አነጻጻሪ ደቂቅ አገባብ***

- ❖ በ----በቁም ቀሪ፣እንደ፣ወደ፣ጊዜ፣ጋራ፣ቦዝ(ቸልታ)
- ❖ ለ----በቁም ቀሪ፣ለ፣ን፣ስለ፣አቀብሎሽሽ
- ❖ ምስለ----ጋራ፣እንደ፣ና፣ከ

ምሳሌ፡---ኢይከብር ነቢይ በሀገሩ(ነቢይ በሀገሩ አይከብርም)

---ወተናጸሩ ገጸ በገጽ(ፊት ለፊት ተያዩ)

---ጽድቅ በወልታ የአውደከ(ጽድቅ እንደ ጋሻ ይከብሃል)

---ወመንፈስከ ቅዱስ ይምርሃኒ(መንፈስ ቅዱስ ወደ እውነት ሀገር ይምራኝ)

---በምንዳቤየ ተዘከርኩከ እግዚኦ(አቤቱ በመከራየ ጊዜአስታወስኩህ)

---እግዚአብሔር ይመጽ እ በአእላፊሁ ቅዱሳን(እግዚአብሔር ከአእላፍ ቅዱሳን ጋር ይመጣል)

---መሀሩነ ሐዋርያት በዘብድወ ጠሊ(ሐዋርያት የፍየል ለምድ ለብሰው አስተማሩ)

---መኑ ይትዔርዮ ለእግዚአብሐር በደመና(ከደመናት እግዚአብሔርን ማን ይተካከለዋል)

---ጻድቅ ለዓለም ኢያንቀለቅል(ጻድቅ ለዘላለም አይናወጽም)

---ኢትጼሊ ለዝንቱ ሕዝብ(ስለዚህ ሕዝብ አትጸልይ)

---ጥበቡ ለብእሲ ትውልድ ጥበብ(የሰውየው ጥበብ እውቀትን ታፈልቃለች)

---ዝንቱ ይመውት ምስለ አብዳን(ይህ ከሰነፎች ጋር ይሞታል)

---አበስነ ምስለ አበዊነ(እንደ አባቶቻችን በደልን)

በዐሥሩ መራሕያን ሲዘረዘሩ

| | | |
|---|---|---|
| ብየ--በኔ | ልየ/ሊተ | ምስሌየ |
| ብነ--በእኛ | ለነ | ምስሌነ |
| ብከ--በአንተ | ለከ | ምስሌከ |
| ብኪ--በአንቺ | ለኪ | ምስሌኪ |
| ብክሙ--በእናንተ | ለክሙ | ምስሌክሙ |
| ብክን--በእናንተ | ለክን | ምስሌክን |
| ቦቱ--በእርሱ | ሎቱ | ምስሌሁ |
| ቦሙ--በእነርሱ | ሎሙ/ሎቶሙ | ምስሌሆሙ |
| ባቲ--በእርሷ | ላቲ | ምስሌሃ |
| ቦቶን--በእነሱ | ሎቶን | ምስሌሆን |

***ሠ.ትእምርተ ቤዛነት ፣ምትክነት፣መማጸን ደቂቅ አገባብ***

ይህ አገባብ አንድ አካል ለአንድ አካል /አንድ ነገር ለአንድ ነገር ተተክቶ /ተለውጦ መተካቱን/መሞቱን የሚያመለክት ነው።

- ❖ ቤዛነት/ለውጥ የሚያመለክት----ቤዛ(ስለ ፣ቤዛ)
- ❖ ምትክነትን የሚያመለክት----ተክለ(ስለ/በ፣ምትክ)
- ❖ ልመናን/መማጸንን የሚያመለክት----በእንተ/ስለ

ምሳሌ፡--ቤዛ አባግዒሁ ይሜጦ ነፍሶ(ሰውነቱን ስለበጎቹ ቤዛ ይሰጣል)

--ቤዛ ይስሐቅ ተሦዐ በግዕ(ስለ ይስሐቅ ቤዛ በግ ተሰዋ»

--ተክለ አቤል ተወልደ ሴት(በአቤል ምትክ ሴት ተወለደ)

--ተክለ ይሁዳ ተሰይመ ማትያስ(በይሁዳ ምትክ ማትያስ ተሾመ )

--በእንተ  አብርሃም ፍቁርከ ተዘከር ኪዳነከ(ስለ ወዳጅህ አብርሃም ቃል ኪዳንህን አስብ)

--በእንተ ማርያም ወላዲትከ ርድአነ ወትረ(ስለ ወላጅህ ማርያም ዘወትር እርዳን)

<u>በዐሥሩ መራሕያን</u>

| | | |
|---|---|---|
| ቤዛየ | ተክልከሙ | በእንቲአየ |
| ቤዛነ | ተክልከን | በእንቲከ |
| ቤዛከ | ተክሉ | በእንቲኪ |
| ቤዛኪ | ተክላ | በእንቲአክሙ |
| | ተክሎሙ | በእንቲአክሙ |

***ረ.ትእምርተ ጊዜና ቦታ ደቂቅ አገባብ***

- የጊዜ ማንጸሪያ /አመልካች---ጊዜ(በ-ጊዜ)
  ----ዓለም(ዘለዓለም፣ዘወትር)
  ---ቅድም ፣አቅዲሙ(ቀድሞ፣አስቀድሞ)

- የቦታ ማንጸሪያ /አመልካች---አድያም፣ደወል(አውራጃ)
  ---ብሔር(ሀገር፣ክፍል፣ንጋት)
  ---ዝየ(በዚህ፣ከዚህ)
  ---ህየ(በዚያ፣ከዚያ)
  ---አፍአ(ውጭ፣በውጭ)
  ---ከሃ(ወዲያ፣ወደዚያ)
  ---ለፌ(ወዲህ፣ወዲያ)

ምሳሌ፡---ጊዜ ስድስቱ ስዓት ሰቀልዎ ለኢየሱስ (በስድስት ሰዓት ጊዜ ኢየሱስን ሰቀሉት)
---ወጽድቁሰ ለእግዚአብሔር ይሄሉ ለዓለም
(የእግዚአብሔር ፍርድ ግን ለዘለዓለም ይኖራል)
---አቅዲሙ ነገረ በኦሪት(አስቀድሞ በኦሪት ነገረን)
---ያደ ዮሐንስ አድያመ ዮርዳኖስ(ዮሐንስ የዮርዳኖስን አውራጃ ዞረ)
---ወበጽሐ እግዚእ ኢየሱስ ደወለ ቂሳርያ(ጌታ ኢየሱስ ከቂሣርያ አውራጃ ደረሰ)

---ገዳም ውእቱ ብሔር(ሀገሩ/ቦታው በረሐ ነው)
---ብሔረ አሪት(የአሪት ክፍሎች)
---ንነበር ዝየ ወንግበር ሠለስተ ማኅደረ(ከዚህ እንቀመጥ ሦስት ማደሪያዎችንም እንስራ)
---ወነበሩ የአቅብዎ ህየ(በዚያ ይጠብቁት ነበር)
---ህየ ንሰግድ ኵልነ(ሁላችንም በዚያ እንሰግዳለን)
---አሐውር ከሃ ወእጼሊ(ወደዚያ ሄጀ እጸልያለሁ)
---ወነጸረ ሙሴ ለፌ ወለፌ(ሙሴ ወዲያ ወዲህ ተመለከተ)

እነዚህ አገባቦች ሌላ አገባብ በመነሻ ሲወድቅባቸው

ምሳሌ፡---እምጊዜ ልደቱ እስከ ጊዜ ዕርገቱ(ከልደቱ ጊዜ እስከ እርገቱ ጊዜ)

---እምዓለም ወእስከ ለዓለም (ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም)

---ሰባሕኩከ በቅድመ ሙሴ ወኤልያስ (በኤልያስና በሙሴ ፊት ገለጥሁሕ)

---በህየ እገብር ፋሲካ(በዚያ ፋሲካን አከብራለሁ)

---ብእሲ ዘመጽኣ እምነ ከሃ(ከወዲያ የመጣ ሰው)

---አሐደ እምለፌ ወአሐደ እምለፌ(አንዱን ከወዲያ አንዱን ከወዲያ)

<u>በዐሥሩ መራሕያን መዘርዘር ይችላሉ፡፡</u>

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጊዜየ | ቅድሜነ | ቅድሜኪ | አድያምየ |
| ጊዜከ | ቅድሜክሙ | ቅድሜክን | አድያምነ |
| ጊዜሁ | ቅድሜሆሙ | ቅድሜሃ | አድያምከ |
| | ቅድሜሆን | አድያምኪ | |

ደወልየ ብሔርክሙ

ደወልክሙ ብሔርክን

ደወሎሙ ብሔሮሙ

ደወሎን ብሔሮን

***ሲአንጻሪ ደቂቅ አገባብ /አወዳዳሪ ደቂቅ አገባብ***

ከመ<br>
አያተ<br>
ጽላሎተ

} «እንደ» የሚል ትርጉም ሲኖራቸው አገባባቸው ሊለያይም ላይለያይም ይችላል።

ምሳሌ፡---ወናሁ አነ እፌንወክሙ ከመ አባግዕ ማዕከለ ተኩላት

(አሁን እኔ እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ)

---ሰላም ለአስናኒከ አያተ አፅናቁ እለተሰከዐ(እንደ እንቁዎች ለተሰኩ ጥርሶችህ ሰላምታ ይገባል)

---ጽላሎተ ጸበል ተዘርወ ሥጋሁ (ሥጋው እንደ ትቢያ ተበተነ)

| | | |
|---|---|---|
| ከማየ | አያትየ | ጽላሎትከ |
| ከማነ | አያቲነ | ጽላሎትኪ |
| ከማከ | አያቲከ | ጽላሎቱ |

# <u>ምዕራፍ ---፲፫</u>

## <u>ቅኔ</u>

ቅኔ ማለት ምን ማለትነው?

፩.ቀነየ--ገዛ ከሚለው የግዕዝ ግስ የተገኘ ጥሬ ዘር ነው ወይም ቀነየ ገዛ የሚለውን አንቀጽ ያስገኘ ጥሬ ዘር ነው ፍቹም መገዛት ማለት ነው።«ቁሙ እንከ ወኢትሑሩ ውስተ አርኡተ ቅኔ»

--ትርጉሙ ይህ ከሆነ ከተለያዩ ሰዎች በየጊዜው የሚመነጨው እንግዳ ድርሰት ስለምን ቅኔ ተባለ ቢሉ ፍጡር አዳዲስ ምስጋና እየደረሰ በማቅረብ ለፈጣሪው መገዛቱን የሚገልጽበት ስለሆነ ነው ።

--ቅኔ የሚቀኘው /የሚደርሰው ቅኔ ከሚደረስለት ጻድቅ /ቅዱስ በታች ስለሆነ ከእርሱ በላይ ላለ ምስጋና አዘጋጅቶ ማቅረብ በራሱ መገዛት ነው፤

፪.ሕዋሳተ አፍአን እና ሕዋሳተ ውስጥን ለሕሊና አስገዝቶ በተወሰነ ቁጥር ሐሳብ የሚታሰብ ስለሆነ ቅኔ ተብሎአል።

፫.ቅኔ ማለት ቃነየ ቃኘ ፣ደረደረ፣አዜመ፣አንጎራጎረ፣መራ ፣ገጠመ፣አመሰገነ፣አራቀ ተናገረ፣ካለው የወጣ ጥሬ ዘር ነው።

ስለዚህ ቅኔ ማለት ጥቅልል ትርጓሜው ባጭሩ ሰው ከራሱ አንቅቶ ለእግዚአብሔር አዲስ ምስጋና ላቅርብ ባለጊዜ ምሳል መስሎ ምሥጢር አሻሽሎ ግጠም በመግጠም የልቦናውን እውቀት የአእምሮውን ርቀት የሚገልጽበት የሰማዒውንም ልቡና የሚያነቃቃበት እና የሚያራቅቅበት ድርሰት ማለት ነው።

የቅኔ አመሰራረቱ ከብሉይ ኪዳን አበው ጀምሮ እንደሆነ ሊቃውንት ይናገራሉ በሐዲስ ኪዳንም አባታችን ቅዱስ ያሬድ እንደ ስድ ንባብም እንደ ግጥምም እያደረገ በጸዋትዎ ዜማው አልፎ አልፎ አስቀምጦታል።ሌሎች ሊቃውንትም እርሱን እንደ መነሻ አድርገው መንፈስ ቅዱስ በገለጻላቸው መጠን እየተቀኙ /እያስተማሩ ለዚህ አድርሰውታል።

### <u>የቅዱስ ያሬድ እና የመምህራን ቅኔ ልዩነት</u>

፩.የያሬድ ቅኔ እንደ መላእክት ምሥጋና «ቅዱስ(፫) እግዚአብሔር  የሚል ዓይነት ነው እንጂ የሚያመራምር አይደለም፡፡የመምህራን ግን በሰምና ወርቅ ፣በኅብር፣በሰም ለበስ እና በውስጠ ወይራ በመሳሰሉት የተሸፈነ ነው፡፡አንዱ የሌላውን ቅኔ መፍታት የሚያቅትበት ጊዜ አለ።

፪.የቅዱስ ያሬድ በስድም በግጥም ሊቀርብ ይችላል፡፡የሊቃውንት ገን በቃላት፣በሐረግ ፣በቤትና በቅኔ ዜማ ልክ የተወሰነ ነው።

፫.የያሬድ ቅኔ በየዓመቱ ድግግሞሽ ነው የመምህራን ግን ጀሮ ያልነካው በየቀኑ አዳዲስ ድርሰት ነው፡ስለዚህም ነው የቅኔው መምህር ምን ተቀኘ ምን ይቀኝ ተብሎ በጉጉት የሚጠበቀው።

፬.የያሬድ ቅኔ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል የሚደርስ ቅኔ ነው የመምህራን ግን ምንም እንኳን ቅዱስ መንፈስ ባይለያቸውም በትምህርት ገበታ የሚገኝ ነው፡፡

ወደ ቅኔ ክፍሎች /ደረጃዎች ከመሔዳችን በፊት «የነገረ ሰዋስውን»ትርጓሜ ማየት እንጀምራለን፡፡

## <u>ነገረ-ሰወስው</u>

በፊደል ስብስብ ተመስርቶ በቅሩጻን ቃላት የተዋቀረውና በአገባብ የተሰካው /የተያያዘው ሰውስው በተግባር ላይ የሚውልበት የአነጋገር ስልት ነገረ ሰወስው ይባላል።ነገረ ሰወስው ማለት የሰወስው አነጋገር የሰዋስው ተግባራዊ ትምህርት ማለት ነው።

ነገረ ሰዋስው በሁለት ይከፈላል፡- ፩.የዋሕ ነገረ ሰዋስው

፪.ጥበብ ነገረ ሰዋስው ናቸው፡፡

### *፩.የዋሕ ነገረ ሰዋስው*

ምሳሌ ሳይኖረው በነጠላ ንባብ ተነቦ በነጠላ አፈታት የሚፈታ ሰዋስው የሚነገርበት ስልት የዋሕ ነገረ ሰዋስው ይባላል፡፡የሰዋስው ቀና፣ቀላልና ግልጽ አነጋገር /አፈታት ማለት ነው፡፡

ለምሳሌ፡--ጸውዐ---ጠራ

ሐሰሰ--ፈለገ

ተከዘ--አዘነ፣ተከዘ

ፈነወ--ለካ

ዐርገ--ወጣ፣አረገ

ጸሐፈ--ጻፈ

ሞተ--ሞተ

ተምዐ--ተቆጣ

ለአከ--ላከ

ምሳሌ--ጸውዖሙ ጲላጦስ ለሊቃነ ካህናት

---የሐስሱ አይሁድ ይቅትልዎ

---ፈነወ ዳዊት ዕደወ

---ጸሐፈ ጲላጦስ መጽሐፈ

---ሞተ ሙሴ በምድረ ሞዐብ ወዘተ

የመጻሕፍት ነጠላ ፍችና ነጠላ ንባብ መሠረቱ እና መሪ መንገዱ ይህ የሰዋስው ዓይነት ነው፡፡

***፪.ጥበብ ነገረ ሰዋስው***

ቀጥተኛ ባልሆነ መተርጐም ቢፈለግ ስልት የሚነገር የሰወስው አነጋገር እና አፈታት ጥበብ ነገረ ሰዋስው ይባላል፡፡ጥበብ/ርቅት፣መራቀቅ/ ያለው የሰዋስው አነጋገርና አፈታት ወይም ፍልስፍና የሆነ የሰዋስው ትምህርት ማለት ነው፡፡

ጥበብ ነገረ ሰዋስው በሁለት ክፍሎች ይከፈላል

፩.ወርቅ ለበስ /ስም ረገፍ/ነገረ ሰዋስው

፪.ምሳሌያዊ ነገረ ሰዋስው ናቸው፡፡

***፩.ወርቅ ለበስ/ ስም ረገፍ/ ነገረ ሰዋስው-***

ያለምሳሌ በነጠላ ንባብ ተነብቦ ከፊደላት ትርጓሜ /ፍች/ በተጨማሪ የተለያዩ ምሥጢራትን /ሐሳቦችን የሚያስተረጉም ነጠላ ሰዋስው ወርቀ ለበስ /ሰም ረገፍ ነገረ ሰዋስው ይባላል፡፡

በወርቅ /በዋና ንባብ /ሐሳብ እየተነበበ ምሥጢር ያለው /የሚሥጢር ትርጓሜን የሚያስተረጉም የሰዋስው አነጋገር የሰዋስው አተረጓጎም ማለት ነው፡፡

ምሳሌ፡ገብረ--አደረገ-ሠራ------ፈጠረ(ምሥጢራዊ ትርጉም)

ለሐኰ--ሠራ ------ፈጠረ(ምሥጢራዊ ትርጉም)

ሰብሐ--አመሰገነ-----ገለጠ፣በራ፣አከበረ(ምሥጢራው ትርጉም)

ተበቀለ--ተበቀለ/በቀለኛ ሆነ----ፈረደ(ምሥጢራዊ ትርጉም)

ፈጠረ--ፈጠረ-------አከበረ(ምሥጢራዊ ትርጉም)

ተምዐ--ተቆጣ------ፈረደ(ምሥጢራዊ ትርጉም)

ምሳሌ፪፡-ገብረ ጸላዊ ዘንተ(ጠላት ይህን አደረገ)

---ለሐኰ ለሐኰ ልሑኰተ(ሸክላ ሠራ  ሸክላን ሠራ)

---ሰብሑ መላእክት ፈጣሪሆሙ(መላእክት ፈጣሪያቸውን አመሰገኑ)

---ኢትትቤቀሉ ለሊክሙ በቀለ(ራሣችሁ በራሣችሁ በቀልን አትበቀሉ)

---ፈጠረ እግዚአብሔር ዓለመ(እግዚአብሔር ዓለምን ፈጠረ)

---ተምዑ አበው ላዕለ ውሉዶሙ(አባቶች በልጆቻቸው ላይ ተቆጡ)

ከዚህ ባለይ የተመለከትነው ፊደላዊ ትርጓሜው /ነጠላ ትርጓሜው ሲሆን ቀጥሎ ደግሞ ምሥጢራዊ ትርጓሜውን እንመለከታለን፡፡

----በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ(በመጀመሪያ እግዚአብሄር ሰማይና ምድርን ፈጠረ)

----ለሐኮ አንተ ለሰብእ(አንተ ሰውን ፈተርኸው)

----ሰባሕኩከ አነ በደብር(እኔ በተራራ ገለጥሁህ)

----እትቤቀል አነ ላዕሌሁ(እኔ በእርሱ ላይ እፈርዳለሁ)

----ፈጠርከ አንተ ማኅበረከ (አንተ ማኅበርህን አከበርክ) መዝ ፸፫፥፩

----ተማዕከ አንተ መዓተከ(አንተ ፍርድህን ፈረድህ) መዝ ፸፫፥፪

ያለምሳሌ በነጠላ ንባብ ተነቦ በአንድምታ ትርጓሜ የሚተረጐም ንባብ መጻሕፍትና መሠረቱና መሪ መንገዱ ይህ የሰዋስው ዓይነት ነው፡፡

***<u>፪.ምሳሌ አዊ ነገረ ሰዋስው /ቅኔ/</u>***

ቋሚ ሐሳቡ በምሳሌ የሚነገርበት ሰዋስው ምሳሌ አዊ ነገረ ሰዋስው ይባላል ፡፡በምሳሌ የሚነገር ወይም ምሳሌ ያለው የሰዋስው አነጋገር የሰዋስው ትምህርት ነው፡፡

የተሰየመበት ምክንያት--ነገረ ሰዋስው ከሚስማማው /ሠሪና ሥራ ሐዳሪና ማደሪያ አጥፊና ጠፊ ወዘተ አይመስሉም)ምሳሌ ጋር ተመስሎ የመነገሩ ምክንያት የረቀቀ ቋሚ ሐሳብን /ምሥጢርን በአጕሊ /ረቂቁን ሐሳብ አጉልቶ በሚያሳይ ምሳሌ ገልጦ ለማስረዳት ነው፡፡

ምሳሌ አዊ ነገረ ሰዋስው /ቅኔ/ በሁለት ክፍሎች ይከፈላል ፡፡

፩.ተራ ምሳሌያዊ ሰዋስው

፪.ሰም ለበስ ምሳሌያዊ ሰዋስው

<u>፩.ተራ ምሳሌያዊ ሰዋስው</u>

«ሰም ወርቅ »በመባል ተሰይመው ምሳሌውን እና ቋሚ ሐሳቡን የሚገልጡ ሁለት ቃላት በትጓደኛ /ጐን ለጐን/ተነበው እየተፈቱ ወይም በሰም ንባብ ብቻ ተነበው በሰምና በወርቅ አፈታት እየተፈቱ አንድ ቃል ሆነው የሚነገሩበት ምሳሌያዊ ሰዋስው ተራ ምሳሌያዊ ሰዋስው ይባላል ፡፡ግልጽ ምሳሌ፣የሚታይ ምሳሌ፣ያለው ሰዋስው ማለት ነው፡፡

ምሳሌ፡-ንኅብ + ሰሎሞን----ንብ ሰሎሞን

--ገብር + ጴጥሮስ ----አገልጋይ ጴጥሮስ

--ነዳይ + ሙሴ ----ችግረኛ ሙሴ

--ሐራሲ + ጳውሎስ ----አራሽ ጳውሎስ

---ሐራዊ + ኤልያስ ---ወታደር ኤልያስ

---ጽጌ + ጥበብ ----አበባ ጥበብ

---ጾረ + ተሰቅለ ----ተሸከመ ተሰቀለ

---ቀነተ + ጸለየ ----ታጠቀ ጸለየ/ለመነ

---የአንቀጽ ስምና ወርቅ ምሳሌ በተጓዳኝ /ጐን ለጐን/ አይቀመጥም አይነገርም ፡፡አንቀጽ በስም ብቻ ተነግሮ ወርቁን ወርቁን በትርጓሜ ያመጣልና ።

ኢ.ተናባቢ ምሳሌ

ስም + ወርቅ ---ንህብ ሰሎሞን ቀስመ ጽጌ ጥበብ(ንህብ ሰሎሞን አበባ ጥበብን ለቀመ)

---ገብር ጴጥሮስ ጾረ አርዑተ መስቀል(አገልጋይ ጴጥሮስ ቀንበር መስቀልን ተሸከመ)

---ነዳይ ሙሴ በልዐ ኅብስተ ሃይማኖተ(ደኻ ሙሴ እንጀራ ሃይማኖትን ተመገበ)

---ሐራሲ ጳውሎስ ይዘርእ ዘርአ ወንጌለ(ገበሬ ጳውሎስ ዘርእ ወንጌለን ዘራ )

---ሐራዊ ኤልያስ ቀነተ ሰይፈ ጸሎተ(ወታደር ኤልያስ ሰይፍ ጸሎትን ታጠቀ)

ወርቅ + ስም ---ሰሎሞን ንህብ ቀሰመ ጥበበ ጽጌ

---ጴጥሮስ ገብር ጾረ መስቀለ አርዑተ ሲል ይገኛል፡፡

ተናባቢ ምሳሌ

ስም + ወርቅ ----ንህብ ሰሎሞን ቀስመ ጽጌ ጥበብ

----ገብር ጴጥሮስ ጾረ አርዑተ መስቀል

----ነዳይ ሙሴ በልዐ ኅብስተ ሃይማኖት

----ሐራሲ ጳዉሎስ ይዘርእ ዘርአ ወንጌል

----ሐራዊ ኤልያስ ቀነተ ሰይፈ ጸሎት

ምሳሌያዊ ነገረ ሰዋስው በሚነበብበት ጊዜ ስም ቀድሞ ወርቅ ተከትሎ ይመጣል እንጅ ወርቅ ቀድሞ ስም ተከትሎ አይመጣም አይደረግም።ቢመጣ ግን ግንባር ጸያፍ ይባላል፡፡ካልተናበበ ግን ከላይ እንደተመለከትነው ይቻላል፡፡

የተራ ምሳሌያዊ ነባር ሰዋስው መሰረቱ /መነሻው የቅዱሳት መጸሕፍት ተራ/ግልጽ ምሳሌያዊ ንባብ ነው፡፡

ቅዱሳት መጸሕፍት በየዋሕ ነገረ ሰዋስው /በነጠላ ንባብ መነገራቸውን ያህል በትራ ምሳሌያዊ ሰዋስው ተናግረዋል፡፡

ለምሳሌ፡-ኢሳይያስ እና መዝሙረ ያሬድ እንደዚህ ዓይነት ነገሮች አሏቸው፡፡

<u>ኢሳይያስ</u>፡---አጸደ ወይን ኮነ ለፍቁር(ለወዳጅ የወይን ቦታ ነበረው)

---ወእምዝ ጸናሕከሙ ለወይንየ ከመ ይፈርይ አስካለ

(ከዚህ በኋላ ሎሚ ያፈረ ዘንድ ወይኔን ጠብቄው ነበር)

---ወፈረየ አሥዋከ(ነገር ግን እሾህን አፈራ)

---አጸደ ወይኑሰ ለእግዚአብሔር ጸባዖት ቤተ ፯ኤል ውእቱ ወሰብአ ይሁዳ ውእቱ

(የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የወይን ቦታ የ፯ኤል ወገን ነው የይሁዳም ወገን ነው)

---ወጸናሕከሙ ከመ ይገብር ጽድቀ ወገብሩ ዐመፃ

(ጽድቅን ያደርግ ዘንድ ጠብቀው ነበር ነገር ግን ዐመጽን አደረጉ)

| <u>ስም</u> | <u>ወርቅ</u> |
|---|---|
| ፍቁር | እግዚአብሔር ጸባዖት |
| ዐጸደ ወይን | ቤተ ፯ኤል ሰብአ ይሁዳ |
| ጸናሕክዎ | ጸናሕከወ(ተአባዕክዎ) |
| ከመ ይፈርያ አስካለ | ከመ ይገብር ጽድቀ |
| ወፈረየ አሥዋከ | ወገብሩ ዐመፃ |

<u>፪.ሰብ ለበስ ምሳሌያዊ ሰዋስው</u>

በስም ንባብ ብቻ ተነቦ በስምና በወርቅ (በምሳሌና በቋሚ ሐሳብ) አፈታት እየተፈታ የሚነገር ሰወስው ስም ለበስ ይባላል፡፡በስም/በምሳሌ/የተሸፈነ ማለት ነው፡፡

ምሳሌ፡---ሐነጸት--አነጸች(ፈጠረ፣ሠራ/መሠረተ)

---ይስእመኒ--ይስመኛል(ይጠራኛል፣ያስተምረኛል፣ሐሞት እና ከርቤ ይጠጣልኛል፡፡)

---ይገዝምወ--ይቆርጡታል(ነፍሱን ከሥጋው ይለዩታል፡፡)

---ያውእይዎ--ያቃጥሉታል(በገሀነም ፍዳ ስቃይ ያጸኑበታል፡፡)

---ጥበብ--ጥበብ(እግዚአብሔር ወልድ)

---ቤተ--ቤትን(ዓለምን ፣ቤተ ክርስትያንን)

---በስዕመተ አፉሁ(በአፉ አሳሳም በቃሉ አጠራር፣በቃለ ወንጌል፣በምክሩ በፍቅሩ)

## <u>የቅኔ ክፍሎች /ደረጃዎች ትርጉማቸው የቤት ብዛታቸው</u>

ቅኔ በውስጡ የተለያዩ ክፍሎች ወይም ደረጃዎች ያሉት ሲሆን በቤት/ስንኝ/ ብዛታቸው ከአጭር ወደ ረጅም እንመለከታቸዋለን፡፡

***<u>፩.ጉባኤ ቃና</u>--***

ቅኔውን በመጀመሪያ የተቀኘው ሰው ሠምረ አብ ሲሆን ቀኑ የቃና ዘገሊላ ስለሆነ ይህን ስያሜ አግኝቷል።

---ሁለት ቤት ሆኖ በበዓላት እና በአደራረስ ጊዜ የሚደረስ ነው፡፡

***<u>፪.ዘአምኪዮ</u>--***

የአምላኪየ ነገር ይህ ነው /እንዲህ ነው ማለት ነው/ሠምረ አብ/

---ሦስት ቤት ሆኖ አገልግሎቱ እንደ ጉባኤ ቃና ነው፡፡

***<u>፫.ሚበዙኁ</u>--***

ንጉሡ በዕደ ማርያም ከቅዱስ ያሬድ ገብቶ እግዚአ ማበዝሁ ብሎ ተናግሯል ማለትም የሥላሴ ምሥጢር ምን ይበዛ ሲል ነው፡፡

---ሦስት ቤት ነው በተለያዩ በዓላት እና ሥርዓታት ላይ ያገለግላል፡፡

***<u>፬.ዋዜማ</u>--***

ለመምህር ሠምረ አብ ደርሷቸው ተናግረውታል፡፡

---የሠርክ መስዋዕት በሠርክ የሚደረግ ማለት ነው፡፡

---ዓምስት ቤት አለው በተለያዩ የክብረ በዓላት ዋዜማ ላይ ይጠቅማል፡፡

***፫.ሥላሴ---***

ሥላሴ ለንጉሡ በዕደ ማርያም ደርሶት በሥላሴ ቸርነት ሦስት ቅኔ ደርሰኝ ሲል ሥላሴ ብሎታል፡፡

---ስድስት ቤት ሲሆን በክብረ በዓል ዋዜማ ላይ በሙታን ፍትሐት እና በተለያዪ ሥርዓተ ቤተክርስትያን ላይ አገልግሎት ይሠጣል፡፡

***፮.ዘይዜ---***

ለመምህሩ ለሠምረ አብ ደርሶት የዛሬ ነገር ምን ያምር ሲል ይህን ተናግሯል፡፡

---ዓምስት ቤት ሲሆን ለክብረ በዓለት ፡በአጽዋማት አገልግሎት ይሰጣል፡፡

***፯.መወድስ---***

ለንጉሡ በዕደ ማርያም ደርሶት የዕለተ ሰንበት የዕሑድ ምስጋና ሲል ሰይሞታል፡፡

---ቤቱ ዐሥር ሲሆን በበዓላት እንዲሁ ስሙ እንደሚገልጸው በጾም ወራት ሌሊት ዐርባዕት በሚደረስበት ጊዜ አገልግሎት ይሠጣል፡፡

***፰.እጣነ ሞገር---***

ከቁርባን በኋላ የሚደረስ መገዝት ነው፡፡

---ቁጥሩ /ቤቱ ለእዝል ዐሥራ አንድ ሲሆን ለግዕዝ ግን ሰባት ነው፡፡

***፱.ክብር ይእቲ---***

ይህ ድርገት ሊወርድ ሲል የሚደረስ ነው፡፡

---የቤቱ ብዛት ዕዝልም ግዕዝም ዐራት ነው፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት መ/ር ሠምረ አብ እና ንጉሡ አፄ በዕደ ማርያም በጋራ ሱባኤ ገብተው ተገልጾላቸው ከቅዱስ ያሬድ ዜማ ጋር በማገናኘት ስለተናገሩ ነው፡፡በተለይ መ/ር ሠምረ አብ ከመምሩ የያዘውን በዕደ ማርያም ትክክል አይደለም ስለአሉ ሱባኤ እንግባ ተባብለው በመግባታቸው እንዲህ ተገለጸላቸው፡፡

<u>ጉባኤ ቃና ቅኔ</u>

እንግዳ ዐባይ ድንገት ቢመጣ ሲመሽ፣

አዘጋጅተዋል ግብጾች የሚተኛበት ፍራሽ፡፡

<u>ዘአምላኪየ ቅኔ</u>

እንግዲህ አላቸው በድምፅ የብዙዎች አባት ደመና፣

ዕፅዋት ነቃ ነቃ በሉ ሰማዩን እዩና፣

ከራስ ከሌለ ንቃት ተረስቶ መቅረት አለና፡፡

<u>ሚ በዝኁ ቅኔ</u>

<u>መወድስ ቅኔ</u>

ለምን እኔን ትሰድቡኛላችሁ፣

ማደሪያ የሌለው ዐባይ ግንድ ይዞ ይዞራል እያላችሁ፣

ተናደድሁኝ እና እኔም ወደሱዳን አገርገባሁ፣

በጣም ለመራቅ ወደ ግብፅ አገር ሸሸሁ፣

ወደሲናም በርሃም ተሸጋገርሁ፣

ይልቅ ሥራ ስጡኝ ዛሬም ከተሰደድሁበት መልሳችሁ፡፡

ለእድገትሂ ኢትዮጵያ ያጠባቻችሁ፣

በአንድ ቀን ሌሊት ለዘር  ወላድ ምድር አረገዘች ለደመና፣
መቼም የወላድ ሆድ ንጹሕ ጦም አያድርምና፣
የተባረከም ይሁን የማሕፀኗ ፍሬ ቅዱስ ለሰላም ለጤና፡፡

ምክሬን ካልሰማችሁ በጽሞና መከራ ይምከራችሁ፣
ሌላም ሰው አይደለ ይህን የተናገራችሁ ፣
እኔ ነኝ አባይ የጎጃሙ የመከራ ቀን አለኝታችሁ

ዋዜማ ቅኔ

ደመና ሰማይ ባለ ጉራ ፣
ቢያዘምርበት ለሞት በምድረ ሸዋና በትግሬ፣
ድርቅ የበጋ ተዋጊ ተፈታ በወሬ፣
እነቅመሞ እንኳ አሳዩ ጠላት ሳገድሉ ጎፈሬ፣
ተግባራቸውንም ደገፈ ኮስታራው በርበሬ፣
ገና ገና ያሳየናል ፍሬ፡፡

ሥላሴ ቅኔ

ዕፅዋት ተሻሻሉ፣
ልብሶቻቸውንም ለዋወጡ፣
በወርኀ ክረምት ለጋስ ፎቶ ግራፍ ሊነሱ፣
ካኪውን አውልቀው ገበሪድን ለበሱ፣
ልብስ ነውና መቼም ለሰውነታቸው ሞገሱ፣
በእድገታቸውም ገሰገሱ፣
ተሠርቷል እና ለክብር የአበሻ ቀሚሱ፣
ችግርንም ከነሱ ቀነሱ፡፡

ዘይዜ ቅኔ

ደመና ቀላል መጠጥ ወዳጅ፣
ሰክሮ ተንዛዛ በጣም ከእነ አቶ ባሕሩ ቤት ገብቶ፣
ዝርጥርጡም ወጣ በየቦታው፣

የሚቀጥለው ቅኔ ስለቅኔ ቆጣሪ ጀማሪ ተማሪ የዘረፈው ነው፡፡

ንባብ

ንዒ ንዒ ጉባኤ ቃና ድመት፣
አምጣነ ተከዕወ ለኪ ልበ ተማሪ ወተት፡፡

የቃላት ትርጉም

ንዒ ንዒ----ነይ ነይ
ጉባኤ ቃና ---የቅኔ ስም
ድመት----በቁሙ
አምጣነ----እና፣ስለ
ተከዕወ---ፈሰሰ
ለኪ----ላንቺ
ልብ----በቁሙ
ወተት----በቁሙ

ፍቺ

ድመት ጉባኤ ቃና ነይ ነይ፣
የተማሪ ልብ ወተት ፈሶልሻልና፡፡

ምሳሌና ሙያ

ንዒ ንዒ---ማሰሪያ አንቀጽ
ድመት ጉባኤ ቃና---ምሳሌ ድመት ስም
ጉባኤ ቃና----ወርቅ ተመስሎ የሰሚ

ያለአቅም ያንን ከባድ መጠጥ ጠጥቶ ጠጥቶ፣ (የዐረፍተ ነገሩ)ባለቤት

ብቻውን መሳቅ ጀመረ ደኅና የነበረው ተበላሽቶ፣ አምጣነ----አገባብ ፍቺው እናሙያው አስረጂ

አልቅስ አልቅስም አለው ከዚያ ተንዘራግቶ፣ አስረጂነቱ ለንዒ ንዒ

ነጎድጓድ የሚባል አፋም መጥፎ በዓል እንጀራ አበጅቶ፡፡ ተከዕወ----ያስር ነበር አምጣነ ወድቆ አስቀርጦታል፡

ለ---አገባብ ፍቺው በቁም ቀሪ ሙያው አቀባይ

ኪ---የአቀባይ ባለቤት

ወተት ልብ---ምሳሌ

ወተት -----ስም

ልብ ---ወርቅ ተመስሎ የአስረጂ ባለቤት

ተማሪ---የልብ ዘርፍ

ማራቀቅ

ሰሙ--ድመት ወተት ፈስሶልሻልና ነይ ነይ፡፡

ወርቁ--ተማሪ ለቅኔ ቆጠራ መዘጋጀቱን ለመናገር ነው፡፡

ከዚህ ላይ ባለቅኔው ለቅኔ ቆጣሪው ተማሪ ሐሳብ እንዲመጣለት፣ምሥጢር እንዲገለጽለት፣ተስፋ እንዳይቆርጥ ያባብለዋል፡ያደፋፍረዋል፡፡መልካም ምኞቱንም ይገልጽለታል እኛም ይህን ምሳሌ በማድረግ ጀማሪዎች ተማሪዎቻችንን ማበረታታት እና ማሞካሸት ማደፋፈር ይኖርብናል፡፡

- በድሮ ዘመን የግብጽ ንጉሥ ፈርኦን እስራኤሎችን ውኃ እያስቀዳና ጭቃ እያስረገጠ ለብዙ ዘመናት ሲገዛቸው ኖሯል፡፡ከዚያ ግፍ ለማምለጥ እስራኤሎች በሙሴ መሪነት ሸሽተው ሲሄዱ የኤርትራ ባሕር ተከፍቶ በሰላም ተሻግረዋል፡፡ፈሮንም እነሱን እይዛለሁ ብሎ ሠራዊቱን አስከትሎ በፈረስ እየሰገረ ሲደርስ ተከፍሎ የነበረው ባሕር እንደገና ተጋጥሞ ከነሠራዊቱ እና ከእነፈረሱ አብሮ ሰጠሙ፡፡የሚቀጥለው ቅኔ የተዘረፈው ይህንን በተመለከተ ነው፡፡

ንባብ

ኢይተርፍ ግፍዕ ለዘ ዕድሜሁ ጐንደየ፣

እስራኤል ለፈሮን እስመ አጾርዋ ማየ፡፡

<u>የቃላት ትርጉም</u>

ኢይተርፍ----አይቀርም

ግፍዕ----ግፍ

ለ---በቁሙ

ዘ----የ

ዕድሜሁ----ዕድሜው

ጕንደየ----ዘገየ

እስራኤል----የነገድ ስም

ለ----በቁሙ

ፈርኦን----የግብጽ ንጉሥ

እስመ----እና ፣ስለ

አጾርዎ-----አሸከሙት

ማይ----ውኃ

<u>ምሳሌና ሙያ</u>

ኢተርፍ---ማሰሪያ አንቀጽ

ግፍዕ----የቅኔ(የዐረፍተ ነገር)ባለቤት

ለ----አገባብ ፍችው በቁሙ ሙያው አቀባይ

ዘ----አገባብ ፍችው የሙያው በቂ ሆኖየአቀባይ ባለቤት

እድሜ----የቅጽል ባለቤት

ጕንደየ----ያስር ነበር ዘ ወድቆ አስቀርቶታል፡፡

እስራኤል----የአስረጂ ባለቤት

ለ----አገባብ ፍቹው«ን» ሙያው ተጠቃሽ ተጠቃሽነቱ ለአጾረዎ

ፈርኦን----የተጠቃሽ ባለቤት

እስመ----አገባብ ፍችው እና ሙያው አስረጂ

አስረጂነቱ ለኢይተርፍ

አጾርዎ-----ያስር ነበር እስመ ወድቆ አስቀርቶታል፡፡

ማይ----ተሳቢ ተሳቢነቱ ለአጾርዎ

<u>ፍቺ</u>

ዕድሜው ለዘገየ ሰው ግፍ አይቀርም፡

እስራኤሎች ፈርኦንን ውኃ አሸከመውታልና፡፡

<u>ማራቀቅ</u>

ሰሙ፡-ግፍ አይቀርም፡ሰዎች ዉኃ ሲያስቀዳቸው የነበረውን ሰው በተራቸው ውኃ አስቀድተውታልና፡፡

ወርቁ፡-እስራኤሎች ፈርኦንን ውኃ አሸከሙት ማለት ሸሽተው ሲሄዱ ፈርኦን ከእነፈረሱ በእነሱ ምክንያት መስጠሙን መናገር ነው፡፡

ከዚህ ላይ ባለቅኔው የሚያሳስበው ግፍ የሚዋልበት ሰው ሁሉ ብድሩን እንደማያጣ ግፍ የሚሰራ ደግሞ ተመልሶ በራሱ ላይ እንደሚውል ያሳስባል፡፡

ይህ ባለቅኔ በዓለም ላይ ያሉ አምባገነኖች ያለ ጥንቃቄ በሰዎች ላይ የሚያደርሱትን ግፍ እንዲቀንሱ የሚከተለውን ምክር አዘል ይየቅስባቸዋል፡፡

«ድሮ ነበር እንጂ መጥኖ መደቆስ ፣

አሁን ምን ያደርጋል ድስቱን ጥዶ ማልቀስ፡፡

የሚቀጥለው ቅኔ ደግሞ በድነጋይ ተደብድቦ ስለተገደለው ስለ ሰማዕቱ እስጢፋኖስ ነው፡፡

<u>ንባብ</u>

ከንቱ ውእቱ ትምህርቱ ለእስጢፋኖስ ካህን፣

እስመ በላእሌሁ ነበሩ ዘኢተምህሩ አእባን፡፡

<u>የቃላት ትርጉም</u>

ከንቱ---በቁሙ ብላሽ

ውእቱ---ነው

ትምህርቱ---ትምርቱ

ለ-----የ

እስጢፋኖስ----የሰማዕት ስም

ካህን----በቁሙ

እስመ----እና፣ስለ

ላዕሌሁ----በላዩ

ነበሩ-----ተቀመጡ

ኢተምህሩ-----አልተማሩም

አእባን----ድንጋይ

<u>ፍቹ</u>

የካህን እስጢፋኖስ ትምህርት ከንቱ ነው፣

ያልተማሩ ድንጋዮች በላዩ ላየ ተቀምጠዋልና፡፡

<u>ምሳሌውና ሙያው</u>

ከንቱ ----የውእቱ ተለዋጭ

ውእቱ----ማሰሪያ አንቀጽ

ትምህርት ----የቅኔ (የዐረፍተ ነገሩ )ባለቤት

ለ----አገባብ ፍችው «የ» ሙያው  ዘርፍ አያያዥ ዘርፍ አያያዥነቱ ትምህርተ እስጢፋኖስ ካህን የሚያሰኝ፡፡

ካህን እስጢፋኖስ---ምሳሌ

ካህን----ሰም

እስጢፋኖስ----ወርቅ ተመስሎ የትምህርት ዘርፍ

እስመ----አገባብ ፍችው እና ሙያው አስረጂ አስረጂነቱ ለውእቱ

በ----አገባብ ፍችው በቁም ቀሪ ሙያው ማድረግ

ላዕሌሁ----የማድረጊያ ባለቤት

ነበሩ----ያስር ነበር እስመ ወድቆ አስቀርቶታል

ዘ----አገባብ ፍችው የሙያው ቅጽል ወይም አዝማች ቅጽል ቅጽልነቱ ለአእባን፡፡

ኢተምህሩ---ያስር ነበር ዘ ወድቆ አስቀርቶታል፡፡

አእባን----የአስረጂ ባለቤት

ማራቀቅ

ሰሙ፡--የካህኑ ትምህርት ከንቱ ነው ፡፡በላዩ ላይ ያልተማሩ ደናቁርት

ተቀምጠዋልና ፣ተሾመዋልና

ወርቁ፡--ሰማዕቱ እስጢፋኖስ በድንጋይ ተደብድቦ መገደሉን ለመናገር ነው፡፡በላዩ ላይ

የተከመረው ድንጋይም አንድ ቤተክርስትያን ያሠራ ነበር ይባላል፡፡

ባለቅኔው የሚነግረን ያለፉት የሃይማኖት ሰዎች ከእምነታቸው ያልተናጉ ገንዘብ ያላታለላቸው የሹመት ጦር ያልወጋቸው እና ፈጣሪያቸውን ይወዱ የነበሩ መኾናቸውን ነው፡፡በሀገራችን በኢትዮጵያም እውነተኛ ሃይማኖታቸውና ስለሀገራቸው በፋሽስት እጅ የተሰውትን እነ አቡነ ጴጥሮስን እንድናስታውስ ያደርገናል፡፡

- ጌታ ኢየሱስ በቤተልሔም በተወለደ ጊዜ ለንጉሥ ሄሮድስ መንግሥትህን የሚቀናቀን ሕፃን ተወለደ ብለው ነገሩት፡እርሱን አገኛለሁ ብሎ ብዙ ሕፃናትን በሰይፍ ፈጀ፣ገደለ፡ዮሴፍም ይህን በሰማ ጊዜ ከሰሎሜ ጋር ሕፃኑን እና እናቱን ድንግል ማርያምን ይዞ ወደ ግብጽ ተሰደደ የሚቀጥለው ቅኔ የተነገረው ስለዚህ ነው፡፡

ንባብ

መሰለ ዮሴፍ ዘየአውዕያ ለግብጽ፣

አኮኑ ወረደ በነሲአ እሳት ወዕፅ፡፡

| የቃላት ትርጉም | |
|---|---|
| መሰለ---መሰለ | አኮኑ----እና |
| ዮሴፍ---የሰው ስም | ወረደ----ወረደ |
| ዘ----የ | በ----በቁሙ |
| የአውዕያ----ያቃጥላል | ነሲእ----መያዝ |
| ለ----ን | እሳት----በቁሙ |
| ግብጽ-----የአገር ስም | ወ----እና |
| | ዕፅ----ዕንጨት |

ፍቺ

ዮሴፍ ግብጽን የሚያቃጥላት መሰለ፡እሳት እና

እንጨት ይዞ ወርዷልና፡፡

ምሳሌና ሙያ

መሰለ---ማሰሪያ አንቀጽ

ዮሴፍ----የቅኔ(የዐረፍተ ነገሩ) ባለቤት

ዘ----አገባብ ፍቺው የሙያው ተሳቢ ተሳቢነቱ ለመሰለ

የአውዕያ ---ያስር ነበር ዘ ወድቆ አስቀርቶታል፡፡

ለ----አገባብ ፍቺው«ን» ሙያው ተጠቃሽ ተጠቃሽነቱ ለአውዕያ

ግብጽ---የተጠቃሽ ባለቤት

አኮኑ----አገባብ ፍቺው እና ሙያው አስረጂ አስረጅነቱ ለመሰለ

ወረደ---ያስር ነበር አኮኑ ወድቆ አስቀርቶታል

በ----አገባብ ፍቺው በቁሙ ቀሪ ሙያው ማድረግ

ነሲእ---የማድረጊያ ባለቤት

እሳትናዕፅ ---በ«ወ»ተጫፍረው የነሲእ ዘርፍ

ወ---አገባብ ፍቺው እና ሙያው አጫፋሪ

ማራቀቅ

ሰሙ፡ --ዮሴፍ ግብጽን የሚያቃጥላት መሰለ፣እሳት እና

እንጨት ይዞ ወረደ፡፡

ወርቁ፡--እሳት--በቁሙ፣ዕፅ--እንጨት

እሳት--ጌታ ዕፅ---እመቤታችን

ዮሴፍ እሳትና እንጨት ይዞ ወረደ ማለት ጌታን እና እመቤታችንን ይዞ ወደ ግብጽ መሰደዱን ለመናገር ነው፡፡

በቅኔ ቤት አንዱ ቃል ሁለት ትርጉም ይዞ ሲገኝ ኅብር ይባላል፡፡ለምሳሌ ያህል ከዚህ በላይ ያየነውን ቅኔ ማስተዋል በቂ ነው፡፡

ባለቅኔው ይህንን ቅኔ አስታኮ ችግር በመጣ ጊዜ ራሳችንን እንድናድን ያስጠነቅቀናል፡፡ድንጋይ እና ጦር ቢወረወርብን ጠበንጃም ቢደገንብንም ዝቅ ወይም ዞር ብለን እንድናሳልፍ እንጂ ለከንቱ ውዳሴ ደፋር ይበሉን ብለን ደረታችንን ገልብጠን ለጠላት መጋለጥ እንደሌለብን ይነገረናል፡፡ራሳችንን ካዳንን በኋላ ግን ጠላታችንን እንደምናሸንፍ ያስተምረናል፡፡

ቅጸላ(ጥናት)

ከዘአምላኪየ እስከ መወድስ ቅኔ የሚቀጥለው ዘአምላኪየ ቅኔ ወርኀ ክረምትን ይመለከታል፡፡

ዘአምላኪየ ቅኔ ንባብ

ምንተ ኮነ በዐውደ ክረምት እግዚኡ፣

ገብር ደመና ዘጸሊም መልክዑ፣

አኮኑ ይሥሐቅ እሰከ ይወርድ አንብኡ፡፡

የቃላት ትርጉም

ምንት---ምን ጸሊም---ጠቋራ፣የተቆረ

በ---በቁሙ መልክዐ---መልኩ

ዐውድ---አደባባይ አኮኑ----እና ፣ስለ

ክረምት---በቁሙ ይሥሐቅ---ይሥቃል

እግዚኡ---ጌታው እስከ----ድረስ

ገብር----አገልጋይ ይወርድ----ይወርዳል

ዘ----የ አንብኡ----እንባው

ፍቺ

መልኩ የተቆረ አገልጋይ ደመና በጌታው፣

ክረምት አደባባይ ምን ሆነ?ምን ነካው?

እንባው እስኪረግፍ ይሥቃልና፡፡

ምሳሌና ሙያ

ምንት ---ተሳቢ ተሳቢነቱ ለኮነ

ኮነ ---ማሰሪያ አንቀጽ ይስባል እንጂ አይሳብም፡፡

በ ---አገባብ ፍቺው በቁም ቀሪ ሙያው ማድረጊያ

ዐውድ ----የማድረጊያ ባለቤት

እግዚኡ ክረምት ----ምሳሌ እግዚኡ ስም ክረምት ወርቅ ተመስሎ የዐውድ ዘርፍ

ገብር ደመና---- ምሳሌ ገብር ስም ደመና ወርቅ ተመስሎ የቅኔ (የዐረፍተ ነገር ባለቤት)

ዘ ---- አገባብ ፍቺው የሙያው ቅጽል ቅጽልነቱ ለገብር ደመና

ጸሊም ---- ውስጠ ዘ ሆኖ ያስር ነበር ዘ ወድቆ አስቀርቶታል፡፡

መልክዑ ---- የቅጽል ባለቤት

አኮኑ ---- አገባብ ፍቺው እና ሙያው አስረጅ አስረጅነቱ ለኮነ

ይሥሕቅ ---- አንቀጽ ያስር ነበር አኮኑ ወድቆ አስቀርቶታል ፡፡

እስከ ----- አገባብ ፍቿው ድረስ ሙያው መድረሻ

ይወርድ ---- ያስር ነበር እስከ ወድቆ አስቀርቶታል

አንብኡ ---- የመድረሻ ባለቤት

ማራቀቅ

ሰሙ፡- ዛሬ ይኼ ጠቋራ አገልጋይ ምን ነካው? ምንስ ሆነ?

በጌታው ፊት እንባው እስከሚረግፍ ይሥቃልና፡፡

ወርቁ፡-ዝናብ በደመና አማካኝነት መዝነቡን ለመናገር ነው፡፡ይሠቃል ማለትም ዝናብ በሚዘንብበት ጊዜ

ሰማዩ ብልጭ ድርግም ማለቱን ለመናገር ነው፡፡

የሚቀጥለውን ቅኔ ስለ ጌታ ሥጋ መልበስና መሞት የተነገረ ነው፡፡

ሚ፣በዝኍ ቅኔ ንባብ

ሐሜተ ክልኤቱ አኃው ዘኢይፈርህ ወልድ በልዐ በተክበቶ፣

ሥጋ ጥዑመ እንዘ የዐዱ ጥኅተ ፣

ወፍሉጠ ሞት ኮነ ባሕቲቶ ዘበልዐ እስመ ይመውት ባሕቲቶ፡፡

የቃላት ትርጉም

| | |
|---|---|
| ሐሜት ---- አሜት | ጥዑም --- ጣፋጭ |
| ክልኤቱ ---- ሁለት | የዐጹ --- ይዘጋል |
| አኀው ---- ወንድማማቾች | ጥኅቶ ---- በሩን |
| ዘ ---- የ | እንዘ ---- እየ(አፍዛዥ) |
| ፈርሀ ---- ፈራ | ፍሉጥ ---- የተለየ |
| ወልደ --- ልጅ | ሞት ---- በቁሙ |
| በልዐ ---- በላ | ባሕቲቶ ---- ብቻውን |

በ ----በቁሙ　　　　　　　　　　እስመ ---- እና ፣ስለ

ተከብቶ ---- መደበቅ፣መሸሸግ　　　　ይመውት ----- ይሞታል

ሥጋ ---- በቁሙ

ፍቺ

የሁለቱን ወንድማማቾች ሐሜት ያልፈራ ልጅ በሩን ዘግቶ፣

ብቻውን ጣፋጭ ሥጋ በላ ፣ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል፡፡

እና በሞትም የተለየ ሆነ፡፡

ምሳሌ እና ሙያው

ሐሜት --- ተሳቢ ተሳቢነቱ ለኢፈርሀ

ክልኤቱ ---- ቅጽል ቅጽልነቱ ለአኃው

አኃው ---- የሐሜት ዘርፍ

ዘ ---- አገባብ ፍቺው «የ» ሙያው ቅጽል ቅጽልነቱ ለወልድ

ኢ ---- አገባብ ፍቺው የሙያው ቅጽል ቅጽልነቱ ለወልድ

ኢ ----- አገባብ ፍቺው አል(ያል) ሙያው አፍራሽ (አሉታ)

ኢፈርሀ ---- ያስር ነበር ዘ ወድቆ አስቀርቶታል ፡፡

ወልድ ---- የቅኔ (የዐረፍተ ነገር )ባለቤት

በልዐ ---- ማሰሪያ አንቀጽ ይሰባል እንጂ አይሳብም፡፡

በ ---- አገባብ ፍቺው በቁም ቀሪ ሙያው ማድረጊያ

ተከብቶ ---- የማድረጊያ ባለቤት

ሥጋ ---- ተሳቢ ተሳቢነቱ ለበልዐ

ጥዑም ---- ቅጽል ቅጽልነቱ ለሥጋ

እንዘ --- አገባብ ፍቺው እየ(ቸልታ) አፍዛዥ ሙያው ማንጸሪያ

የዐጹ ----- ያስር ነበር እንዘ ወድቆ አስቀርቶታል፡፡

ኆኅት ---- ተሳቢ ተሳቢነቱ ለየዐጹ

ወ ---- አገባብ ፍቺው ም ሙያው ዋዌ

ፍሉጥ ---- ተሳቢ ተሳቢነቱ ለኮነ

ሞት ---- የፍሉጥ ዘርፍ

ኮነ ---- በዋዌ የተደገመ ማሰሪያ አንቀጽ

ባሕቲቶ ---- ተሳቢ ተሳቢነቱ ለበለዐ

ዘ ----- አገባብ ፍችው የሙያው በቂ ሆኖ የአስረጅ ባለቤት

በልዐ ---- ያስር ነበር ዘ ወድቆ አስቀርቶታል፡፡

እስመ ---- አገባብ ፍቺው እና ሙያው አስረጅ አስረጅነቱ ለኮነ

ይመውት ----- ያስር ነበር ዘ ወድቆ አስቀርቶታል ፡፡

ባሕቲቶ ---- ተሳቢ ተሳቢነቱ ለይመውት

ማራቀቅ

ሰሙ፡ --- ሐሜት የማይፈራ ሰው ቤቱን ዘግቶ ያረደውን ሥጋ ብቻውን በላ፡፡

በደጎና ጊዜ ጐረቤትና ወገን የማይወድ ሰው የሚመጣውን መከራ

ሁሉ ለብቻው ይቀበላል፡፡ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታልና፡፡

ወርቅ፡---- ሁለት ወንድማማቾች የተባሉትም አብና መንፈስ ቅዱስ ናቸው፡፡

ወልድ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ተለይቶ ሥጋ ለብሷል፡፡

ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል፡፡ማለትም ከአብና ከመንፍስ

ቅዱስ ተለይቶ ሥጋ ስለለበሰ በሞትም ብቸኛ ኾነ፣ብቻውን ሞተ

ማለት ነው፡፡ባለቅኔው የሚያስተምረን ጌታ በለበሰው ሥጋ ጸዋትወ መከራን መቀበሉን ነው፡፡

ዋዜማ ቅኔ

በአንድ ቤተክርስትያን አንድ የደብር አለቃ ተሹሞ ሳለ በላዩ ላይ አዲስ አለቃ ተሹሞ መጣበት፡፡

ይህም አዲሱ ሹም መልአከ ይባል ነበር ፡፡በእድሜና በአካልም ገዝፎ ይታይ ነበር ይባላል፡፡

ብዙን ጊዜ ነባር አለቆች በላያቸው ላይ ሌላ ሲሾምባቸው አይወዱም ደስ አይላቸውም፡፡

ስለዚህ ቀደም ብሎ የነበረው የደብር አለቃ አዲሱን ሹም በሚከተለው ቅኔ ተቸው፡፡

<u>ንባብ</u>

ለመልአክ ኢናከብሮ ለእመ አሥረጸ ክንፈ በመጠነ ነዊኀ ቆሙ፣

ለአፍ ወለ ትንንያ እስመ ክንፍ ቦሙ፣

ወበ ሢበቱ ለሰብእ ኢናከብሮ ቀዲሙ፣

ጸዐዳ ሢበት እስመ ሀለዎሙ፣

ለዕፅው ወአእባን ኩሎሙ፡፡

<u>የቃላት ትርጉም</u>

| | |
|---|---|
| ለ ----ን | ቦሙ ----አላቸው |
| መልአክ ----በቁሙ | ሢበት ----ሽበት |
| ኢናከብሮ ----አናከብርም | ሰብእ -----ሰው |
| እመ -----ቢ | ቀዲሙ -----አስቀድሞ |
| አሥረጸ ----አበቀለ | ጸዐደ -----ነጭ |
| ክንፍ ----በቁሙ፣ልክ | ሀለዎሙ -----አላቸው |
| ነዊኀ -----ረጅም | ዕፅው ----ዕንጨቶች |
| ቆሙ ----ቁመቱ | አእባን ----ደንጋዮች |
| ለ -----በቁሙ | ኩሎሙ ----ሁሉም |
| አፍ ----ወፍ | ወ ---- እና |
| ትንንያ ----ትንኝ | |

<u>ፍቺ</u>

- በቁመቱ ልክ ክንፍ ቢያበቅል መልአክን አናከብረውም ክንፍስ ለወፍና ለትንኝም አላቸውና፡፡ሰውንም በሽበቱ አስቀድመን አናከብረውም ፡፡ነጭ ሽበትማ ለዕፅዋትና ለድንጋዮቹ ሁሉ አላቸውና፡፡

<u>ምሳሌና ሙያ</u>

ለ ---- አገባብ ፍቺው«ን» ሙያው ተጠቃሽ ተጠቃሽነቱ ለኢናከብሮ

መልአከ ----- የተጠቃሽ ባለቤት

ኢናከብሮ ---- ማሰሪያ አንቀጽ ይሰባል እንጂ አይሳብም

ለ ----- አዳማቂ ትርጉም የለሽ

እመ ---- አገባብ ፍቺው ቢ ሙያው ማንጸሪያ

አሥረጸ ---- ያስር ነበር እመ ወድቆ አስቀርቶታል፡፡

ክንፍ ----- ተሳቢ ተሳቢነቱ ለአሥረጸ

በ ----- ያለው አገባብ ፍቺው በቁም ቀሪ ሙያው ማድረጊያ

መጠን ----- የማድረጊያ ባለቤት

ነዊኅ ---- ቅጽል ቅጽልነቱ ለቆሙ

ቆሙ ----- የመጠን ዘርፍ

ለ ----- አገባብ ፍቺው በቁም ቀሪ ሙያው አቀባይ

አፍ ትንንያ ----- በወ ተጫፍረው የአቀባይ ባለቤት

ወ ----- አገባብ ፍቺው በቁም ቀሪ ሙያው አቀባይ

እስመ ---- አገባብ ፍቺው እና ሙያው አጫፋሪ

ክንፍ ---- የአስረጅ ባለቤት

ቦሙ ---- ያስር ነበር እስመ ወድቆ አስቀርቶታል፡፡

ወ ----- አገባብ ፍቺውም ሙያውም ዋዌ

በ ----- አገባብ ፍቺው በቁም ቀሪ ሙያው ማድረጊያ

ሢበት ---- የማድረጊያ ባለቤት

ለ ---- አገባብ ፍቺው «ን» ሙያው ተጠቃሽ ተጠቃሽነቱ ለኢናከብሮ

ሰብእ ---- የተጠቃሽ ባለቤት

ኢናከብሮ ----- በዋዌ የተደገመ ማሰሪያ አንቀጽ

ቀዲሙ ----- አንቀጽ አጎላማሽ

ጸዐዳ ----- ቅጽል ቅጽልነቱ ለሢበት

ሢበት ----- የአስረጂ ባለቤት

እስመ ---- አገባብ ፍቺው እና ሙያው አስረጅ አስረጅነቱ ለኢናከብሮ

ሀለዎሙ ----- ያስር ነበር እስመ ወድቆ አስቀርቶታል፡፡

ለ ----- አገባብ ፍቺው በቁም ቀሪ ሙያው አቀባይ

ዕፅውና አእባን ----- በ ወ ተጫፍረው የአቀባይ ባለቤት

ወ ----- አገባብ ፍቺው እና ሙያው አጫፋሪ

ኵሎሙ ----- ቅጽል ቅጽልነቱ ለዕፅውና ለአእባን

<u>ማራቀቅ</u>

ሰሙ፡--መልአክን በቁመቱ ልክ ክንፍ አለው ብለን እናከብረውም፡፡ክንፍማ ለወፎችና ለትንኞችም አላቸውና፡፡

ሰውንም ቢሆን ሽበት አለው ብለን አስቀድመን አናከብረውም ፡ሽበትማ ለእንጨቶችና ድንጋዮች አላቸውና፡፡

ወርቅ፡---ቀደም ብሎ የተሾመው ሰውዬ በእንጀራው ላይ ስለ መጣበት በኋላ የመጣውን አለቃ ማጥላላቱ ነው፡፡ምንም እንኳን በኋላ የመጣው አለቃ አምሮ ጠምጥሞ ቢታይም በችሎታው ይህን ያህል አልነበረም፡፡ሰውን በሽበት አናከብረውም ፡ማለት በአስተዋይነቱ እና በእውቀቱ እናከብረዋለን እንጂ በእድሜና በሽበት ግን ልናከብረው አንችልም፡፡ባለቅኔው «አኮ በሢበት አላ በአእምሮ(በዕውቀት እንጂ በሽበት )» ሊከበር አይችልም የሚለውን ያስታውሰናል፡

ከዚህ በላይ እንዳየነው ከሆነ ሁለቱ ተሿሚዎች በስልጣን ሽሚያ ዐይን እና አፈር ሆነዋል፡፡ይህ የተሿሚዎች ስሕተት አይደለም፡፡በዳኝነት ሲታይ የሿሚው ስሕተት ነው፡፡ሿሚው መጀመሪያ ለሾመው ሰው ቦታ ሳይሰጥ ፡ቦታውን ለሹመት ሳያጸዳ የሹመት ደብዳቤ አስይዞ ሁለተኛውን ሰው ልኳል፡፡ጠቡ የተፈጠረው በዚህ ጊዜ ነው፡፡ይህ ዐይነቱ ነገር ወደፊት ባይደጋገም ለሿሚዎችም ሆነ ለተሿሚዎች ይበጃል፡፡

እንደ ባለቅኔው አስተሳሰብ አንዳንድ ሰዎች ዕድሜያቸው የማይፈቅደውን በአነጋገርም ሆነ በተግባር የሚያሳዩ ካሉ በዕድሜያቸውም ሆነ በሽበታቸው ከዚህ መጥፎ ተግባራቸው እስካልተቆጠቡ ድረስ ለከበሩ

አይችሉም፡፡ይሁን እንጅ አሪት «አክብር ገጸ አረጋዊ» ስለምትል በዕድሜ ጠና ያሉ ሰዎችን ማክበር አስፈላጊ ነው፡፡በኋላም ብድራችንን እናገኛለን፡፡

ሥላሴ ቅኔ

ሰቃልያን ጌታን በአምስት ችንካሮች ቸንከረውታል፡፡ቅኔውም ይህን በተመለከተ ነው፡፡

ንባብ

ወልድ ፈደለ አልፋ ላዕሌሁ ለዕፅ አመ ተሰፍሐ፡

ሕማማተ ሥጋ ደቂቅ ከመኪያሁ ያንብቡ፣

ሣዕረ ቀኖት ሐጺን ነሢአሙ ቀርቡ፣

ለመምህሮሙ ትጉህ ይሁዳ እንተ ፈድፈደ ጥበቡ፣

ሠላሳ ብሩር አምጣነ ዐስቡ፣

ወጽሕፈተ ዝንቱ ፊደል በማይ ኅጸቡ፣

እስመ ሖረ ውስተ ደይን ምስካቡ፡፡

የቃላት ትርጉም

| | |
|---|---|
| ወልድ ---- ልጅ | ቀኖት ------ ችንካር |
| ፈደል ----- በቁሙ | ሐጺን ------ ብረት |
| አልፋ ----- የመጀመሪያ | ነሢአሙ ----- ይዘው |
| ላዕሌሁ ----- በላይ | ቀርቡ ----- ቀረቡ |
| ለ ------ የ | መምህሮሙ ----- መምህራቸው |
| ዕፅ -----እንጨት | ትጉህ ----- በቁሙ፣ታታሪ |
| አመ ----- ጊዜ | እንተ ----- የ |
| ተሰፍሐ ---- ተዘረጋ | ፈድፈደ ---- በዛ |

ሕማማት ----- መከራዎች ሠላሳ ----- በቁሙ

ሥጋ ------ በቁሙ ብሩር ------ ብር

ደቂቅ ----- ልጆች አምጣነ ----- እና ፣ስለ

አመ ----- አዳማቂ ትርጉም አልባ ዐስቡ ----- ደሞዙ

ኪያሁ ----- እሱን ጽሕፈት ----- በቁሙ

ያንብቡ -----ያነቡ ዘንድ ዝንቱ ----- ይህ

ሣዕር ----- ሣር ማይ ----- ውኃ

ኀጸቡ --- አጠቡ ደይን ------ መከራ

እስመ ----- እና ምስካብ ----- መኝታ

ውስተ ----- ውስጥ ይሁዳ ------- የሰው ስም

ፍቺ

የመጀመሪያው ወልድ ፊደል በዕንጨት ላየ በተዘረጋ ጊዜ የሥጋ

መከራዎች ልጆች እሱን ያነቡት ዘንድ የብረትን ችንካር ሣር ይዘው ቀረቡ፡፡

ጥበቡ የበዛ መምህራቸው ይሁዳ በሠላሳ ብር ተቀጥሮላቸዋልና፡፡እሱ ወደ መከራ

መኝታ ቤቱ ስለሄደ የወልድ ፊደል ጽሕፈትን በውኃ አጠቡ፡ደመሰሱ፡፡

ምሳሌና ሙያው

ፊደል ወልድ ---- ምሳሌ ፊደል ስም ወልድ ወርቅ ተመስሎ የማንጸሪያ ባለቤት

አልፋ ----- የፊደል ዘርፍ

ላዕሌሁ ----- የማድረጊያ ባለቤት

ለ ----- አገባብ ፍቺው የሙያው ዘርፍ አያያዥ ዘርፍ አያያዥነቱ ላዕለ ዕፀ የሚያሰኝ፡

ዕፀ ------ የላዕለ ዘርፍ

አመ ----- አገባብ ፍቺው ጊዜ ሙያው ማንጸሪያ

ተሰፍሐ ----- ያስር ነበር አመ ወደቀ አስቀርቶታል፡፡

ደቂቅ ሕማማት ------ ምሳሌ ደቂቅ ስም ሕማማት ወርቅ ተመስሎ የቅኔ (የዐረፍተ ነገሩ ባለቤት)

ሥጋ ----- የሕማማት ዘርፍ

ከመ ------- አዳማቂ

ኪያሁ ------- ተሳቢ ተሳቢነቱ ለያንብቡ

ያንብቡ ------ ዘንድ አንቅጽ

ሣዕር ቀኖት ------ ምሳሌ ሣዕር ስም ቀኖት ወርቅ ተመስሎ ተሳቢ ተሳቢነቱ ለነሢአሙ

ሐጺን ----- የቀኖት ዘርፍ

ነሢአሙ ----- ቦዝ አንቀጽ

ቀርቡ ----- ማሰሪያ አንቀጽ

ለ ------ አገባብ ፍቺው የሙያው ዘርፍ አያያዥ ዘርፍ አያያዥነቱ ዐስበ መምህር ይሁዳ የሚያሰኝ

መምህር ይሁዳ ------ ምሳሌ መምህር ስም ይሁዳ ወርቅ ተመስሎ የዐስብ ዘርፍ

እንተ ----- አገባብ ፍቺው የሙያው ቅጽል ቅጽልነቱ ለመምህር ይሁዳ

ፈድፈደ ----- ያስር ነበር እንተ ወድቀ አስቀርቶታል፡፡

ጥበብ ----- የቅጽል ባለቤት

ሠላሳ ----- የብሩር ቅጽል

ብሩር ------ ኀብር ሆኖ የአስረጅ ባለቤት

አምጣነ ----- አገባብ ፍቺው እና ሙያው አስረጅ አስረጅነቱ ለቀርቡ

ዐስቡ ----- ያስር ነበር አምጣነ ወድቀ አስቀርቶታል፡፡

ወ ------ አገባብ ፍቺው ም ሙያው ዋዌ

ጽሕፈት ----- ተሳቢ ተሳቢነቱ ለኀፀቡ

ፊደል ----- የጽሕፈት ዘርፍ

በ ------- አገባብ ፍቺው በቁም ቀሪ ሙያው ማድረጊያ

ማይ ----- የማድረጊያ ባለቤት

ኀፀቡ ------ በዋዌ የተደገመ ማሰሪያ አንቀጽ ይስባል እንጂ አይሳብም

እስመ ----- አገባብ ፍቺው እና ሙያው አስረጂ አስረጅነቱ ለኀፀቡ

ሖረ ------ ያስር ነበር እስመ ወድቆ አስቀርቶታል፡፡

ምስካብ ደይን ------ ምሳሌ ምስካብ ስም ደይን ወርቅ ተመስሎ የውስተ ዘረፍ

ማራቀቅ

ሰሙ፡--- ልጆች የፌደል ገበታ በተዘረጋ ጊዜ ሀ ሁ ን ለመማር መጠንቆያሣር

ይዘው ቀረቡ፡፡መምህር በሠላሳ ብር ተቀጥሮላቸዋልና መምህራቸውም

ደክሞት ወደ መኝታ ቤት ስለሄደ ሕፃን መሆን አይቀርምና የፊደሉን

ገበታ በውኃ ፣ አጠቡት ፣ፊደሎችም ተደመሰሱ፡፡

ወርቁ፡--- ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በተሰቀለ

ጊዜ መከራ ተቀብሏል፡በብረት ችንካሮችም ተቸንክሯል፡፡ይህ መከራ

እንዲፈጸምበት ይሁዳ በሠላሳ ብር ሸጦታልና ፡በጦር በተወጋ ጊዜም

ደምና ውኃ ፈስሷል፡፡ይሁዳም ወደደይን ሄዷል ማለት ተፈረዶበት ተቀጣ ማለት ነው፡፡

የሸያጭ ነገር ከተነሳ ዘንድ የያዕቆብ ልጆች አባታቸው ስለወደደው ቀንተው ወንድማቸውን ዮሴፍን በሠላሳ ብር ለግብጻውያን ሸጠዋል፡፡ዮሴፍ ግን ተሸጦ በሄደበት የግብፅ ሕዝብ እና ንጉሥ ዘንድ ክብርና ሞገስ አግኝቶ ተሾመ፡፡በግብፅና በእስራኤል ረሀብ በሰፈነ ጊዜና ወንድሞቹ እህል ፍለጋ በመጡ ጊዜ የሠሩትን በደል ይቅር ብሎ ለወንድሞቹ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ሰጥቷቸዋል፡፡ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም አስረው የሾህ አክሊል በራሱ ጭነው ፡መስቀሉን አሸክመው እየተዘባበቱበት በችንካር መትተው የሰቀሉትን እና ውኃ እያለ ሐሞት(ሬት) ያጠጡትን እና ጎኑን በጦር የወጉትን አይሁድ «አባት ሆይ የሚሠሩትን አያውቁትምና ይቅር በላቸው» ብሎ ነው የጸለየላቸው፡፡

ዘይዜ ቅኔ

የሚቀጥለው ቅኔ ድንግል ማርያም ጌታን በመውለዷ የተነገረ ነው፡፡

ንባብ

እምጥንት ኢመልኡ እስከ ይእዜ፣

አዳም ወሔዋን ዘአበዊሆሙ ቤተ፣

አመይወልዱ ክልኤተ ክልኤተ፣

ማርያም ሰ ዘነሥአት ቅድስተ ቅዱሳን በረከተ፣

መልአት ምድረ ወሰማያተ ፣

ወሊዳ ዋሕደ ወተወሊዳ አሐተ፣

መልአት ምድረ ወሰማያተ፡፡

የቃላት ትርጉም

| | |
|---|---|
| እም ---- ከ፣ጀምሮ | ነሥአት ---- ወሰደች |
| ጥንት ------ ድሮ | ቅድስት ----- ክብርት |
| ኢ ------ አፍራሽ | ቅዱሳን ----- የተከበሩ |
| መልአ ----- ምሉ | በረከት ----- በቁሙ |
| ይእዜ ----- ዛሬ | መልአት ----- ሞላች |
| አዳም ----- የሰው ስም | ምድር ---- በቁሙ |
| ሔዋን ----- የሰው ስም | ሰማያት ------ ሰማዮች |
| ዘአበዊሆሙ ----- የአባቶቻቸው(ሥላሴ) | ወሊዳ ----- ወልዳ |
| ቤት ------ በቁሙ | ዋሕድ ------አንድ |
| አመ ------ ጊዜ | ተወሊዳ ----- ተወልዳ |
| ይወልዱ ----- ይወልዳሉ | አሐተ ----- አንድ ኹና |

ክልኤተ ክልኤተ ---- ሁለት ፣ሁለት ማርያም ----- የጌታ እናት

ሰ ----- ግን ፣ነገር ግን ዘ ------- የ

ፍቺ

አዳምና ሔዋን ከጥንት ጀምሮ ሁለት ሁለተ በወለዱ ጊዜ፣ የአባቶቻቸውን የሥላሴን ቤት አልመሉም ፡፡ከቅዱሳን ይልቅ የተከበረች በረከትን የተቀበለች ማርያም ግን አንድ ወልዳ እና አንድኹና ተወልዳ ምድር እና ሰማይን ሞላች፡፡

ምሳሌና ሙያ

እም ---- አገባብ ፍቺው ከሙያው መነሻ

ጥንት ----- የመነሻ ባለቤት

ኢመልኡ ----- ማሰሪያ አንቀጽ ይስባል እንጅ አያስብም

እስከ ----- አገባብ ፍቺው ድረስ ሙያው መነሻ

ይእቲ ------ የመድረሻ ባለቤት

አዳምና ሔዋን ----- በ ወ ተጫፍረው የቅኔ ባለቤት

ዘ ----- አገባብ ፍቺው የ ዘርፍ ደፊ ዘርፍ ደፊነቱ ቤተ አበዊሆሙ የሚያሰኝ ፡፡

አበዊሆሙ ----- የቤት ዘርፍ

ቤት ------- ተሳቢ ተሳቢነቱ ለይወልዱ

ማርያም ----- የአፍራሹቅኔ ባለቤት

ሰ ----- አገባብ ፍቺው ግን ሙያው አፍራሽ

ዘ ------ አገባብ ፍቺው የ ሙያው ቅጽል ቅጽልነቱ ለማርያም

ነሥኦት ----- ያሥር ነበር ዘ ወድቆ አስቀርቶታል፡፡

ቅድስት ----- ቅጽል ቅጽልነቱ ለበረከት

ቅዱሳን ----- የቅድስት ዘርፍ

በረከት ----- ተሳቢ ተሳቢነቱ ለነሥአት

መልአት ------ የአፍራሹ ቅኔ ማሰሪያ አንቀጽ

ምድርና ሰማያት ----- በ ወ ተጫፍረው ተሳቢ ተሳቢነታቸው ለመልአት

ወ ----- አገባብ ፍቺው እና ሙያው አጫፋሪ

ወሊዳ ------ ቦዝ አንቀጽ

ዋሕድ ------- ተሳቢ ተሳቢነቱ ለወሊዳ

ወ ------ አገባብ ፍቺውም ሙያውም አጫፋሪ

ተወሊዳ ------ ቦዝ አንቀጽ

አሐተ ----- ተሳቢ ተሳቢነቱ ለተወሊዳ

ማራቀቅ

ሰሙ፡---አዳምና ሔዋን ሁለት ሁለት ቢወልዱም የአባቶቻቸውን (የሥላሴን)

ቤት አልሞመሉም፡፡አንዲት ሴት ግን አንድ ወልዳና አንድ ኹና ተወልዳ

ቤት ሙሉ ኾናለች ማለት ነው፡፡

ወርቁ፡---ባለቅኔው አዳምናሔዋንን ከማርያም ጋር አወዳድሯል ፣በውድድሩም መሠረት

አዳምናሔዋን መንታ መንታ ቢወልዱም ምድርን አለመሙላታቸውን፡

ማርያም ግን ሰማይና ምድርን የፈጠረውን ስለወለደች ምድርን ሞልታታለች ይላል ባለቅኔው፡፡

ይህ ቅኔ አፍራሽ ቅኔ ይባላል፡፡አዳምና ሔዋንንአኮስሶ ማርያምን አሞግሶ ተቀኝቷል፡፡አባቶቻችንስ «አምሣ ቢወለድ አምሣ ነው ጉዱ ከተባረከ ይበቃል አንዱ» ይሉ የለ፡፡

መወድስ ቅኔ

የሚቀጥለው ቅኔም የጌታን ስቅለት የተመለከተ ነው፡፡

ንባብ

ኦ አብርሃም መድኀኔዓለም ተአንገዱ ብከ አናግደ ሐጺን ቅንዋት፣

ወአመ በገጽከ ቀርቦ ተጸፍዖተ ገጽ ኀብስት፣

ነበረ በጥቃ ዚአከ እንግዳ ኵይናት፣

ወላእከ ትእዛዝ ገቦ ዚአከ ጽሩየ ማየ አቅረበ ለኀጽበት፡፡

ለዓለም

ይትሐነጽሂ ለአረጋዊ ሕንጻ ቤተከ ስቅለት፣

በሐብል ተመጠነ ዘባንከ መሠረት፣

ወእመ ይጠፍእ ብከ ብርሃነ ፀሐይ ማኅቶት፣

ዕለተ ሞትከ አረጋዊ ነበረ በጽልመት፡፡

የቃላት ትርጉም

| | |
|---|---|
| ኦ ----- ሆይ | ተጸፍዖት ----- በጥፊ መመታት |
| አብርሃም ---- የሰውስም | ገጽ ------ ፊት |
| መድኃኒ ------ አዳኝ | ኀብስት ----- እንጀራ |
| ዓለም------ በቁሙ | ነበረ ------ ተቀመጠ |
| ተአንገዱ ------ እንግዳ ሆኑ | ጥቃ ------ አጠገብ |
| ብከ --------- ባንተ | ዚአከ ----ያንተ |
| አናግድ ----- እንግዶች | ላእከ ----- ተላላኪ(መላክተኛ) |
| ሐጺን ------ ብረት | ትእዛዝ ----- ትዛዝ |
| ቅንዋት ------ ችንካሮች | ገቦ ----- ጎን |
| ወ ------ ም | ጽሩይ ----- ጥሩ |
| አመ ------ ጊዜ | ማይ ----- ውኃ |
| በገጽከ ----- በፊትህ | አቅረበ ----- አቀረበ |
| ቀርበ ------ ቀረበ | ለ ----- በቁሙ |

ኀፅበት ------- ማስታጠብ(እጥበት) ዘባንከ ----- ጀርባህ

ይትሐነጽ ----- ይሠራ ዘንድ መሠረት ----- በቁሙ

ሂ ------------ ም(ከፋይ) አመ -------- ጊዜ

አረጋዊ ----- ሽማግሌ ይጠፍእ ----- ይጠፋል

ሕንጻ ----- በቁሙ ብከ ----- ባንተ

ቤትከ ------ ቤትህ ብርሃን ------ በቁሙ

ስቅለት ----- ስቅለት ፀሓይ ---- በቁሙ

በሐብል ------ ጠመደ ማኅቶት ----- ብርሃን ፣ጧፍ

ተመጠነ ----- ተለካ ዕለተ ምትከ ----- የሞትህ ቀን

ጽልመት ----- ጨለማ ነበረ ----- ተቀመጠ

ፍቺ

አብርሃም የዓለም መድኃኒት ሆይ የብረት ችንካሮች እንግዶች፣

መጡብህ፡፡በጥፊ መመታት ገበታም በፊትህ በቀረበ ጊዜ እንግዳ ጦር

ከአጠገብህ ተቀምጦ፣ቁጭ አለ፡፡ትዛዝ ፈጻሚ ተላላኪ ጐንህም ለማስታጠብ ጥሩ ውኃ አቀረበ፡፡

ለዓለም

የቤትህ ሕንፃ ስቅለት ለሽማግሌው ይሠራ ዘንድ መሠረቱ ጀርባህ በገመድ

ተለካ፡፡የፀሐይ ሻማ ብርሃንም በጠፋ ጊዜ ሽማግሌው የሞትህ ቀን

በጨለማ ተቀመጠ፡፡

ምሳሌና ሙያው

አ ---- ቃለ አጋኖ

አብርሃም መድኃኒ ----- ምሳሌ አብርሃም ስም መድኃኒ ወርቅ ተመስሎ የሰሚ ባለቤት

ዓለም ---- የመድኃኒት ዘርፍ

ተአንገዱ ------ ማሰሪያ አንቀጽ

በ ----- አገባብ ፍቺው በቁም ቀሪ ሙያው ማድረጊያ

ከ ------ ማድረጊያ ባለቤት

አናግድ ቅነዋት ------ ምሳሌ አናግድ ስም ቅንዋት ወርቅ ተመስሎ የቅኔ(የዐረፍተ ነገሩ)ባለቤት

ሐጺን ------ የአናግድ ዘርፍ

ወ ------- አገባብ ፍቺውም ሙያው ዋዌ

አመ ------ አገባብ ፍቺው ጊዜ ሙያው ማንጸሪያ

በ ------ አገባብ ፍቺው በቁም ቀሪ ሙያው ማጸሪያ

ገጽ ----- የማድረጊያ ባለቤት

ቀርበ ----- ያስር ነበር አመ ወድቆ አስቀርቶታል

ተጸፍዖተ ኅብስት ----- ምሳሌ ኅብስት ስም ተጸፍዖት ወርቅ ተመስሎ የማንጸሪያ ባለቤት

ገጽ ------ የተጸፍዖት ዘርፍ

ነበረ ----- በዋዌ የተደገመ ማሰሪያ አንቀጽ

በ ----- አገባብ ፍቺው በቁም ቀሪ ሙያው ማድረጊያ

ጥቃ ----- የማድረጊያ ባለቤት

ዚአከ ----- የጥቃ ዘርፍ

እንግዳ ኵይናት ----- ምሳሌ እንግዳ ሰም ገቦ ወርቅ ተመስሎ የዋዌ ባለቤት

ትእዛዝ ------ የላእከ ዘርፍ

ዚአከ ------ የገቦ ዘርፍ

ጽሩይ ------ ቅጽል ቅጽልነቱ ለማይ

ማይ ------ ተሳቢ ተሳቢነቱ ለአቅረበ

አቅረበ ------ በዋዌ የተደገመ ማሰሪያ አንቀጽ ይስባል እንጂ አይሳብም

ለ ----- አገባብ ፍቺው በቁም ቀሪ ሙያው አቀባይ

ኅፅበት ----- ኅብር ሆኖ የአቀባይ ባለቤት

ይትሐነጽ ----- ዘንድ አንቀጽ ሙያው አዋዋይ

ሂ ------ አገባብ ፍቺው ም ሙያው ከፋይ

ለ ------ አገባብ ፍቺው ም ሙያው አቀባይ

አረጋዊ ------ የአቀባይ ባለቤት

ሕንፃ ስቅለት ----- ምሳሌ ሕንፃ ሰም ስቅለት ወርቅ ተመስሎ የዘንድ ባለቤት

ቤት ------ የሕንፃ ዘርፍ

በ ------ አገባብ ፍቺው በቁም ቀሪ ማየው ማድረጊያ

ሐብል ------ የማድረጊያ ባለቤት

ተመጠነ ------ ማሰሪያ አንቀጽ

መሠረት ዘባን ------ ምሳሌ መሠረት ሰም ዘባን ወርቅ ተመስሎ የቅኔ(የዐረፍተ ነገሩ)ባለቤት

ወ ----- አገባብ ፍቺው ም ሙያው ዋዌ

አመ ----- አገባብ ፍቺው ጊዜ ሙያው ማገናጸሪያ

ይጠፍእ ------ ያስር ነበር አመ ወድቆ አስቀርቶታል፡፡

በ -----አገባብ ፍቺው በቁም ቀሪ ሙያው ማድረጊያ

ማኅቶት ብርሃን ------ ምሳሌ ማኅቶት ስም ብርሃን ወርቅ ተመስሎ የማገናጸሪያ ባለቤት

ሞት ------ የዕለት ዘርፍ

ነበረ ----- በዋዌ የተደገመ ማሰሪያ አንቅጽ

በ ------ አገባብ ፍቺው በቁም ቀሪ ሙያው ማድረጊያ

ጽልመት ------- ኅብር ሆኖ የማድረጊያ ባለቤት

ማራቀቅ

ሀ

ኦ አብርሃም መድኃኔዓለም

ተአንገዱ ብከ አናግደ ሐጺን ቅንዋት፣

ሰሙ፡--- በአንተ ቤት ሊስተናገዱ እንግዶች መጡብህ

ወርቁ፡--- የብረት ችንካሮች መጡብህ ማለት ጌታ በመስቀል ላይ

በተሰቀለ ጊዜ በብረት ቸንካሮች መመታቱን (መቸንከሩን )ለመናገር ነው፡፡

ለ

ወአመ በገጽከ ቀርበ ተጽፍዖተ ገጽ ኅብስት፣

ነበረ በጥቃ ዚአከ እንግዳ ኩይናት፣

ሰሙ፡--- ገበታ(ማእድ)በቀረበ ጊዜ እንግዳው በአጠገብህ ተቀመጠ ፡፡

ወርቁ፡---- ጌታ በአንድ በኩል በጥፊ እየተመታ ሳለ በእንድ በኩል ደግሞ ጎኑን በጦር

መወወጋቱን ለመናገር ነው፡፡

ሐ

ወጻእከ ትእዛዝ ገቦ ዚአከ ጽሩይ ማየ አቅረበ ጎጽበተ፣

ሰሙ፡--- ራት ሊቀርብ ሲል የቤት የቤት አሽከር እጅ ለማስታጠብ ውኃ ያቀርባል፡፡

ወርቁ፡--- ጌታ ጎኑን በጦር በተወጋ ጊዜ ከጎኑ ጥሩ ውኃ ፈስሷል ማለት ነው፡፡

ለዓለም

መ

ይትሐነጽሂ ለአረጋዊ ሕንፃ ቤተ ክርስትያን ስቅለት፣

በሐብል ተመጠነ ዘባንከ መሠረት፣

ሰሙ፡--- ቤት ሲሠራ በሜትር ፣በገመድ ይለካል

ወርቁ፡--- ጀርባው በገመድ ተለካ በማለት በመስቀል ላይ በተሰቀለ ጊዜ ስፍር ቁጥር

የሌለው ግርፋት መገረፉን ነው፡፡

ሠ

ወአመ ይጠፍእ ብከ ብርሃነ ፀሐይ ማሕቶት ፣

ዕለተ ሞትከ አረጋዊ ነበረ በጽልመት፡፡

ሰሙ፡--- በቤት ውስጥ ይበራ የነበረው መብራት ከጠፋ ቤተሰቡ ሁሉ በጨለማ መቀመጡ ነው፡፡

ወርቁ፡--- ጌታ በመስቀል ላይ በተሰቀለ ጊዜ ፀሐይ ብርሃኗን ከልክላለች ፡የጌታም ስቅለት በጨለማ ተጋርዶ

የቆየ መሆኑን ለመናገር ነው፡፡

ይህ ባለቅኔ ግሩም ሰምና ወርቅ አዋቂ ነው ቅኔውንም ያቀረበው በተንጣለለ ሰምና ወርቅ ነው፡፡ባለቅኔው የተራኪና የሥዕላዊ ድርሰትም ባለሙያ ነው፡፡ምክንያቱም የጌታችንን የሥነ ስቅለት ታሪክ በሁለቱም የድርሰት ዓይነቶች ነግሮናልና ፡፡ ከዚህም ሌላ ባለቅኔው የስብከት ባለሙያ ነው፡፡ብዙዎቻችን ስብከት የሚሰበከው መጽሐፍ ቅዱስን በመዘርጋት ብቻ ይመስለን ነበር፡፡ባለቅኔው ግን በቅኔው ጌታችን በችንካር መቸንከሩን በጥፊ መመታቱን ፣በጦር መወጋቱን፣ከጎኑ ጥሩ ውኃ መፍሰሱን ዕርቃኑን ሆኖ ከልክ በላይ በጅራፍ መገረፉን በዚህም ምክንያት ፀሐይ ብርሃኗን በመከልከሏ ስቅለቱም በጨለማ መከለሉን ሰብኮናል፡ነግሮናል፡፡

እንግዲህ የግዕዝ ቅኔ ትንሽ ተናግረን ብዙ የምንማርበት እና ብዙ የምናስተምርበት ድርሰት ነው፡፡ለምሳሌ ባሕልን ሃይማኖትን ታሪክን እና ልዩ ልዩ ጥበባትን በቅኔ መማርና ማስተማር እንችላለን፡፡ምክንያቱም ከዚህ በላይ ከአየነው መወድስ ቅኔ ሐሳቡን ወስደን ጌታ ወደዚህ ዓለም መጥቶ በምን ምክንያት እንደተሰቀለ ብንጽፍ ከአንድ መጽሐፍ ይበልጣልና፡፡

ከዚህ በላይ ሁለት ሙሉ ቤት ቅኔዎች አይተናል፡፡አንደኛው ሙሉ ቤት የግዕዝ ቅኔ መልክ በአማርኛ ቋንቋ ሁለተኛው ሙሉ ቤት በግዕዝ ቋንቋ መዘረፉን አይተናል፡፡

እንግዲህ ወጣቶች የቅኔውን ጸጉሩን፣ ግንባሩን፣ቅንድቡን፣ጆሮውን፣ዐይኑን፣አፍንጫውን፣ጥርሱንና ከንፈሩን በጠቅላላ መልኩን አይታችሁታል፡፡ከአሁን ጀምሮ ተዋወቁት የቅኔያችን መጀመሪያ ጉባኤ ቃና መጨረሻው ደግሞ መወድስ መሆኑን ልብ አድርጉ፡፡

ቅኔውን ሙሽራ ይመስል ዐይን ዐይኑን ማየት ብቻ አይበቃም፡፡ቅኔ ጥሩ አንባቢ ያስፈልገዋል፡፡በቅኔ ውስጥ ያሉ ቃላት ሐረጎችና ቤት መምቻዎች በንባብ በኩል የራሳቸው የንባብ አጀማመር እና አጨራረስ አላቸው፡፡

ጥሩ አንባቢ የሌለው ቅኔ እና ፍሬ የሌለው ዛፍ ይመሳሰላሉ፡፡ዛፉ የሚበላ ፍሬ እንደ ሌለው ሁሉ ቅኔውም ጥሩ አንባቢ ከሌለው ጆሮ አይስብም አይነሽጥም ፣ወኔም አይቀሰቅስም፣«ማለፊያ ነው ይበል ይበልም» አያስኝም፡፡ስለዚህ በቅድሚያ ከዚህ በላይ የተሰጡትን ቅኔዎች ጥሩ ቅኔ የሚያውቅ ሰው ቢያነባቸው የተሻለ ነው፡፡ከዚያ በኋላ ግን መለማመዱ ጠቃሚ ነው፡፡

ከዚህ በላይ እንዳየነው መምህሩ ከጉባኤቃና እስከ መወድስ ሲዘርፍ ሙሉ ቤት ቅኔ ዘረፈ ይባላል፡፡ጀማሪው የቅኔ ተማሪም ቅኔ እየቆጠረ ከጉባኤ ቃና እስከ መወድስ ሲደርስ ተማሪ እገሌ ቤት ሞላ ይባላል፡፡ሙሉ ቤት ማለትም የቅኔው መጨረሻ ማለት ነው፡፡ሌሎች ተጨማሪ ቅኔዎች ቢኖሩም ከዚህ ውጪ አይደሉም በአጠቃላይ ከጉባኤ ቃና እስከ መወድስ ያሉት ቅኔዎች ሙሉ ቤት ቅኔ ይባላሉ፡፡ቤት ሞላ ማለት ደግሞ ቅኔውን ጨረሰ ማለት ነው፡፡ሙሉ ቤት ቅኔ በስልሳ ስድስት ሐረጎች እና በሠላሳ ሁለት ቤት ይነገራል፡፡የግዕዝ ቅኔያት የቃላቱን አቀማመጥ የሐረጎቹን አሳሳብ፣የቤቶችን አመታትና የዜማቸውን ልክ ስንመለከታቸው የአማርኛ ቅኔዎች ግልባጮች ናቸው፡፡በአማርኛ ቅኔዎች እና በግዕዝ ቅኔያት መካከል የሚታይ ልዩነት ቢኖር የቋንቋ ለውጥ ብቻ ነው፡፡